# መጽሐፈ ኢያሱ

## መግቢያ

### አሰያየሙና መሪ ሐሳቡ

መጽሐፈ ኢያሱ ተስፋዪቱን ምድር በውጊያ ስለ መውረስና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ ተገባው ቃል መፈጸም የሚተርክ ነው:: በግብፅ ብዙ ዓመት በባርነት ከቈዩና በምድረ በዳ 40 ዓመት ከተንከራተቱ በኋላ፣ ለአባቶቻቸው በተገባው ቃል መሠረት እስራኤላውያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ገብተዋል:: ዘመኑን ሁሉ በመጻተኛነት የኖረው አብርሃም ወደዚያ የተላከበትን ምድር አልወረሰም፤ የእርሱ ልጆች ግን የእግዚአብሔር ኪዳን ለእነርሱም ሆኖ ከነዓንን በሙሉ ወረሱ (ዘፍ 15፥13:16:18፤17፥8 ይመ):: ኢያሱም ይህን ተስፋ እውን ለማድረግ የታደለ ሆነ::

መጽሐፈ ኢያሱ አራት ዘዳግም ከቆመበት በመቀጠል የእስራኤል ነገዶች ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ እንደ ሰፈሩ ይናገራል:: ትረካውንም የሚጀምረው እስራኤላውያን ወደ ፊት እንዲሄዱና ወንዙን በደረቅ ምድር እንዲሻገሩ እግዚአብሔር በሚሰጣቸው ትእዛዝ ነው:: በመቀጠልም በመካከለኛው፣ በደቡባዊውና በሰሜናዊው የከነዓን ምድር ድል ስለ መቀዳጀታቸውና ደጋውንና ቈላውን ምድር ሁሉ ስለ መቈጣጠራቸው፣ የእስራኤል ነገዶች ርስት ስለ መከፋፈላቸውና ኢያሱ ለሕዝቡ ያደረገውን የመጨረሻ ንግግር በማውሳት ያጠቃልላል:: ስለዚህ የመጽሐፉ መሪ ሐሳብ የእስራኤል ሕዝብ በተስፋዪቱ ምድር መተከሉ ነው::

ኢያሱ ቀድሞ ይጠራበት የነበረው ስም "አውሴ" ሲሆን (ዘኍ13፥8:16)፣ ትርጒሙም "ድነት" ማለት ነው:: ኋላ ግን ሙሴ ስሙን ወደ ኢያሱ አለው፤ ይህም "*እግዚአብሔር ያድናል*" (ወይም "*እግዚአብሔር* ድልን ይሰጣል") ማለት ነው:: ይህ ስም በግሪክ ቋንቋ "ኢየሱስ" ይባላል:: ለማርያም የበኵር ልጅም የተሰጠው ስም ይኸው ሲሆን (ማቴ1፥21)፣ ከስሞች ሁሉ በላይ የሚወደድ ስም ሆኖአል::

በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የመጽሐፈ ኢያሱ አቀማመጥ "ቀደምት ነቢያት" በተባለው ክፍል የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው፤ ይህም ክፍል መጽሐፈ መሳፍንትን፣ መጽሐፈ ሳሙኤልን (1ኛ እና 2ኛ) እንዲሁም መጽሐፈ ነገሥትን (1ኛ እና 2ኛ) ያካተተ ነው:: እነዚህም ስለ እስራኤል መንግሥት፣ ከሙሴ ጊዜ ጀምሮ እስከ ይሁዳ ውድቀት (586 ዓ.ቅ.ክ.) ያለውን ታሪክ በመዘገብ ብቻ አያበቁም፤ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በማመልከት እንዴት በኢያሱ፣ በመሳፍንት፣ በሳሙኤልና በዳዊት አማካይነት ቃሉን እንደ ፈጸመና እንደ ጠበቀ ከማስረዳታቸው በላይ የእስራኤልን ዐመፀኝነት እንዴት እንደ ማረና እንደ ቀጣ ያሳያሉ:: በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ ተዋግቶ ድል ያደረገውና "ለአባቶቻቸው የማለውን ምድር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው እግዚአብሔር ነው" (21፥43)::

### ጸሐፊውና የተጻፈበት ጊዜ

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት፣ መጽሐፈ ኢያሱ ከነገሥታት ዘመን በኋላ እንደ ተጻፈ ይገምታሉ፤ ይኸውም መጽሐፉ የተጻፈው የመጽሐፉ ታሪክ ከተፈጸመ ከስምንት መቶ ዓመት በኋላ ነው ማለታቸው ነው:: ይሁን እንጂ ከዚህ ግምት ገሸሽ የሚያስደርግና ከዚያ እጅግ ቀደም ብሎ እንደ ተጻፈ የሚያሳምን ብዙ ነጥብ አለ:: "ታልሙድ" በተባለው የአይሁድ ትውፊት መጽሐፍ ስለ ሞቱና ስለ ቀብሩ ከሚያወራው ክፍል በስተቀር፣ ይህን መጽሐፍ የጻፈው ኢያሱ ራሱ እንደ ሆነ ይናገራል፤ የተጠቀሰውንም መደምደሚያ የጻፈለት የአሮን ልጅ አልዓዛር እንደ ሆነ ይታመናል::

በመጽሐፉ ውስጥ ሁለት ቦታ እንደ ተጠቀሰው፣ መጽሐፉ በኢያሱ ትእዛዝ ወይም በራሱ በኢያሱ እንደ ተጻፈ ተገልጾአል፤ በ18፥8 ላይ ኢያሱ አንዳንድ ዘገባ እንዲጻፍ ማዘዙን የሚገልጽ ታሪክ ሲኖር፣ በመጽሐፉ መጨረሻ (24፥25) ላይ ደግሞ ኢያሱ "ሥርዐትንና ፍርድን አደረገላቸው" የሚል ስላለ ኢያሱ ራሱ የጻፈው ክፍል እንዳለ ያመለክታል:: በ5፥1:6 ላይ የተዘገበው ታሪክ ደግሞ ጸሐፊው ራሱ በድርጊቱ ውስጥ ተሳታፊ እንደ ነበረ የሚገልጹ ቃላት አሉት::

በተጨማሪም ጸሐፊው ስለ ድርጊቶች ያለው አስተውሎት እጅግ ትክክለኛ ነው:: የአንዳንድ ከተሞችን የቀድሞ ስም በትክክለኛነት ጠቅሶ ይገኛል፤ ኢየሩሳሌምን "የኢያቡስ ከተማ" (15፥8፤18፥16:28) ኬብሮንን "ቂርያትአርባቅ" (14፥15፤15፥54፤20፥7፤21፥11)፣ ሲዶንን "ታላቂቱ ሲዶን" (11፥8፤19፥28) በማለት አቅርቦአል:: ጢሮስ፣ በኢያሱ ዘመን ገና የምትታወቅ ወደብ ስላልነበረች፣ ከቶ አልተጠቀሰችም::

አንዳንድ ሁነቶች የኢያሱን የሕይወት ዘመን ቢጠቍሙም፣ አንዳንዶቹ ከኢያሱ ሕይወት ዘመን በኋላ የተከሠቱ እንደ ሆኑ የሚያመለክቱ ሐሳቦችም አሉ:: ለምሳሌ በኤሎን ሸለቆ ላይ ፀሓይ ስለ መቆሟ ድጋፍ ከሌላ ምንጭ፣ ከያሻር መጽሐፍ (10፥13)፣ ተጠቅሶአል:: ታምሩን በዐይኑ ያየ፣ እንደ ኢያሱ ያለ ሰው እንዲህ ይጽፋል ማለት ያዳግታል:: በሌላም በኩል ጸሓፊው "እስከ ዛሬ ድረስ" የሚል ሐረግ 12 ጊዜ ተጠቅሞ ይገኛል::

ስለዚህ እስራኤል ገና በነገሥታት መስተዳደር ከጀመረችበት ጊዜ አንሥቶ፣ መጽሐፉ በግርድፍ መልኩም ቢሆን እንደ ነበረ መገመቱ የሚያስሄድ ነው:: አንዳንዶች፣ ሳሙኤል በማሰባሰቡና መልክ በማስያዙ ውስጥ ድርሻ ይኖረዋል የሚሉ አሉ፤ ይሁን እንጂ የመጽሐፉ የመጨረሻ ትክክለኛ ጸሐፊ ወይም አርታዒ እገሌ ነው ለማለት አያስደፍርም::

### የኢያሱ ሕይወት

የኢያሱ ሕይወት በደስታ፣ በለውጥ፣ በስኬትና በክብር የተሞላ መልክ ነበረው። በእግዚአብሔር ላይ ባለው ጥብቅ እምነቱና "የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሰው" (ዘኍ 27፥18) በመባል የታወቀ ነበር። በወጣትነት ዕድሜው የግብፅን ባርነት የቀመሰ፣ እግዚአብሔርም ከዚያ ባርነት ነጻ ሲያወጣቸው ያደረገውን ታላቅ ታምራትና ከግብፃውያንም ለማምለጥ በወጡ ጊዜ ቀይ ባሕር ሲከፈል ያየ ሰው ነበር። ከአማሌቃውያን ጋር በተደረገው ጦርነት የእስራኤልን ሰራዊት የመራና (ዘፀ17፥8-13)፣ ከሙሴ ጋር በቅርብ ሆኖ የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማትን የተለማመደ ሰው ነበር (ዘፀ 24፥13-14)። ደግሞም መቅደሱ በቋሚነት ከመተከሉ በፊት፣ ጊዜያዊ መገናኛ ድንኳኑን ለመጠበቅ ዘብ ይቆም ነበር (ዘፀ 33፥11)።

ኢያሱ የከነዓንን ምድር ለመሰለል የራሱን ነገድ ኤፍሬምን እንዲወክል ተመርጦ በተላከ ጊዜ፣ እርሱና ካሌብ ብቻ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመከተልና ምድሪቱን ለመውረስ ፈቃደኞች ሆኑ (ዘኍ 14፥26-34)። ሌሎቹ እንዲሁም ሙሴ እንኳ ሳይቀር በምድረ በዳ ሞቱ፤ ስለዚህም መሪነቱ ለኢያሱ ተላለፈ። እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር እንደ ነበረ ኢያሱንም እንደሚመራውና እንደሚያበረታው ተስፋ ሰጠው (ዘዳ31፥23)።

ኢያሱ የተዋጣለት የጦር መሪ ብቻ ሳይሆን፣ የእስራኤልን ነገዶች በማስተዳደርም ብቃት አሳይቶአል። ከሁሉም በላይ፣ ሙሴ የጀመረውን ሥራ ከግብ ለማድረስና የእስራኤልን መንግሥት በተስፋዪቱ ምድር ለመመሥረት እግዚአብሔር የመረጠው ሰው ነበር (24፥29፤የዘዳ34፥5 ማብ ይመ)። ኢያሱ በብሉይ ኪዳን የነበረው ሚና የክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ጐልቶ የሚታይበት ጥላ (ምሳሌ) ነው (የዕብ4፥1፡6-8 ማብ ይመ)።

### ታሪካዊ ዳራው

እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ለመግባት በሚጓዙበት ዘመን፣ በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ የነበሩ መንግሥታት ከእስራኤል አንጻር ደከም ያሉ ነበሩ። ኬጢያውያን ኀይላቸው መንምኖአል። ባቢሎንና ግብፅም በከነዓን ምድር የጦር ኀይል አልነበራቸውም። አሦራውያንም ቢሆኑ ሰራዊታቸው ወደዚህ ስፍራ የመጣው ከብዙ ዘመን በኋላ ነበር።

በዚህ ጊዜ እስራኤልን የሚቋቋመው ኤዶም ብቻ ነበር። ሞዓብ ሳይወድ በግዱ እስራኤላውያን በምድሩ መካከል እንዲያልፉና እንዲሰፍሩም ጭምር ፈቅዶአል። ሁለቱ የአሞራውያን ነገሥታት እስራ ኤልን ለመቋቋም ቢነሡም፣ በቀላሉ ተሸንፈው ምድራቸው ተወርሶአል።

የመጽሐፍ ቅዱስን ሥነ ቅርስ በቍፋሮ የሚያጠኑ ተመራማሪዎች ይህን ዘመን "የኋለኛው የናስ ዘመን" ይሉታል (1550-1200 ዓ.ቅ.ክ.)። አንዳንድ በቍፋሮ የተገኙ የቅርሳ ቅርስ መረጃዎች እንደሚጠቍሙት፣ እስራኤል በሰፈረችበት በከነዓን ምድር የአረማውያን የባህልና የአምልኮ ዕቃዎች፣ መቅደሶችና መሠዊያዎች በብዛት መኖራቸው ምን ዐይነት ሕዝቦች በእስራኤል ዙሪያ እንደ ነበሩ ያመለክታል። ብዙ የሥነ ቅርስ የቍፋሮ ማስረጃዎች ኢያሱ ከነዓንን የወረረው በ1250 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ እንደ ነበረ ያመለክታሉ፤ በዘልማድ ግን 1406 ዓ.ቅ.ክ. እንደ ነበረ ይገመታል።

### ወረራውና ጦርነቱ ከግብረ ገብ አንጻር ሲታይ

የኢያሱን መጽሐፍ (ሌሎችንም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት) የሚያነቡ ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ውስጥ የጦርነት ሚና ምን ሊሆን እንደሚገባ ጥያቄ ይሆንባቸዋል። አንዳንዶችም ይህን ጥያቄ ለማስወገድ ከአዲስ ኪዳን ዘመን በፊት የነበረ ታሪክ በመሆኑ ክርስቲያናዊ ግብረ ገብ አይመለከተውም ይላሉ፤ ነገር ግን ልብ ሊባል የሚገባው፣ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ጦርነት ሰው ፍላጎቱን ያገኘበት መንገድ ሳይሆን፣ ከአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ጀምሮ እግዚአብሔር መለኮታዊ ጸጋውንና ፍርዱን የገለጠበት የማዳን ታሪክ ቀጥያ መሆኑ ነው። ኢያሱ፣ እስራኤላውያን ከነዓንን ለመውረስ በእግዚአብሔር ርዳታ ባደረጉት የድል ጦርነቶች ውስጥ ዋነኛ ሰው ሳይሆን፣ ምድርና ሞላዋ የእርሱ የሆነችው እግዚአብሔር በአንድ የማዳን ታሪክ ደረጃ ላይ የምድርን አንድ ክፍል ከዚህ ዓለም ገዥ እንዴት ነጥቆ እንደ ወሰደና በሐሰተኛ አማልክትና በጠራቸው የሚመኩ መታመኛቸው ከንቱ እንደ ሆነ ያሳየበት ታሪክ ነው። ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር በባሪያው በኢያሱ መሪነት ኀጢአቷ እጅግ የበዛውን ከነዓንን ቀጥቶ ሕዝቡ ምድራቸውን እንዲወርስ ያደረገበትን ታሪክ የሚያወሣ ነው (በዚህ ጊዜ ኀጢአታቸው ከልክ አልፎ ፍርድ እየጋበዘ ነበር፤ ዘፍ15፥16ይመ)።

መጽሐፈ ኢያሱ፣ በምድር ላይ የነበሩ ብሔሮችንና መንግሥታትን የፈጠሩና የሚያስተዳድሩ ባዕዳን አማልክት እንደ ሆኑ በሚታመንበት ዘመን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እንዴት ወደ ዓለም ሕዝቦች መካከል ዘልቃ እንደ ገባች የሚያሳይ መጽሐፍ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በከነዓናውያን ላይ የበላይነቱን በመግለጡ፣ የእስራኤል አምላክ ብቻ ምድርን የሚያስተዳድር እውነተኛና ሕያው አምላክ መሆኑን ለዓለም አረጋግጦአል። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመጋፋትም ሆነ ለመቃወም የሚነሣ መንግሥት የሚፈነገል መሆኑና በአንጻሩም ደግሞ ጌትነቱን ተቀብሎ የሚያገለግለው መንግሥት ብቻ እንደሚጸና ማስጠንቀቂያ ሆኖአል። የእግዚአብሔር መንግሥት ፍርድንና ማዳንን አጣምራ የያዘች እንደ መሆኗ፣ የታሪክን ፍጻሜና ሰውን ጨምሮ የፍጥረትን ሁሉ የመጨረሻ ግብ ታመለክታለች።

ስለዚህ የከነዓንን ጦርነት በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ሆኖ፣ በተለየ ጊዜ የተገለጠ ቅዱስ ጦርነት ነው። የተወረሰችው ምድርና በውስጧ የነበረው ሀብት የእግዚአብሔር እንጂ ለእስራኤላውያን የሚሰጥ አልነበረም። እስራኤል በዚህ መሠረት የእግዚአብሔር መንግሥት አምሳያ ሆና ለሕዝቦች ምስ

ክፎና በረከት እንድትሆን ተመሠረተች፤ ነገር ግን እርሷ ራሷ ታማኝ መሆኗ ቀርቶ የከነዓናውያንን የኑሮ ዘይቤ ብትከተል፣ በከነዓን ላይ የደረሰው ሁሉ ይደርስባታል።

ጦርነት የሰው ዘር በእኩይ መንገድ ግዛቱን ለማስፋፋት ሲል በራሱ ላይ የሚያመጣው መርገም ነው። ነገር ግን እግዚአብሔርን በማይሰሙትና በማይታዘዙት ላይ ሊመጣ ካለው የመጨረሻው ርግማን አንጻር ይህኛው ርግማን ቀላል ሆኖ ይገኛል። ሁለተኛውም ኢያሱ (ኢየሱስ)፣ ምንም እንኳ አሁን ዓለም በወንጌል እስክትዳረስ ቢታገሥም፣ የፍርድ ሰይፉን መዞአል (ራእ 19፥11-16)፤ ፍርዱም ተቃርቦአል።

**አስተዋፅኦ**

1. ወደ ተስፋዪቱ ምድር መግባት (1፥1-5፥12)
   - ሀ. ለመውረር የተሰጠ መመሪያ (ም1)
   - ለ. ኢያሪኮን መሰለል (ም2)
   - ሐ. የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገር (ም3-4)
   - መ. በጌልጌላ መቀደስ (5፥1-12)
2. የተስፋዪቱን ምድር መውረስ (5፥13-12፥24)
   - ሀ. የመጀመሪያዎቹ ጦርነቶች (5፥13-8፥3)
     - (1) በኢያሪኮ የተገኘው ድል (5፥13-6፥27)
     - (2) በአካን ኀጢአት ምክንያት በጋይ ያጋጠመው ሽንፈት (ም7)
     - (3) በጋይ የተገኘው ድል (8፥1-29)
     - (4) በሴኬም የኪዳኑ መታደስ (8፥30-35)
   - ለ. በደቡብ የነበረው ዘመቻ (ም9-10)
     - (1) ከገባዖን ሰዎች ጋር የተደረገ ውል (ም9)
     - (2) በገባዖን ላይ የቀን መራዘም (10፥1-15)
     - (3) በደቡብ የነበሩ ከተሞች መያዛቸው (10፥16-43)
   - ሐ. በሰሜን የነበረው ዘመቻ (ም11)
   - መ. የተሸነፉ የከነዓን ነገሥታት (ም12)
3. የርስት ክፍፍል (ም13-21)
   - ሀ. ገና ያልተወረሱ ቦታዎች (13፥1-7)
   - ለ. ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለው ምድር ለሮቤል፣ለጋድና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ መሰጠቱ (13፥8-33)
   - ሐ. በጌልገላ ለይሁዳና ለ"ዮሴፍ" ነገዶች የተሰጠው ምድር (ም14-17)
   - መ. ለተቀሩት ነገዶች የተሰጠው ምድር (ም18-19)
     - (1) የመገናኛው ድንኳን በሴሎ (18፥1-10)
     - (2) ለብንያም፣ለስምዖን፣ለዛብሎን፣ለይሳኮር፣ለአሴር፣ለንፍታሌምና ለዳን የተከፋፈለው ርስት(18፥11-19፥48)
     - (3) ለኢያሱ የተሰጠው ከተማ (19፥49-51)
   - ሠ. ለሌዋውያን የተሰጡ ከተሞች (ም20-21)
     - (1) ስድስቱ የመጸተኞች ከተሞች (ም20)
     - (2) አርባ ስምንቱ የካህናት ከተሞች (ም21)
4. መዝጊያ ክፍል፤ የነገዶች አንድነትና ለጌታ ታማኝ መሆን (ም22-24)
   - ሀ. በዮርዳኖስ አጠገብ ለምስክር የተሠራው መሠዊያ (ም22)
   - ለ. የኢያሱ የስንብትና የምክር ቃል (ም23)
   - ሐ. በሴኬም የኪዳኑ እንደ ገና መታደስ (24፥1-28)
   - መ. የኢያሱና የአልዓዛር መሞት፣ መቀበር (24፥29-33)

## እግዚአብሔር ኢያሱን አዘዘ

**1** የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ከሞተ በኋላ፣
እግዚአብሔር የሙሴን አገልጋይ የነዌን
ልጅ ኢያሱን እንዲህ አለው፤ 2“እነሆ፤ ባሪ
ያዬ ሙሴ ሞቶአል፤ እንግዲህ አሁንም አን
ተና ይህ ሕዝብ ሁሉ ተነሡ፤ ለእሥራኤላው
ያን ወደምሰጣቸው ምድር ለመግባት የዮር
ዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ:: 3ለሙሴ በሰጠሁትም
ተስፋ መሠረት፣ እግራችሁ የሚረግጠውን
ቦታ ሁሉ እሰጣችኋለሁ:: 4የርስታችሁ ዳርቻ
ከምድረ በዳው እስከ ሊባኖስ፣ ከታላቁ ወንዝ
ከኤፍራጥስ አንሥቶ፣ የኬጢያውያንን ምድር
በሙሉ ይዞ፣ በምዕራብ በኩል እስከ ታላቁ
ባሕር[ሀ] ይደርሳል:: 5በሕይወት በምትኖርበት
ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም፤ ከሙሴ
ጋር እንደ ነበርሁ ሁሉ ከአንተም ጋር እሆ
ናለሁ፤ ከቶ አልጥልህም፤ አልተውህም::
6“ጽና፤ ለቀደሙት አባቶቻቸው እሰጣችኋ
ለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር እንዲወርሱ፣
ይህን ሕዝብ የምትመራው አንተ ነህና በርታ::
7አይዞህ፤ ብቻ አንተ በርታ፤ ባሪያዬ ሙሴ
የሰጠህን ትእዛዝ ሁሉ በጥንቃቄ ጠብቅ፤
በምትሄድበትም ሁሉ እንዲሳካልህ፣ ወደ
ቀኝም ወደ ግራም አትበል:: 8ይህ የሕግ
መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ በውስጡ የተጻፈ
ውን ሁሉ በጥንቃቄ እንድትፈጽመውም
ቀንም ሆነ ሌት ከሐሳብህ አትለየው፤ ይህን
ካደረግህ ያሰብኸው ይቃናል፤ ይሳካልም፤
9በምትሄድበት ሁሉ እግዚአብሔር አምላክህ
ከአንተ ጋር ነውና አይዞህ፤ በርታ፤ ጽና፤ አት
ፍራ፤ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?”
10ኢያሱም የሕዝቡን አለቆች እንዲህ ሲል
አዘዛቸው፤ 11“ወደ ሰፈር ግቡ፤ ለሕዝቡም፣
‘ስንቃችሁን አዘጋጁ፤ ከአሁን ጀምሮ ባሉት
ሦስት ቀናት ውስጥ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ፣
እግዚአብሔር አምላካችሁ ርስት አድርጎ የሚ
ሰጣችሁን ምድር ገብታችሁ ትወርሳላችሁ’
በሏቸው::”
12ኢያሱ የሮቤልን ነገድ፣ የጋድን ነገድና
የምናሴን ነገድ እኩሌታ እንዲህ አላቸው፤
13“የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ እንዲህ ሲል
የሰጣችሁን ትእዛዝ አስቡ፤ ‘እግዚአብሔር
አምላካችሁ ያሳርፋችኋል፤ ይህችንም ምድር

1፥1 ዘፀ14፥31፤17፥9 ዘዳ34፥5፤ራእ15፥3
1፥2 ዘፍ15፥14፤ ዘኍ13፥29፤35፥10፤ 12፥7፤ዘዳ1፥25
1፥3 ዘፍ50፥24፤ዘኍ 13፥2፤ዘዳ1፥8፤11፥24፤
1፥4 ዘፍ2፥14፤10፥ 15፤23፥10፤ዘፀ3፥8፤ ዘኍ34፥2-12፤ ዘዳ3፥25፤ዕዝ4፥20
1፥5 ቍ17፤ዘፍ26፥3፤ 28፥15፤ዘዳ4፥31፤7፥24፤ 39፥2፤መሳ6፥12፤1ሳሙ 10፥7፤ኤር1፥8፤30፥11
1፥6 ዘዳ1፥21፤31፥ 6፤መሳ5፥21፤2ሳሙ2 ፥7፤1ነገ2፥2፤ኢሳ41፥ 6፤ኤር3፥18፤7፥7፤ኢል 3፥9-10፤
1፥7 ቍ2፤9፤15፤ዘኍ 12፥7፤ዘዳ4፥2፤5፥3፤3 2፤11፥8፤29፥9፤ኢሱ 11፥15፤23፥6፤1ነገ2፥ 3፤3፥3፤ዕዝ7፥26፤ኢዮ 1፥8፤42፥7፤መዝ78፥ 10፤119፥136፤ኢሳ 42፥24፤ኤር26፥4- 6፤32፥23፤44፥10
1፥8 ዘፍ24፥63፤ዘፀ 4፥15፤ዘዳ28፥61፤29፥ 9፤1ሳሙ18፥14፤ መዝ1፥1-3፤147፥19፤ ኢሳ52፥13፤53፥10፤ 59፥21፤ኤር23፥5

1፥9 ቍ7፤ዘዳ1፥21፤31፥6፡8፤ኢሱ10፥8፤ኢዮ4፥5፤2ነገ19፥6፤ኢሳ35፥5፤37፥6፤ኤር1፥8 1፥10 ዘዳ1፥15 1፥11 ዘፍ40፥13፤ዘኍ35፥10፤33፥53፤ኢሱ3፥2፤1ሳሙ17፥22፤ኢሳ10፥28 1፥12 ዘኍ 32፥33
1፥13 ዘፀ33፥14፤መዝ55፥6፤ኢሳ11፥10፤28፥12፤30፥15፤32፥18፤40፥31፤ኤር6፥16፤45፥3፤ሰቆ5፥5

[ሀ]4 *የሜድትራኒያን ባሕር*

*1፥1-18* እግዚአብሔር፣ የመረጠውን (ዘዳ 31፥1-8) ኢያሱን በሙሴ ምትክ በመሾም እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ የሚያካሂዱትን እንቅስቃሴ እንዲቀጥሉ ያደርጋል፤ ያደፋፍራቸዋል፤ እንደሚያሳካላቸውም ቃል ይገባላቸዋል:: ይህ የሚደረግላቸው ግን ሕዝቡ በሙሴ አማካይነት የተሰጣቸውን የእግዚአብሔርን ሕግ ሙሉ በሙሉ ሲፈጽሙ ብቻ ነው:: ምዕራፉ በይዘትና በቅደም ተከተል የታወቁ ንግግሮችን ይዞአል፤ እግዚአብሔር የሕዝቡ መሪ እንዲሆን ለሾመው ለኢያሱ ትእዛዝ ይሰጣል (ቍ 1-9)፤ ኢያሱ እግዚአብሔርን ወክሎ ለእስራኤላውያን ንግግር ያደርጋል (ቍ 10-15)፤ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ወኪልና የሙሴ ምትክ ለሆነው ለኢያሱ እንደሚታዘዙ ምላሽ ይሰጣሉ:: እንግዲህ የመጽሐፉ ሁነቶች በቅደም ተከተል ተቀምጠዋል፤ በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱ የዋና ዋና ተዋንያንም ድርሻ በግልጽ ሰፍሮአል::

1፥1 *ሙሴ ከሞተ በኋላ፤* ታሪኩ አሪት ዘዳግም ካቆመበት ከሙሴ ሞት የሚጀምር መሆኑን በማሳየት ድርጊቱ የተፈጸመበትን ጊዜና የድርጊቱን ሁናቴ ወዲያውኑ ይገልጻል፤ “ኢያሱ ከሞተ በኋላ” (መሳ 1፥1) ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ:: *የእግዚአብሔር ባሪያ፤* የዘፀ 14፥31፤ የዘዳ 34፥5፤ የመዝ 18 ርእስ፤ የኢሳ 41፥8-9፤ 42፥1 ማብ ይመ:: *የሙሴ አገልጋይ፤* ኢያሱ የሙሴ ምክትል ሆኖ ለብዙ ዓመት ያገለገለበት ማዕረግ ነው (ዘኍ 1፥2 እንዲሁም ዘፀ 24፥13፤ 33፥11፤ ዘዳ 1፥38 ይመ)::

1፥2 *የዮርዳኖስ ወንዝ፤* ወንዙ በያመቱ አብዛኛውን ጊዜ በኢያሪኮ አቅራቢያ ከፍተኛ የውሃ መጠን የለውም (በዚህ ጊዜ ወርዱ ከ24.37 እስከ 30.46 ሜትር ቢደርስ ነው)፤ በሚሞላበት ጊዜ ግን ወርዱ እስከ 1.6 ኪሎ ሜትር ይደርሳል፤ በዚህ ጊዜ ወንዙን ለመሻገር እጅግ አዳጋች ነው:: *ወደምሰጣቸው ምድር፤* የአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት መሪ ሐሳብ ነው (ዘፍ 12፥1፤ 50፥24፤ ዘፀ 3፥8፤ 23፥31፤ ዘዳ 1፥8 ይመ):: ኢያሱ ይህን የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል ፍጻሜ በጥንቃቄ መዝግቦአል::

*1፥3-5፤* ዘዳ 11፥24-25 ይመ::

*1፥4፤* ለእስራኤል ሊሰጥ ቃል የተገባው ምድር የቆዳ ስፋቱ ከየት እስከ የት እንደሆነ የሚገልጹ ክፍሎች ያላቸው ሐሳብ የተለያየ ነው (ይህን ክፍልና ዘፍ 15፥18ን ከዘዳ 34፥1-4 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሆኖም በዚህ ክፍል ላይ የምናነበው የምድሪቱን ከፍተኛ የቆዳ ስፋት ሲሆን፣ እስራኤላውያን ይህን ያህል ከፍተኛ የቆዳ ስፋት ያለውን ምድር የያዙት፣ ዳዊትና ሰሎሞን ጠላቶቻቸውን ድል ካደረጉ በኋላ ነው:: የከነዓን ምድር ኬጢያውያን ወደ ሰሜን አፈግፍገው ከሰፈሩ በኋላ እንኳ “የኬጢ ምድር” ተብላ ትጠራ ነበር:: ኢያሱ ግን እንዲይዝ የታዘዘውን ምድር ሁሉ መያዝ ነበረበት፤ እግሩ የረገጠው ምድር ሁሉ የእርሱ ነው:: የኢያሱ ድል ዐሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች አብዛኛውን ማእከላዊ ተራራማ አገርና የኔጌብን ክፍል እንዲይዙ አስችሎአቸዋል::

1፥5 *ከአንተም ጋር እሆናለሁ፤* መምራት፣ መበርታትና ድል ማድረግ እንዲችል ነው::

1፥6 *ለቀደሙት አባቶቻቸው ... የማልሁላቸውን ምድር፤* ረጅም ዘመን ሲጠበቅ የኖረው፣ ለአብርሃምና (ዘፍ 15፥7፡8-21) ለያዕቆብ ዘሮች (ዘፍ 28፥13) ሊሰጥ ቃል የተገባው ርስት ነው::

1፥7 *በጥንቃቄ ጠብቅ፤* ድል ማድረግ የሚቻለው እግዚአብሔር የሰጠውን መመሪያ በሙሉ መጠበቅ ሲቻል ብቻ ነው (ዘዳ 8፥1፤ 11፥8፡22-25 ይመ)::

1፥8 *የሕግ መጽሐፍ፤* የእግዚአብሔርን ቃል የያዙትን አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት የሚመለከት ነው:: እግዚአብሔር ሕጉን በሲና ተራራ ላይ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ሕጉ በሚገባ ተመዝግቦ ተይዞ ነበር:: *ከአፍህ፤* ዘዳ 4፥9-10፤ 6፥6-7፤11፥19 ይመ:: ሕጉ አብዛኛውን ጊዜ በቃል ይነበባል (ከዘዳ30፥9-14፤ ከሐሥ 8፥30 ጋር ያነጻጽሩ):: ከሐሳብህ አትለየው፤ መዝ 1፥2 ይመ::

1፥9 *አላዘዝሁህምን?* የተናጋሪውን ሥልጣን የሚያመለክት መልስ አዘል ጥያቄ ነው::

1፥10 *ኢያሱም ... አዘዛቸው፤* በዚህ ጊዜ ኢያሱ ሕዝቡን የማዘዝ ሙሉ ሥልጣን ነበረው:: *አለቆች፤* ምናልባት ሙሴ በሕዝቡ ላይ የሾማቸውን ሰዎች የሚያመለክት ነው (ዘፀ 18፥21፤ ዘዳ 1፥15)::

1፥11 *ስንቃችሁን፤* ወደፊት ለሚጠብቃቸው ረጅም ጕዞ የሚያስፈልጋቸውን ምግብ ነው::

*1፥12-15፤* ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ የሚገኙት ሁለቱ ነገሥታትና ከሞዓብ ምድር በስተ ሰሜን፣ እንዲሁም ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ የሚገኘው ምድር በወታደራዊ ድል ተያዘ:: በዚያ ለመቅረት የጠየቁት፣ የሮቤልና የጋድ እንዲሁም የምናሴ እኩሌታ ነገዶች ተዋጊ ጦረኞቻቸውን እንዲልኩና ከነዓንን ለመያዝ በሚደረገው ጦርነት ላይ እንዲካፈሉ ሙሴ አዝዞአቸው ነበር (ዘኍ 21፥21-35፤ 32፥2-27):: የተስፋዪቱን ምድር ለመውረስ በሚደረገው ዘመቻ ላይ መላው የእስራኤል ሕዝብ መሳተፍ አለበት::

1፥13 *ያሳርፋችኋል፤* በብሉይ ኪዳን ውስጥ ትልቅ ስፍራ ይዞ የሚገኝ እሳቤ ነው (የዘዳ 3፥20፤ የ2ሳሙ 7፥1፡11 ማብ ይመ)፤ ይህም ድንበርን በንቃት መጠበቅን፤ ከጎረቤት አገሮች ጋር በሰላም መኖርንና በምድሪቱ ውስጥ ለሕይወትና ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማስወገድ ያጠቃልላል (የ1ነገ 5፥4 ማብ ይመ)::

ይሰጣችኋል::” [14]ሚስቶቻችሁና ልጆቻችሁ
እንዲሁም ከብቶቻችሁ ሙሴ በሰጣችሁ ከዮ
ርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ባለው ምድር ይቆዩ፤
ነገር ግን ተዋጊዎቻችሁ ሁሉ፣ ከነሙሉ ትጥቃ
ቸው፣ ከወንድሞቻችሁ ቀድመው ይሻ
ገሩ፤ እናንተም ከወንድሞቻችሁ ጐን ተሰ
ለፉ:: [15]ይህም፣ እግዚአብሔር እስኪያሳርፋቸ
ውና ለእናንተም እንዳደረገው ሁሉ፣ እነር
ሱም እግዚአብሔር አምላካቸው የሰጣቸውን
ምድር እስኪወርሱ ድረስ ነው:: ከዚህ በኋላ
እናንተም ተመልሳችሁ የእግዚአብሔር
ባሪያ ሙሴ የሰጣችሁን፣ በፀሐይ መውጫ
ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለውን ምድር
ትወርሳላችሁ::”

[16]እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ሲሉ መለ
ሱለት፤ “ያዘዝኸንን ሁሉ እናደርጋለን፤ ወደ
ምትልከንም ሁሉ እንሄዳለን:: [17]ለሙሴ ሙሉ
በሙሉ እንደ ታዘዝን ሁሉ፣ ለአንተም እን
ታዘዛለን፤ ብቻ እግዚአብሔር አምላክህ ከሙሴ
ጋር እንደ ነበረ፣ አሁንም ከአንተ ጋር ይሁን::
[18]በትእዛዝህ ላይ የሚያምፅና ለቃልህ የማ
ይታዘዝ ሁሉ ይገደል፤ ብቻ አንተ ጽና፤
አይዞህ፤ በርታ::”

## ረዓብና እስራኤላውያን ሰላዮች

**2** ከዚያም የነዌ ልጅ ኢያሱ፣ “ሂዱና
ምድሪቱን፣ በተለይም የኢያሪኮን ከተማ
ሰልሉ” ብሎ ከሰጢም ሁለት ሰላዮች በስውር
ላከ፤ ሰዎቹም ሄደው ረዓብ ከተባለች ጋለ
ሞታ ቤት^ ገቡ፤ በዚያም ዐደሩ::
[2]ለኢያሪኮም ንጉሥ፣ “እነሆ፤ ምድሪቱን
ሊሰልሉ ጥቂት እስራኤላውያን በሌሊት ወደ
ዚህ መጥተዋል” ተብሎ ተነገረው:: [3]የኢያ
ሪኮም ንጉሥ፣ “ወደ አንቺ መጥተው ወደ
ቤትሽ የገቡት ሰዎች ምድሪቱን በሙሉ
ለመሰለል ስለሆነ፣ እንድታስወጪአቸው”
የሚል መልእክት ወደ ረዓብ ላከ::

[4]ሴቲቱ ግን ሁለቱን ሰዎች ተቀብላ ሸሽ
ጋቸው ስለ ነበር፣ እንዲህ አለች፤ “በእር
ግጥ ሰዎቹ ወደ እኔ መጥተዋል፤ ነገር ግን
ከወዴት እንደ መጡ አላውቅም:: [5]ጨልሞ
የቅጥሩ በር ከመዘጋቱ በፊት ወጥተው ሄደ
ዋል፤ በየት በኩል እንደሄዱ ግን እኔ
አላውቅም፤ ልትደርሱባቸው ትችላላችሁና
ፈጥናችሁ ተከታተሏቸው::” [6]ነገር ግን ሰዎ
ቹን ጣራ ላይ አውጥታ በረበረበችው የተ
ልባ እግር ውስጥ ደብቃቸው ነበር:: [7]ሰዎቹም
ሰላዮቹን በመከታተል ወደ ዮርዳኖስ መሻ
ገሪያ የሚወስደውን መንገድ ይዘው ሄዱ፣
አሳዳጆቹ ወጥተው እንደሄዱም የቅጥሩ በር
ተዘጋ::

[8]ሰላዮቹ ከመተኛታቸው በፊት ሴቲቱ
ወደ ጣራው ወጥታ፣ [9]እንዲህ አለቻቸው፤
“እግዚአብሔር ይህችን ምድር እንደሰጣችሁ፣
እናንተንም መፍራት እንዳደረብን፣ የዚህች
አገር ነዋሪዎች ሁሉ ልባቸው በፊታችሁ
መቅለጡንም ዐውቃለሁ:: [10]ከግብፅ በወጣ
ችሁ ጊዜ እግዚአብሔር ቀይ ባሕርን* በፊ
ታችሁ እንዴት እንዳደረቀ፣ እናንተም ከዮርዳኖስ
በስተ ምሥራቅ ፈጽሞ ያጠፋችኋቸውን"
ሁለቱን የአሞራውያን ነገሥታት፣

1፥14 ዘፀ13፥18፤ዘኍ32፥26፤ዘዳ3፥19፤ኢሱ 4፥12
1፥15 ዘኍ32፥20-22፤ ኢሱ22፥1-4
1፥16 ዘኍ27፥20፤ 32፥25
1፥17 ዘኍ27፥20
1፥18 ዘኍ32፥25፣ ዘዳ1፥21፤31፥6
2፥1 ቊ4፤ዘፍ42፥9፤ ዘኍ21፥32፤25፥1፤ 33፥48፤ኢሱ3፥1፤6፥ 17፡25፤መሳ18፥2፤ ኢል3፥18፤ዕብ11፥31
2፥3 ኢሱ6፥23
2፥4 ቊ1፤ኢሱ6፥ 17:22
2፥5 መሳ5፥8፤9፥35፤ 16፥2፤ዕብ11፥31
2፥6 ዘፀ1፥19፤ኢሱ 6፥25፤መሳ15፥14፤ 2ሳሙ17፥19፤ምሳ31፥ 13፤ኢሳ19፥9፤
2፥7 ቊ16:22፤ዘኍ 22፥1፤መሳ3፥28፤7፥ 24፤12፥5፡6፤ኢሳ16፥2
2፥8 ዘዳ22፥8፤መሳ 16፥27፤2ሳሙ16፥22፤ ነህ8፥16፤ኢሳ15፥ 3፤22፥1፤ኤር32፥29
2፥9 ዘፍ35፥5፤ ዘፀ15፥14
2፥10 ዘፍ8፥1፤10፥ 16፤14፥7፤ዘፀ14፥ 21፤ዘኍ21፥2:21፤ 23፥22፤ኢሱ3፥17፤ 9፥10፤መዝ74፥15

^1 ምናልባትም፣ *የሆቴል ቤት* ተጠቃሚ *10 ዕብራይስጡ *ያም ሰመፍ* ይላል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው::
"10 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው::

1፥14 *ተዋጊዎቻችሁ … ከነሙሉ ትጥቃቸው፤* ዕድሜያቸው ከሃያ ዓመት በላይ (ለምሳሌ ዘፀ 38፥26 ይመ) የሆነ የጦር መሣሪያ መሸከም የሚችሉትንና ጠረኞች የሆኑትን ማለት ነው::

1፥18 *የሚያምፅ … ሁሉ፤* ሕዝበ እስራኤል ኢያሱ ከተናገረው ጋር ሙሉ በሙሉ የተቀበሉ መሆናቸውን በመሐላ ካረጋገጡ በኋላ የተናገረውን ቃል የማይፈጽም ሰው በመካከላቸው ቢኖር፣ በሞት እንዲቀጣ ተስማሙ (ለምሳሌ የአካን ሞት፤ 7፥15):: *ጽና፤ አይዞህ* ሕዝቡ ኢያሱን ያበረታታበት ቃል፣ እግዚአብሔር ኢያሱን ለማበረታታት የተናገረውን ቃል የሚያንጸባርቅና የሚያጠናክር ነው (ቍ 6-7:9)::

*2፥1-24፤* የሁለቱን ሰላዮች ተልእኮና የረዓብን ታሪክ የያዘ ክፍል ነው:: እንደ ጦርነት ሁሉ ስለላም ረጅም ዕድሜ አለው (ከመሳ 7፥10-11፤ ከ1ሳሙ 26፥16 ጋር ያነጻጽሩ):: ረዓብ የእስራኤልን አምላክ የምታመልክና በዕብራውያንም መካከል የምትታወቅ ሴት ሆነች:: በአዲስ ኪዳንም ስለ እምነቷና (ዕብ 11፥31) ስለ መልካም ሥራዋ (ያዕ 2፥25) ተመስግናለች::

2፥1 *ከሰጢም … ላከ፤* ውጊያው የሚካሄደው በዮርዳኖስና በኢያሪኮ ትይዩ በሚገኘው የሞዓብ ምድር ላይ ነው (ዘኍ 33፥48-49):: “ሰጢም” የሚለው የዕብራይስጡ ቃል “የግራር እንጨት” ማለት ሲሆን፣ የሚገኘውም ከፊል በረሓማ በሆኑ አካባቢዎች ነው:: በተለይም የኢያሪኮን ከተማ፤ ሰላዮቹ በተለየ ሁኔታ እንዲያጠኗት ተደርጓአል:: ኢያሪኮ በግንብ የተቀጠረች፣ ዘወትር ለምንቷን ጠብቃ እንድትኖር የሚያስችላት የውሃ ምንጭ ያላትና ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ ከተማ ናት:: ስሟ፣ “የጨረቃ ከተማ” የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል፤ የሥነ ቅርስ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ከተማዋ ከ7000 ዓ.ቅ.ክ ወዲህ ለበርካታ ጊዜ ስትወረር ኖራለች:: *ጋለሞታ፤* ጆሴፈስና ሌሎች የጥንት ጸሐፊዎች እንደሚያመለክቱት፣ ረዓብ “ባለ ቡና ቤት” ናት:: ይሁን እንጂ ዕብ 11፥31፤ ያዕ 2፥25 ይመ::

2፥2 *የኢያሪኮ ንጉሥ፤* የከነዓን ዋና ዋና ከተሞች የየራሳቸው መንግሥት የነበራቸው ሲሆን፣ ለያንዳንዳቸውም ንጉሥ ነበራቸው (በዐሥራ አራተኛው ምዕተ ዓ.ቅ.ክ የተጻፉት “የአማርኛ ደብዳቤዎች” ይህንኑ ያረጋግጣሉ)::

2፥6 *የተልባ እግር ውስጥ ደብቃቸው ነበር፤* በመካከለኛው ምሥራቅ፣ የቤት ጣራዎች እስከ ዛሬ ድረስ የእህልና የአገዳ ማስጫ በመሆን ያገለግላሉ:: ረዓብ ሁለቱን የእስራኤል ሰዎች ከሞት ያተረፈችው፣ የራስዋን ሕይወት ለአደጋ በማጋለጥ ነው::

2፥7 *ዮርዳኖስ መሻገሪያ፤* መሻገሪያው የወንዙ ጥልቀት እጅግ አነስተኛ በሆነበት፣ ከበዛም ሦስት ጫማ ያህል ብቻ ከፍ በሚልበት መልካ በኩል ነው::

*2፥8-11፤* የረዓብ እምነት አንድ ጕዳይ ላይ የሚያተኵር መዋቅር አለው፣

ሀ. “ዐውቃለሁ”
ለ. “በዚህች አገር የምንኖረው … ታላቅ ፍርሃት ያሳደራችሁብን … ”
ሐ. “ሰምተናል”
ለለ. “ልባችን ቀለጠ”
ሀሀ. “እግዚአብሔር አምላካችሁ… አምላክ ነውና”

የረዓብ እምነት ውጫዊውን ሁኔታ ይገልጻል፤ (ሀ. - ሀሀ.)፤ ውስጣዊው ሁኔታ (ለ.-ለለ) ሰላዮቹ ተመልሰው ለኢያሱ ያቀበሉትን ወታደራዊ መረጃ ይገልጻል፤ የመዋቅሩ እምብርት ደግሞ (ሐ፤ ቍ 10) የከነዓናውያንን ልብ ያቀለጠውንና ረዓብ ከነዓንንና የከነዓናውያንን አማልክት ትታ የእስራኤልን አምላክ ያህዌን እንድትቀበል ያደረጋትን ዜና ባጭሩ ይዞአል:: ረዓብ በእግዚአብሔር ላይ ያላት እምነትና እግዚአብሔር በኀያላን ጠላቶች ላይ ስለ ተቀዳጀው ድል ያገኘችው ትክክለኛ ዜና አስገራሚ ነው:: የከነዓናውያን ልብ “በፍርሃት መቅለጥን” መስማት (ቍ 9) ለሰላዮቹ እጅግ ጠቃሚ መረጃ ነበር::

2፥10 *ፈጽሞ ያጠፋችኋቸውን፤* አማራጭ ትርጒሙን ይመ::

ሴዎንንና ዐግን ምን እንዳደረጋችኋቸው
ሰምተናል:: 11ይህን በሰማን ጊዜ ልባችን
ቀለጠ፤ እናንተን ከመፍራት የተነሣም ያል
ተሸበረ ሰው አልነበረም፤ *እግዚአብሔር* ስም
ላካችሁ በላይም በሰማይ፣ በታችም በምድር
እርሱ ስምላክ ነውና:: 12እንግዲህ እኔ በጎነ
ትን እንዳሳየኋችሁ ሁሉ፣ እናንተም በጎነ
ትን ለአባቴ ቤት እንድታሳዩ *በእግዚአብሔር*
*ማሉልኝ፤ መተማመኛ የሚሆን ምልክትም*
ስጡኝ፤ 13የአባቴንና የእናቴን፣ የወንድሞ
ቼንና የእኅቶቼን እንዲሁም የእነርሱ የሆነ
ውን ነፍስ ሁሉ እንድታተርፉልኝ፤ ከሞትም
አድኑን::"

14ሰዎቹም፣ "የእናንተን ሞት ለእኛ ያድ
ርገው! እኛ የምናደርገውን ሁሉ ካልተናገራ
ችሁ፣ *እግዚአብሔር ምድሪቱን በሚሰጠን ጊዜ*፣
*በጎነትና ታማኝነት* እናሳይሻለን" አሏት::

15*መኖሪያ ቤቷ የከተማውን ቅጥር ተጠግቶ*
*የተሠራ ስለ ነበር*፣ ሰዎቹን በመስኮት አሾ
ልካ በገመድ አወረደቻቸው:: 16እርሷም፣
"የሚከታተሏችሁ ሰዎች እንዳያገኟችሁ፣ ወደ
ኰረብታዎቹ ሂዱ፤ እነርሱ እስኪመለሱም
ድረስ ሦስት ቀን በዚያ ተሸሸጉ፤ ከዚያ
በኋላ መንገዳችሁን ትቀጥላላችሁ" አለቻ
ቸው::

17ሰዎቹም እንዲህ አሏት፤ "ባማልሽን
በዚህ መሐላ የምንያዘው፣ 18ወደ ምድሪቱ
በገባን ጊዜ፣ ይህን ቀይ ፈትል እኛን ባወረ
ድሽበት መስኮት ላይ አስረሽ ካንጠለጠል
ሽው፣ እንዲሁም አባትሽንና እናትሽን፣
ወንድሞችሽንና የአባትሽን ቤተ ሰዎች ሁሉ
ወደ ቤትሽ ካመጣሻቸው ብቻ ነው:: 19ማንም
ከቤትሽ ወጥቶ መንገድ ላይ ቢገኝ፣ ደሙ

2፥11 ዘፍ14፥19፤ 42፥28፤ዘፀ15፥14፤ ዘኍ20፥14፤ዘዳ2፥25፤ ኢሱ5፥1፤7፥5፤2ሳሙ 4፥1፤2ነገ5፥15፤ 19፥15፤መዝ22፥14፤1 07፥26፤ኢሳ13፥7፤ 19፥1፤ኤር51፥30፤ዳን 6፥26፤ዮና1፥5 ናሆ2፥10፤
2፥12 ዘፍ24፥8:12: 14፤47፥31፤ዘፀ3፥12፤ ኢሱ4፥6፤ሩት3፥10፤ 1ሳሙ2፥34፤2ነገ19፥29
2፥13 ቁ18፤ኢሱ 6፥23
2፥14 ዘፍ47፥29፤1ነገ 20፥39:42፤2ነገ10፥24
2፥15 ቁ18:21፤ዘፍ 26፥8፤መሳ5፥28፤ 1ሳሙ19፥12፤ኤር 38፥6:11
2፥16 ቁ7:22፤ዘፍ 14፥10፤ ዕብ11፥31
2፥17 ዘፍ24፥8
2፥18 ቁ13:15:21
2፥19 ዘሌ20፥9፤ ማቴ27፥25
2፥20 ዘፍ24፥8፤ 47፥31
2፥21 ቁ15:18
2፥22 ቁ7:16
2፥24 ዘፀ15፥15፤ኢሱ 10፥8፤11፥6፤መሳ3፥2 8፤7፥9:14፤20፥28፤1 ሳሙ14፥10
3፥1 ዘፍ13፥10፤ኢሱ 2፥1፤ኢዮ40፥23
3፥2 ዘፍ40፥13፤ዘዳ 1፥15፤ኢሱ1፥11፤2፥16
3፥3 ቁ8:17፤ዘኍ 4፥15፤10፥33፤ዘዳ31፥ 9፤1ሳሙ6፥15፤ 1ነገ8፥3
3፥4 ዘኍ35፥5

በራሱ ላይ ነው፤ እኛ አንጠየቅበትም፤ ነገር
ግን ከአንቺ ጋር እቤት ውስጥ ያለ ማንኛ
ውም ሰው ከተነካ የደሙ ባለ ዕዳ እኛ እንሆ
ናለን:: 20እኛ የምናደርገውን ብትናገሪ ግን፣
ካስማልሽን መሐላ ነጻ እንሆናለን::"

21እርሷም፣ "ይሁን፤ ባላችሁት ተስማም
ቻለሁ" ስትል መለሰች፤ ከዚያም ሰደደቻ
ቸው፤ እነርሱም ሄዱ፤ ቀይ ፈትሉንም
በመስኮቷ ላይ አንጠለጠለችው::

22እነርሱም ወጥተው ወደ ኰረብቶቹ
ሄዱ፤ የሚከታተሏቸውም ሰዎች በየመንገዱ
ሁሉ ላይ ፈልገውና አጥተው እስኪመለሱ
ድረስ፣ ሦስት ቀን በዚያው ተሸሸጉ::
23ሁለቱም ሰላዮች ተመለሱ፤ ከኰረብቶቹም
ወርደው ወንዙን በመሻገር፣ ወደ ነዌ ልጅ
ወደ ኢያሱ መጥተው ያጋጠማቸውን ነገር
ሁሉ ነገሩት:: 24ለኢያሱም፣ "በእርግጥ *እግዚ*
*አብሔር* ምድሪቱን በሙሉ በእጃችን አሳ
ልፎ ሰጥቶናል፤ በዚያ የሚኖረውም ሕዝብ
ሁሉ እኛን ከመፍራቱ የተነሣ ልቡ
መቅለጡን አይተናል" አሉት::

## እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ተሻገሩ

3 ኢያሱም ማልዶ ተነሣ፤ ከእስራኤላውያ
ንም ሁሉ ጋር ከሰጢም ወደ ዮርዳኖስ
መጥተው፣ ወንዙን ከመሻገራቸው በፊት
በዚያ ሰፈሩ:: 2ከሦስት ቀን በኋላም የጦሩ
አለቆች በሰፈር ውስጥ አለፉ፤ 3ሕዝቡንም
እንዲህ ሲሉ አዘዙ፤ "ሌዋውያን ካህናቱ
የአምላካችሁን *የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን*
*ታቦት* ተሸክመው ስታዩ፣ ከስፈራችሁ ተነ
ሥታችሁ ታቦቱን ተከተሉ፤ 4ካሁን በፊት
በዚህ መንገድ ሄዳችሁ ስለማታውቁ፤ በየት
በኩል መሄድ እንዳለባችሁ በዚህ ትረዳላችሁ፤

2፥12 *በጎነትን ለአባቴ ቤት እንድታሳዩ፤* "በጎነትን" የሚለውን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል አብዛኛውን ጊዜ "ፍቅር" ወይም "ዘላለማዊ ፍቅር" ተብሎ የተተረጐመ ሲሆን፣ ቃሉ ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚገልጸውን ኪዳናዊ ፍቅር ወይም ሰዎች ለሌሎች ማሳየት የሚገባቸውን ፍቅር ነው:: ረዓብ ሰላዮቹን የተቀበለቻቸው ልክ እንደ አንዲት እስራኤላዊት ሆና ነው፤ እዚህ ላይ እነርሱም በበኩላቸው እርሷን እንደ እስራኤላዊት እንዲያዩአት ትለምናለች:: *መተማመኛ የሚሆን ምልክትም፤* ቤተ ሰቧን በሙሉ ለማትረፍ በመሐላ ቃል ገቡላት (ቍ 14)::

*2፥14፤* "ቃላችንን ያልጠበቅን እንደሆነ እኛ በአንቺ ምትክ እንሙት" ማለታቸው ነው:: *በጎነትና ታማኝነት፤* ሰላዮቹ የገቡት ቃል ረዓብ በቍ 12 ላይ የጠየቀችውን የሚያዘክር ነው:: *እግዚአብሔር ምድሪቱን በሚሰጠን ጊዜ፤* እስራኤላውያን በኢያ ሪኮ ከተማ ላይ ድል እንደሚጎናጸፉ እርግጠኞች ሆነዋል::

*2፥15 የመኖሪያ ቤቷ የከተማውን ቅጥር ተጠግቶ የተሠራ ስለ ነበር፤* የኢያሪኮ ከተማ ነዋሪዎች ቤቶቻቸውን የሚሠሩት ከከተ ማው ቅጥር ጋር አያይዘው እንደሆነ የሥነ ቅርስ ጥናት መረጃዎች ያመለክታሉ:: ይህ መረጃ ከኢያሱ ዘመን በፊት ይሠሩ የነበሩትን ቤቶች የሚያመለክት ቢሆንም፣ ስለዚህ ቅርስ በሚገባ እንድንረዳ አስተዋ ጽኦ ያደርጋል:: ባንጻሩም በጥንት ዘመን የሚሠሩ ቅጥሮች በውስጥ በኩል ለመኖሪያ የሚያገለግሉ ክፍሎች ያሏቸው ስለሆነ፣ ረዓብ ምናልባት ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ አንዱን ወይም ሁለቱን ሳትይዝ አትቀርም::

2፥18 *ይህን ቀይ ፈትል ... መስኮት ላይ፤* የዚህ ቀይ ፈትል ምልክት አገልግሎት፣ እግዚአብሔር የግብፅን በኵራት በመታ ጊዜ የፋሲካው በግ ደም ከሰጠው አገልግሎት ጋር ተመሳሳይ ነው (ዘፀ 12፥13፡ 22-23 ይመ):: የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የደም መልክ ያለውን ፈትል የክርስቶስ የሥርየት መሥዋዕት አምሳል አድርጋ ትመለከተው ነበር::

2፥19 *የደሙ ባለ ዕዳ እንሆናለን፤* በሌላ ሰው ሞት በኀላፊነት ተጠያቂ ለመሆን የሚቀርብ መሐላ ነው::

2፥22 *ወደ ኰረብቶቹ፤* ከጥንታዊቷ የኢያሪኮ ከተማ በስተ ምዕራብ በኩል የሚገኘው ስፍራ ተራራማና ሸለቆአማ በመሆኑ ሁለቱን ሰላዮች ካሳዳጆቻቸው በቀላሉ እንዲያመልጡ አስችሉአቸዋል::

*3፥1-4፥24፤* እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገራቸውንና ጌልገላ በሚገኘው ሰፈር የመታሰቢያ ድንጋዮች መተከላቸውን የሚያወሳ ክፍል ነው:: ይህ ክፍል እስራኤላውያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ለመግባት የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገራቸውን ስለሚጠቅስና ከግብፅ ወጥተው "ቀይ ባሕርን" ሲሻገሩ በባሕሩ ላይ ከተፈጸመው ታምር ጋር ስለሚነጻጸር (ዘፀ14-15) የታሪኩን ታላቅነት አጕልቶ ማሳየት ተገቢ ነው:: የእስራኤላውያን እምነት በጽኑ ሊፈተን በተቃረበ ጊዜ፣ በአባቶቻቸው አምላክ ላይ ያላቸው እምነት እየታደሰና እየጠ ነከረ ሄደ፤ ባንጻሩ ከነዓናውያን በታላቅ ፍርሃት እየተዋጡ መጡ (5፥1):: የዚህ ታሪክ ጸሓፊ ልዩ የአጻጻፍ ስልት በመጠቀም እስራ ኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ እንዴት እንደተሻገሩ የሚገልጸውን ትረካ ከደመደመ በኋላ (ም3)፣ በተፈጸመው ሁነት ውስጥ ወዳሉት ነጥቦች በመመለስ በርካታ ዝርዝር ሐሳቦችን ያቀርባል፤ እነዚህም ዝር ዝር ሐሳቦች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤ ስለ መታሰቢያ ድንጋዮች (4፥1-9)፤ መላው እስራኤል ዮርዳኖስን ስለ መሻገሩ (4፥10-14)፤ እስራኤላውያን ከተሻገሩ በኋላ ወንዙ እንደቀድሞው መውረድ ስለ መቀጠሉ (4፥15-18):: ምዕራፍ 4 በመጨረሻው አንቀጽ (ቍ 19-24) በ3፥17 ላይ የተነገረውን ታሪክ መነሻ አድርጎ እስራኤላው ያን በጌልገላ መስፈራቸውንና የመታሰቢያ ድንጋይ ማቆማቸ ውን በማውሳት ይደመድማል::

3፥3 *የቃል ኪዳን ታቦት፤* በመገናኛው ድንኳን ከሚገኙት ሁሉ እጅግ የተቀደሰ ነው (ዘፀ 25፥10-22 ይመ):: ታቦቱ የእግዚ አብሔርን ዙፋን የሚያመለክት በመሆኑ፣ ሕዝቡን ወደ ዕረፍት ምድር እየመራቸው ሳለ እግዚአብሔር ራሱ ከእነርሱ ፊት በመሆን ወደ ዮርዳኖስ ገባ (ዘኍ 10፥33-36 ይመ)::

3፥4 *የሁለት ሺህ ክንድ ያህል ርቀት፤* እስራኤላውያን በካህናቱና በታቦቱ መሪነት በሰልፍ ይጓዙ እንደ ነበር ያመለክ ታል:: ታቦቱን በተሸከሙት ካህናትና በሕዝቡ መካከል የተወሰነ

ሆኖም በታቦቱና በእናንተ መካከል የሁለት
ሺህ ክንድ[ሠ] ያህል ርቀት ይኑር፤ ወደ ታቦ
ቱም አትቅረቡ።"
5ከዚያም ኢያሱ ሕዝቡን፣ "በነገው ዕለት
እግዚአብሔር በመካከላችሁ አስደናቂ ነገር
ስለሚያደርግ ራሳችሁን ቀድሱ" አላቸው።
6ኢያሱም ካህናቱን፣ "የቃል ኪዳኑን ታቦት
ተሸክማችሁ ሕዝቡን ቀድማችሁ ሂዱ" አላ
ቸው፤ እነርሱም ታቦቱን ተሸክ መው ሕዝ
ቡን ቀድመው ሄዱ።
7እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለው፤
"ከሙሴ ጋር እንደ ነበርሁ ሁሉ፣ ከአንተም
ጋር መሆኔን ያውቁ ዘንድ፣ በእስራኤል ሁሉ
ፊት አንተን ከፍ ከፍ ማድረጌን በዛሬዋ ዕለት
እጀምራለሁ፡ 8የቃል ኪዳኑን ታቦት የሚሸከሙ
ትንም ካህናት፣ 'ከዮርዳኖስ ውሃ ዳር ስትደርሱ፣
በወንዙ ውስጥ ገብታችሁ ቁሙ' በላቸው።"
9ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝብ "ወደዚህ
ቀርባችሁ፣ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል
ስሙ" አላቸው፤ 10እንግዲህ ሕያው አምላክ
በመካከላችሁ መሆኑንና እርሱም በእርግጥ
ከነዓናውያንን፣ ኬጢያውያንን፣ ኤዊያውያንን፣
ፌርዛውያንን፣ ጌርጌሳውያንን፣ አሞራውያን
ንና ኢያቡሳውያንን ከፊታችሁ እንዴት
አድርጎ እንደሚያሳድዳቸው የምታውቁት
በዚህ ነው። 11እነሆ፤ የምድር ሁሉ ጌታ የቃል
ኪዳኑ ታቦት ቀድሞአችሁ ወደ ዮርዳኖስ
ይገባል። 12እንግዲህ ከእስራኤል ነገዶች ዐሥራ
ሁለት ሰው ምረጡ፤ ከየነገዱም አንዳንድ
ሰው ይሁን። 13የምድርን ሁሉ ጌታ የእግዚ
አብሔርን ታቦት የተሸከሙት ካህናት ገና
እግራቸውን በዮርዳኖስ ውሃ ውስጥ እንዳስገቡ፣
ቍልቍል የሚወርደው ውሃ ወዲያውኑ ይቋ
ረጣል፤ እንደ ክምርም ሆኖ ይቆማል።"
14ስለዚህ ሕዝቡ ዮርዳኖስን ለመሻገር ሰፈሩን
ለቀው ሲወጡ፣ የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸ
ከሙት ካህናት ከፊታቸው ቀድመው ሄዱ።
15ወቅቱም የመከር ጊዜ በመሆኑ፣ የዮርዳ
ኖስ ወንዝ ሞልቶ ነበር፤ ታቦቱን የተሸከ
ሙት ካህናት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በደረሱ
ጊዜ እግራቸው ውሃውን እንደነካ፣ 16ከላይ
የሚወርደው ውሃ ቆመ፤ በጻርታን አጠገብ
"አዳም" ተብላ እስከምትጠራው ሩቅ ከተማ
ድረስ በመከማቸት እንደ ክምር ተቈለለ፤
ቍልቍል ወደ ዓረባ ጨው ባሕር[ረ] የሚወ
ርደውም ውሃ ፈጽሞ ተቋረጠ፤ ሕዝቡም
ከኢያሪኮ ትይዩ ባለው አቅጣጫ ተሻገሩ።
17የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት
የተሸከሙት ካህናትም፣ ሕዝቡ ሁሉ ማለትም
እስራኤል በሙሉ ፈጽመው እስኪሻገሩ ድረስ፣
በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል በደረቁ ምድር
ላይ ቀጥ ብለው ቆመው ነበር።

4 ሕዝቡ ሁሉ ዮርዳኖስን ከተሻገረ በኋላ፣
እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው፤
2"ከሕዝቡ መካከል ከየነገዱ አንዳንድ ሰው፣
በድምሩ ዐሥራ ሁለት ሰው ምረጥ፤ 3እንዲ
ሁም ከዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ልክ ካህናቱ
ከቆሙበት ስፍራ ዐሥራ ሁለት ድንጋይ
አንሥተው በመሸከም ከእናንተ ጋር እንዲ
ሻገሩና ዛሬ በምታድሩበት ቦታ እንዲ
ያኖሯቸው ንገራቸው።"
4ስለዚህ ኢያሱ ከእያንዳንዱ የእስራኤል
ነገድ የሾማቸውን ዐሥራ ሁለት ሰዎች ጠራ፤
5እንዲህም አላቸው፤ 'ከአምላካችሁ ከእግዚአብሔር
ታቦት ፊት ቀድማችሁ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ
መካከል ዕለፉ፤ እያንዳንዳችሁም በእስራኤል
ነገድ ቍጥር አንዳንድ ድንጋይ በትከሻችሁ ተሸ
ከሙ፤ 6ይህም በመካከላችሁ ምልክት እንዲሆና
ችሁ ነው። ወደ ፊት ልጆቻችሁ፣ 'እነዚህ ድን
ጋዮች ምንድን ናቸው?' ብለው ቢጠይቋችሁ፣

3፥5 ዘፀ29፥1፤ዘሌ 11፥44፤መሳ6፥13፤ 1ዜና16፥9:24፤መዝ2 6፥7፤75፥1
3፥6 ኢሱ1፥5፤4፥14፤ 1ዜና29፥25
3፥8 ቍ3
3፥10 ዘፍ26፥34፤ዘፀ 3፥8፤23፥23፤ዘዳ5፥26 ፤7፥1:21፤ኢሱ9፥1፤ 11፥3፤12፥8፤17፥15፤ 24፥11፤መሳ1፥4፤3፥5፤ 19፥11፤1ሳሙ17፥26: 36፤2ነገ19፥4:16፤1ዜና 11፥4፤መዝ18፥46፤42 ፥2፤84፥2፤ኢሳ37፥4: 17፤ኤር10፥10፤23፥ 36፤ዳን6፥26፤ሆሴ1፥ 10፤ማቴ16፥16፤
3፥11 ቍ13፤ዘፀ19፥ 5፤ዘዳ9፥3፤10፥14፤ ኢዮ9፥10፤28፥24፤ 41፥11፤መዝ50፥12፤9 7፥5፤ዘካ6፥5
3፥12 ኢሱ4፥2:4
3፥13 ቍ11:16፤ዘፀ 14፥22፤ኢሱ4፥7፤ ኢሳ11፥15
3፥14 መዝ132፥8፤ ሐሥ7፥44-45
3፥15 ዘፍ8፥22፤ ኢሱ4፥18፤2ነገ2፥6፤ 1ዜና12፥15፤ኢሳ8፥7፤
3፥16 ቍ13፤ዘፍ 14፥3፤8፥1፤ዘፀ14፥22፤ ዘዳ1፥1፤ኢዮ 38፥37፤ 1ነገ4፥12፤7፥46፤2ነገ 2፥4፤መዝ33፥7፤66፥6 ፤74፥15፤114፥3
3፥17 ቍ3፤ዘፀ 14፥22፤ኢሱ2፥10፤ 4፥3:5:8:9:10
4፥1 ዘዳ27፥2
4፥2 ኢሱ3፥12
4፥3 ቍ19:20፤ ኢሱ 3፥17
4፥4 ኢሱ3፥12
4፥5 ኢሱ3፥17
4፥6 ቍ21፤ ዘፀ10፥2፤12፥26፤

[ሠ]4 የዕብራይስጡ ትርጒም 900 ሜትር ይላል።
[ረ]16 የሙት ባሕር ነው።

ርቀት እንዲኖር የተደረገው፣ የእግዚአብሔር ህልዎት መገኛ ምሳሌ ለሆነው ለተቀደሰው ታቦት ክብር መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት ነው።

3፥5 *ራሳችሁን ቀድሱ፤* እስራኤላውያን በሲና ተራራ ላይ በእግዚአብሔር ፊት ከመቅረባቸው በፊት አስቀድሞ ራሳቸውን ሲቀድሱ፣ ልብሳቸውንና ሰውነታቸውን በሙሉ መታጠብ ነበረባቸው፤ ከዚህም በተጨማሪ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መቈጠብ አለባቸው (ዘፀ 19፥10:14-15 ይመ)።

3፥7 *አንተን ከፍ ከፍ ማድረጌን ... እጀምራለሁ፤* እግዚአብሔር በዮርዳኖስ ወንዝ ላይ ታላቅ ኀይሉን የገለጠው የኢያሱን አመራር እስራኤላውያን እንዲቀበሉት ለማድረግ ነው። "ቀይ ባሕር" ለሁለት በተከፈለ ጊዜ ከታየው ታምር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ታምር እዚህም ላይ የተፈጸመው፣ እንደ ሙሴ ሁሉ ኢያሱም የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።

3፥10 *የምታውቁት በዚህ ነው፤* እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ የዮርዳኖስን ወንዝ እንዲሻገር የሚያደርግበት መንገድ ብቸኛውና እውነተኛው አምላክ ከእስራኤል ጋር እንደ ሆነና ከነዓናውያንን ከምድሪቱ እንደሚነቃቅል ያረጋግጣል። እዚህ ላይ ሁለት ወሳኝ ጥያቄዎች ይነሣሉ፤ (1) ኀያልና እውነተኛ የሆነው አምላክ ማን ነው? የእስራኤል አምላክ ወይስ ከነዓናውያን የሚያመልኩት በኣል (የባሕር አምላክን ድል ነሥቶ የአማልክት ሁሉ ንጉሥ ለመሆን በቅቶአል ብለው የሚታመኑበት) እግዚአብሔር እጅግ የሞላውን የዮርዳኖስን ወንዝ ለሁለት ከፍሎ ሕዝቡን እንዲሻገሩ በማድረግ በውሆች ላይ ጌታ መሆኑን ("በቀይ ባሕር"፣ በጥፋት ውሃና በፍጥረት ጊዜ እንዳደረገው) እና በዓለም ላይ የገዛ ራሱን ሥርዐት መመሥረት እንደሚችል አሳየ፤ 1ነገ 20፥23፤ 2ነገ 18፥32-35 ይመ። (2) ምድሪቱ የማን ናት? የጌታ ወይስ የከነዓናውያን? (መሳ 11፥27 ይመ)። እግዚአብሔር በሰራዊቱ ፊት የዮርዳኖስን ወንዝ ለሁለት ከፍሎ በማለፉ ምድሪቱ ለእርሱ እንደምትገባ አረጋገጠ። *ከነዓናውያንን ... ኢያቡሳውያንን፤* የዘፍ 9፥25፤ 10፥6: 15-16፤ 13፥7፤ 15፥16፤ 23፥3፤ ዘፀ 3፥8፤ የመሳ 3፥3፤ 6፥10 ማብ ይመ።

3፥12 *ዐሥራ ሁለት ሰው ምረጡ፤* የመታሰቢያ ድንጋይ እንዲያቆሙ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትእዛዝ ኢያሱ ከወዲሁ የተረዳው ይመስላል (4፥2-3 ይመ)።

3፥13 *ይቋረጣል፤* ወንዙ መውረዱን ያቆማል ለማለት ነው። *እንደ ክምርም ሆኖ ይቆማል፤* "ክምር" የሚለውን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል እዚህና ቍ 16 ላይ እንዲሁም ሙሴና የእስራኤል ሕዝብ ቀይ ባሕርን ከተሻገሩ በኋላ በዘመሩት መዝሙር ውስጥ (ዘፀ 15፥8፤ መዝ 78፥13) ይገኛል።

3፥15 *ሞልቶ ነበር፤* ወንዙ ሊሞላ የቻለው በጸደዩ ወራት ከዘነበው ዝናብና ከአርሞንዔም ተራራ ላይ እየቀለጠ ከሚወርደው የበረዶ ውሃ የተነሣ ነው። *መከር፤* መከር የሚሰበሰበው በሚያዝያና በግንቦት ወራት ነው።

3፥17 *ታቦት የተሸከሙት ካህናት ... በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል በደረቁ ምድር ላይ ቀጥ ብለው ቆመው ነበር፤* እስራኤላውያን በሙሉ እስኪሻገሩ ድረስ እግዚአብሔር ራሱ ባደገኛው ስፍራ ላይ መቆሙን ያመለክታል።

4፥3 *ዛሬ በምታድሩበት ቦታ፤* ሕዝቡ በሙሉ ዮርዳኖስን የተሻገረው በአንድ ቀን መሆኑን ያመለክታል።

4፥6 *እነዚህ ድንጋዮች ምንድን ናቸው?* የመታሰቢያ ድንጋዮች የሚቆሙት ወደፊት የሚነሣው ትውልድ በዚያ ስፍራ ምን እንደ ተደረገ እንዲያስታውስ ነው፤ የድንጋይ ሐውልቶችን ለዚህ ዓላማ

7የዮርዳኖስ ወንዝ በእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ
ታቦት ፊት መቆሙን፤ እንዲሁም ታቦቱ የዮርዳ
ኖስን በሚሻገርበት ጊዜ፣ የዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ
መቆሙን፣ እነዚህ ድንጋዮች ለእስራኤል ሕዝብ
የዘላለም መታሰቢያ መሆናቸውን ንገሯቸው::"
8እስራኤላውያንም ኢያሱ እንዳዘዛቸው
አደረጉ፤ እግዚአብሔር ለኢያሱ በነገረውም
መሠረት፣ በእስራኤል ነገዶች ቍጥር ልክ ዐሥራ
ሁለት ድንጋዮች ከዮርዳኖስ ወንዝ መካከል
አነሡ፤ ወደ ሰፈራቸውም ይዘው በመሻገር
በዚያ አኖሯቸው:: 9ኢያሱም የቃል ኪዳኑን
ታቦት የተሸከሙት ካህናት ቆመውበት በነበ
ረው በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ሌሎች ዐሥራ
ሁለት ድንጋዮችን አቆመ፤ እነዚህም ድንጋዮች
እስከ ዛሬ ድረስ[a] በዚሁ ስፍራ ይገኛሉ::
10ሙሴ ለኢያሱ በሰጠው መመሪያ መሠ
ረት፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲነግር ኢያ
ሱን ያዘዘው እስኪፈጸም ድረስ፣ ታቦቱን
የተሸከሙት ካህናት በዮርዳኖስ መካከል
ቆመው ቈዩ፤ ሕዝቡም ፈጥነው ተሻገሩ፤
11ሕዝቡ ሁሉ ተሻግረው እንዳበቁ፣ የእግዚ
አብሔር ታቦትና ካህናቱ፣ ሕዝቡ እያዩአ
ቸው ተሻገሩ:: 12የሮቤል ነገድና የጋድ ነገድ፣
የምናሴም ነገድ እኩሌታ ሙሴ ባዘዛቸው
መሠረት፣ የጦር መሣሪያቸውን ይዘው ከእ
ስራኤላውያን ፊት ቀድመው ተሻገሩ:: 13አርባ
ሺህ ያህሉ ጦርና ጋሻቸውን ይዘው፣ ለውጊያ
ዝግጁ ሆነው፣ በእግዚአብሔር ፊት ወደ
ኢያሪኮ ሜዳ ተሻገሩ::
14በዚያች ዕለት እግዚአብሔር ኢያሱን
በእስራኤል ሁሉ ፊት ከፍ ከፍ አደረገው፤
ሕዝቡ ሙሴን እንዳከበሩት ሁሉ፣ ኢያሱ
ንም በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አከበሩት::
15ከዚያም እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ
አለው፤ 16"የምስክሩን ታቦት የተሸከሙትን
ካህናት ከዮርዳኖስ ወንዝ እንዲወጡ እዘዛቸው::"
17ኢያሱም ካህናቱን "ከዮርዳኖስ ውጡ"
ብሎ አዘዛቸው::
18ካህናቱ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን
ታቦት ተሸክመው ከውሃው በመውጣት እግ
ራቸው ደረቁን መሬት ልክ ሲነካ የዮርዳ
ኖስ ውሃ ወደ ስፍራው ተመለሰ፤ እንደቀድ
ሞው ሁሉ ሞልቶ በዳሩ ሁሉ ይፈስ ጀመር::
19የመጀመሪያው ወር በገባ በዐሥረኛው
ቀን ሕዝቡ ዮርዳኖስን ተሻግሮ በኢያሪኮ
ምሥራቃዊ ዳርቻ በጌልገላ ሰፈረ:: 20ኢያ
ሱም ከዮርዳኖስ ወንዝ ያወጧቸውን ዐሥራ
ሁለት ድንጋዮች በጌልገላ ተከላቸው፤ 21እስ
ራኤላውያንንም እንዲህ አላቸው፤ "ልጆቻ
ችሁ ወደ ፊት፣ 'እነዚህ ድንጋዮች ምንድን
ናቸው?' ብለው አባቶቻቸውን ቢጠይቁ፣
22'እስራኤል ይህን ዮርዳኖስ በደረቅ ምድር
ተሻገረ' ብላችሁ ንገሯቸው፤ 23እኛ እስክንሻ
ገር ድረስ አምላካችሁ እግዚአብሔር ቀይ ባሕርን[b]
እንዳደረቀው ሁሉ እናንተም እስክትሻገሩ
ድረስ አምላካችሁ እግዚአብሔር የዮርዳኖስን
ወንዝ በፊታችሁ አደረቀው:: 24ይህን ያደረ
ገውም፣ የእግዚአብሔር ክንድ ብርቱ መሆ
ኑን የምድር ሕዝቦች ሁሉ እንዲያውቁና
እናንተም አምላካችሁን እግዚአብሔርን ለዘላለም
እንድትፈሩ ነው::"

## በጌልገላ የተደረገ ግዝረት

5 በዚህ ጊዜ ከዮርዳኖስ ማዶ በምዕራብ
በኩል ያሉት የአሞራውያን ነገሥታት
ሁሉ፣ በባሕሩም ዳርቻ ያሉ የከነዓናውያን
ነገሥታት በሙሉ እግዚአብሔር ዮርዳኖስን
እስክንሻገር ወንዙን በእስራኤላውያን ፊት
እንዴት እንዳደረቀው በሰሙ ጊዜ፣ ልባቸው
በፍርሃት ቀለጠ፤ እስራኤላውያንንም ለመቋ
ቋም ድፍረት አጡ::
2በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ኢያሱን፣ "የባል
ጩት መቍረጫ አዘጋጅተህ፣ ያልተገረዙ
ትን እስራኤላውያንን ለሁለተኛ ጊዜ ግረዛቸው"

13፥14፤ኢሱ2፥12
4፥7 ዘፀ28፥12፤ ኢሱ3፥13
4፥8 ቍ20፤ዘፀ 28፥21፤ኢሱ3፥17
4፥9 ዘፍ28፥18፤ 35፥20፤ኢሱ24፥ 26፤1ሳሙ7፥12፤
4፥12 ዘኁ29፥32፤ 30፥11፤41፥51፤ዘኁ 32፥27:29
4፥13 ዘፀ13፥18፤ ዘኁ32፥17
4፥14 ኢሱ3፥7
4፥16 ዘፀ25፥22
4፥18 ዘፀ14፥27፤ ኢሱ3፥15
4፥19 ዘጸ11፥30
4፥20 ቍ3:8
4፥21 ቍ6
4፥22 ዘፀ14፥22
4፥23 ዘፀ14፥19-22
4፥24 ዘፀ14፥31፤ 15፥16፤1ነገ8፥60፤18 ፥36፤2ነገ5፥15፤1ዜና2 9፥12፤መዝ44፥3፤67፥ 2፡83፥18፤89፥13፤98፥ 1፤106፥8፤118፥15-16፤ ኢሳ37፥20፤ 52፥10
5፥1 ዘፍ42፥28፤ ዘኁ13፥29
5፥2 ዘፍ17፥10:12: 14፤ዘፀ4፥25

[a]9 ወይም *ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች አቆመ* [b]23 *ዕብራይስጡ ያም ሱፍ* ይላል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው::

ማቆም በወቅቱ የተለመደ ተግባር ነበር (24፥26፤ 1ሳሙ 7፥12)::

4፥9 *ኢያሱ ... ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች አቆመ፤* እያን ዳንዱ ነገድ ለሐውልቱ መሥሪያ የሚሆን ድንጋይ ከወንዙ ዳር በመልቀም በጌልገላ ወደሚገኘው አዲሱ ሰፈር አመጣ፤ ኢያ ሱም ሐውልቱን በዚያ አቆመ:: አንዳንድ ትርጕሞች ኢያሱ ሁለ ተኛ ሐውልት በወንዙ መካከል አቆመ ይላሉ፤ አግራጌ ትርጕሙን ይመ::

4፥13 *አርባ ሺህ ያህል፤* ይህ አኀዝ በዘኍ 26 ላይ ከተጠቀሱት ከሮቤል፣ ከጋድና ከምናሴ እኩሌታ ሰዎች አኀዝ ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ይመስላል፤ ከየነገዱ የተውጣጣውን ሠራ ዊት የሚወክሉ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ምክንያቱም ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኙትን ሰዎች ያለጠባቂ መተው አግባብ አይደለም (በ22፥8 ላይ "ወንድሞች" ከተባሉትና ከዘኍ 32፥17 ጋር ያነጻጽሩ)::

4፥19 *የመጀመሪያው ወር በገባ በዐሥረኛው ቀን፤* የፋሲ ካው በግ የሚመረጠው በዚህ ዕለት ነው (ዘፀ 12፥3):: *ጌልገላ፤* አብዛኛውን ጊዜ ከኢያሪኮ ሦስት ኪሎ ሜትር ተኩል ርቃ ከምትገኘው ከቂርበት ኤል ማፈር ጋር አንድ ተደርጋ ትወሰዳለች::

4፥23 *እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ወንዝ ... አደረቀው፤* "ውሃው ተቋረጠ"፣ "እንደ ክምር ቆመ"፣ "ወንዙ መውረዱን አቆመ" (3፥16) የሚሉት በተጨማሪ በወንዙ ላይ የተደረጉትን ታምራት የሚገልጹ ናቸው::

4፥24 *ሁሉ እንዲያውቁ፤* "ቀይ ባሕርን" መሻገራቸውን እንዲ ሁም ሲዎንና ዖግን ድል ማድረጋቸውን እንደ ሰሙ ሁሉ፣ (2፥10) እግዚ አብሔር በእስራኤላውያን መካከል የገለጠው ኀይል ታላቅ መሆኑን ከነዓናውያን ሁሉ ሰምተዋል (5፥1 ይመ):: *እናንተም፤* ዕብራይስጡ "እነርሱም" ተብሉ ሊተረጐም ይችላል:: *እግዚአብሔርን ... እንድትፈሩ ነው፤* በትእዛዙ መሠረት እንዲያመልኩትና እንዲያገለግሉት ነው::

*5፥1-12፤* በሲና በተሰጠው ሕግ መሠረት፣ ሁለት የኪ ዳን በዓላት እንደ ገና በጌልገላ ተከብረዋል፤ እነዚህም በዓላት የግዝረትና የፋሲካ በዓላት ናቸው:: ሁለቱም በዓላት የተስፋዪቱን ምድር ለመውረስ ሕዝቡን የሚያዘጋጁ ናቸው::

5፥1 *የአሞራውያን ... የከነዓናውያን፤* አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ሁለት ስሞች ተወራራሽ ሲሆኑ፣ በምድሪቱ የሚኖሩ በርካታ ትናንሽ ሕዝቦችን የሚጨምሩ ናቸው:: አሞራውያን ማለት "ምዕራባውያን" ማለት ሲሆን፣ ከነዓናውያን የሚለው ደግሞ በሜድትራኒያን ባሕር ጠረፍ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦ ችን ያመለክታል:: ይህ ቍጥር፣ የዮርዳኖስ ወንዝ እንዴት ባለ ታምር እንደ ደረቀና ይህም ነገር በከነዓናውያን ላይ ያስከተለ ውን ጫና የሚገልጽ በመሆኑ፣ ወንዙን እንዴት እንደ ተሻገሩ የሚያወሣውን ታሪክ የሚያጠቃልል ሳይሆን አይቀርም (የ3፥10ን ማብ ይመ)::

5፥2 *የባልጩት መቍረጫ፤* ከብረት የተሠሩ መቍረ ጫዎች በዚያን ዘመን የነበሩ ቢሆንም፣ ዘመናዊ ሕክምና እንዳ ረጋገጠው፣ በተለይ ከባልጩት የተሠሩ መቍረጫዎች ለቀዶ ሕክ ምና ብቁ መሣሪያዎች ነበሩ:: እስራኤል ለውጊያ ከመውጣቷና የተስፋዪቱን ምድር ለመውረስ ከመሄዷ በፊት ለእግዚአብሔር

አለው:: 3ስለዚህ ኢያሱ የባልጩት መቍ
ረጫ አዘጋጅቶ በጊብዓዝ ዓረሎት* በተባለ
ስፍራ እስራኤላውያንን ገረዛቸው::
4እንግዲህ ኢያሱ እስራኤላውያንን የገረዘ
በት ምክንያት ይህ ነው፤ ዕድሜያቸው መሣ
ሪያ ለመያዝ የደረሱ ወንዶች ሁሉ ከግብፅ
ከወጡ በኋላ በመንገድ ላይ ሳሉ በምድረ
በዳ ሞቱ:: 5ከዚያ የወጡት ሰዎች ሁሉ
ተገርዘው ነበር፤ ከግብፅ ከወጡ በኋላ በም
ድረ በዳ በጕዞ ላይ ሳሉ የተወለዱት ግን
በሙሉ አልተገረዙም ነበር:: 6ግብፅን ለቀው
በወጡ ጊዜ መሣሪያ ለመያዝ የደረሱ ወንዶች
ሁሉ ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ፣ እነርሱ
ሞተው እስኪያልቁ ድረስ፣ እስራኤላውያን
በምድረ በዳ አርባ ዓመት ይንከራተቱ ነበር::
እግዚአብሔር ለእኛ ይሰጠን ዘንድ ለአባቶ
ቻቸው ቃል የገባላቸውን ያችን ማርና ወተት
የምታፈስ ምድር እንደማያዩአት ምሎአልና::
7ስለዚህ በእነርሱ ምትክ ወንዶች ልጆቻቸ
ውን አስነሣ፤ እንግዲህ ኢያሱ የገረዛቸው
እነዚህን ነበር፤ በጕዞ ላይ ሳሉ ባለመገረዛ
ቸው ከነሸለፈታቸው ነበሩና:: 8ሕዝቡ ሁሉ
ከተገረዙ በኋላ ቍስሉ እስኪሽር ድረስ እዚ
ያው በሰፈሩበት ቦታ ቈዩ::
9ከዚያም እግዚአብሔር ኢያሱን፣ "እነሆ፤
ዛሬ የግብፅን ነውር ከእናንተ ላይ አንከባል
ያለሁ" አለው፤ ከዚህም የተነሣ የዚያ ቦታ
ስም እስከ ዛሬ ድረስ ጌልገላ° ተባለ::
10እስራኤላውያን በኢያሪኮ ሜዳ በጌልገላ
ሰፍረው ሳሉ፣ ወሩ በገባ በዐሥራ አራተኛው
ቀን ምሽት የፋሲካን በዓል አከበሩ:: 11ከፋሲካም
በኋላ በዚያኑ ዕለት የምድሪቱን ፍሬ ማለት
ያልቦካ ቂጣና የተጠበሰ እሸት በሉ:: 12የም
ድሪቱን ፍሬ በበሉበት ቀን+ መናው መው
ረዱ ቀረ፤ ከዚያ በኋላ ለእስራኤላውያን መና
አልወረደላቸውም፤ ነገር ግን በዚያኑ ዓመት
የከነዓንን ምድር ፍሬ በሉ::

## የኢያሪኮ መውደቅ

13ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ፣ ቀና ብሎ
ሲመለከት የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ
አንድ ሰው ከፊቱ ቆሞ አየ፤ ኢያሱም ወደ
እርሱ ቀርቦ፤ "ከእኛ ወገን ነህ ወይስ ከጠላ
ቶቻችን?" ሲል ጠየቀው::
14እርሱም፣ "አይደለሁም፤ ነገር ግን የእግዚ
አብሔር ሰራዊት አለቃ በመሆኔ እነሆ፤
መጥቻለሁ" ሲል መለሰለት፤ ኢያሱም በግ
ንባሩ ተደፍቶ ሰገደና፣ "ጌታዬ ለባሪያው
የሚነግረው ምንድን ነው?" አለው::
15የእግዚአብሔር ሰራዊት አለቃም ኢያ
ሱን፣ "ጫማህን ከእግርህ አውልቅ፤ የቆምህ
ባት ምድር የተቀደሰች ናትና" አለው፤ ኢያ
ሱም እንደታዘዘው አደረገ::

6 በዚህ ጊዜ እስራኤላውያንን ከመፍራት
የተነሣ፣ ኢያሪኮ ፈጽማ ተዘግታ ነበር፤
ወደ ውጭ የሚወጣም ሆነ ወደ ውስጥ የሚገባ
አልነበረም::

5፥4 ዘኍ1፥3፤ዘዳ 2፥14
5፥6 ዘፀ3፥8፤16፥35፤ ዘኍ14፥23:29-35፤ 32፥13፤ ዘዳ2፥14፤ኢሱ 14፥10፤መዝ107፥4
5፥8 ዘፍ34፥25
5፥9 ዘዳ11፥30
5፥10 ዘፀ12፥6:11
5፥11 ዘፀ12፥15፤ ዘሌ 23፥14፤ ዘኍ15፥19
5፥12 ዘፀ16፥35
5፥13 ዘፍ18፥2፤ ዘኍ22፥23
5፥14 ዘፍ17፥3፤ 19፥1
5፥15 ዘፍ28፥17፤ዘፀ 3፥5፤ሐሥ7፥33
6፥1 ኢሱ24፥11

*3 ትርጓሜውም የሸለፈት ኩረብታ ማለት ነው::
°9 በዕብራይስጡ ጌልገላ የሚለው የቃል ድምፅ መንከባለል ከሚለው ቃል ጋር አንድ ዐይነት ነው::
+12 ወይም በበሉበት ጊዜ ተብሎ መተርጐም ይቻላል::

አገልግሎት መለየት አለባት (ከዘፀ 4፥24-26 ጋር ያነጻጽሩ):: *ገረዛቸው፤* ግዝረት እግዚአብሔርን ከማምለክ ጋር በተያያዘ መልኩ፣ ማንኛውንም ወንድ የአብርሃም ልጅ እንዲሆን አድርጎታል (ዘፍ 17፥10-11)፤ በፋሲካ በዓል ለመሳተፍም አስቀድሞ መገረዝ ያስፈልጋል (ዘፀ 12፥48)::

5፥3 *በጊብዓዝ ዓረሎት፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ::

5፥6 *አርባ ዓመት፤* ከግብፅ ከወጡበት ዕለት አንሥቶ የዮርዳኖስን ወንዝ እስከ ተሻገሩበት ዕለት ድረስ ያለው ጊዜ ነው:: ቃዴስ ባርኔን ትተው ከሄዱ ሠላሳ ስምንት ዓመት ብቻ ሆኖአቸው ነበር (ዘኍ 14፥20-22፤ ዘዳ 2፥14)::

5፥9 *የግብፅን ነውር፤* እዚህ ላይ ይህ ሐረግ እስራኤላውያን በግብፅ ምድር በባርነት ያሳለፉትን ሕይወት የሚያመለክት ቢመስልም፣ በበለጠ የሚያተኩረው ግን እስራኤላውያን በበረሓ ወድቀው ቢቀሩ ኖሮ፣ በእስራኤል አምላክና በእስራኤል ላይ ግብፃውያን የሚሰነዝሩትን ነቀፋ በማሳየት ላይ ነው (ዘፀ 32፥12፤ ዘኍ 14፥13፤ ዘዳ 9፥28 ይመ):: አሁን ግን የበረሓው ጕዞ ተጠናቀቀ፤ እስራኤልም በግዝረት ሥርዐት ለእግዚአብሔር ተለይታና የእርሱም ልዩ ሕዝብ ሆና በሰላም ወደ ተስፋዋ ምድር ገባች፤ የግብፅም ውርደት ከላይዋ ላይ ተንከባሎ ወደቀ::

5፥10 *የፋሲካን በዓል፤* በዓሉ የሚከበረው የዓመቱ መጀመሪያ ወር በሆነው በአቢብ ወር ነው (ዘፀ 12፥2):: በወሩ 14ኛ ቀን ጀምበር ልትጠልቅ ስትቃረብ፣ የፋሲካው በግ ይታረዳል፤ ከዚያም በእሳት ተጠብሶ በዚያኑ ሌሊት ይበላል (ዘፀ 12፥5-8):: እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ ከአንድ ዓመት በኋላና በሲና ተራራ ላይ የፋሲካን በዓል ከማክበራቸው በፊት፣ በከነዓን ድንበር አካባቢ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፀው ስለ ነበር፣ ከግብፅ ምድር የወጣው ትውልድ ሁሉ በምድረበዳ እንዲንከራተት ተቀጣ (ዘኍ 14፥21-23:29-35):: በመሆኑም ለዚህ ትውልድ የፋሲካን በዓል ማክበር (ከፍርድ ማምለጥ) የጐላ ትርጕም ላይሰጠው ይችላል::

5፥11 *ያልቦካ ቂጣና፤* ያለ እርሾ የተጋገረ ቂጣ ነው:: ይህም የፋሲካ በዓል ከሚውልበት ቀን ቀጥሎ ባሉት ሰባት የበዓል ቀናት የሚበላ ነው (ዘፀ 12፥15፤ ዘሌ 23፥6)::

5፥12 *መና አልወረደላቸውም፤* እስራኤላውያን መና ከመብላት "የምድሪቱን ፍሬ" (ቍ 11) ወደ መብላት በተሸጋገሩ ጊዜ ለ40 ዓመታት እግዚአብሔር በሚያዘጋጅላቸው ልዩ ምግብ ላይ መደገፋቸው አበቃ:: መና፣ እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለሕዝቡ ያዘጋጀው ልዩ ምግብ ነው፤ ከዚህ በኋላ ግን ከተስፋዪቱ ምድር የሚገኘውን ፍሬ ሰጣቸው::

*5፥13-6፥5፤* የተስፋዋን ምድር ለመውረስ የተደረገውን ፍልሚያ የሚያወሣው ታሪክ የሚጀምረው ድንገት በታየውና ራሱን "የእግዚአብሔር ሰራዊት አለቃ" (5፥14) ብሎ በጠራው ሰማያዊ መልእክተኛ ነው::

5፥13 *ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ፤* የእግዚአብሔርን ሰራዊት የሚመራው ኢያሱ በቅርብ የሚገኘውን የከነዓናውያንን ምሽግ ለመሰለል ወጥቶ ነበር፤ ነገር ግን ሌላ የጦር አለቃ ቀድሞት በቦታው ተገኘ:: *ሰው ... ቆሞ፤* ይህን ገጠመኝ ብዙዎች እግዚአብሔር ራሱ በሰው አምሳል (አስተርእዮ እግዚአብሔር) እንደ ተገለጠ ይረዱታል፤ ሌሎች ደግሞ ክርስቶስ (አስተርእዮ ክርስቶስ) እንደ ተገለጠ ያስባሉ:: ይሁን እንጂ መላእክትም ለተመሳሳይ ተልዕኮ በዚሁ መልክ የተገለጡበት ጊዜ አለ (መሳ 6፥11፡ 13፥3)፤ የቀሩትም የሰማይ ሰራዊት ነው ይላሉ(ዳን 10፥5:20፤12፥1)::

5፥14 *አይደለሁም፤* ኢያሱና እስራኤላውያን ስፍራቸውን ማወቅ አለባቸው፤ እግዚአብሔር ከእነርሱ ወገን ስለ ሆነ ሳይሆን፣ ውጊያው የእግዚአብሔር በመሆኑ መዋጋት ይገባቸዋል:: *የእግዚአብሔር ሰራዊት አለቃ፤* እግዚአብሔር በምድር ያለውን ውጊያ እንዲመራ የሰማይ ሰራዊቱን አለቃ ልኮአል፤ ኢያሱም ከዚህ ከእግዚአብሔር ሰራዊት አለቃ ትእዛዝ መቀበል ይገባዋል (6፥2-5)፤ በተጨማሪም ቈይተው የታዩ ሁነቶች እንደሚያረጋግጡት የሰማይ ሰራዊት ለእስራኤል እንደሚዋጋ ማወቅ አለበት:: *ጌታዬ፤* የበላይ ለሆነ የሚሰጥ የአክብሮት ስም ነው::

*5፥15፤* ሙሴ ፈርዖንን እንዲቋቋም በእግዚአብሔር ተሹሞ እንደ ነበረ ሁሉ (ዘፀ 3፥5)፣ ኢያሱንም የእግዚአብሔርን ውጊያ እንዲመራና ከነዓንን እንዲይዝ እግዚአብሔር ሾመው::

6፥1 *ኢያሪኮ፤* በአሁኑ ጊዜ ቴል ኤስ ሡልጣን ተብሎ የሚጠራ ስፍራ ሲሆን፣ በዚህ ስፍራ ከሃያ አራት በላይ የሚሆኑ ጥንታዊ ከተሞች በተለያየ ጊዜ ፈርሰው እንደገና ተቈርቍረዋል:: ብዙዎቹ ከተሞች ጠንካራና ድርብ ቅጥር የነበራቸው ሲሆን በኢያሱ

2እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለው፤
“እነሆ፤ ኢያሪኮን ከንጉሥዋና ከተዋጊዎቿ ጋር
አሳልፌ በእጅህ ሰጥቻለሁ። 3ከተማዪቱን ከተ
ዋጊዎቻችሁ ጋር አንድ ጊዜ ዙሩ፤ ይህንም ስድ
ስት ቀን አድርጉ። 4ሰባት ካህናት፣ ሰባት ቀንደ
መለከት ተሸክመው በታቦቱ ፊት ይውጡ፤
በሰባተኛውም ቀን ካህናቱ መለከት እየነፉ
ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ይዙሩ። 5የማያቋርጥ የመ
ለከት ድምፅ ሲነፉ በምትሰሙበት ጊዜ፣ ሕዝቡ
ሁሉ ከፍ ያለ ጩኸት ያሰማ፤ ከዚያም የከተማ
ዪቱ ቅጥር ይፈርሳል፤ ሕዝቡም ወደ ላይ ይወ
ጣል፤ እያንዳንዱም ሰው በቀጥታ ይገባል።”
6ስለዚህ የነዌ ልጅ ኢያሱ ካህናቱን ጠርቶ፣
“የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸከሙ፤ ሰባት ካህናትም
ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው *በእግዚአብሔር*
*ታቦት ፊት ይሂዱ*” አላቸው። 7ሕዝቡንም፣
“ወደ ፊት ሂዱ፤ ከተማዋን ዙሩ፤ የታጠቀ ተዋጊ
ዎችም *በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ቀድመው*
ይሂዱ፤ ከተማዪቱንም ዙሩ” ሲል አዘዛቸው።
8ኢያሱም ለሕዝቡ ከተናገረ በኋላ፣ ሰባቱ
ካህናት *በእግዚአብሔር ፊት* ሰባት ቀንደ
መለከት ይዘው መለከታቸውን እየነፉ ወደ
ፊት ቀደሙ፤ *የእግዚአብሔር* የቃል ኪዳን
ታቦትም ተከተላቸው። 9የታጠቀ ተዋጊዎችም
መለከት ከሚነፉት ካህናት ፊት ቀድመው
ሲሄዱ፣ ደጀን የሆኑት ጠባቂዎች ደግሞ ታቦ
ቱን ተከተሉ፤ በዚህ ጊዜ ሁሉ መለከቶቹ
ባለማቋረጥ ይነፉ ነበር። 10ኢያሱ ሕዝቡን፣
“የማሽበሪያ ጩኸት አታሰሙ፤ ድምፃችሁ ከፍ
ብሎ አይሰማ፤ ጩኸ እስከምላችሁም ቀን

6፥2 ቊ16፤ዘዳ7፥24፤ ኢሱ 8፥1
6፥4 ዘፀ19፥13፤ዘሌ 25፥9
6፥5 ቊ20፤ዘፀ19፥13፤1ሳሙ4፥5፤2ሳሙ 6፥15፤ዕዝ3፥11፤10፥12፤መዝ42፥4፤95፥1፤ ኢሳ8፥9፤42፥13
6፥6 ቊ4
6፥7 ዘፀ14፥15፤ዘኁ 10፥35፤1ሳሙ4፥3፤ 7፥1
6፥9 ቊ13፤ዘኁ 2፥31፤ ኢሳ52፥12
6፥10 ቊ20፤ 1ሳሙ4፥5፤ዕዝ3፥11
6፥15 1ነገ18፥44፤2 ነገ4፥35፤5፥14
6፥16 ቊ2
6፥17 ቊ21፡25፤ዘሌ 27፥28፤ዘዳ20፥17፤ኢሱ 2፥1፡4፤ኢሳ13፥5፤24፥1፤ 34፥2፡5፤ሚል4፥6

ድረስ ከአፋችሁ አንዲት ቃል አትውጣ፤ የም
ትጮኹት ከዚያ በኋላ ነው” ሲል አዘዛቸው።
11ስለዚህ ኢያሱ *የእግዚአብሔርን ታቦት* ተሸ
ክመው፣ ከተማዪቱን አንድ ጊዜ እንዲዞሩ አደ
ረገ። ከዚያም ሕዝቡ ወደ ሰፈር ተመልሰው
ዐደሩ።
12ኢያሱ በማግሥቱ ማልዶ ተነሣ፤ ካህናቱም
*የእግዚአብሔርን ታቦት* ተሸከሙ። 13ሰባቱም
ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው *በእግዚ*
*አብሔር ታቦት ፊት* እየሄዱ፣ መለከቱን
ባለማቋረጥ ይነፉ ጀመር፤ የታጠቁ ተዋጊዎ
ችም እነዚህን በመቅደም ሲሄዱ፣ የደጀን
ጠባቂዎቹ ደግሞ *የእግዚአብሔርን ታቦት*
ይከተሉ ነበር፤ ካህናቱም ሳያቋርጡ መለከት
ይነፉ ነበር። 14በሁለተኛውም ቀን ከተማዪቱን
አንድ ጊዜ ከዞሩ በኋላ ወደ ሰፈር ተመለሱ፤
ስድስት ቀን ሙሉም እንዲሁ አደረጉ።
15በሰባተኛው ቀን ገና ጎሕ ሲቀድ ተነሡ፤
እንደ በፊቱም ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዞሩ፤ ከተ
ማዪቱን ሰባት ጊዜ የዞሯትም በዚያን ቀን
ብቻ ነው። 16በሰባተኛው ዙር ላይ ካህናቱ
መለከቱን ሲነፉ፣ ኢያሱ ሕዝቡን እንዲህ
ሲል አዘዘ፤ “*እግዚአብሔር* ይህችን ከተማ
ሰጥቶአችኋልና ጩኹ! 17ከተማዪቱና በውስጧ
ያለው ሁሉ *ለእግዚአብሔር* የተለየ ስለ ሆነ
ፈጽማችሁ አጥፉ[*]፣ እኛ የላክናቸውን ሰላ
ዮች ስለሸሸገች ጋለሞታዪቱ[†] ረዓብ ብቻና ከእ
ርሷ ጋር በቤቷ ውስጥ ያሉት ሁሉ ይትረፉ።

[*]17 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው።

[†]17 በዚህም ሆነ በቍጥር 22 እና 25 ላይ *የሆቴል ቤት ተጠቃሚ* ተብሉ ሊተረጐም ይችላል።

ሰራዊት የፈረሰው የትኛው ቅጥር እንደሆነ በውል ማረጋገጥ አልተቻለም። የፍርስራሹ ክምር 366.72 ሜትር በ183.36 ሜትር ያህል ነበር። ኢያሪኮ የጨረቃ አምላክ ማምለኪያ ማእከል በመሆኗ (ኢያሪኮ ማለት “የጨረቃ ከተማ” ማለት ነው)፣ እግዚአብሔር ያጠፋው የከነዓናውያንን ከተሞች ብቻ ሳይሆን እምነታቸውንም ጭምር ነበር።

6፥2 *እግዚአብሔር፤* የእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ ኢያሱ የመጣው የመጀመሪያዋን የከነዓንን ከተማ እንዲወር ትእዛዝ በሰጠው፣ “በእግዚአብሔር ሰራዊት አለቃ” (5፥14) ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።

6፥3 *ከተማይቱን … ዙሩ፤* ስድስት ቀን ተደጋግሞ መፈጸም የነበረበት፣ የአንድን ከተማ መከበብ የሚያመለክት ሥርዐት ነው።

6፥4 *ከበግ ቀንድ የተሠራ ቀንደ መለከት፤* መለከቱ የሙዚቃ መሣሪያ ሳይሆን፣ ሕዝቡን ለጦርነት ወይም ለሃይማኖታዊ በዓላት የሚያዘጋጅ ነው (እዚህ ላይ ጦርነትና ሃይማኖታዊ ሥርዐት በአንድነት ተጠቅሰዋል)። በሰባተኛው ቀን መለከት ይነፋል (ቍ 8)፤ የመለከቱ መነፋት የእግዚአብሔርን በሕዝቡ መካከል መገኘት ያውጃል (2ሳሙ 6፥15፤ 1ዜና 15፥28፤ ዘካ 9፥14 ይመ)። *ታቦቱ፤* እግዚአብሔር ከተማዪቱን እንደከበበ ያሳያል። *ሰባተኛው ዕለት፤* የኢያሪኮን ከተማ ለሰባት ቀን ከበው ሲቀመጡ ስለ ሰንበት የተወሳ ምንም ነገር የለም፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ቃል በገባላቸው መሠረት፣ የዕረፍት ምድር የሆነችውን ከነዓንን ለእስራኤላውያን የሰጣቸው በዚሁ ዕለት ሳይሆን አይቀርም። ከረጅም ጕዞ በኋላ፣ በሰባተኛው ቀን ካሰቡበት ቦታ መድረስ በጥንት የመካከለኛው ምሥራቅ ሥነ ጽሑፎች ውስጥ የሚገኝ ዐቢይ ሐሳብ ነው። የሰባት ቍጥር ተደጋግሞ መጠቀስ (ቀንደ መለከት የያዙ ሰባት ካህናት፣ ሰባት ቀን፣ በሰባተኛው ቀን፣ ሰባት ጊዜ መዞር) የሁነቱን ታላቅነት ያመለክታል (የዮሐንስን ራእይ መግቢያ ይመ)፤ ይህም ምናልባት የፍጥረት ሥራ በሰባት ቀናት ውስጥ እንደ ተጠናቀቀ በማስታወስ እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ አንድ ሥርዐት መጀመሩን የሚጠቍም ሳይሆን አይቀርም።

6፥5 *የማያቋርጥ… ድምፅ … ከፍ ያለ ጩኸት፤* ጦርነቱ መጀመሩን የሚያመለክት ሲሆን፣ ፍርሃትንና ሽብርን እንዲያስከትል የታቀደ የሥነ ልቡና ጦርነት ነው (መሳ 7 ይመ)። “የብርሃን ልጆችና የጨለማ ልጆች ጦርነት” የሚለው የሙት ባሕር ጥቅልል ሊዋውያን የጠላትን ልብ ለማራድና ለማቅለጥ መለከት እንዲነፉ መታዘዛቸውን ይገልጻል። *እያንዳንዱም ሰው በቀጥታ ይገባል፤* የከተማዪቱ ቅጥር የሚፈርሰው በከፊል ሳይሆን እንዳለ ሙሉ በሙሉ ነው፤ ይህም በሁሉም አቅጣጫ ወደ ከተማዋ ለመግባት ያስችላል።

6፥7 *የታጠቀ ተዋጊዎችም፤* ይህን ሐረግ ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በቍ 3 ላይ ከገባው ቃል ጋር ምናልባት ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም። ሰልፉን የሚመራው ታቦቱ ነው። እንዲህ ከሆነ፣ በዚህ ቦታ “የታጠቀ ተዋጊዎችም” የተባሉት የክብር ዘቦች ሊሆኑ ይችላሉ (ቍ 9 እና ማብ ይመ)።

*6፥8-14፤* በዚህ ክፍል ውስጥ የእግዚአብሔር ታቦት ልዩ ትኵረት ተሰጥቶታል፣ ይህም ከተማዋን የከበበው ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ያሳያል።

6፥9 *ደጀን የሆኑት ጠባቂዎች፤* ደጀን የሆኑት ጠባቂዎች የተውጣጡት ከጠቅላላው ሰራዊት መካከል ከሆነ (ዘኍ 10፥25 ይመ)፣ በቍ 7 እና 9 ላይ የተጠቀሱት የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች የሰራዊቱ ዋና አካል ናቸው ማለት ነው።

*6፥12-14፤* የቃላቱ መደጋገም የድርጊቱን መደጋገም የሚያሳይ ሲሆን፣ እንዲህ ያለው የአጻጻፍ ስልት በጥንቱ የመካከለኛው ምሥራቅ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የተለመደ ነው።

6፥17 *የተለየ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። በዚህ ዐይነት ለእግዚአብሔር የተሰጠው ፈጽሞ ይደመሰሳል (ቍ 18 እና 21 ይመ)። የኢያሪኮ ነዋሪዎች ሙሉ በሙሉ እንዲደመሰሱ ሲወሰን፣ ሊደመሰስ የማይችል የከተማዋ ሀብትና ንብረት ግን ለእግዚአብሔር የተለየ ነበር (ቍ 19)። በሙሴ ሕግ መሠረት ድምስሰው ለመሥዋዕት በሚቀርቡ እንስሳት፣ ለእግዚአብሔር በሚሰጡ ንብረቶችና ሞት በሚገባው ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል (ዘሌ 27፥28-29)። የከነዓን ነዋሪዎች በሙሉ በሞት “የተለዩ” እንዲሆኑ ሕግ ያወጣው ራሱ ሙሴ ነው፤ ፈጽሞ እንዲደመሰሱም የተወሰነው፣ ጣዖት አምላኪና ክፉ አድራጊ በመሆናቸው ነው (ዘዳ 20፥16-18)። የዘዳ 2፥34 ማብ ይመ። *ረዓብ ብቻና … በቤትዋ ውስጥ ያሉት ሁሉ ይትረፉ፤* ሁለቱ ሰላዮች የገቡትን ቃል ለማክበር ነው (2፥14)።

18እናንተ ግን እርም ከሆኑት ነገሮች አንዳች
በመውሰድ በራሳችሁ ላይ ጥፋት እንዳታ
መጡ እጃችሁን ሰብስቡ፤ ያለዚያ የእስራኤ
ልን ሰፈር ለጥፋት ትዳርጋላችሁ፤ ክፉ ነገር
እንዲደርስበትም ታደርጋላችሁ፤ 19ብሩና
ወርቁ እንዲሁም የናሱና የብረቱ ዕቃ ሁሉ
*ለእግዚአብሔር* የተቀደሰ ስለ ሆነ፣ ወደ
*እግዚአብሔር* ግምጃ ቤት ይግባ::"
20መለከቱ ሲነፋ ሕዝቡ ጮኸ፤ የመለከቱ
ድምፅ ተሰምቶ፣ ሕዝቡ በኀይል ሲጮኽ
ቅጥሩ ፈረሰ፤ እያንዳንዱ ሰው ሰተት ብሎ
ገባ፤ ከተማዪቱም በእጃቸው ወደቀች:: 21በከ
ተማዪቱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ማለትም ወን
ዱንና ሴቱን፣ ወጣቱንና ሽማግሌውን፣ ከብ
ቱንና በጉን እንዲሁም አህያውን በሰይፍ
ስለት ፈጽመው አጠፉ::
22ኢያሱ ምድሪቱን የሰለሉትን ሁለቱን
ሰዎች፣ "ወደ ጋለሞታዪቱ ቤት ሂዱ፤ በማ
ላችሁላትም መሠረት እርስዋንና የእርሷ
የሆነውን ሁሉ ከዚያ አውጡ" አላቸው::
23ስለዚህ ሁለቱ ወጣት ሰላዮች ገብተው
ረዓብን፣ አባቷንና እናቷን፣ ወንድሞቿንና
የእርሷ የሆኑትን ሁሉ ከዚያ አወጧቸው::
ቤተ ዘመዶቿንም ሁሉ አውጥተው ከእስራ
ኤል ሰፈር ውጭ አስቀመጧቸው::
24ከዚያም ከተማዪቱን በሙሉ፣ በውስጧ
ያለውንም ሁሉ አቃጠሉ፤ ብሩንና ወርቁን፣
የናሱንና የብረቱን ዕቃ ግን *በእግዚአብሔር*
ግምጃ ቤት አኖሩ:: 25ኢያሪኮን እንዲሰልሉ
ኢያሱ የላካቸውን ሰዎች ስለ ደበቀች፣
ጋለሞታዪቱን ረዓብን፣ ቤተ ሰቧንና የእርሷ
የሆኑትን ሁሉ አዳናቸው፤ እርሷም እስከ ዛሬ
ድረስ በእስራኤላውያን መካከል ትኖራለች::
26በዚያን ጊዜም ኢያሱ፣ እንዲህ ሲል ማለ፤
"ይህችን ከተማ መልሶ የሚሠራት ሰው *በእግዚ
አብሔር* ፊት የተረገመ ይሁን፤

"መሠረቷን ሲጥል፣

6፥18 ኢሱ7፥1:12:
25:26፤1ዜና2፥7፤
6፥19 ቍ-24፤ዘኍ
31፥22
6፥20 ቍ-5:10፤ዘሌ
25፥9፤መሳ6፥34፤7፥2
2፤1ነገ1፥41፤ኢሳ18፥
3፤27፥13፤ኤር4፥21፤
42፥14፤አሞ2፥2፤
ዕብ11፥30
6፥21 ቍ-17፤ዘዳ
20፥16
6፥22 ዘፍ42፥9፤ዘኍ
21፥32፤ኢሱ2፥4:14፤ዕብ
11፥31
6፥23 ኢሱ2፥13
6፥24 ቍ-19፤ዘኍ
31፥10፤ዘዳ13፥16
6፥25 ቍ-17፤ኢሱ
2፥1:6፤መሳ1፥25
6፥26 ዘኍ5፥21፤
1ሳሙ14፥24፤1ነገ
16፥34
6፥27 ዘፍ39፥2፤ዘኍ
14፥43፤ኢሱ9፥1፤1
ዜና14፥17
7፥1 ቍ-18:26፤ዘፀ
4፥14፤32፥20፤ዘሌ10፥
6፤ዘኍ1፥4፤ኢሱ6፥18፤
22፥20፤ 1ዜና2፥7
7፥2 ዘፍ12፥8፤ዘኍ
21፥32፤ኢሱ8፥1:28፤
12፥16፤16፥1፤18፥12፤
መሳ1፥22፤1ሳሙ13፥
5፤14፥23፤30፥27፤
2ነገ23፥15፤ኤር48፥
13፤ሆሴ4፥15፤5፥8፤10፥
5፤አሞ3፥14፤4፥4፤5፥
5-6፤7፥10:13
7፥4 ዘሌ26፥17፤ዘዳ
28፥25
7፥5 ዘፍ42፥28፤ኢሱ
22፥7መዝ22፥14፤ኢሳ
13፥7፤ሕዝ21፥7፤ናሆ
2፥10
7፥6 ዘፍ17፥3፤37፥
29፤ኢሱ8፥10፤9፥11፤
20፥4፤23፥2፤መሳ20፥
23፤1ሳሙ-4፥12፤2ሳ
ሙ-13፥19፤15፥32፤
1ዜና21፥16፤ነህ9፥1፤
ኢዮ2፥12፤ሰቆ2፥

የበኵር ልጁ ይጥፋ፤
ቅጥሮቿንም ሲያቆም፣
የመጨረሻ ልጁ ይጥፋ" ብሎ ማለ::

27ስለዚህ *እግዚአብሔር* ከኢያሱ ጋር ነበር፤
ዝናውም በምድሪቱ ሁሉ ላይ ወጣ::

## የአካን ኀጢአት

7 እስራኤላውያን ግን እርም የሆነውን ነገር˥
ባለማጥፋታቸው በደሉ፤ ይህም ከይሁዳ
ነገድ የሆነው አካን የከርሚ ልጅ፣ የዘንበሪ˥
ልጅ፣ የዛራ ልጅ እርም ከሆነው ነገር ስለ
ወሰደ *የእግዚአብሔር* ቍጣ በእስራኤል
ልጆች ላይ ነደደ::
2ኢያሱ ከቤቴል በስተ ምሥራቅ ካለችው
ከቤትአዌን አጠገብ ወደምትገኘው ወደ
ጋይ ከኢያሪኮ ሰዎችን ልኮ፣ "ወደዚያ
ውጡ፤ አገሪቱንም ሰልሉ" አላቸው፤ ሰዎቹም
ወጥተው ጋይን ሰለሉ::
3ወደ ኢያሱም ተመልሰው፣ "ጋይን ለመ
ውጋት ሕዝቡ ሁሉ መሄድ አያስፈልገውም፤
በዚያ ያለው ሕዝብ ጥቂት ስለ ሆነ፣ ከተ
ማዪቱን ለመውጋት ሁለት ወይም ሦስት
ሺህ ሰው ስለሚበቃ ሕዝቡ ሁሉ ወደዚያ
በመሄድ አይድከም" አሉት:: 4ስለዚህ ሦስት
ሺህ ያህል ሰው ወጣ፤ ከጋይም ሰዎች ፊት
ሸሸ፤ 5የጋይም ሰዎች እስራኤላውያንንም
ከከተማዪቱ ቅጥር በር ጀምሮ እስከ ሸባሪም^
ድረስ በማባረር ቍልቍለቱ ላይ መቷቸው፤
ከእነርሱም ሠላሳ ስድስት ያህል ሰው ገደሉ
ባቸው:: ከዚህ የተነሣም የሕዝቡ ልብ
ቀለጠ፤ እንደ ውሃም ፈሰሰ::
6በዚህ ጊዜ ኢያሱ ልብሱን ቀደደ፤ *በእግዚ
አብሔርም* ታቦት ፊት በግንባሩ ተደፋ፤

˥1 በዚህም ሆነ በቍጥር 11:12:13 እና 15 ላይ የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው:: ˥1 1ዜና 2፥6 እና የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ይመ፤ በዚህም ሆነ በቍጥር 17 እና 18 ላይ ዕብራይስጡ *ዘብዲ* ይላል:: ^5 ወይም እስከ *ድንጋይ መፍለጫው* ተብሎ መተርጉም ይቻላል::

6፥18 *በራሳችሁ ላይ ጥፋት …፤* የቍ 17 አማራጭ ትርጉም ይመ:: እስራኤል፣ እግዚአብሔር ፈጽሞ ይደምሰስ ያለውን ነገር ለራሷ ብትወስድ፣ እርሷ ራሷ ፈጽማ ትደመሰሳለች::

6፥25 *በእስራኤላውያን መካከል ትኖራለች፤* የረዓብ እምነት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ጊዜ በምሳሌነት ተጠቅሶአል (ዕብ 11፥31፤ ያዕ 2፥25)::

6፥26 *ሰው … የተረገመ ይሁን፤* እግዚአብሔር በክፉ ከነዓናውያን ላይ ለሚያመጣው ፍርድ ቋሚ ምልክትና የምድሪቱም የበኵራት መሥዋዕት መሆኗን ለማመልከት ኢያሪኮ ራሷ ለእግዚአብሔር የተለየች መሆን አለባት:: ይህም ድል የተመታችው ምድር የእግዚአብሔር መሆኗ ማረጋገጫ መንገድ ነበረ:: እርግማኑ በንጉሥ አክዓብ የዐመፅ ዘመን ተፈጸመ (1ነገ 16፥34)::

*7፥1-26፤* በዚህ ክፍል ውስጥ የምናገኘው የአካን አሳዛኝ ታሪክ ከረዓብ ታሪክ ጋር በእጅጉ ይጻረራል:: ቀደም ባለው ታሪክ ውስጥ እንደምናነበው፣ አንዲት ከነዓናዊት ጋለሞታ፣ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር አንድ ለመሆንና የእስራኤልንም አምላክ ለማምለክ በወሰደችው ጽኑ አቋም ከሞት ልትተርፍና ወደ እስራኤልም ጉባኤ ልትቀላቀል ቻለች:: ለእግዚአብሔርና ለእስራኤል ስትል ከነዓንንና የከነዓንን አማልክት እርግፍ አድርጋ ተወች፤ በዚህም ምክንያት ከነዓንን እንደገና አገኘች (ወረሰች):: በዚህ ታሪክ ውስጥ እንደምናነበው ደግሞ አንድ እስራኤላዊ (ያውም ከይሁዳ ነገድ የሆነ) ለእግዚአብሔርና ለእስራኤል ታማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ እንደ ከነዓናውያን ተደመሰሰ:: የከነዓንን ሀብት ከእግዚአብሔር በመስረቁ በተስፋዪቱ ምድር ርስቱን አጣ:: ከዚህም በተጨማሪ የአንድ ሰው በደል መላውን ሕዝብ እንዴት ክፉኛ እንደበከለ ይህ ታሪክ በግልጽ ያሳያል:: በዚህ ታሪክ ውስጥ (እንዲሁም በሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እንደሚነበበው) እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ባላት ኪዳንና ለእርሱም በምትሰጠው አገልግሎት እንደ አንድ አካል ተቈጥራለች:: በመሆኑም በአንድ ሰው (በአካን) ወይም በጥቂት ሰዎች ድርጊት (3000 ሰዎች በጋይ ድል ተደረጉ) መላው የእስራኤል ሕዝብ ተሳታፊ ነው (ቍ 1፥11፤ 22፥20 ይመ)::

7፥2 *ወደ ጋይ ከኢያሪኮ፤* ወደ መካከለኛው የፓለስቲና ተራተር ጫፍ ለመውጣት በሸለቆው በኩል ሽቅብ 24 ኪሎ ሜትር ያህል መጓዝ ያስፈልጋል:: ከውጊያው ስልት አንጻር፣ እስራኤል ከጌልገላ ወደ ጋይ በመንቀሳቀስ የዮርዳኖስን ሸለቆ እንድትሻገርና የመካከለኛውን አገር ከፍተኛ ቦታዎች እንድትይዝ ያስችላታል:: በዕብራይስጥ ቋንቋ ጋይ ማለት "ፍርስራሽ" ማለት ነው:: ጋይ አብዛኛውን ጊዜ 'ኤቴል' ተብላ ከምትጠራው ከተማ ጋር አንድ እንደ ሆነች ይገመታል (በዐረብኛ ቋንቋ ኤቴል ማለት "ፍርስራሽ" ማለት ነው)፤ ኤቴል ከቤቴል 3.2 ኪሎ ሜትር ርቃ ትገኛለች፣ ጋይና ኤቴል አንድ ናቸው የሚለውን አባባል አንዳንዶች አይቀበሉትም:: *ቤትአዌን፤* ትርጒሙ "የዐመፅ ቤት" ማለት ሲሆን፣ ቤቴልን ወይም በአቅራቢያዋ የሚገኘውን ቤተ ጣዖት ለማንቋሸሽ የተሰጠ ስም ነው (1ሳሙ 13፥5፤ ሆሴ 4፥15፤ አሞ 5፥5 ይመ):: *አገሪቱንም ሰልሉ፤* የ2፥1-24ን ማብ ይመ::

7፥5 *ሸባሪም፤* የድንጋይ መፍለጫ ወይም ካባ ማለት ነው፤ ይህም ከዮርዳኖስ ሸለቆ ማዶ የሚታየውን ድንጋያማ ቦታ የሚገልጽ ትክክለኛ ስያሜ ነው::

7፥6 *ኢያሱ ልብሱን ቀደደ፤* የታላቅ ኀዘን ምልክት ነው

የእስራኤል ሽማግሌዎችም እንደዚሁ አደ
ረጉ፤ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ። [7]ኢያ
ሱም እንዲህ አለ፤ “ወዮ! ልዑል *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ ዮርዳኖስን አሻግረህ ይህን ሕዝብ ወደ
ዚህ *ያመጣኸው* ለአሞራውያን አሳልፈህ በመ
ስጠት እንዲያጠፉን ነውን? ምነው ሳንሻገር
እዚያው ማዶ በቀረን ኖሮ! [8]ጌታ ሆይ፤ እስ
ራኤል በጠላቱ ፊት ሲሸሽ እኔ ምን ልበል?
[9]ከነዓናውያንና ሌሎቹ የምድሪቱ ነዋሪዎች
ሁሉ ይህን ሲሰሙ ይከቡናል፤ ስማችንንም
ከምድር ገጽ ያጠፉታል፤ እንግዲህ ስለ ታላቁ
ስምህ ስትል የምታደርገው ምንድን ነው?”
[10]*እግዚአብሔር* ኢያሱን እንዲህ አለው፤
“ተነሥ! ለምን በግንባርህ ተደፋህ? [11]እስራ
ኤል በድሎአል፤ እንዲጠብቁ ያዘዝኋቸውን
ቃል ኪዳኔን ጥሰዋል፤ እርም የሆነውን ነገር
ወስደዋል፤ ሰርቀዋል፤ ዋሽተዋል፤ የወሰዱ
ትንም ከራሳቸው ንብረት ጋር ደባልቀዋል።
[12]እንግዲህ እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን
ለመቋቋም ያልቻሉት በዚህ ምክንያት ነው።
ጀርባቸውን አዙረው የሸሹትም ለጥፋት
በመዳረጋቸው ነው። እርም የሆነውን ነገር
ከመካከላችሁ ካላጠፋችሁ፣ ከዚህ በኋላ ከእ
ናንተ ጋር አልሆንም።
[13]“ተነሣ፤ ሕዝቡን ቀድስ፤ እንዲህም በላ
ቸው፤ ‘እስራኤል ሆይ፤ እርም የሆነ ነገር
በመካከላችሁ ስላለ፣ ይህን ካላስወገዳችሁ
ጠላቶቻችሁን ለመቋቋም እንደማትችሉ፣
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ተናግሮአ
ልና፣ ለነገ ራሳችሁን ለማዘጋጀት ሰውነታ
ችሁን ቀድሱ።
[14]“ ‘ማለዳ በየነገድ በየነገዳችሁ ሆናችሁ
ቅረቡ፤ እግዚአብሔር የሚለየው ነገድ በየጐሣ
በየጐሣው ሆኖ ከሕዝቡ መካከል ወደ ፊት
ይወጣል፤ እንዲሁም *እግዚአብሔር* የሚለ
የው ጐሣ በየቤተሰቡ ሆኖ ወደ ፊት ይወጣል፤
*እግዚአብሔር* የሚለየው ቤተ ሰብ ደግሞ
በግለሰብ በግለሰብ ሆኖ ወደ ፊት ይወጣል።
[15]እርሙ የተገኘበት ሰው፣ እርሱና ያለው

10፡ሕዝ9፥8፡27፥30፤ ራእ18፥19
7፥7 ዘፀ5፥22፤ዘኍ14፥16፤1ሳሙ4፥3
7፥9 ዘፀ32፥12፤ዘዳ9፥28፤28፥58፤1ሳሙ12፥22፤መዝ48፥10፤106፥8፤ኤር14፥21
7፥11 ቍ15፡21፤ዘፀ9፥27፤ዘዳ29፥27፤ኢሱ6፥17-19፤23፥16፤24፥16-27፤መሳ2፥20፤1ሳሙ15፥24፤2ነገ17፥7፤መዝ78፥10፤ሆሴ10፥9፤ሐሥ5፥1-2፤
7፥12 ዘሌ26፥17፡37፤ኢሱ6፥18፤መዝ18፥40፤21፥12፤44፥9፤60፥10
7፥13 ዘሌ11፥44
7፥14 1ሳሙ10፥19፤ምሳ16፥33
7፥15 ቍ11፤ዘፍ34፥7፤ዘዳ7፥25፤ኢሱ6፥18፤1ሳሙ14፥39፤2ነገ25፥9፤1ዜና14፥12፤ኢሳ37፥19፤ኤር43፥12፤ሕዝ30፥16
7፥17 ዘኍ26፥20
7፥18 ቍ1፤ዘሌ24፥11፤ዮና1፥7
7፥19 ዘፀ14፥17፤ዘሌ5፥5፤1ሳሙ6፥5፤14፥43፤መዝ96፥8፤ኢሳ42፥12፤ኤር13፥16፤ዮሐ9፥24
7፥21 ዘፍ34፥29፤49፥27፤ዘዳ7፥25፤ኤፌ5፥5፤1ጢሞ6፥10
7፥24 ቍ26፤ዘኍ16፥27፤ኢሱ15፥7፤ኢሳ65፥10፤ሆሴ2፥15

ሁሉ በእሳት ይቃጠላል፤ *የእግዚአብሔርን*
*ቃል ኪዳን* አፍርሶአል፤ በእስራኤልም ዘንድ
አሳፋሪ ተግባር ፈጽሞአልና።”
[16]በማግሥቱ ጥዋት ኢያሱ ማልዶ ተነሣ፤
እስራኤልንም በየነገድ በየነገዳቸው ሆነው
እንዲቀርቡ አደረገ፤ ከዚያም የይሁዳ ነገድ
ተለየ፤ [17]የይሁዳንም ጐሣዎች ወደ ፊት
አቀረበ፤ ከእነዚህም የዛራን ጐሣ ለየ፤ እነዚ
ህን ደግሞ በየቤተሰባቸው እንዲወጡ አደ
ረገ፤ ከእነዚህም ዘንበሪ ተለየ። [18]ኢያሱ የዘ
ንበሪን ቤተ ሰብ አባላት አንድ በአንድ
ወደፊት እንዲቀርቡ አደረገ፤ ከዚያም ከይ
ሁዳ ነገድ የሆነውም የዛራ ልጅ፣ የዘንበሪ
ልጅ፣ የከርሚ ልጅ አካን ለብቻው ተለየ።
[19]ኢያሱም አካንን፣ “ልጄ ሆይ፤ ለእስራ
ኤል ስምባክ[ከ] *ለእግዚአብሔር* ክብርን ስጥ፤
ለእርሱም ተናዘዝ፤ ያደረግኸውን ሳትደብቅ
ንገረኝ” አለው።
[20]አካንም መልሶ ኢያሱን እንዲህ አለው፤
“እውነት ነው! የእስራኤልን ስምባክ *እግዚ*
*አብሔርን* በድያለሁ፤ ያደረግሁትም ይህ ነው፤
[21]ከምርኮው ዕቃ መካከል ከሰናዖር[ገ] የመጣ
አንድ የሚያምር ካባ፣ ሁለት መቶ ሰቅል[ወ]
ብርና[ዐ] ክብደቱ አምሳ ሰቅል የሚሆን የወ
ርቅ ቡችላ አይቼ ጐመጀሁ፤ ወሰድኋቸ
ውም፤ ዕቃውም ብሩ ከታች ሆኖ፣ በድን
ኳኔ ውስጥ መሬት ተቀብሮአል።”
[22]በዚህ ጊዜ ኢያሱ መልእክተኞች ላከ፤
እነርሱም ወደ ድንኳኑ ሮጡ፤ በዚያም ብሩ
ከታች ሆኖ ዕቃው እንደ ተቀበረ አገኙ።
[23]ከድንኳኑም አውጥተው፣ ኢያሱና እስራ
ኤላውያን ሁሉ ወዳሉበት አምጥተው *በእግ*
*ዚአብሔር ፊት* አኖሩ።
[24]ኢያሱም ከመላው እስራኤል ጋር ሆኖ፣
የዛራን ልጅ አካንን፣ ብሩን፣ ካባውን፣
የወርቁን ቡችላ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹን፣
የከብቱን መንጋ፣ አህዮቹንና በጎቹን እንዲ

[ከ]19 እውነትን ለመናገር የሚደረግ መሐላ ነው። [ገ]21 አንዳንድ ቅጂዎች *ባቢሎን* ይላሉ። [ወ]21 2.3 ኪሎ ግራም ያህል ነው። [ዐ]21 0.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

(ዘፍ 37፥29፡34፤ 44፥13፤ መሳ 11፥35 ይመ)። በቀረበው ጸሎት ውስጥ እንደ ተመለከተው የኢያሱ (እንዲሁም የሕዝቡ) ኀዘን የመነጨው፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል ሰራዊት ጋር ያልወጣ መሆኑን ከመገንዘብ ነው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ካልወጣ ደግሞ የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገራቸው ምንም ፋይዳ የለውም። ከዚህም በተጨማሪ ከነዓናውያን፣ እስራኤልም ሆነች አምላኳ ከቶ የማይሸነፉ አይደሉም ብለው ያስባሉ። እስራኤል በዮርዳኖስ ሸለቆ ውስጥ እንዳለች፣ ያለ የሌለ ኀይላቸውን አሰባስበው ሊዘምቱባትና ዶግ ዐመድ ሊያደርጓት ይችላሉ።

7፥9 *ታላቁ ስምህ፤* በሕዝቡ ኀጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር ክብር በዓለም ፊት ዝቅ እንዳይል ኢያሱም እንደ ሙሴ ማለደ (ዘኍ 14፥13-16፤ ዘዳ 9፥28-29)።

7፥11 *እስራኤል በድሎአል፤* አንድ ወታደር ለእግዚአብሔር የተቀደሰውን ዕቃ በመስረቁ፣ መላው ሕዝብ በደለኛ ሆነ (22፥20 ይመ)። *ቃል ኪዳኔን ጥሰዋል፤* ቍ 15 ይመ። የእስራኤል ትልቁ በደል ይህ ነው፤ ከዚህ በኋላ ያለው ክፍል አንድ በደለኛ ሰው እንዴት መቀጣት እንዳለበት ተጨማሪ መመሪያ ይሰጣል።

7፥12 *እርም የሆነውን፤* የ6፥18 ማብ ይመ።

7፥13 *ሰውነታችሁን ቀድሱ፤* እያንዳንዱ እስራኤላዊ እግዚአብሔርን ለመገናኘት በሃይማኖታዊ በዓላት ወይም እግዚአብሔር በጠራው ልዩ ጉባኤ ላይ ከመገኘቱ በፊት ተከታታይነት ያለው የመንጻት ሥርዓት መፈጸም አለበት (የ3፥5 ማብ ይመ)። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚጠራው ለፍርድ ነው።

7፥14 *እግዚአብሔር የሚለየው ነገድ፤* ዕጣ በሚጣልበት ጊዜ፣ በመጀመሪያ ከነገዶቹ አንዱ “በእግዚአብሔር ይለያል”፤ ከዚያም ከቤተ ሰቦቹ አንዱ፣ ቀጥሎ ግለሰቡ ይለያል፤ በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር በደለኛውን ሰው ነጥሎ ያወጣዋል። ዕጣው የሚጣለው ምናልባት ሊቀ ካህናቱ በሚለብሰው ኤፉድ ውስጥ በሚገኙት በኡሪምና በቱሚም አማካይነት ሊሆን ይችላል (የዘፀ 28፥30፤ የ1ሳሙ 2፥28 ማብ ይመ፤ የ1ሳሙ 14፥41 አግራጌ ትርጕም ይመ።

7፥15 *በእስራኤልም ዘንድ አሳፋሪ ተግባር፤* እስራኤል የእግዚአብሔር የኪዳን ሕዝብ በመሆኗ፣ በመካከሏ የተፈጸመው ተግባር እጅግ አስነዋሪ መሆኑን ለመግለጽ የገባ ቃል ነው (ዘዳ 22፥21፤ መሳ 19፥23-24፤ 20፥6፡10፤ 2ሳሙ 13፥21 ይመ)።

7፥19 *ልጄ ሆይ፤* ኢያሱ አካንን እንደ ልጁ ተመለከተው። *ለእግዚአብሔር ክብርን ስጥ፤* አግራጌ ትርጕሙን ይመ። *ለእርሱም ተናዘዝ፤* “አመስግነው” ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

7፥21 *ከሰናዖር የመጣ ... ካባ፤* ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የገባ ውድ ልብስ ነው።

7፥23 *በእግዚአብሔር ፊት፤* እዚህ ላይ ዳኛ ሆኖ የሚፈርደው እግዚአብሔር ነው።

7፥24 *ኢያሱም ከመላው እስራኤል ...፤* ኢያሱና መላው የእስራኤል ሕዝብ፣ እግዚአብሔር በከነዓናውያንም ሆነ ኪዳኑን በሚተላለፉ ሁሉ ላይ ፍርዱን የሚያስፈጽምባቸው ወኪሎቹ ናቸው።

ሁም ድንኳኑንና የእርሱ የሆነውን ሁሉ
ወደ አኮር ሸለቆ አስወሰደ። 25ኢያሱም፣
“እንዲህ ያለውን መከራ ለምን አመጣብህን?
እነሆ፤ ዛሬ በአንተም ላይ *እግዚአብሔር*
*መከራ ያመጣብሃል*” አለው፤ ከዚያም እስራ
ኤል በሙሉ በድንጋይ ወገሩት፤ የቀሩትንም
እንደዚሁ ከወገሩ በኋላ በእሳት አቃጠሏ
ቸው። 26በአካንም ላይ እስከ ዛሬ ድረስ
የሚታየውን ታላቅ የድንጋይ ቍልል
ከመሩበት፤ ከዚያም *እግዚአብሔር* ከአስፈሪ
ቍጣው ተመለሰ፤ ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ
ያ ስፍራ የአኮር" ሸለቆ ተባለ።

## የጋይ ከተማ ተደመሰሰ

8 ከዚያም *እግዚአብሔር* ኢያሱን እንዲህ
አለው፤ “አትፍራ፤ አትደንግጥ፤ ሰራዊቱን
ሁሉ ይዘህ በመውጣት ጋይን ውጋ፤ የጋይን
ንጉሥ፣ ሕዝቡን፣ ከተማውንና ምድሩን አሳ
ልፌ በእጅህ ሰጥቼሃለሁና። 2በኢያሪኮና በን
ጉሥዋ ላይ ያደረግኸውንም ሁሉ፣ በጋይና
በንጉሥዋ ላይ ትደግመዋለህ፤ በዚህ ጊዜ
ግን ምርኮውንና ከብቱን ለራሳችሁ ታደርጉ
ታላችሁ፤ ታዲያ ከከተማዪቱ በስተጀርባ
የደፈጣ ጦር አዘጋጅ።”

3ስለዚህ ኢያሱና ሰራዊቱ በሙሉ ጋይን
ለመውጋት ወጡ፤ ኢያሱም ምርጥ ከሆኑት
ተዋጊዎቹ ሠላሳ ሺህ ጦር አዘጋጅቶ በሌሊት
ላካቸው፤ 4እንዲህ የሚል ትእዛዝም ሰጣቸው፤
“እነሆ፤ ከከተማዪቱ በስተጀርባ ታደፍጣላ
ችሁ፤ ከከተማዪቱ አትራቁ፤ ሁላችሁም ነቅ
ታችሁ ተጠባበቁ፤ 5እኔና አብረውኝ ያሉት
ሁሉ ወደ ከተማዪቱ እንጠጋለን፤ ሰዎቹ
ከዚህ በፊት እንዳደረጉት ሊወጉን ወደኛ
ሲመጡ፤ እኛ ደግሞ እንሸሻለን፤ 6እነርሱም፣
‘ከዚህ ቀደም እንዳደረጉት አሁንም ከእኛ
በመሸሽ ላይ ናቸው’ በማለት ከከተማዪቱ
እስክናርቃቸው ድረስ ይከታተሉናል፤ በዚህ
ሁኔታ እኛም እንሸሻለን፣ 7እናንተም ከተደ
በቃችሁበት ትወጡና ከተማዪቱን ትይዛላ
ችሁ፤ ስምባካችሁ *እግዚአብሔር* ከተማዪቱን

7፥25 ዘፍ38፥24፤ ዘሌ20፥2፤ዘዳ17፥5፤ ኢሱ6፥18፤1ነገ12፥18፤2ዜና10፥18፤24፥21፤ነህ9፥26፤
7፥26 ቍ24፤ዘፍ 5፥20፤ዘኍ25፥4፤ 2ሳሙ18፥17
8፥1 ዘፍ26፥24፤ዘኍ 14፥9፤ዘዳ1፥21፤31፥6፤ኢሱ6፥2፤7፥2፤9፥31 10፥1፡7፤12፥9፤6፥2
8፥2 ቍ4:12:27፤ ዘፍ49፥27፤ዘዳ20፥14፤መሳ9፥43፤20፥29
8፥7 መሳ7፥7፤ 1ሳሙ 23፥4
8፥8 ቍ19፤መሳ20፥29-38
8፥9 2ዜና13፥13
8፥10 ዘፍ22፥3፤ ኢሱ7፥6
8፥14 ዘዳ1፥1፤ መሳ20፥34
8፥15 ኢሱ15፥61፤ 16፥1፤18፥12፤ መሳ20፥36
8፥16 መሳ20፥31

በእጃችሁ አሳልፎ ይሰጣችኋልና። 8ከተማዪ
ቱን ስትይዙም በእሳት አቃጥሏት፤ *እግዚ*
*አብሔር* ያዘዘውንም አድርጉ፤ እነሆ አዝዣ
ችኋለሁ።”

9ከዚያም ኢያሱ ሰዎቹን ላካቸው፤ እነር
ሱም ሄደው ከጋይ በስተ ምዕራብ በቤቴልና
በጋይ መካከል ባለው ቦታ አደፈጡ፤ ኢያሱ
ግን እዚያው ከሕዝቡ ጋር ዐደረ።

10በማግስቱ ጧት ኢያሱ ማልዶ በመነ
ሣት ወንዶቹን ሰበሰበ፤ እርሱና የእስራኤል
አለቆችም ከፊት ሆነው እየመሯቸው ወደ
ጋይ ወጡ፤ 11ከእርሱ ጋር የነበሩትም ተዋጊ
ዎች በሙሉ ወጥተው ወደ ከተማዪቱ
በመጠጋት ከፊት ለፊቷ ደረሱ፤ ከዚያም
ከጋይ በስተ ሰሜን መካከል ካለው ሸለቆ
ማዶ ሰፈሩ። 12ኢያሱ ቀደም ብሎ አምስት
ሺህ ሰው ያህል በመውሰድ ከከተማዪቱ
በስተ ምዕራብ፣ በቤቴልና በጋይ መካከል
እንዲያደፍጡ አድርጎ ነበር። 13ከከተማዪቱ
በስተ ሰሜን የነበሩትንም፣ ከከተማዪቱ በስተ
ምዕራብ የሸመቁትንም ወታደሮች ሁሉ
ስፍራ ስፍራቸውን እንዲይዙ አደረጋቸው፤
በዚያችም ሌሊት ኢያሱ ወደ ሸለቆው
ሄደ።

14የጋይ ንጉሥ ይህን ባየ ጊዜ እርሱና
የከተማዪቱ ወንዶች ሁሉ ማልደው በመገ
ሥገሥ፣ እስራኤልን ለመውጋት ከዓረባ
ፊት ለፊት ወደሚገኘው ስፍራ መጡ፤ ንጉሡ
ግን ከከተማዪቱ በስተ ጀርባ ያደፈጠ
ኀይል የሚጠባበቀው መሆኑን አያውቅም
ነበር። 15ኢያሱና እስራኤል በሙሉ ድል
የተመቱ መስለው በመታየት፣ ወደ ምድረ
በዳው ሸሹ። 16የጋይ ሰዎች በሙሉ እንዲ
ያሳድዷቸው ተጠሩ፤ ኢያሱንም አሳደዱት፤
በዚህ ሁኔታም የጋይ ሰዎች ከከተማዪቱ
እንዲርቁ ተደረገ። 17እስራኤልን ለማሳደድ
ከጋይና ከቤቴል ያልወጣ ወንድ አልነበረም፤
ከተማዪቱንም ከፍተው ትተው እስራኤልን
ማሳደድ ያዙ።

"26 *አኮር* ማለት ችግር ወይም መከራ ማለት ነው።

*የእርሱ የሆነውን ሁሉ፤* አካን የቤተ ሰቡ መሪ (ምሳሌም) እንደ መሆኑ፣ በእርሱ ኀጢአት ምክንያት መላ ቤተ ሰቡ በፍርድ ሥር ወደቀ። ይህም የሆነው መላው ኅብረተሰብ በአንድ ሰው ይወከላል በሚለው መርሕ መሠረት ነው።

7፥25 *በድንጋይ ወገሩት፤* በድንጋይ የተወገረው የቅዱሱን የእግዚአብሔርን ኪዳን በመተላለፉና በደለኛም ሆኖ በመገኘቱ ነው (ዘፀ 19፥13፤ ዘሌ 24፥23፤ ዘኍ 15፥36 ይመ)። ከዚያም በኋላ ምድሪቱ ከከፋት ትጠራ ዘንድ የአካንና የቤተ ሰቡ አስከሬን ተቃጠለ።

7፥26 *ታላቅ የድንጋይ ቍልል፤* በጌልገላ ከተተከለው የመታሰቢያ ሐውልት በተጨማሪ ሕዝቡ ያደረገውን ውጊያ ለማስታወስ የቆመ ሁለተኛው የመታሰቢያ ድንጋይ ነው። *አኮር፤* ለአካን የተሰጠ ሌላው ስም ነው (1ዜና 2፥7 ይመ)፤ አማራጭ ትርጕሙን ይመ።

*8፥1-29፤* ይህ ክፍል እስራኤላውያን ከዚህ በኋላ ላለባቸው ውጊያ እንዴት መዘጋጀትና ኃይን እንዴት መያዝ እንዳለባቸው የሚያሳስብ ነው።

8፥1 *አትፍራ፤* አሁን እስራኤል ካለባት በደል ሁሉ ጸድታለች፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ኢያሱን እንደ ገና ያበረታታዋል (1፥3-5፤ 3፥11-13፤ 6፥2-5 ይመ)።

8፥2 *ምርኮውንና ... ለራሳችሁ ታደርጉታላችሁ፤* እግዚአብሔር የከነዓን ሀብት ሁሉ የእርሱን ውጊያ ለሚዋጋው ሰራዊቱ እንዲሰጥ አዘዘ። *የደፈጣ ጦር አዘጋጅ፤* ሰራዊቱን የሚመራው እግዚአብሔር በመሆኑ፣ የውጊያውንም ስልት የሚነድፈው እርሱ ነው።

8፥3 *ሠላሳ ሺህ፤* አድፍጦ አደጋ ለመጣል ይህ ቍጥር እጅግ ብዙ ይመስላል፤ ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ሰዎች “ሺህ” የሚለውን ቃል “አለቃ” ብለው ይተረጕሙታል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ፣ ኢያሱ በደፈጣ ተዋጊነት የላከው ሠላሳ አለቆችን ነው ማለት ነው።

8፥4 *ከከተማዪቱ በስተጀርባ፤* በምዕራብ በኩል ማለት ነው (ቍ9 ይመ)።

8፥12 *አምስት ሺህ፤* ቍጥር 3 ሠላሳ ሺህ ወታደሮች ለደፈጣ ተዋጊዎች ደጀን መሆናቸውን ይገልጣል። ምናልባት ኢያሱ አስተማማኝ ድልን ለመቀዳጀት ሌሎች ሁለት የተለያዩ ክፍሎችን ሳይመድብ አይቀርም። ወይም ደግሞ ከተሰለፈው ሠላሳ ሺህ ወታደር ውስጥ አምስቱ ሺህ ጋይን እንዲወጋ፣ የተቀረው ሃያ አምስት ሺህ ደግሞ ከቤቴል በኩል ሊሰነዘር የሚችለውን ጥቃት እንዲመክት ሳያደርግ አይቀርም (ቍ 17 ይመ)።

8፥13 *በስተ ሰሜን የነበሩትንም፤* የኢያሱ ሰራዊት ከከተማዪቱ በስተ ሰሜን በኩል ሄዶ ሰፈረ፤ ከዚያም በስተ ምሥራቅ በኩል የሸሸ ለመምሰል ሰራዊቱን እንዳለ ነቅሎ አስወጣ።

8፥17 *ከጋይና ከቤቴል፤* ምንም እንኳ ሁለቱም የየራሳቸው ንጉሥ ቢኖራቸውም (12፥9:16)፣ እርስ በርስ ለመተባበር

18*እግዚአብሔርም* ኢያሱን፣ "ከተማዪቱን
በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ፣ የያዝኸውን
ጦር ወደ ጋይ አነጣጥር" አለው፤ ኢያሱም
ጦሩን ወደ ጋይ አነጣጠረ። 19ይህን እንዳ
ደረገም ያደፈጡት ሰዎች ከተደበቁበት
ስፍራ በፍጥነት ወጥተው ወደ ፊት ሮጡ፤
ገብተው ከተማዪቱን ያዟት፤ ወዲያውኑም
በእሳት አቃጠሏት።
20የጋይ ሰዎች ወደ ኋላ ዞረው ሲመለከቱ
የከተማዪቱ ጢስ ወደ ሰማይ ሲወጣ አዩ፤
ወደ ምድረ በዳ ይሸሹ የነበሩት እስራ
ኤላውያን ፊታቸውን ስላዞሩባቸውም፣ በየ
ትኛውም በኩል ማምለጫ መንገድ አልነበ
ራቸውም። 21ኢያሱና እስራኤል ሁሉ ያደ
ፈጠው ጦር ከተማዪቱን መያዙንና ጢሱ
ወደ ላይ መውጣቱን ሲያዩ፣ ወደ ኋላ
ተመልሰው በጋይ ሰዎች ላይ አደጋ ጣሉብ
ቸው፤ 22ያደፈጡትም ሰዎች እንደዚሁ ከከተ
ማዪቱ ወጥተው መጡባቸው፤ ስለዚህ እስራ
ኤላውያን በዚያም በዚህም ስለ ከበቧቸው
የጋይን ሰዎች ከመካከል አደረጓቸው፤ እስ
ራኤላውያንም ሰዎቹን ፈጇቸው፤ አንድ
እንኳ የተረፈ ወይም ያመለጠ አልነበረም፤
23ነገር ግን የጋይን ንጉሥ ከነሕይወቱ ይዘው
ወደ ኢያሱ አመጡት።
24እስራኤላውያን የጋይን ወንዶች ሁሉ
ባሳደዷቸው ሜዳና ምድረ በዳ ከጨረሷቸ
ውና እያንዳንዳቸውንም በሰይፍ ከፈጁ በኋላ፣
ወደ ከተማዪቱ ተመልሰው በዚያ ያገኙትን
ሁሉ ገደሉ። 25በዚያች ዕለት የጋይ ሰዎች
ሁሉ አለቁ፤ የወንዶቹና የሴቶቹም ብዛት
ዐሥራ ሁለት ሺህ ነበር። 26ኢያሱ በጋይ
የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ፈጽሞ እስኪያጠፋ
ቸው* ድረስ ጦር ያነጣጠረባትን እጁን አላ
ጠፈም ነበር። 27እስራኤላውያንም *እግዚአ
ብሔር* ኢያሱን ባዘዘው መሠረት፣ በከተማ
ዪቱ ያገኙትን እንስሳትና ምርኮ ብቻ ለራሳ
ቸው አደረጉ።
28ስለዚህ ኢያሱ ጋይን አቃጠላት፣ እስከ
ዛሬ እንደሚታየውም ለዘላለም የዐመድ
ቍልልና ባድማ አደረጋት። 29የጋይንም ንጉሥ
በዛፍ ላይ ሰቀለው፤ ሬሳውንም እስኪመሽ
ድረስ እዚያው እንዳለ ተወው፤ ፀሐይ ስትጠ
ልቅም፣ ኢያሱ ሬሳውን እንዲያወርዱትና
በከተማው በር ላይ እንዲጥሉት አዘዘ፤
የትልልቅ ድንጋይ ቍልልም ከመሩበት፤
ይህም እስከ ዛሬ ድረስ እዚያው ይገኛል።

## ቃል ኪዳኑ በጌባል ተራራ ታደሰ

30ከዚያም ኢያሱ በጌባል ተራራ ላይ
ለእስራኤል አምላክ *ለእግዚአብሔር* መሠዊያን
ሠራ። 31መሠዊያዉንም የሠራው *የእግዚ
አብሔር* ባሪያ ሙሴ፣ እስራኤላውያንን ባዘ
ዛቸው መሠረት ሲሆን፣ ይህንም የሠራው
በሙሴ የሕግ መጽሐፍ እንደ ተጻፈው ባል
ተጠረበና የብረት መሣሪያ ባልነካው ድን
ጋይ ነው፤ በዚህም ላይ የሚቃጠል መሥ
ዋዕት አቀረቡ፤ የኅብረት መሥዋዕትም†
ሠዉ። 32ኢያሱም ሙሴ የጻፈውን የሕግ
መጽሐፍ እስራኤላውያን እያዩ በድንጋዮች

*26 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው። †31 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት፤* ይባላል።

8፥18 ቍ26፤ዘፀ4፥2፤17፥9-12፤ኢዮ41፥26፤መዝ 35፥3
8፥19 ቍ8፤መሳ 20፥33
8፥20 መሳ20፥40
8፥22 ዘዳ7፥2፤ ኢሱ10፥1
8፥23 1ሳሙ15፥8
8፥25 ዘዳ20፥16-18
8፥26 ቍ18፤ ዘፀ17፥12፤ዘኍ21፥2
8፥27 ቍ2
8፥28 ዘፍ35፥20፤ ዘኍ31፥10፤ዘዳ13፥16፤ ኢሱ7፥2፤10፥1፤ኤር 49፥3
8፥29 ዘዳ21፥23፤ 2ሳሙ18፥17፤ዮሐ 19፥31
8፥30 ቍ33፤ዘፀ 20፥24፤ዘዳ11፥29
8፥31 ዘፀ20፥25፤ ዘዳ27፥6-7
8፥32 ዘዳ27፥8

የወሰዱት እርምጃ በመካከላቸው ጥብቅ ስምምነት መኖሩን ያስገነዝባል።

*8፥18-19፤* ኢያሱ አድፍጦ ለሚጠባበቀው ሰራዊት ምልክት ያስተላለፈው በጦሩ ስለት ላይ የፀሐይ ብርሃን ነጸብራቅ እንዲታይ በማድረግ ነው።

8፥26 *እስኪያጠፋቸው፤* ኢያሱ የከነዓን ከተማ ነዋሪዎች ሙሉ በሙሉ እንዲደመሰሱ ለሁለተኛ ጊዜ የተቀደሰ ትእዛዙን አስተላለፈ (የ6፥17ን ማብ ይመ)።

8፥28 *ጋይን አቃጠላት፤* ኢያሪኮን (6፥24)፣ በኋላም አሦርን እንዳቃጠለ ሁሉ (11፥11) ማለት ነው። *እስከ ዛሬ . . . ባድማ፤* ጋይ የፍርስራሽ ክምር መሆኗ በትክክል ከተረጋገጠ (የ7፥2ን ማብ ይመ)፣ ከ1200-1100 ዓ.ቅ.ክ. ጀምሮ በዚያ አካባቢ ሰዎች ይኖሩ እንደ ነበር ምልክት ሊሆን ይችላል።

8፥29 *የጋይንም ንጉሥ በዛፍ ላይ ሰቀለው፤* እስራኤላውያን ሰውን በስቅላት አይገድሉም፤ "ዛፍ" የሚለው ቃል ምናልባት ንጉሡ ከተገደለ በኋላ ሬሳው የተሰቀለበት ግንድ ሊሆን ይችላል (የዘዳ 21፥22ን ማብ ይመ)። *እስኪመሽ ድረስ፤* ይህ የሆነው በሙሴ ሕግ መሠረት ነው (ዘዳ 21፥22-23 ይመ)። *የትልልቅ ድንጋይ ቍልል፤* በምድሪቱ የቆመ ሦስተኛው የመታሰቢያ ሐውልት ነው (የ7፥26ን ማብ ይመ)።

*8፥30-35፤* ሙሴ ባዘዘው መሠረት (ዘዳ 11፥26-30፤ 27፥1-8)፣ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ባደሱ ጊዜ የመጀመሪያው ውጊያ ተጠናቀቀ (የመጽሐፈ ኢያሱን መግቢያ ይመ)። በከነዓን የተቀዳጁት ድል የእግዚአብሔርን ማንነት በሚገባ አሳይቶአቸዋል። ይህም የመጨረሻ ሁኔት (ኢያሱ በመጨረሻ ለሕዝቡ ያደረገውን ንግግር በም 24 ላይ ይመ) በአጽንዖት የሚያመለክተው፣ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላት ግንኙነት የጌታና የአገልጋይ ግንኙነት መሆኑን ነው። እስራኤል ለውጊያ ስትወጣና አገር ስትወርስ ለእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ የምትገዛ የእግዚአብሔር መንግሥት ሕዝብ መሆኗን ከልብ መቀበል አለባት (የ5፥14 ማብ ይመ)።

እስራኤል ተጨማሪ ውጊያ ስታካሂድ በጌባልና በገሪዛን ተራራ መካከል እንዴት በሰላም መስፈር እንደ ቻለች በትክክል መግለጥ አይቻልም፤ ከዚህ የተነሣ አንዳንድ ሰዎች የእስራኤልን ታሪክ በሌላ አቅጣጫ ለማዮትና ሊታረቋም ሌላ ቅርጽ ለማስጠት ተገደዋል። ይሁን እንጂ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች፣ በተቻላቸው ዐቅም የሁኔቶቹን ቅደም ተከተል ጠብቀው ከመጻፍ ይልቅ የታሪኩን ፍሬ ሐሳብ ብቻ ተከትለው የሚጽፉበት ጊዜ እንዳለ ልብ ማለት ያሻል። እዚህም ላይ የምናየው ይህንኑ ዓይነት የአጻጻፍ ስልት ሳይሆን አይቀርም፤ ምክንያቱም ስለ ገባዖን ሰዎች ማታለልና እጅ መስጠት (ም 9) የተነገረው ታሪክ፣ እስራኤል የተቀረውን የከነዓንን ምድር እንዴት እንደ ወረሰች በሚያወሳው ታሪክ ውስጥ ቍልፍ ቦታ ይዞ እናገኘዋለን (በ9፥1-2 ላይ ያለውን የጸሐፊውን መግቢያ ይመ)። የሴኬም ሰዎች (በሁለቱ ተራሮች መካከል የምትገኝ ዋና ከተማ ናት) ኤዊያውያን ናቸው (ወይም ደግሞ በኤዊያውያን አገዛዝ ሥር የሚኖሩ ናቸው፤ ዘፍ 34፥2 ይመ)፤ በመሆኑም ከገባዖን ከተማ ነዋሪዎች ጋር የቅርብ ዝምድና አላቸው (9፥7፤ 11፥19)። ከዚህም በተጨማሪ በገባዖንና በሴኬም መካከል አንድም ታዋቂ ከተማ የለም (ቤቴልና ጋይ ድል ተደርገዋል)። በእስራኤልና በገባዖን ሰዎች መካከል የተደረገው እጅ የመስጠት ስምምነት (ም9)፣ የሴኬምን ኤዊያውያን ሳይጨምር አይቀርም፤ ከጊዜ ቅደም ተከተል አንጻር ያየን እንደሆነ በም 8 መደምደሚያ ላይ የምናገኘው የቃል ኪዳኑ መታደስ ሥርዐት (ቀደም ሲልም የተጠቀሰው ትረካ) የተፈጸመው በምዕ 9 ላይ ከተነገረው ሁኔት በኋላ ነው። ይህ አባባል ትክክል ከሆነ፣ እስራኤል የገባችውን ኪዳን እንደገና ስታድስ (ቍ 33፡35) የገባዖን ሰዎች ወይም ወኪሎቻቸው "መጻተኞች" ከተባሉት መካከል ሳይሆኑ አይቀሩም።

8፥30 *በጌባል ተራራ፤* በዚህ ተራራ ጫፍ ላይ የሴኬም ከተማ ምሽግ ይገኛል፤ አብርሃም መሠዊያ የሠራውም በዚሁ ተራራ ላይ ነው (ዘፍ 12፡6-7)።

8፥31 *የሚቃጠል መሥዋዕት፤* ዘሌ 1፡1-17 ይመ። *የኅብረት መሥዋዕት፤* ዘሌ 3፥1-17፤ 7፥11-18 ይመ።

8፥32 *በድንጋዮች ላይ ቀረጸው፤* ሕዝቡ በመጀመሪያ ድንጋዮቹን እንዲለስኑ፣ ከዚያም ሕጉን እንዲጽፉባቸው ሙሴ አዝዞ ነበር (ዘዳ 27፥2-4)። እነዚህ ድንጋዮች በምድሪቱ አራተኛ

ላይ ቀረጸው። [33]እስራኤል በሙሉ መጻተኛ
ውም ሆነ ተወላጁ፣ ሽማግሌዎቻቸውም ሆኑ
ሹማምንታቸው እንዲሁም ዳኞቻቸው የእግዚ
አብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ተሸከ
ሙት ሌዋውያን ካህናት ፊታቸውን አዙረው፣
በታቦቱ ግራና ቀኝ ቆመው ነበር። የእግዚ
አብሔር ባሪያ ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እን
ዲባርኩ መመሪያ በሰጠ ጊዜ፣ አስቀድሞ
ባዘዘው መሠረት፣ ግማሹ ሕዝብ በገሪዛን
ተራራ፣ ግማሹ ደግሞ በጌባል ተራራ ፊት
ለፊት ቆመ።
[34]ከዚህ በኋላ ኢያሱ፣ የሕጉን ቃላት
በሙሉ ማለትም በረከቱንና መርገሙን ሁሉ፣
ልክ በሕጉ መጽሐፍ እንደተጻፈው አነበበ።
[35]ኢያሱ በመላው የእስራኤል ጉባኤ ፊት
ሴቶች፣ ሕፃናትና በመካከላቸው የኖሩ
መጻተኞች ባሉበት ያነበበው፣ አንድም ሳይ
ቀር ሙሴ ያዘዘውን ቃል ሙሉ በሙሉ ነበር።

## የገባዖን ሰዎች የፈጸሙት ማታለል

**9** በዮርዳኖስ ምዕራብ ባለው በተራራማው
አገር፣ በቈላማው ምድር እንዲሁም እስከ
ሊባኖስ በሚደርሰው በመላው በታላቁ ባሕር[ፉ]
ዳርቻ የነበሩት የኬጢያውያን፣ የአሞራው
ያን፣ የከነዓናውያን፣ የፌርዛውያን፣ የኤዊያ
ውያን፣ የኢያቡሳውያን ነገሥታት ይህን በሰሙ
ጊዜ፣ [2]ኢያሱንና እስራኤልን ለመውጋት
በአንድነት መጡ።
[3]የገባዖን ሰዎች ግን ኢያሱ በኢያሪኮና
በጋይ ላይ ያደረገውን በሰሙ ጊዜ፣ [4]ለማ
ታለል ፈለጉ፤ ስለዚህም ያረጀ ስልቻና የተ
ጣፈ አሮጌ የወይን ጠጅ አቀማዳ በአህያ
የጫነ[ፓ] መልእክተኛ መስለው ሄዱ። [5]ሰዎ
ቹም ያረጀና የተጠጋገነ ነጠላ ጫማ አድር
ገዋል፤ አሮጌ ልብስ ለብሰዋል፤ ለስንቅ
የያዙት እንጀራም በሙሉ የደረቀና የሻገተ
ነበር። [6]ከዚያም ኢያሱ ወደ ሰፈረበት ወደ
ጌልገላ ሄደው ኢያሱንና የእስራኤልን ሰዎች፣
"የመጣነው ከሩቅ አገር ነው፤ ከእኛ ጋር
ቃል ኪዳን ግቡ" አሏቸው።

8፥33 ዘሌ16፥29፤ ዘዳ11፥29፤31፥12 የሐ4፥20
8፥34 ዘዳ28፥61፤ 31፥11
8፥35 ዘፀ12፥38፤ ዘዳ31፥12
9፥1 ቊ7፤ዘፍ13፥7፤ ዘኍ13፥17፤34፥6፤ዘዳ 3፥25፤ኢሱ3፥10፤ 11፥19
9፥3 ቊ17፤ዘፍ12፥ 8፤ኢሱ8፥1፤10፥10፤ 11፥19፤18፥25፤21፥1 7፤2ሳሙ2፥12፤5፥25፤ 20፥8፤1ነገ3፥4፤9፥2 1ዜና8፥29፤14፥16፤1 6፥39፤21፥29፤2ዜና1 ፥3፤ነህ3፥7፤ኢሳ28፥ 21፤ኤር28፥1፤41፥12
9፥6 ቊ22፤ዘፍ26፥ 28፤ዘዳ11፥30
9፥7 ቊ1፤ዘፀ23፥ 32፤1ነገ5፥12
9፥8 2ነገ10፥5
9፥9 ቊ24፤ዘዳ20፥ 15፤ዘኍ23፥22
9፥10 ዘኍ21፥24፡ 25፡33፡35፤21፥ 24፡35፤ኢሱ2፥10
9፥14 ዘፀ16፥28፤ ዘኍ27፥21
9፥15 ቊ3፡7፡21፤ ኢሱ10፥1፡4፤11፥19፤ መሳ1፥21፤2ሳሙ21፥ 2፤24፥1፤መዝ106፥34

[7]የእስራኤልም ሰዎች ሒዋውያኑን፣ "እናንተ
የምትኖሩት እዚሁ ቅርብ ቢሆንስ? ታዲያ
ከእናንተ ጋር እንዴት ቃል ኪዳን እንገባ
ለን?" አሏቸው።
[8]እነርሱም ኢያሱን፣ "እኛ ባሪያዎችህ ነን"
አሉት።
ኢያሱ ግን፣ "እናንተ እነማን ናችሁ?
የመጣችሁትስ ከየት ነው?" ሲል ጠየቃቸው።
[9]እነርሱም እንዲህ ብለው መለሱለት፤ "እኛ
ባሪያዎችህ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ዝና
ሰምተን፣ እጅግ ሩቅ ከሆነ አገር መጥተ
ናል፤ ዝናውንና በግብፅ ያደረገውንም ሁሉ
ሰምተናል፤ [10]እንዲሁም ከዮርዳኖስ ማዶ
ባሉት በሁለቱ የአሞራውያን ነገሥታት
ማለትም በሐሴቦን ንጉሥ በሴዎን፣ አስታ
ሮትን ይገዛ በነበረው በባሳን ንጉሥ በዐግ
ያደረገውን ሁሉ ነው። [11]ሽማግሌዎቻችንና
በአገራችን የሚኖሩት ሁሉ፣ 'ለመንገዳችሁ
የሚሆን ስንቅ ያዙ፤ ሄዳችሁም ተገናኟቸው፤
እኛ ባሮቻችሁ እንሆናለን፤ ከእኛ ጋር ቃል
ኪዳን ግቡ በሉአቸው' አሉን። [12]ይህ የያዝ
ነው እንጀራ ወደ እናንተ ለመምጣት ከቤ
ታችን በተነሣንበት ቀን ትኩስ ነበር፤
አሁን ግን እንዴት እንደ ደረቀና እንደ
ሻገተ ተመልከቱ። [13]እነዚህ የወይን ጠጅ
አቀማዳዎቻችን ያን ጊዜ ስንሞላቸው አዲስ
ነበሩ፤ አሁን ግን እንዴት እንደተቀዳደዱ
ተመልከቱ፤ ልብሳችንና ጫማችንም ብዙ
መንገድ በመጓዛችን አልቀዋል።"
[14]የእስራኤልም ሰዎች ከስንቃቸው ላይ
ጥቂት ወሰዱ፤ ስለ ጒዳዩ ግን እግዚአብሔ
ርን አልጠየቁም ነበር። [15]ኢያሱም በሰላም
ለመኖር የሚያስችላቸውን ቃል ኪዳን ከእነ
ርሱ ጋር አደረገ፤ የጉባኤውም መሪዎች
ይህንኑ በመሐላ አጸኑላቸው።

[ፉ]1 የሜድትራኒያን ባሕር ነው። [ፓ]4 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጂ ዎች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ነገር ግን አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጂዎች፣ የቡልጌት፣ የሱርስቱ ትርጒም እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናት ቅጂ *የሚያስፈልጋቸውን ነገር አዘጋጁ፤ በአህዮቻቸውም ላይ* ጫኑ ይላሉ።

የመታሰቢያ ሐውልት ናቸው (የቍ 29 ማብ ይመ)።

8፥33 *መጻተኛውም ሆነ ተወላጁ፤* አሁን የእስራኤል ሕዝብ ጉባኤ ከግብፅ የወጡ "ሌሎች ሕዝቦች" (ዘፀ 12፥38) እንዲሁም በምድረ በዳ ሲንከራተቱ በነበሩበት ወቅት ከእነርሱ ጋር የተቀላቀሉ ሕዝቦችን አጠቃሎ ይዞአል (የቍ 30-35ን ማብ ይመ)።

8፥34 *በረከቱንና መርገሙን፤* ዘዳ 27፥28 እና ማብ ይመ።

*9፥1-27፤* ይህ ምዕራፍ የሚያትተው የገባዖን ሰዎች የነገድ መሪዎችን እንዴት እንዳታለሉና ከእስራኤልም ጋር በሰላም ለመኖር እንዴት የስምምነት ፈቃድ እንዳገኙ ነው። ታሪኩም እስራኤል የምድሪቱን ታላቅ ክፍል እንዴት እንደ ያዘች ከሚናገሩት ሦስት ክፍሎች ውስጥ የመጀመሪያው ነው፤ ቍ 1-2 እነዚህን ሦስት ክፍሎች ያስተዋውቀናል።

9፥1 *በዮርዳኖስ ምዕራብ ... የነበሩት ... ነገሥታት፤* ትንንሽና ነጻ የከተማ መንግሥታት በከነዓንና በአካባቢዋ ይገኙ ነበር፤ ነዋሪዎቻቸውም ከከነዓን ምድር ውጭ ከየቦታው ፈልሰው የመጡ የተለያዩ ሕዝቦች ነበሩ (ቍ 1-2 ከዘፍ 15፥19 ጋር ያነጻጽሩ)።

9፥3 *የገባዖን፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ኤል-ጂብ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ የሚገኝ ቦታ ሲሆን፣ በኋለኛው የናስ ዘመን እጅግ መልካም የውሃ አቅርቦት የነበረበት የአንድ ከተማ ቅሪት ያሳያል። ገባዖናውያን በዙሪያቸው ከሚገኙ በርካታ ከተሞች ጋር የኅብረት ስምምነት ነበራቸው (ቍ 17)፤ በኅብረቱ ውስጥ የበላይነት የነበራቸው ግን እነርሱ ሳይሆኑ አልቀሩም።

9፥4 *ለማታለል ፈለጉ፤* ገባዖናውያን የእስራኤልን አምላክ እጅግ ስለ ፈሩ፣ ኢያሱን በማታለል በሕይወት የሚኖሩበትን ስምምነት አደረጉ።

9፥6 *ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን ግቡ፤* የገባዖን ሰዎች ይህን ጥያቄ ያቀረቡት ለእስራኤላውያን የሚገዙ ባሪያዎች አድርገው ራሳ ቸውን በመስጠት ነው (በቍ 11 ላይ ራሳቸውን "እኛ ባሮቻችሁ" ብለው እንደጠሩ ይመ፤ ይህ አባባል የወቅቱ ዓለም ዐቀፋዊ የዲፕሎ ማሲ ቋንቋ ነው)። ከፊታቸው የሚጠብቃቸውን ሞት ከመሞት ይልቅ ራሳቸውን ባሪያ ማድረግ መረጡ (ቍ 24)።

9፥7 *ሒዋውያኑ፤* ምናልባት ሖራውያን በመባል የሚታወቁ፣ በከነዓን የሚኖሩ ጐሳዎችና በሰሜናዊ ሜስጴጦሚያ ከሚኖሩ ሖራውያን ጋር የሚዛመዱ ሳይሆኑ አይቀርም (11፥19፤ ዘፍ 10፥17፤ ዘፀ 23፥23፤ መሳ 3፥3)።

9፥9 *ዝና ሰምተን፤* በኢያሪኮ ከተሰማው ዝና ጋር (2፥10 ይመ) አንድ ነው።

*9፥10፤* ገባዖናውያን እስራኤል በቅርቡ የተቀዳጀቻቸውን ድሎች (ከሩቅ መጥተው ቢሆን ኖሮ፣ ሊያውቋቸው የማይ ችሏቸውን) ባለመጥቀስ ብልጣብልጥ ለመሆን ሞከሩ።

9፥14 *እግዚአብሔርን አልጠየቁም፤* ለዚህ ተልእኮ ያሰማ ራቸውን ንጉሥ እግዚአብሔርን አላማከሩትም።

9፥15 *በሰላም ለመኖር፤* የገባዖንን ሰዎች ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ለመኖር የሚያስችላቸው የቃል ኪዳን መሐላ የተደረገው

16እስራኤላውያን ከገባዖን ሰዎች ጋር ቃል
ኪዳኑን ካደረጉ ከሦስት ቀን በኋላ፣ ሰዎቹ
እዚያው አጠገባቸው የሚኖሩ ጎረቤቶቻቸው
መሆናቸውን ሰሙ:: 17ስለዚህ እስራኤላው
ያን ተጕዘው በሦስተኛው ቀን ገባዖን፣ ከፊራ፣
ብኤሮትና ቂርያትይዓይሪም ወደ ተባሉት
የገባዖን ሰዎች ወደሚኖሩባቸው ከተሞች
መጡ:: 18ሆኖም እስራኤላውያን አልወጓቸ
ውም፤ የጉባኤው መሪዎች በእስራኤል ስም
ባክ በእግዚአብሔር ስም ምለውላቸው ነበ
ርና:: ማኅበሩም ሁሉ በመሪዎቹ ላይ አጕረ
መረሙ፤ 19ነገር ግን መሪዎቹ ሁሉ ለማኅ
በሩ እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ "በእስራኤል ስም
ባክ በእግዚአብሔር ስም ስለማልንላቸው፣
አሁን ጕዳት ልናደርስባቸው አንችልም፤
20እንዲህ እናደርግላቸዋለን፤ የገባንላቸውን
መሐላ በማፍረስ ቍጣ እንዳይደርስብን፣
በሕይወት እንዲኖሩ እንዲሁ እንተዎቸዋለን፤
21ነገር ግን ለማኅበረ ሰቡ በሙሉ ዕንጨት
እየቈረጡ ውሃ እየቀዱ ይኑሩ::" ስለዚህ
መሪዎቹ የገቡላቸው ቃል ተጠበቀ::
22ከዚያም ኢያሱ የገባዖንን ሰዎች ጠርቶ እንዲህ
አላቸው፤ "እዚሁ አጠገባችን መኖራችሁ የታወቀ
ሆኖ ሳለ፣ 'የምንኖረው ከእናንተ በሩቅ ስፍራ
ነው' ብላችሁ ያታለላችሁን ለምንድን ነው?
23ስለዚህ አሁን የተረገማችሁ ናችሁ፤ ጥቂቶቻች
ችሁም ስለአምላኬ ቤት ምን ጊዜም ዕንጨት
ቈራጭ፣ ውሃ ቀጂ ባሮች ትሆናላችሁ::"
24እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ብለው መለ
ሱለት፤ "አምላክህ እግዚአብሔር ባሪያውን
ሙሴን እንዳዘዘው፣ ምድሪቱን በሙሉ ለእ
ናንተ እንደሚሰጣችሁና ነዋሪዎቿንም ከፊ
ታችሁ እንደሚያጠፋቸው በእርግጥ ለእኛ
ለባሪያዎችህ ተነግሮናል፤ ስለዚህ ከእናንተ
የተነሣ ለሕይወታችን በመሥጋት ይህን አድ
ርገናል:: 25እነሆ፤ አሁን በእጅህ ውስጥ ነን፤
በጎና ትክክል መስሎ የታየህን ነገር ሁሉ
አድርግብን::"
26ስለዚህ ኢያሱ የገባዖንን ሰዎች ከእስራ
ኤላውያን እጅ አዳናቸው፤ እነርሱም አልገ
ደሏቸውም:: 27በዚያችም ዕለት ኢያሱ የገባዖንን
ሰዎች ለማኅበረ ሰቡና እግዚአብሔር በሚ
መርጠው ስፍራ ለሚቆመው የእግዚአብሔር
ለሆነው መሠዊያ እስከ ዛሬ ድረስ ዕንጨት
ቈራጮችና ውሃ ቀጂዎች አደረጋቸው::

9፥16 ቍ22
9፥17 ኢሱ15፥9፡60፤ 18፥14፡15፡25፤መሳ 18፥12፤1ሳሙ6፥21፤ 7፥2፤2ሳሙ4፥2፤23፥3 7፤መዝ132፥6፤ኤር 26፥20
9፥18 ቍ15፤ዘፀ 15፥24፤መሳ21፥1፡7፡ 18፤1ሳሙ20፥17፤መዝ 15፥4
9፥20 ዘፍ24፥8
9፥21 ቍ15፤ዘዳ 29፥11
9፥22 ቍ6፡16
9፥23 ዘፍ9፥25
9፥24 ቍ9
9፥25 ዘፍ16፥6፤ ኤር26፥14
9፥27 ዘፀ1፥11፤ዘዳ 12፥5፤29፥11
10፥1 ቍ3፤ዘዳ20፥ 16፤ኢሱ8፥1፡22፤9፥ 3፡15፤12፥10፤15፥8፡6 3፤18፥28፤መሳ1፥7
10፥3 ቍ5፡23፡31፡ 34፡36፡38፤ዘፍ13፥ 18፤ኢሱ11፥21፤12፥ 11-13፤13፡26፤15፥ 7፡35፡39፡49፤21፥15፡ 29፤መሳ1፥11፤2ነገ 14፥19፤1ዜና6፥58፤ 2ዜና11፥9፤25፥27፤ 32፥9፤ነህ11፥29፡30፤ ኢሳ36፥2፤37፥8፤ኤር 34፥7፤ሚክ1፥13፤9፥ 3፡15፤12፥10፤15፥8፡ 63፤18፥28፤መሳ1፥7፤
10፥4 ኢሱ9፥15
10፥5 ቍ16፤ዘኍ 13፥29፤ዘዳ1፥7

## ፀሐይ ቆመች

10 የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒጼዴቅ፣
ኢያሱ ጋይን ይዞ እንደ ደመሰሳት[1]፣
እንደዚሁም በኢያሪኮና በንጉሥዋ ላይ ያደ
ረገውን ሁሉ፣ በጋይና በንጉሥዋ ላይ ማድ
ረጉን፣ የገባዖን ሰዎችም ከእስራኤል ጋር
የሰላም ውል አድርገው በአጠገባቸው መኖ
ራቸውን ሰማ፤ 2በዚህም እርሱና ሕዝቡ ደነ
ገጡ፤ ምክንያቱም ገባዖን እንደ ነገሥታቱ
ከተማ ሁሉ ታላቅ ከተማ፣ በስፋቷም ከጋይ
የምትበልጥ፣ ሰዎቿም ብርቱ ተዋጊዎች
ነበሩ:: 3ስለዚህ የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒ
ጼዴቅ፣ ሆሃም ወደ ተባለው የኬብሮን ንጉሥ
ጲርአም ወደ ተባለው የየርሙት ንጉሥ፣
ያፊዓ ወደ ተባለው የለኪሶ ንጉሥና ዳቤር
ወደተባለው የዔግሎን ንጉሥ በመላክ፣ 4"ወደ
ዚህ ወጥታችሁ አግዙኝ፤ ከኢያሱና ከእስራ
ኤላውያን ጋር ሰላምን መሥርታለችና ገባዖ
ንን እንምታ" አላቸው::
5ከዚያም አምስቱ የአሞራውያን ነገሥ
ታት ማለት የኢየሩሳሌም ንጉሥ፣ የኬብሮን
ንጉሥ፣ የያርሙት ንጉሥ፣ የለኪሶ ንጉ
ሥና የዔግሎን ንጉሥ ያላቸውን አስተባ
ብረው፣ ሰራዊታቸውንም ሁሉ ይዘው በመው
ጣት ገባዖንን ወጓት::

[1] የዕብራይስጡ ቃል በዚህም ሆነ በቍጥር 28:35:37:39 እና 40 ላይ ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው::

በነገድ አለቆች አማካይነት በቅዱሱ በእግዚአብሔር ስም ነው:: እንዲህ ዐይነቱ መሐላ በእስራኤል ዘንድ የጸና ነው (ዘፀ 20፥7፤ ዘሌ 19፥21፤ 1ሳሙ 14፥24 ይመ)::

9፥18 ***ማኅበሩም ሁሉ … አጕረመረሙ፤*** ምናልባት እስራኤላውያን የፈሩት ከዚህ በፊት ከነዓናውያንን ሙሉ በሙሉ እንዲያጠፉ የተሰጣቸውን መለኮታዊ ትእዛዝ አለመፈጸም የሚያስከትለውን መዘዝ ሊሆን ይችላል፤ እዚህ ላይ ሕዝቡ ያጕረመረሙበት ምክንያት ግን የገባዖናውያንን ከተሞችና ንብረት መውሰድ ካለመቻላቸው የተነሣ ሳይሆን አይቀርም::

9፥21 ***ዕንጨት እየቈረጡ ውሃ እየቀዱ፤*** በዚያን ዘመን ይህ ሐረግ የቤት አገልጋዮችን ተግባር የሚገልጥ የተለመደ አባባል ነው::

9፥23 ***የተረገማችሁ፤*** አንድ ቀን ከነዓን "የሴም ባሪያ" እንደምትሆን (ዘፍ 9፥25-26) ኖኅ የተናገረው ትንቢት እዚህ ላይ በከፊል ተፈጽሞአል:: ***ለአምላኬ ቤት፤*** ምናልባት የገባዖን ሰዎች "ማኅበረሰቡን በሙሉ" (ቍ 21) እንዴት እንደሚያገለግሉ በግልጽ የሚያመለክት ነው:: በመገናኛው ድንኳን (ኋላም በቤተ መቅደሱ) ውስጥ ለሚደረገው የአምልኮ ሥርዐት ብዙ ዕንጨትና ውሃ (ለመሥዋዕቱ ማቃጠያና ለመታሰቢያ) ያስፈልግ ነበር፤ ይህም ብዙ ዝቅተኛ ሥራ እንዲኖር አድርጎአል:: ከዚህ በኋላ ይህ ሥራ የሚሠራው በገባዖናውያን ሲሆን፣ የሚከናወነውም በፈረቃ ነው:: በዚህ ዐይነት ገባዖናውያን ወደ እግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ገቡ:: ሰሎሞን በነገሠ ጊዜ፣ የማደሪያው ድንኳንና መሠዊያው በገባዖን ነበሩ (2ዜና 1፥3፡5)::

9፥27 ***እግዚአብሔር በሚመርጠው ስፍራ፤*** ኢያሱ የመገናኛውን ድንኳን (መሠዊያውንም) ወደ ሴሎ ወሰደ፤ እስከ ነቢዩ ሳሙኤል ዘመን ድረስም በዚሁ ስፍራ ቆየ (1ሳሙ 4፥3):: ኋላ ግን እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን መረጠ (1ነገ 9፥3)::

10፥1-43፤ በኢያሱ የሚመራው ሰራዊት ገባዖንን ለመከላከል ወጣ፤ የደቡብ ነገሥታት ጥምር ኀይልም በኢሉን ድል ነሣ፤ ከዚያም በይሁዳና በኔጌብ የሚገኙትን የደቡብ ከተሞች ሁሉ አስገበረ::

10፥1 ***አዶኒጼዴቅ፤*** "የጽድቅ ጌታ" ወይም "ጌታዬ ጻድቅ ነው" ማለት ነው:: ከዚህ ጊዜ በፊት የነበረው የኢየሩሳሌም ንጉሥ ተመሳሳይ ስም ነበረው (መልከ ጼዴቅ፤ ዘፍ 14፥18 እና ማብ ይመ):: ***ኢየሩሳሌም፤*** የኢያቡሳውያን ከተማ ነበረች::

10፥2 ***ታላቅ ከተማ፤*** ገባዖን ከቤቴል ወይም ከጋይ በስፋት የምትበልጥ ብቻ ሳይሆን፤ ከሁለቱም ከተሞች ይልቅ ለኢየሩሳሌም ትቀርብ ነበር:: ቤቴልና ጋይ ድል በመመታታቸውና የገባዖናውያን ንብረትም እጅ በመስጠቱ፣ እስራኤላውያን ማእከላዊ በሆነው ከፍተኛ ቦታ ተረጋግተው ሰፈሩ፤ ቦታውም ምድሪቱን መኻል ለመኻል የሚከፍል ነበር:: ይህን ሁሉ ያየው የኢየሩሳሌም ንጉሥ ሥጋት አደረበት፤ ስለዚህም ከነዓናውያንን በሙሉ አስተባብሮ በእስራኤል ላይ ለማስነሣት ፈለገ:: ምናልባትም የገባዖንን ከተሞች የመግዛት ፍላጎት ስለነበረው፣ የገባዖን ሰዎች እጆቻቸውን ለእስራኤላውያን መስጠታቸውን እንደ ዐመፅ ሳይቈጥረው አልቀረም:: ***ብርቱ ተዋጊዎች፤*** በውጊያ ላይ ባላቸው ጀግንነት በጣም የታወቁ ሰዎች ናቸው፤ ከእስራኤልም ጋር የሰላም ስምምነት ማድረጋቸው አስተዋይ መሆናቸውን ያሳያል::

10፥5 ***አምስቱ የአሞራውያን ነገሥታት፤*** በደቡባዊው ተራራማ ክፍል የሚገኙና አምስቱን ታላላቅ ከተሞች የሚገዙ ናቸው:: እዚህ ላይ በኰረብታማው ክፍል የሚኖሩ አሞራውያን በባሕር ጠረፍ አካባቢ ከሚኖሩት ከነዓናውያን ተለይተው ተጠቅሰዋል::

6የገባዖንም ሰዎች በጌልገላ ወደ ሰፈረው
ወደ ኢያሱ፣ "በተራራማው አገር የሚኖሩ
የአሞራውያን ነገሥታት ኀይላቸውን አስተ
ባብረው ተሰልፈውብናል፤ እኛን ባሮችህን
አትተወን፤ ርዳን፤ ፈጥነህ በመድረስም አድነን"
ሲሉ ላኩበት።
7ስለዚህ ኢያሱ ምርጥ የሆኑትን ተዋጊ
ዎች ሁሉ ጨምሮ ሰራዊቱን በሙሉ ይዞ
ከጌልገላ ወጣ። 8እግዚአብሔርም ኢያሱን፣
"አትፍራቸው፤ ሁሉንም አሳልፌ በእጅህ ሰጥ
ቻቸዋለሁ፤ አንዳቸውም እንኳ ሊቋቋሙህ
አይችሉም" አለው።
9ኢያሱ ከጌልገላ ሌሊቱን ሁሉ ሲገሠግሥ
አድሮ ድንገት ወረራቸው። 10እግዚአብሔርም
የአሞራውያንን ነገሥታት በእስራኤል ፊት
አሸበራቸው፤ በገባዖን እጅግ መታቸው፤ ወደ
ቤትሖሮን በሚያስወጣውም መንገድ ሽቅብ
ተከተላቸው፤ እስከ ዓዜቅና እስከ መቄዳም
ድረስ አሳድዶ መታቸው። 11ከቤትሖሮን
ወደ ዓዜቃ ቊልቊል በሚወስደው መንገድ
ላይ፣ ከእስራኤላውያን ፊት በሚሸሹበት ጊዜ፣
እግዚአብሔር ከሰማይ ትልልቅ የበረዶ
ድንጋይ አወረደባቸው፤ በእስራኤላውያን
ሰይፍ ካለቁት ይልቅ በወረደው የበረዶ
ድንጋይ ያለቁት በልጠው ተገኙ።
12እግዚአብሔር አሞራውያንን ለእስራኤል
አሳልፎ በሰጠባት ዕለት፣ ኢያሱ እግዚአ
ብሔርን በእስራኤል ፊት እንዲህ አለው፤

"ፀሓይ ሆይ፤ በገባዖን ላይ ቁሚ፤
ጨረቃም ሆይ፤ በኤሎን ሸለቆ ላይ ቀጥ በዪ፤
13ስለዚህ ሕዝቡ ጠላቶቹን እስኪበቀል
ድረስ[መ]፣
ፀሓይ ባለችበት ቆመች፤
ጨረቃም አልተንቀሳቀሰችም።
ይህም በያሻር መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል።

ፀሓይ በሰማዩ መካከል ቆመች፤ ለመጥለ
ቅም ሙሉ ቀን ፈጀባት። 14እግዚአብሔር
የሰውን ቃል የሰማበት እንደዚያ ያለ ዕለት
ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ አልነበረም፤
እግዚአብሔር ለእስራኤል ተዋግቶ ነበርና።
15ከዚያም ኢያሱ ከመላው እስራኤል ጋር
ጌልገላ ወዳለው ሰፈር ተመለሰ።

## አምስቱ የአሞራውያን ነገሥታት ተገደሉ

16በዚህ ጊዜ አምስቱ የአሞራውያን ነገሥ
ታት ሸሽተው በመቄዳ ዋሻ ተደብቀው ነበር።
17ኢያሱም አምስቱ ነገሥታት በመቄዳ ዋሻ
ውስጥ ተደብቀው መገኘታቸውን ሰማ፣ 18እን
ዲህም አለ፤ "ትልልቅ ድንጋዮች ወደ ዋሻው
አፍ አንከባሉ፤ ጠባቂ ሰዎችንም በዚያ አቁሙ፤
19ጠላቶቻችሁን አሳዱአቸው እንጂ ችላ አት
በሉ፤ ከበስተ ኋላ ሆናችሁም አደጋ ጣሉብ
ቸው፤ ወደ ከተሞቻቸው እንዳይገቡ ከልክሏ
ቸው፤ እነሆ፤ እግዚአብሔር አምላካችሁ በእ
ጃችሁ አሳልፎ ሰጥቶአቸዋልና።"
20ስለዚህ ኢያሱና እስራኤላውያን እስከ
መጨረሻው ደመሰሷቸው፤ የተረፉት ጥቂ
ቶቹ ግን ወደ ተመሸጉት ከተሞቻቸው ለመ
ድረስ ቻሉ። 21ከዚያም ሰራዊቱ ሁሉ በደ
ኅና ተመልሶ፣ ኢያሱ ወደ ሰፈረበት ወደ
መቄዳ መጣ፤ በእስራኤላውያንም ላይ አን
ዲት ቃል የተናገረ ሰው አልነበረም።
22ኢያሱም፤ "ዋሻውን ከፍታችሁ እነዚያን
አምስቱን ነገሥታት አውጥታችሁ አምጡ
ልኝ" አላቸው። 23እነርሱም አምስቱን ነገሥ
ታት ማለትም የኢየሩሳሌምን ንጉሥ፣ የኬ
ብሮንን ንጉሥ፣ የያርሙትን ንጉሥ፣ የለኪ
ሶን ንጉሥ የዔግሎንን ንጉሥ አውጥተው
አመጡለት። 24እነዚህን ነገሥታት ባመጡለ
ትም ጊዜ፣ ኢያሱ መላውን የእስራኤልን
ወንዶች ከጠራ በኋላ አብረውት የመጡትን
የጦር አዛዦች፣ "ወደዚህ ቅረቡና እግሮቻ
ችሁን በእነዚህ ነገሥታት አንገት ላይ አድ
ርጉ" አላቸው፤ እነርሱም ወደ ፊት ቀርበው
እግራቸውን በነገሥታቱ አንገት ላይ አሳረፉ።
25ኢያሱም፣ "አትፍሩ፤ አትደንግጡ፤ በርቱ፤
ጽኑ፤ እንግዲህ በምትወጓቸው ጠላቶች ሁሉ
ላይ እግዚአብሔር እንደዚሁ ያደርጋልና"
አላቸው። 26ከዚያም ኢያሱ ነገሥታቱን
መትቶ ገደላቸው፤ በአምስትም ዛፎች ላይ
ሰቀላቸው፤ ሬሳቸውም እስኪመሽ ድረስ
አልወረደም ነበር።

[መ]13 *ወይም ሕዝቡ እስኪያሸንፍ ድረስ*

10፥6 ዘዳ11፥30
10፥7 ኢሱ8፥1
10፥8 ዘዳ3፥2፤7፥24፤ኢሱ1፥9፤2፥24
10፥10 ቊ16:17:21፤ዘፀ14፥24፤ዘዳ7፥23፤ኢሱ9፥3፤12፥16፤15፥35:41፤16፥3:5፤18፥13:14፤21፥22፤1ሳሙ13፥18፤17፥1፤1ነገ9፥17፤1ዜና6፥68፤7፥24፤2ዜና8፥5፤11፥9፤25፥13፤ነህ11፥30፤ኤር34፥7
10፥11 ዘፀ9፥18፤መሳ5፥20፤መዝ18፥12፤ኢሳ28፥2:17፤32፥19፤ሕዝ13፥11:13
10፥12 ኢሱ19፥42፤21፥24፤መሳ1፥35፤12፥12፤1ሳሙ14፥31፤1ዜና 6፥69፤8፥13፤2ዜና11፥10፤28፥18፤አሞ2፥9፤
10፥13 2ሳሙ1፥18፤ኢሳ38፥8፤ዕን3፥11
10፥14 ቊ42፤ዘፀ14፥14፤መዝ106፥43፤136፥24፤ኢሳ63፥10፤ኤር21፥5
10፥15 ቊ43
10፥16 መዝ68፥12
10፥20 ዘዳ20፥16፤2ዜና11፥10፤ኤር4፥5፤5፥17፤8፥14፤35፥11
10፥24 ዘዳ7፥24፤2ሳሙ22፥40፤መዝ110፥1፤ኢሳ51፥23፤ሚል4፥3
10፥25 ዘዳ31፥6

10፥6 *ፈጥነህ … አድነን፤* "እግዚአብሔር ያድናል" የሚል ትርጒም ባለው ስም የሚጠራ አንድ ሰው በፍጥነት መጥቶ እንዲታደጋቸው የቀረበ ጥሪ ነው። ኢያሱ ከገባዖን ሰዎች ጋር ያደረገው ስምምነት፤ አንድ ገዥ በሚገዛው ሕዝብ ላይ ጥቃት ሲደርስበት መርዳት እንዳለበት ያስገድዳል።

10፥9 *ሌሊቱን ሁሉ ሲገሠግሥ አድሮ፤* ጌልገላ ከገባዖን በስተ ምሥራቅ 32 ኪ.ሜ. ያህል ርቃ የምትገኝ ቦታ ናት። ኢያሱ የላካቸው ሰዎች ወደ ጌልገላ ሲሄዱ አቀበቱን መውጣት ነበረባቸው። *ሳይታሰብ ድንገት፤* ኢያሱ በጠላቶቹ ላይ ጥቃት የሰነዘረው ገና ጨረቃ ወጥታ እንዳለች (ቊ 12) በማለዳ ነበር።

10፥10 *አሸበራቸው፤* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል መራድንና መንቀጥቀጥን ያመለክታል።

10፥11 *ከቤትሖሮን … ቍልቍል፤* ወደ ኤሎን ሸለቆ የሚወስድ ረጅም ተዳፋት ሲሆን፣ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን፣ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ከሚወስደው መስቀለኛ መንገድ ጀምሮ ያለው አካባቢ ነው። *ትልልቅ የበረዶ ድንጋይ፤* እግዚአብሔር ተፈጥሮአዊ ነገሮችን እንደ መሣሪያ አድርጎ ስለ መጠቀሙ መሳ 5፥20፤ 1ሳሙ 7፥10፤ ኢዮ 38፥22 ይመ።

10፥13 *በያሻር መጽሐፍ፤* የእስራኤልን የውጊያ ውሎ የሚተርክ መጽሐፍ ነው (ምናልባት መጽሐፉ በሙሉ በግጥም መልክ ሳይጻፍ አይቀርም፤ 2ሳሙ 1፥18፤ እንዲሁም የመሳ 5፥1-31ን ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ ይህ መጽሐፍ የቀኖና መጻሕፍት ክፍል አይደለም። *ለመጥለቅም ሙሉ ቀን ፈጀባት፤* እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ድል እስኪያደርጉ ድረስ እግዚአብሔር ቀኑን አስረዘመላቸው።

10፥16 *በመቄዳ፤* በዓዜቃ አቅራቢያ የምትገኝ (ቊ 10) የኢያሱ ሰራዊት የሰፈረባት ከተማ ናት፤ የምትገኘውም በስተ ምዕራብ ባለው ኰረብታማ አካባቢ ነው።

10፥19 *ጠላቶቻችሁን አሳዱአቸው፤* በስተ ደቡብ የሚገኙትን ከተሞች ከሚጠብቁት ተዋጊዎች አብዛኞቹ፣ ወደ ምሽጎቻቸው ከመድረሳቸውና ከማምለጣቸው በፊት ተይዘው ተገድለዋል።

10፥21 *አንዲት ቃል የተናገረ ሰው አልነበረም፤* የዚህ ሐረግ ሐሳብ ከዚህ በኋላ በእስራኤላውያን ላይ አፉን ሊከፍት የደፈረ እንኳ አልነበረም የሚል ይመስላል።

10፥24 *እግሮቻችሁን በ…አንገት ላይ አድርጉ፤* በመካከለኛው ምሥራቅ የተሸነፈን ጠላት በዚህ መንገድ በአደባባይ እንዲዋረድ ማድረግ የተለመደ ነው።

10፥26 *በአምስትም ዛፎች ላይ ሰቀላቸው፤* የዘዳ 21፥22 ማብ ይመ።

[27]ፀሐይ ለመጥለቅ በማዘቅዘቅ ላይ ሳለች
ኢያሱ ትእዛዝ ሰጠ፤ ከዚያም የነገሥታቱን
ሬሳ ከዛፎቹ ላይ አውርደው ቀድሞ ተደ
ብቀው ወደ ነበሩበት ዋሻ ውስጥ ጣሏቸው። በዋ
ሻውም አፍ ትልልቅ ድንጋዮች አኖሩ፤ ድን
ጋዮቹም እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ ይገኛሉ።
[28]በዚያች ዕለት ኢያሱ መቄዳን ያዘ፤
ከተማይቱንና ንጉሥዋንም በሰይፍ ስለት
መታ፤ አንድም ሰው ሳያስቀር በውስጧ ያለ
ውን ሁሉ ፈጽሞ ደመሰሰ፤ በኢያሪኮ ንጉሥ
ላይ ያደረገውንም ሁሉ፣ በመቄዳ ንጉሥ
ላይ አደረገ።

## የደቡብ ከተሞች መያዝ

[29]ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ከመቄዳ ወደ ልብና
አለፉ፤ ወጓትም። [30]እንዲሁም እግዚአብሔር
ከተማይቱንና ንጉሥዋን በእስራኤል እጅ
አሳልፎ ሰጣቸው፤ ኢያሱ ከተማይቱንና
በውስጧ ያለውን ሁሉ በሰይፍ ስለት አጠፋ፤
አንድም ሰው አላስተረፈም፤ በኢያሪኮ ንጉሥ
ላይ ያደረገውንም በልብና ንጉሥ ላይ ደገ
መው።
[31]ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ከልብና ወደ ለኪሶ
አለፉ፤ ወጓትም። [32]*እግዚአብሔር* ለኪሶን
አሳልፎ ለእስራኤል ሰጠ፤ ኢያሱም በሁለ
ተኛው ቀን ያዛት፤ በልብና እንዳደረገው
ሁሉ እዚህም ከተማይቱንና በውስጧ ያሉ
ትን ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈጃቸው። [33]በዚህ
ጊዜ የጌዝር ንጉሥ ሆራም ለኪሶን ለመር
ዳት መጣ፤ ኢያሱ ግን አንድ እንኳ ሳያስ
ተርፍ ንጉሡንና ሕዝቡን መታቸው።
[34]ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ከለኪሶ ወደ ዔግ
ሎን አለፉ፤ ወጓትም። [35]በዚያኑ ዕለት
ያዟት፤ በሰይፍም ስለት አጠፏት፤ በለኪሶ
እንዳደረጉት ሁሉ እዚህም በውስጧ የሚገ
ኙትን ፈጽመው ደመሰሷቸው።
[36]ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ከዔግሎን ወደ
ኬብሮን ወጡ፤ ወጓትም። [37]ከተማይቱንም
ከንጉሥዋ፣ ከመንደሮቿና በውስጧ ካሉት
ጋር ሁሉ አንድም ሰው ሳያስቀሩ በሰይፍ
ስለት ፈጇቸው፤ በዔግሎን እንዳደረጉት
ሁሉ እዚህም ከተማይቱንና በውስጧ
ያለውን ሁሉ ፈጽመው ደመሰሱ።
[38]ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ወደ ኋላ ተመል
ሰው ዳቤርን ወጓት። [39]ከተማይቱን፣ ንጉ
ሥዋንና መንደሮቿን ይዘው በሰይፍ ስለት
ፈጇቸው፤ በውስጧ ያለውንም ሁሉ አንድም
ሳያስቀሩ ደመሰሱ፤ በልብናና በንጉሥዋ
እንዲሁም በኬብሮን ያደረጉትን ሁሉ እዚ
ህም በዳቤርና በንጉሥዋ ላይ ደገሙት።
[40]በዚህ ሁኔታም ኢያሱ ተራራማውን አገር
ኔጌብን፣ የምዕራቡን ቈላና የተራራውን
ሽንተረሮች ጨምሮ ምድሪቱን በሙሉ ከነገ
ሥታቷ ጋር ያዘ፤ የእስራኤል አምላክ *እግዚ
አብሔር* ባዘዘውም መሠረት፣ እስትንፋስ
ያላቸውን ሁሉ ፈጽሞ ደመሰሰ፤ ማንንም
በሕይወት አላስቀረም፤ [41]ኢያሱም ከቃዴስ
በርኔ እስከ ጋዛ እንዲሁም የጎሶምን ምድር
ሁሉ እስከ ገባዖን ድረስ በሙሉ ያዘ። [42]ኢያሱ
እነዚህን ሁሉ ነገሥታትና ምድራቸውን
ያሸነፈው በአንድ ዘመቻ ብቻ ነበር፤ የእስ
ራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* ለእስራኤላው
ያን ተዋግቶላቸዋልና።
[43]ከዚህ በኋላ ኢያሱ ከመላው እስራኤላው
ያን ጋር ጌልገላ ወዳለው ሰፈር ተመለሰ።

## የሰሜን ነገሥታት ድል መሆን

**11** የአሦር ንጉሥ ኢያቢስ ይህን በሰማ
ጊዜ፣ ወደ ማዶን ንጉሥ፣ ወደ ዮባብ
ንጉሥ፣ ወደ ሺምሮን ንጉሥ፣ ወደ አዚፍ
ንጉሥ ላከ፤ [2]እንዲሁም በተራራማው አገር
ከኪኔሬት ደቡብ በዓረባ፣ በምዕራቡ ቈላ
አገርና ከዶር ኰረብታ[a] በስተ ምዕራብ ወዳ
ሉት ነገሥታት ላከ፤ [3]ደግሞም በምሥራቅና

[a]2 *ወይም ከዶር ከፍታማ ስፍራ*

10፥27 ዘፍ35፥20፤ ዘዳ21፥23
10፥28 ቍ30፡32፡35፡39፤ ዘዳ20፥16፤ ኢሱ6፥21
10፥29 ዘኍ33፥20
10፥31 ቍ3
10፥33 ኢሱ12፥12፤ 16፥3፡10፤ 21፥21፤ መሳ1፥29፤ 2ሳሙ5፥25፤ 1ነገ9፥15፤ 1ዜና6፥67
10፥34 ቍ3
10፥36 ዘፍ13፥18፤ ኢሱ14፥13፤ 15፥13፡20፥7፤ 21፥11፤ መሳ16፥3
10፥37 ቍ28
10፥38 ቍ3
10፥39 ቍ28
10፥40 ዘፍ12፥9፤ ዘዳ1፥7፤ 7፥24፤ 20፥16-17፤ ኢሱ12፥8፤ 15፥19፡21፤ 18፥25፤ 19፥8፤ 1ሳሙ30፥27
10፥41 ዘፍ14፥7፤ 10፥19፤ ኢሱ11፥16፤ 15፥51
10፥42 ቍ14
10፥43 ቍ15፤ ኢሱ5፥9፤ 1ሳሙ7፥16፤ 10፥8፤ 11፥14፤ 13፥12
11፥1 ቍ10፤ ኢሱ12፥19፡20፤ 15፥23፡25፤ 19፥15፡25፡36፤ መሳ4፥2፡7፡17፡23፤ 1ሳሙ12፥9፤ 1ነገ4፥15፤ 2ነገ15፥29፤ ነህ11፥33፤ መዝ83፥9፤ ኤር49፥28፡33
11፥2 ቍ16፤ ዘኍ34፥11፤ ዘዳ1፥1፡3፥17፤ ኢሱ12፥1፡23፤ 17፥11፤ 18፥18፤ 19፥35፤ መሳ1፥27፤ 1ነገ15፥20፤ 4፥11፤ 1ዜና7፥29
11፥3 ኢሱ3፥10፤ ዘኍ13፥17፤ ዘፀ3፥8፤ ዘዳ7፥1፤ መሳ3፥3፡5፤ 1ነገ9፥20፤ ዘዳ3፥8፤ ቍ8፤ ዘፍ31፥49፤ ኢሱ15፥38፤ 18፥26፤ መሳ11፥11፤ 20፥1፤ 21፥1፤ 1ሳሙ7፥5፡6፤ 1ነገ15፥22፤ 2ነገ25፥23

10፥27 *ትልልቅ ድንጋዮች አኖሩ፤* ከነዓንን ለመያዝ በተደረገው ፍልሚያ፣ ይህ አምስተኛው የድል መታሰቢያ ሐውልት ነው (የ8፥32 ማብ ይመ)።

10፥28 *አንድም ሰው ሳያስቀር... ደመሰሰ፤* የመደምሰስ እርምጃ እንዲወሰድ የተሰጠው ቅዱስ ትእዛዝ ተግባራዊ የሆነው በመቄዳ ሕዝቦች ላይ ነው፤ መቄዳ ማለት "ለሞት የተዳረጉ" ማለት ነው፤ የመቄዳ ሕዝቦች ለሞት የተሰጡት በኀጢአታቸው ምክንያት ነው (የቍ1 አግራጭ ትርጕም ይመ)። በስተ ደቡብ የሚገኙ ታላላቅ ከተሞችም ተመሳሳይ የመጥፋት ዕጣ ደርሶባቸዋል (ቍ 19-42)።

10፥33 *የጌዝር ንጉሥ ሆራም፤* በአካባቢው እጅግ ኀይለኛ የነበረች ከተማ ንጉሥ ድል መመታቱን የሚገልጽ ጠቃሚ መግለጫ ነው። በመጨረሻ ጌዝር በግብፃውያን ተወሰደች፣ ለንጉሥ ሰሎሞንም የጋብቻ ገጸ በረከት ሆና ተሰጠች (1ነገ 9፥16 ይመ)።

10፥38 *ዳቤርን፤* ቀደም ሲል ዳቤር (ቂርያትሤፍር ተብላ ትጠራ ነበር፤ 15፥15) ከቴል ቤት ሚርሲም ጋር አንድ ተደርጋ ትቈጠር ነበር፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከሔብሮን በስተ ደቡብ ምዕራብ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ከምትገኘው ከቂርቤት ራቡድ ጋር አንድ እንደ ሆነች ይነገራል።

10፥41 *ከቃዴስ በርኔ እስከ ጋዛ፤* በክልሉ ምዕራባዊ አቅጣጫ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለውን ወሰን ያመለክታል። *ጎሶም፤* አልፎ አልፎ በስተ ምሥራቅ የሚገኘው ኔጌብ በዚህ ስም የሚጠራ ሲሆን፣ በግብፅ የዐባይ ወንዝ መፋሰሻ አካባቢ ከሚገኘው ጎሶም ጋር አንድ ሆኖ መታየት የለበትም፤ በተጨማሪም ጎሶም የከተማ መጠሪያ ስም ነው (15፥15)። ጎሶምና ገባዖን በክልሉ ምሥራቃዊ ክፍል ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለውን ወሰን ያመለክታሉ።

*11፥1-23፤* አሁን በጦርነት ያልተያዙት በስተ ሰሜን የሚገኙት ከተሞች ብቻ ናቸው። የገሊላን ኰረብታማ አካባቢዎች ለመያዝ የተደረገው ዋና ጦርነት ተጠናቋል፤ አሦርና የሌሎች ሰሜናዊ የከተማ መንግሥታት ጥምር ኀይልም ድል ተመቶአል። ከዚህ ቀጥሎ የሚገኘው ታሪክ ኢያሱ በደቡብና በማእከላዊ ክፍሎች ያገኘውን ድል ሁሉ የሚያወሳ ታሪክ ነው።

11፥1 *የአሦር ንጉሥ ኢያቢስ፤* ኢያቢስ የሚለው ስም ምናልባት የሥርወ መንግሥት ስም ሳይሆን አይቀርም፤ ስሙ በዘመነ ዲቦራ ተጠቅሶ ይገኛል (መሳ 4፥2)። የሥነ ቅርስ ግኝቶች እንደሚያመለክቱት፣ አሦር በከነዓን ከሚገኙት ከተሞች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትልቅና ምሽጎቿም የጠላትን ጦር ለመከላከል ብቃት ያላቸው ናቸው። የከተማዋ ታችኛ ክፍል 0.708 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ወይም 70.8 ሄክታር ያህል ይሰፋል።

11፥2 *ኪኔሬት፤* የቃሉ ትርጕም "በገና" ማለት ነው፤ የገሊላ ባሕር ለማለት ነው።

በምዕራብ ወደሚገኙት ወደ ከነዓናውያን፣
ወደ አሞራውያን፣ ወደ ኬጢያውያን፣ ወደ
ፌርዛውያንና በኰረብታማው አገር ወደሚ
ኖሩት ወደ ኢያቡሳውያን፣ እንዲሁም ደግሞ
በምጽጳ ምድር በአርሞንዔም ተራራ ግርጌ
ወዳሉት ወደ ኤዊያውያን ነገሥታት መል
እክት ላከ:: 4እነዚህም ሰራዊታቸውን ሁሉ
እጅግ ብዙ ከሆኑ ፈረሶችና ሠረገሎች ጋር
ይዘው ወጡ፤ የሰራዊቱም ብዛት በባሕር
ዳር እንዳለ አሸዋ ነበር:: 5እነዚህ ሁሉ ነገ
ሥታት እስራኤልን ለመውጋት ኀይላቸውን
አስተባብረው በማሮን ውሃ አጠገብ በአንድ
ነት ሰፈሩ::
6እግዚአብሔር ኢያሱን፣ "እነዚህን ሁሉ
ነገ በዚች ሰዓት እንደ ሙት አድርጌ፣ በእ
ስራኤል እጅ አሳልፌ ስለምሰጣቸው አትፍ
ራቸው፤ የፈረሶቻቸውን ቋንጃ ትቈርጣ
ለህ፤ ሠረገሎቻቸውንም ታቃጥላለህ" አለው::
7ስለዚህ ኢያሱና ሰራዊቱ ሁሉ በድንገት
ወደ ማሮን ውሃ መጥተው ወጓቸው:: 8እግዚ
አብሔርም በእስራኤል እጅ አሳልፎ ስለ
ሰጣቸው ድል አደረጓቸው፤ በታላቂቱ ሲዶና
መንገድ መጨረሻ እስከ ማስሮን፣ በስተ
ምሥራቅም እስከ ምጽጳ ሸለቆ ድረስ አሳደ
ዷቸው፤ ከእነርሱም በሕይወት የተረፈ አን
ድም ሰው አልነበረም:: 9ኢያሱ እግዚአብሔር
ባዘዘው መሠረት የፈረሶቻቸውን ቋንጃ
ቈረጠ፤ ሠረገሎቻቸውንም አቃጠለ::
10በዚያን ጊዜም ኢያሱ ወደ ኋላ ተመ
ልሶ ሐጾርን ያዘ፤ ንጉሥዋንም በሰይፍ ገደ
ለው፤ አጾርም ቀድሞ በእነዚህ ሁሉ መንግ
ሥታት ላይ የበላይነት ነበራት:: 11በውስ
ጥዋ ያሉትን ሁሉ በሰይፍ ስለት ገደሉ፤
እስትንፋስ ካለው ፍጡር አንድ እንኳ ሳያስ
ቀሩ ሁሉንም ደመሰሱ[A]፤ ራሷን ሐጾርንም
በእሳት አቃጠሏት::
12ኢያሱ እነዚህን የነገሥታት ከተሞች

11፥4 ዘፍ12፥2፤ መሳ 7፥12፤1ሳሙ13፥5
11፥5 ቍ7፤መሳ 5፥19
11፥6 ቍ9፤ዘፍ49፥6፤ኢሱ2፥24
11፥8 ዘፍ10፥15፤ኢሱ13፥6፤መሳ18፥7
11፥10 ኢሳ3፥25፤ ኤር41፥2፤44፥18
11፥11 ዘኍ31፥10፤ዘዳ7፥2፤20፥16-17
11፥12 ዘኍ33፥50-52፤ዘዳ7፥2
11፥14 ዘዳ20፥16
11፥15 ዘፀ34፥11፤ ዘዳ7፥2፤ኢሱ1፥7
11፥16 ዘኍ13፥17፤ ዘዳ1፥7፤ኢሱ10፥41
11፥17 ዘፍ14፥6፤ ዘኍ24፥18፤ዘዳ3፥25፤ ዘዳ3፥9:25፤7፥24፤33፥2፤ኢሱ12፥7:8፤ 13፥5
11፥19 ኢሱ9፥ 1:3:15
11፥20 ዘፀ4፥21፤ 14፥17፤ዘዳ7፥16፤መሳ 14፥4፤ሮሜ9፥18፤

በሙሉና ነገሥታታቸውን ሁሉ ያዘ፤ በሰይ
ፍም ስለት ፈጃቸው፤ የእግዚአብሔር ባሪያ
ሙሴ ባዘዘውም መሠረት ፈጽሞ ደመሰሳ
ቸው:: 13ያም ሆኖ ግን ኢያሱ ካቃጠላት
ከሐጾር በስተቀር፣ እስራኤላውያን በየተራ
ራው ላይ ያሉትን ከተሞች አላቃጠሉም
ነበር:: 14እስራኤላውያን ምርኮውን በሙሉ፣
ከእነዚህም ከተሞች የተገኙትን እንስሳት ለራ
ሳቸው ወሰዱ፤ ሕዝቡን ግን በሙሉ በሰይፍ
ስለት ፈጁት፤ እስትንፋስ ካለው ፍጡር
አንድም ሳያስቀሩ ፈጽመው ደመሰሱት::
15እግዚአብሔር ባሪያውን ሙሴን እንዳዘ
ዘው ሁሉ፣ ሙሴም ኢያሱን አዘዘው፤ ኢያ
ሱም እንዲሁ አደረገ፤ እግዚአብሔር ሙሴን
ካዘዘው ሁሉ እርሱ ያልፈጸመው አንዳች
ነገር አልነበረም::
16ኢያሱ ያንን ምድር በሙሉ ማለት ተራ
ራማውን አገር፣ ኔጌብን ሁሉ፣ የጎሶምን
ምድር በሙሉ፣ የምዕራቡን ቈላ፣ ዓረባን
እንዲሁም የእስራኤልን አገር ደጋውንና
ቈላውን ጠቅልሎ ያዘ፤ 17እንዲሁም እስከ
ሴይር በሚደርሰው ከሐላቅ ተራራ አንሥቶ
ከአርሞንዔም ተራራ በታች በሊባኖስ ሸለቆ
ውስጥ እስካለው እስከ በኣልጋድ ድረስ
ያለውን ምድር በሙሉ ያዘ፤ ነገሥታታ
ቸውንም ሁሉ ያዘ፤ መትቶም ገደላቸው::
18ኢያሱ ከእነዚህ ነገሥታት ጋር ብዙ
ዘመን የፈጀ ጦርነት አደረገ:: 19በገባዖን
ከሚኖሩ ከኤዊያውያን በስተቀር፣ ከእስራ
ኤላውያን ጋር የሰላም ውል ያደረገ አን
ድም ከተማ አልነበረም፤ ሁሉንም የያዙት
በጦርነት ነው:: 20እግዚአብሔር ሙሴን ባዘ
ዘው መሠረት፣ ያለአንዳች ርኅራኄ ፈጽሞ
ይደመስሳቸው ዘንድ እስራኤልን እንዲወጉ
ልባቸውን ያደነደነው ራሱ እግዚአብሔር

[A]11 የዕብራይስጡ ቃል በዚህም ሆነ በቍጥር 12:20 እና 21 ላይ አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው::

11፥4... *ብዛት እንዳለ ... አሸዋ ነበር፤* የአንድን ነገር ብዛት ለመግለጽ የተለመደ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው (የዘፍ 22፥17ን ማብ ይመ)::

11፥5 *እነዚህ ሁሉ ነገሥታት፤* የኢያቢስ ግዛት በዮር ዳኖስ ሸለቆ እስከ ዓረባና (ቍ 2) ከቀርሜሎስ ተራራ በስተ ደቡብ በሜድትራኒያን ባሕር እስካለው እስከ ዶር ኰረብታ ይደርሳል:: *ማሮን፤* ምናልባት ከሳፌድ ሰሜን ምዕራብ በኩል በዋዲ አሙድ (ማሩን) አቅራቢያ በአሁኑ ጊዜ ሜሩን ተብላ የምትጠራዋ ቦታ ሳትሆን አትቀርም፤ ዋዲ አሙድ ከገሊላ ባሕር በስተ ሰሜን ምዕራብ በኩል 13 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛለች::

11፥6 *የፈረሶቻቸውን ቋንጃ ትቈርጣለህ፤* ፈረሱ እንዲ ሽመደመድ ማለትም ከዚህ በኋላ ሁለተኛ እንዳይጋልብ ከቍርጭምጭሚቱ በላይ ጅማቱ ይቈረጣል:: *ሠረገሎቻቸውንም ታቃጥላለህ፤* የእስራኤል ጦር እስከ ሰሎሞን ዘመነ ንግሥ ድረስ በእንዲህ ዐይነቱ ከባድ የውጊያ እርምጃ አልተጠቀመም (1ነገ 9፥22፤ 10፥26-29 ይመ)::

11፥10 *ኢያሱ ... አጾርን ያዘ፤* ይህ ምናልባት ትልቁ ድል ነው:: የተደራጀውና የታጠቀው የሐጾር ሰራዊት ግን ቀደም ሲል በሜሮን ድል ተመቶአል:: የሥነ ቅርስ ጥናቶች እንደሚያ መለክቱት፣ የከነዓናውያን ከተማ በ1400 እና በ1300 ዓ.ቅ.ክ.፣ እንደገ ናም በ1230 ዓ.ቅ.ክ. ስትቃጠል ከፍተኛ ውድመት ደርሶባታል:: በከተማዋ ላይ በ1300 ዓ.ቅ.ክ. የደረሰው የውድመት ደረጃ እንደሚ ያመለክተው ከተማዋ የተቃጠለችው በፈርዖን ሴቲ ቀዳማዊ ሊሆን ይችላል፤ ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ በ1400 እና በ1230 ዓ.ቅ.ክ. የደረሰው ውድመት በኢያሱ ዘመን ተፈጽሞአል ማለት ነው::

በምድሪቱ የተገኘውን ሰው ሁሉ እንዲያጠፉ የተሰጠው ትእዛዝ አሁንም እዚህ ላይ ሲፈጸም ይታያል (ቍ 11)

11፥13 *በየተራራው፤* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብ ራይስጡ ቃል "ቴል" ይባላል፤ ከጥንት ጀምሮ በአንድ የተወሰነ ቦታ ኢያሌ የሕዝብ ሰፈራ የተካሄደ በመሆኑ፣ በየጊዜው የተጠራቀመው የፍርስራሽ ክምር የፈጠረው ኰረብታ ነው (የ7፥2ን ማብ ይመ)::

11፥15 *ያልፈጸመው አንዳች ነገር አልነበረም፤* የኢያሱ አመራር መለካት ያለበት እስራኤል የኋላ ኋላ ከምትወርሰው የመሬት ስፋት (መጠን) አንጻር ሳይሆን፣ እግዚአብሔር የሰጠ ውን ትእዛዝ ሁሉ ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ከመፈጸሙ አንጻር ነው::

11፥16 *ያንን ምድር በሙሉ፤* የከነዓንን መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ ያሳያል::

11፥17 *ሐላቅ ተራራ፤* ከቃዴስ በርኔ በስተ ምሥራቅ የሚገኝና የእስራኤልን ደቡባዊ ጫፍ የሚያመለክት የምድረ በዳ ጫፍ ነው:: *በኣልጋድ፤* ከአርሞንዔም ተራራ በስተ ምዕራብ የሚገኝ የመጀመሪያው ሸለቆ ነው::

11፥18 *ብዙ ዘመን የፈጀ፤* ኢያሱ ከነዓንን ድል አድርጎ ለመያዝ የፈጀበትን ዘመን ከካሌብ የሕይወት ዘመን አንጻር ማስላት ይቻላል፤ ከነዓንን ለመያዝ ጦርነት ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ (የአሮን ዕድሜ 78 ነው፤ 14፥7 እና ዘዳ 2፥14 ያነጻ ጽሩ) ኬብሮንን እስከ ያዘበት ጊዜ ድረስ (ዕድሜው 85 ሲሆን፤ 14፥10 ይመ) ሰባት ዓመት ፈጅቷል::

11፥20 *ልባቸውን ያደነደነው ... እግዚአብሔር ነውና፤* እግዚአብሔር የታሪክ ጌታና መሪ ነው፤ ይሁን እንጂ ፈቃዱ ግላዊ ምርጫችንንም ሆነ ነጻነታችንን የሚያሳጣ አይደለም (በዘፀ

ነውና::
21በዚያን ጊዜ ኢያሱ ሄዶ በተራራማው
አገር ማለት በኬብሮን፣ በዳቤርና በአናብ
እንዲሁም በመላው የይሁዳና የእስራኤል
ተራራማ አገሮች ያሉትን የዔናቅን ዘሮች
ከነከተሞቻቸው በሙሉ ደመሰሳቸው፤ 22ከእ
ነዚህም ጥቂቶቹ ብቻ በጋዛ፣ በጌትና በአሽ
ዶድ ሲቀሩ፣ በእስራኤል የቀሩ የዔናቅ ዘሮች
ግን አልነበሩም:: 23ስለዚህ ኢያሱ *እግዚአብ
ሔር* ሙሴን ባዘዘው መሠረት ምድሪቱን
በሙሉ ያዘ፤ እንደ ነገዳቸው አከፋፈል በመ
መደብም ርስት አድርጎ ለእስራኤላውያን
ሰጣቸው::
ከዚያም ምድሪቱ ከጦርነት ዐረፈች::

## የተሸነፉ ነገሥታት ስም ዝርዝር

**12** እንግዲህ እስራኤላውያን ድል ያደ
ረጓቸውና ከዮርዳኖስ ማዶ በስተ
ምሥራቅ የሚገኘውን የዓረባን ክፍል በሙሉ
ይዞ፣ ከአርኖን ሸለቆ እስከ አርሞንዔም
ተራራ የሚዘልቀውን ግዛታቸውን የወሰዱባ
ቸው ነገሥታት እነዚህ ናቸው፤

2መቀመጫውን በሐሴቦን አድርጎ የገዛው
የአሞራውያን ንጉሥ ሴዎን፣ ከአርኖን
ሸለቆ ዳርቻ ላይ ካለችው ከአሮዔር ማለት
ከሸለቆው መካከል አንሥቶ፣ የአሞናውያን
ወሰን እስከ ሆነው እስከ ያቦቅ ወንዝ ድረስ
ገዝቶአል፤ ይህም የገለዓድን እኩሌታ
ይጨምራል:: 3እንዲሁም ከኪኔሬት ባሕር[ሀ]
እስከ ሙት ባሕር[ለ] ያለውን ምሥራቃዊ
ውን ዓረባ፣ እስከ ቤት የሺሞትና ከዚያም
በስተ ደቡብ እስከ ፈስጋ ተራራ ግርጌ
ድረስ ገዝቶአል::

4መቀመጫውን በአስታሮትና በኤድራይ
አድርጎ የገዛውና ከመጨረሻዎቹ ከራፋ
ይም ዘሮች አንዱ የሆነው የባሳን
ንጉሥ ዐግ፣ 5የአርሞንዔምን ተራራ፣
ሰልካንን፣ ባሳንን ሁሉ እስከ ጌሹራ
ውያንና እስከ ማዕካታውያን ድንበሮች
እንዲሁም ከገለዓድ እኩሌታ እስከ ሐሴ
ቦን ንጉሥ እስከ ሴዎን ወሰን ድረስ
ገዝቶአል::

6*የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴና እስራ
ኤላውያን እነዚህን ድል አደረጉ፤ *የእግዚ
አብሔር* ባሪያ ሙሴም ምድራቸውን ለሮ
ቤል፣ ለጋድና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት
አድርጎ ሰጣቸው::
7እንግዲህ ኢያሱና እስራኤላውያን ከዮር
ዳኖስ በስተ ምዕራብ ድል ያደረጓቸው
የምድሪቱ ነገሥታት እነዚህ ናቸው፤ ግዛታ
ቸውም በሊባኖስ ሸለቆ ውስጥ ካለው ከበአ
ልጋድ ተነሥቶ በምዕራብ ሴይር እስካለው
እስከ ሐላቅ ተራራ ይደርሳል፤ ኢያሱም
የእነዚህን ነገሥታት ምድር እንደ ነገዳቸው
አከፋፈል ለእስራኤላውያን በማከፋፈል ርስት
አድርጎ ሰጣቸው፤ 8ይህም ተራራማው አገር፤
በስተ ምዕራብ ያለው የኰረብታ ግርጌ፣ ዓረባ፣
የተራራው ሸንተረሮች፣ ምድረ በዳውና ኔጌብ
ማለት የኬጢያውያን፣ የአሞራውያን፣ የከ
ነዓናውያን፣ የፌርዛውያን፣ የኤዊያውያንና
የኢያቡሳውያን ምድር ነው፤ ነገሥታቱም እነ
ዚህ ናቸው፤

| | |
|---|---|
| 9የኢያሪኮ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| ቤቴል አጠገብ ያለችው የጋይ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 10የኢየሩሳሌም ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የኬብሮን ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 11የየርሙት ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የለኪሶ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 12የዔግሎን ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የጌዝር ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 13የዳቤር ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የጌድር ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 14የሔርማ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የዓራድ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 15የልብና ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የዓዶላም ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 16የመቄዳ ንጉሥ፤ | አንድ፣ |
| የቤቴል ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 17የታጱዋ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የአፌር ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 18የአፌቅ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የለሸሮን ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 19የማዶን ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የሐጾር ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 20የሺምሮን ሜሮን ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የአዚፍ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 21የታዕናክ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የመጊዶ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |

11፥21 ዘኍ13፥22፡ 33፤ኢሱ10፥3፤15፥50
11፥22 ዘዳ10፥19፤ ኢሱ12፥17፤15፥47፤ 19፥13፤1ሳሙ5፥1፡8፤ 17፥4፤1ነገ2፥39፤2ነገ 14፥25፤1ዜና8፥13፤ ኢሳ20፥1፤አሞ6፥2
11፥23 ዘፀ33፥14፤ ዘኍ26፥53፤ዘዳ1፥38፤ 12፥9-10፤25፥19፤ኢሱ 13፥7፤14፥15፤21፥43-45፤ ነህ9፥24፤መዝ105፥44
12፥1 ዘኍ32፥19፤ 21፥13፤ዘዳ3፥8፤ኢሱ 11፥2፤መዝ136፥21፤
12፥2 ቍ5፤ዘዳ19፥ 38፤31፥21፤32፥22፡ 26፤ዘኍ21፥21፡25፤ 32፥26፡34፤ዘዳ2፥36፤ 3፥15፤ኢሱ13፥10፡ 11፡16፡25፤17፤1፤20፥ 8፤21፥38፤መሳ5፥17፤ 7፥3፤10፥8፤11፥19
12፥3 ዘዳ14፥3፤ዘኍ 21፥20፤33፥49፤ኢሱ 11፥2፤13፥20
12፥4 ዘዳ14፥5፤ዘኍ 21፥21፡33፤ዘዳ1፥4፤ ኢሱ13፥30
12፥5 ቍ2፤ዘኍ32፥ 33፤ዘዳ3፥10፡14፤ኢሱ 17፥1፤20፥8፤21፥27፤ 22፥7፤13፥2፡13፤ 1ሳሙ 27፥8
12፥6 ዘኍ32፥29፡ 33፤ዘዳ3፥8፤ኢሱ13፥8
12፥7 ኢሱ11፥17
12፥8 ዘዳ1፥7፤ኢሱ 3፥10፤11፥17፤ዕዝ9፥1
12፥9 ዘዳ12፥8፤ዘኍ 33፥48፤ኢሱ8፥1፤ 7፥2፤8፥9፤18፥13፤ መሳ1፥23፤4፥5፤20፥ 18፤21፥2፤ነህ11፥31
12፥10 ኢሱ10፥1
12፥11 ኢሱ10፥3
12፥12 ኢሱ10፥3፡33
12፥13 ኢሱ10፥3
12፥14 ዘኍ14፥45፤ 21፥1
12፥15 ዘዳ38፥1፤ ዘኍ33፥20፤ኢሱ15፥ 35፤ሚክ1፥15
12፥16 ኢሱ7፥2፤ 10፥10
12፥17 ኢሱ11፥22፤ 15፥34፤16፥8፤ 17፥8፤1ነገ4፥10
12፥18 ኢሱ13፥4፤ 19፥30፤መሳ1፥31፤ 1ሳሙ4፥1፤29፥1
12፥19 ኢሱ11፥1
12፥20 ኢሱ11፥1 12፥21 ኢሱ17፥11፤21፥25፤መሳ1፥27፤ 5፥19፤ 1ነገ4፥12

[ሀ]3 ገሊላ ናት:: [ለ]3 የሙት ባሕር፣ የጨው ባሕርም ይባላል::

8፥32፤9፥12 ላይ የሚገኘውን የፊርያንን ገጠመኝ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥21 *የዔናቅ ዘሮች፤* ዐሥራ ሁለቱ ሰላዮች "ቀመተ ረጃጅሞች" ናቸው በማለት መረጃ ያቀረቡባቸውና (ዘኍ 13፥32) እስራኤላውያንም ከፍርሃት የተነሣ እነርሱን ለመውጋት አንወጣም ያሏቸው ሰዎች እነዚህ ናቸው:: ከኔፊሊም ጋር ዝምድና ያላቸው ሲሆን (የዘፍ 6፥4 ማብ ይመ)፣ ስማቸው የመጣው ከነገድ አባታቸው ከዔናቅ ነው:: ኢያሱና ካሌብ በዔናቅ ሰዎች ላይ ድልን ተቀዳጅተዋል (14፥12-15)::

*12፥1-24፤* ለኢያሱ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል መደምደሚያ ሲሆን፣ እስራኤላውያን የተቀዳጁትን ድልና ነገሥታታቸው ድል የተመቱባቸውን ከተሞች ታሪክ አጠር አድርጎ የሚያቀርብ ነው::

12፥1 *ከዮርዳኖስ ማዶ በስተ ምሥራቅ የሚገኘውን ... ክፍል፤* በዚህ ክፍል ውስጥ "ከዮርዳኖስ ማዶ" የሚገኙ አገሮች በሙሉ ተጠቅሰዋል፤ ይህም የእስራኤልን ሕዝብ አንድነት ያረጋግጣል:: *የአርኖን ሸለቆ፤* በደቡብ በኩል ከሞዓብ ምድር ጋር የሚያዋስነውን ድንበር የሚለይ ነው:: *የአርሞንዔም ተራራ፤* በሰሜን በኩል የሚገኘው የእስራኤል ድንበር የት ድረስ እንደሆነ የሚወስን ነው::

12፥4 *የባሳን ንጉሥ ዐግ፤* ዐግና ሴዎን (ቍ 2) በሙሴ መሪነት ድል የተመቱ ነገሥታት ናቸው፤ ይህም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እጅግ ታላቅና ብርቱ አምላክ መሆኑን ለዘመናት ሲያስታውስ የሚኖር ነው (ዘኍ 9፥22፤ መዝ 135፥11 ይመ::)

12፥7 *ከ... በስተ ምዕራብ ... የምድሪቱ... ፤* የከነዓን ምድር በየት በኩል እንደሚገኝ በትክክል የሚያመለክት ነው (9፥7፤ 11፥16-17፤ 24፥11፤ ዘፍ 15፥18-19)::

12፥12 *የጌዝር ንጉሥ፤* ለኪሶ በተደመሰሰች ጊዜ (10፥33) ድል የተመታ ንጉሥ ነው፤ ሆኖም ኢያሱ ይህችን ከተማ ወይም አፌቅን ወይም ታዕናክን ወይም መጊዶን ወይም ደግሞ ዶርን በውጊያ አልያዘም (ቍ 18-23፤ መሳ 1፥27-31 ይመ)::

22የቃዴስ ንጉሥ፣ አንድ፤
በቀርሜሎስ የሚገኘው የዮቅንዓም
ንጉሥ፣ አንድ፤
23በዶር ኩረብታ[ተ] የሚገኘው የዶር
ንጉሥ፣ አንድ፤
በጌልገላ የሚገኘው የጎይም ንጉሥ፣ አንድ፤
24የቲርሳ ንጉሥ፣ አንድ፤
እነዚህ በድምሩ ሠላሳ አንድ ነገሥታት
ናቸው።

## ወደ ፊት የሚያዝ ምድር

13 ኢያሱ በሸመገለና ዕድሜው በገፋ ጊዜ፣
እግዚአብሔር እንዲህ አለው፤ "እነሆ
አርጅተሃል፤ ዕድሜህም ገፍቶአል፤ ነገር ግን
መያዝ ያለበት እጅግ በጣም ሰፊ ምድር ገና አለ።

2"የሚቀረውም ምድር ይህ ነው፤ እርሱም
የፍልስጥኤማውያንና የጌሹራውያን አገር
ሁሉ ነው፤ 3ከግብፅ በስተ ምሥራቅ ከሚ
ገኘው ከሺሖር ወንዝ አንሥቶ፣ በሰሜን
እስከ አቃሮን ወሰን ያለው አገር፣
ሁሉም እንደ ከነዓናውያን ምድር ይቈጠ
ራል፤ ይኸውም በጋዛ፣ በአሽዶድ፣ በአስ
ቀሎና፣ በጌትና በአቃሮን የሚኖሩትን
የአምስቱን የፍልስጥኤማውያን ገዦች
ምድር የሚያካትት ሲሆን፣ ይህም የኤዋ
ውያን ምድር ነበር። 4በደቡብ በኩል
የከነዓናውያን ምድር ሁሉና የሲዶናው
ያን ይዞታ ከሆነችው ከመዓራ አንሥቶ
እስከ አፌቅ ያለው የአሞራውያን ግዛት፣
5የጌባላውያንም ምድር[ሀ]፤ በምሥራቅም
ከበኣልጋድ አንሥቶ በአርሞንዔም ተራራ
ግርጌ አልፎ፣ እስከ ሐማት መተላለፊያ[ለ]
ያለው የሊባኖስ ምድር ሁሉ ነው።

6"ከሊባኖስ እስከ ማሴሮን ባለው ተራራማ
ምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉ፣ ሲዶናውያ
ንንም ጭምር እኔው ራሴ ከእስራኤላውያን ፊት
አሳድጄ አስወጣቸዋለሁ። ብቻ አንተ ባዘዝሁህ
መሠረት ምድሪቱን ርስት አድርገህ ለእስራ
ኤላውያን አካፍል። 7ይህንንም ለዘጠኙ ነገድና
ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት አድርገህ አካፍል።"

## ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለው ምድር አከፋፈል

8ሌላው የምናሴ ነገድ እኩሌታ፣ የሮቤል
ነገድና የጋድ ነገድ *የእግዚአብሔር* ባሪያ
ሙሴ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ እንደየ
ድርሻቸው ከፋፍሎ በመደበላቸው መሠረት፣
ራሱ ሙሴ የሰጣቸውን ርስት ተቀበሉ።

9ይህም ከአርኖን ሸለቆ ዳርቻ ካለው
ከአሮዔርና በሸለቆው መካከል ካለችው
ከተማ አንሥቶ እስከ ዲቦን የሚደር
ሰውን የሜድባን ደጋማ ምድር በሙሉ
ይይዛል፤ 10እንዲሁም በሐሴቦን ተቀ
ምጦ እስከ አሞናውያን ዳርቻ የገዛውን
የአሞራውያንን ንጉሥ የሴዎንን ከተሞች
ሁሉ ያጠቃልላል፤ 11በተጨማሪም ገለዓ
ድን፣ የጌሹራውያንንና የማዕካታውያንን
ግዛት ሁሉ፣ የአርሞንዔምን ተራራ
በሙሉ፣ ባሳንንም ሁሉ እስከ ሰልካ
ድረስ ይይዛል፤ 12ይህም በአስታሮትና
በኤድራይ ሆኖ የገዛውን በባሳን ያለውን
የዐግን መንግሥት በሙሉ ያጠቃል
ላል፤ ዐግም በሕይወት ከቀሩት ከመጨ
ረሻዎቹ ከራፋይም ዘሮች አንዱ ነበር፤
እነዚህንም ሙሴ ድል አደረጋቸው፤
ምድራቸውንም ያዘ፤ 13ነገር ግን እስራ
ኤላውያን የጌሹርንና የማዕካትን ሕዝብ
ስላላስወጡ፣ እስከ ዛሬ ድረስ በመካከላ
ቸው ይኖራሉ።

14ለሌዊ ነገድ ግን ርስት አልሰጠም፤ ለእስራ
ኤል አምላክ *ለእግዚአብሔር* በእሳት የሚቀር
በው ቍርባን፣ በተሰጣቸው ተስፋ መሠረት
ርስታቸው ነውና።

15ሙሴ በየጐሣቸው መድቦ ለሮቤል ነገድ
የሰጠው ርስት ይህ ነው፤

16ድንበራቸው ከአርኖን ሸለቆ ዳርቻ ካለው
ከአሮዔርና ከሸለቆው መካከል ካለችው
ከተማ አንሥቶ ያለው ግዛት ሲሆን፣ ሜድባ
አጠገብ ያለውን ደጋውን አገር በሙሉ፣
17ሐሴቦንና በደጋው ላይ ያሉትን ከተሞ
ችዋን በሙሉ፣ እንዲሁም ዲቦንን፣ ባሞ
ትባኣልን፣ ቤትበኣልምዖን፣ 18ያሀጽን፣
ቅዴሞትን፣ ሜፍዓትን፣ 19ቂርያታይምን፣
ሴባማን፣ በሸለቆው ኩረብታ ላይ ያለች
ውን ጼሬትሻሐርን፣ 20ቤተፌጎርን፣ የፈ
ስጋን ሸንተረሮችና ቤትየሺሞትን፣

12፥22 ኢሱ15፥23፡ 55፤19፥11፡26፡37፤ 20፥7፤21፥32፡34 መሳ4፥6፡9፤1ሳሙ15፥12፤2ሳሙ23፥35
12፥23 ኢሱ11፥2
12፥24 1ነገ14፥17፤ 15፥33፤16፥8፡23፤መሐ 6፥4፤መዝ135፥11፤ 136፥18
13፥1 ዘፍ 24፥1፤ኢሱ 14፥10፤23፥1፡2፤1ነገ1፥1
13፥2 ዘፍ10፥14፤ ኢሱ12፥5፤መሳ3፥31
13፥3 ዘዳ2፥23፤ኢሱ 11፥22፤15፥11፡45፤1 9፥43፤መሳ1፥18፤3፥3፤14፥19፤16፥5፡18፤ 1ሳሙ5፥10፤6፥4፡17፤ 7፥14፤2ሳሙ1፥20፤1 ዜና13፥5፤ኢሳ23፥3፤ 14፥29፤ኤር2፥18፤ 25፥20፤ሕዝ25፥15፤ አሞ3፥9
13፥4 ዘፍ14፥7፤15፥16፤ኢሱ12፥18፤ አሞ2፥10
13፥5 ዘኍ13፥21፤ 34፥8፤ዘዳ3፥8፤1ነገ5፥18፤ኢሱ11፥17፤መሳ 3፥3፤መዝ83፥7፤ሕዝ 27፥9
13፥6 ዘኍ33፥54፤ 34፥13፤ኢሱ11፥8፤ መዝ80፥8
13፥7 ኢሱ11፥23፤ መዝ78፥55
13፥8 ኢሱ12፥6፤ 8፥7
13፥9 ቍ16፡17፡ 21፤ዘኍ21፥30፤32፥3፡34፤ዘዳ2፥36፤መሳ 11፥26፤2ሳሙ24፥5፤ ኢሳ15፥2፤ኤር48፥ 8፡18፡21፡22
13፥10 ዘኍ21፥24፤ ኢሱ12፥2
13፥11 ኢሱ12፥2፡5
13፥12 ዘፍ14፥5፤ ዘኍ21፥33፤ዘዳ1፥4፤ 3፥8፤ኢሱ12፥4
13፥13 ዘዳ3፥12፡ 14፤ኢሱ12፥5
13፥14 ቍ33፤ዘዳ 18፥1-2፤ኢሱ14፥3
13፥16 ቍ9፤ዘኍ 21፥30፤ኢሱ12፥2፤ 1ሳሙ30፥28፤ ኢሳ15፥2
13፥17 ቍ9፤ዘኍ 32፥3፤22፥41፤1ዜና 5፥8፤ኤር48፥23፤ ሕዝ25፥9
13፥18 ዘኍ21፥23፤ዘዳ2፥26፤ኢሱ21፥37፤ኤር48፥21 13፥19 ዘኍ32፥3፡37 13፥20 ዘዳ3፥29 13፥21 ቍ9፤ዘፍ25፥2፤ ዘኍ 25፥15፤31፥8

[ተ]23 ወይም፣ *ናፎት ዶር* ማለት ነው። [ሀ]5 የቢብሎስ አካባቢ ነው። [ለ]5 ወይም፣ *እስከ ሌቦ ሐማት*

*13፥1-32፤* ምድሪቱን በድል የተቈጣጠረው ሰማያዊው ንጉሥ፣ ለየነገዶቹ የተወሰነውን ምድር በማከፋፈል የአስተዳደር ሥራውን ይጀምራል። ከም 13-21 ያለው ክፍል በአብዛኛው የአስተዳደር ጕዳዮች በዝርዝር የተገለጡበት ክፍል ነው። ታሪኩ የሚጀምረው መያዝ ያለበት ምድር (ለየነገዱ መከፋፈል ያለበት) ገና እንዳለ በመጠቈምና ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ የሁለቱ ነገድ እኩሌታ ድርሻ አድርጎ መድቦት የነበረውን በማስታወስ ነው።

13፥1 *ኢያሱ በሸመገለ...ጊዜ፤* ኢያሱ በዘጠናና በመቶ ዓመት የዕድሜ ዘመን መካከል የሚገኝ ሲሆን፣ ካሌብ ደግሞ ሰማንያ አምስት ዓመቱ ነበር (14፥10)።

13፥3 *ከሺሖር ወንዝ* ከጋዛ ወረድ ብሎ፣ በምሥራቅ በኩል በሲና በረሓ መግቢያ ላይ የሚገኘው የዋዲ ኤል አሪሽ ሌላ መጠሪያ ነው። *ገዦች፤* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጥ ቃል የፍልስጥኤማውያን ሥረ መሠረት ከኤጂያን ባሕር መሆኑን ለማመልከት "ጨካኝ ገዥ" የሚል ትርጕም ካለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሳይሆን አይቀርም።

13፥5 *ጌባላውያን፤* ከዛሬዋ ቤይሩት በስተ ሰሜን በኩል ይኖሩ የነበሩ የቢብሎስ ጥንታዊት ከተማ ነዋሪዎች ናቸው (አማራጭ ትርጕሙን ይመ)። ፊንቄያውያንና ፍልስጥኤማውያን እስራኤል ገና ወደፊት የምትወርሰውን አብዛኛውን ምድር የያዙ ሕዝቦች ናቸው።

13፥9 *አሮዔር፤* በአርኖን ወንዝ አጠገብ የምትገኝ ይህች ከተማ፣ የእስራኤልን ደቡባዊ ወሰን ታካልላለች። የእስራኤል ምድር ከዚህ አንሥቶ አሞንን፣ ገለዓድንና ባሳንን በማቋረጥ ከዚህ በፊት ሁለቱ የአሞራውያን ነገሥታት ሲዖንና ዐግ ይገዙት እስከ ነበረው እስከ ኤርሞን ተራራ ይደርሳል።

13፥14 *ቍርባን...ርስታቸው ነውና፤* ዘዳ 18፥1-8፤ የዘዳ 18፥1 ማብ ይመ።

13፥15 *ሙሴ...ለሮቤል...የሰጠው፤* ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ በአርኖን ወንዝና (የሞዓብ ወሰን) በሐሴቦን (የሴዎን

22የቃዴስ ንጉሥ፣ አንድ፤
በቀርሜሎስ የሚገኘው የዮቅንዓም
ንጉሥ፣ አንድ፤
23በዶር ኰረብታ[T] የሚገኘው የዶር
ንጉሥ፣ አንድ፤
በጌልገላ የሚገኘው የጎይም ንጉሥ፣ አንድ፤
24የቲርሳ ንጉሥ፣ አንድ፤
እነዚህ በድምሩ ሠላሳ አንድ ነገሥታት
ናቸው።

## ወደ ፊት የሚያዝ ምድር

13 ኢያሱ በሸመገለና ዕድሜው በገፋ ጊዜ፣
እግዚአብሔር እንዲህ አለው፤ "እነሆ
አርጅተሃል፤ ዕድሜህም ገፍቶአል፤ ነገር ግን
መያዝ ያለበት እጅግ በጣም ሰፊ ምድር ገና አለ።

2"የሚቀረውም ምድር ይህ ነው፤ እርሱም
የፍልስጥኤማውያንና የጌሹራውያን አገር
ሁሉ ነው፤ 3ከግብፅ በስተ ምሥራቅ ከሚ
ገኘው ከሺሖር ወንዝ አንሥቶ፣ በሰሜን
እስከ አቃሮን ወሰን ያለው አገር፣
ሁሉም እንደ ከነዓናውያን ምድር ይቈጠ
ራል፤ ይኸውም በጋዛ፣ በአሽዶድ፣ በአስ
ቀሎና፣ በጌትና በአቃሮን የሚኖሩትን
የአምስቱን የፍልስጥኤማውያን ገዦች
ምድር የሚያካትት ሲሆን፣ ይህም የኤዋ
ውያን ምድር ነበር። 4በደቡብ በኩል
የከነዓናውያን ምድር ሁሉና የሲዶናው
ያን ይዞታ ከሆነችው ከመዓራ አንሥቶ
እስከ አፌቅ ያለው የአሞራውያን ግዛት፣
5የጌባላውያንም ምድር[ሀ]፤ በምሥራቅም
ከበኣልጋድ አንሥቶ በአርሞንዔም ተራራ
ግርጌ አልፎ፣ እስከ ሐማት መተላለፊያ[ለ]
ያለው የሊባኖስ ምድር ሁሉ ነው።

6"ከሊባኖስ እስከ ማሴሮን ባለው ተራራማ
ምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉ፣ ሲዶናውያ
ንንም ጭምር እኔው ራሴ ከእስራኤላውያን ፊት
አሳድጄ አስወጣቸዋለሁ። ብቻ አንተ ባዘዝሁህ
መሠረት ምድሪቱን ርስት አድርገህ ለእስራ
ኤላውያን አካፍል። 7ይህንንም ለዘጠኙ ነገድና
ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት አድርገህ አካፍል።"

## ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለው ምድር አከፋፈል

8ሌላው የምናሴ ነገድ እኩሌታ፣ የሮቤል
ነገድና የጋድ ነገድ የእግዚአብሔር ባሪያ
ሙሴ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ እንደየ
ድርሻቸው ከፋፍሎ በመደበላቸው መሠረት፣
ራሱ ሙሴ የሰጣቸውን ርስት ተቀበሉ።

9ይህም ከአርኖን ሸለቆ ዳርቻ ካለው
ከአሮዔርና በሸለቆው መካከል ካለችው
ከተማ አንሥቶ እስከ ዲቦን የሚደር
ሰውን የሜድባን ደጋማ ምድር በሙሉ
ይይዛል፤ 10እንዲሁም በሐሴቦን ተቀ
ምጦ እስከ አሞናውያን ዳርቻ የገዛውን
የአሞራውያንን ንጉሥ የሴዎንን ከተሞች
ሁሉ ያጠቃልላል፤ 11በተጨማሪም ገለዓ
ድን፣ የጌሹራውያንንና የማዕካታውያንን
ግዛት ሁሉ፣ የአርሞንዔምን ተራራ
በሙሉ፣ ባሳንንም ሁሉ እስከ ሰልካ
ድረስ ይይዛል፤ 12ይህም በአስታሮትና
በኤድራይ ሆኖ የገዛውን በባሳን ያለውን
የዐግን መንግሥት በሙሉ ያጠቃል
ላል፤ ዐግም በሕይወት ከቀሩት ከመጨ
ረሻዎቹ ከራፋይም ዘሮች አንዱ ነበር፤
እነዚህንም ሙሴ ድል አደረጋቸው፤
ምድራቸውንም ያዘ፤ 13ነገር ግን እስራ
ኤላውያን የጌሹርንና የማዕካትን ሕዝብ
ስላላስወጡ፣ እስከ ዛሬ ድረስ በመካከላ
ቸው ይኖራሉ።

14ለሌዊ ነገድ ግን ርስት አልሰጠም፤ ለእስራ
ኤል አምላክ ለእግዚአብሔር በእሳት የሚቀር
በው ቍርባን፣ በተሰጣቸው ተስፋ መሠረት
ርስታቸው ነውና።

15ሙሴ በየጐሣቸው መድቦ ለሮቤል ነገድ
የሰጠው ርስት ይህ ነው፤

16ድንበራቸው ከአርኖን ሸለቆ ዳርቻ ካለው
ከአሮዔርና ከሸለቆው መካከል ካለችው
ከተማ አንሥቶ ያለው ግዛት ሲሆን፣ ሜድባ
አጠገብ ያለውን ደጋውን አገር በሙሉ፣
17ሐሴቦንና በደጋው ላይ ያሉትን ከተሞ
ችዋን በሙሉ፣ እንዲሁም ዲቦንን፣ ባሞ
ትባአልን፣ ቤትበአልምዖን፣ 18ያህጽን፣
ቅዴሞትን፣ ሜፍዓትን፣ 19ቂርያታይምን፣
ሴባማን፣ በሸለቆው ኰረብታ ላይ ያለች
ውን ጼሬትሻሐርን፣ 20ቤተፌጎርን፣ የፈ
ስጋን ሸንተረሮችና ቤትየሺሞትን፣

12፥22 ኢሱ15፥23፡55፤19፥11፡26፡37፤20፥7፤21፥32፡34 መሳ4፥6፡9፤1ሳሙ15፥12፤2ሳሙ23፥35
12፥23 ኢሱ11፥2
12፥24 1ነገ14፥17፤15፥33፤16፥8፡23፤መሓ6፥4፤መዝ135፥11፤136፥18
13፥1 ዘፍ 24፥1፤ኢሱ14፥10፤23፥1፡2፤1ነገ1፥1
13፥2 ዘፍ10፥14፤ኢሱ12፥5፤መሳ3፥31
13፥3 ዘዳ2፥23፤ኢሱ11፥22፤15፥11፡45፤19፥43፤መሳ1፥18፤3፥3፤14፥19፤16፥5፡18፤1ሳሙ5፥10፤6፥4፡17፤7፥14፤2ሳሙ1፥20፤1ዜና13፥5፤ኢሳ23፥3፤14፥29፤ኤር2፥18፤25፥20፤ሕዝ25፥15፤አሞ3፥9
13፥4 ዘፍ14፥7፤15፥16፤ኢሱ12፥18፤አሞ2፥10
13፥5 ዘኍ13፥21፤34፥8፤ዘዳ3፥8፤1ነገ5፥18፤ኢሱ11፥17፤መሳ3፥3፤መዝ83፥7፤ሕዝ27፥9
13፥6 ዘኍ33፥54፤34፥13፤ኢሱ11፥8፤መዝ80፥8
13፥7 ኢሱ11፥23፤መዝ78፥55
13፥8 ኢሱ12፥6፤8፥7
13፥9 ቍ16፡17፡21፤ዘኍ21፥30፤32፥3፡34፤ዘዳ2፥36፤መሳ11፥26፤2ሳሙ24፥5፤ኢሳ15፥2፤ኤር48፥8፡18፡21፡22
13፥10 ዘኍ21፥24፤ኢሱ12፥2
13፥11 ኢሱ12፥2፡5
13፥12 ዘፍ14፥5፤ዘኍ21፥33፤ዘዳ1፥4፤3፥8፤ኢሱ12፥4
13፥13 ዘዳ3፥12፡14፤ኢሱ12፥5
13፥14 ቍ33፤ዘዳ18፥1-2፤ኢሱ14፥3
13፥16 ቍ9፤ዘኍ21፥30፤ኢሱ12፥2፤1ሳሙ30፥28፤ኢሳ15፥2
13፥17 ቍ9፤ዘኍ32፥3፤22፥41፤1ዜና5፥8፤ኤር48፥23፤ሕዝ25፥9

13፥18 ዘኍ21፥23፤ዘዳ2፥26፤ኢሱ21፥37፤ኤር48፥21 13፥19 ዘኍ32፥3፡37 13፥20 ዘዳ3፥29 13፥21 ቍ9፤ዘፍ25፥2፤ ዘኍ25፥15፤31፥8

[T]23 ወይም፣ *ናፎት ዶር* ማለት ነው። [ሀ]5 የቢብሎስ አካባቢ ነው።
[ለ]5 ወይም፣ *እስከ ሌቦ ሐማት*

*13፥1-32፤ ምድሪቱን በድል የተቈጣጠረው ሰማያዊው* ንጉሥ፣ ለየነገዶቹ የተወሰነውን ምድር በማከፋፈል የአስተዳደር ሥራውን ይጀምራል። ከም 13-21 ያለው ክፍል በአብዛኛው የአስተዳደር ጉዳዮች በዝርዝር የተገለጡበት ክፍል ነው። ታሪኩ የሚጀምረው መያዝ ያለበት ምድር (ለየነገዱ መከፋፈል ያለበት) ገና እንዳለ በመጠቈምና ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ የሁለቱ ነገድ እኩሌታ ድርሻ አድርጎ መድቦት የነበረውን በማስታወስ ነው።

13፥1 *ኢያሱ በሸመገለ...ጊዜ፤* ኢያሱ በዘጠናና በመቶ ዓመት የዕድሜ ዘመን መካከል የሚገኝ ሲሆን፣ ካሌብ ደግሞ ሰማንያ አምስት ዓመቱ ነበር (14፥10)።

13፥3 *ከሺሖር ወንዝ* ከጋዛ ወረድ ብሎ፣ በምሥራቅ በኩል በሲና በረሓ መግቢያ ላይ የሚገኘው የዋዲ አል አሪሽ ሌላ መጠሪያ ነው። *ገዦች፤* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጥ ቃል የፍልስጥኤማውያን ሥረ መሠረት ከኤጂያን ባሕር መሆኑን ለማመልከት "ጨካኝ ገዥ" የሚል ትርጉም ካለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሳይሆን አይቀርም።

13፥5 *ጌባላውያን፤* ከዛሬዋ ቤይሩት በስተ ሰሜን በኩል ይኖሩ የነበሩ የቢብሎስ ጥንታዊት ከተማ ነዋሪዎች ናቸው (አማርኛ ትርጒሙን ይመ)። ፊንቂያውያንና ፍልስጥኤማውያን እስራኤል ገና ወደፊት የምትወርሰውን አብዛኛውን ምድር የያዙ ሕዝቦች ናቸው።

13፥9 *አሮዔር፤* በአርኖን ወንዝ አጠገብ የምትገኝ ይህች ከተማ፣ የእስራኤልን ደቡባዊ ወሰን ታካልላለች። የእስራኤል ምድር ከዚህ አንሥቶ አሞንን፣ ገለዓድንና ባሳንን በማቋረጥ ከዚ ህ በፊት ሁለቱ የአሞራውያን ነገሥታት ሲዎንና ዐግ ይገዙት እስከ ነበረው እስከ ኤርሞን ተራራ ይደርሳል።

13፥14 *ቍርባን...ርስታቸው ነውና፤* ዘዳ 18፥1-8፤ የዘዳ 18፥1 ማብ ይመ።

13፥15 *ሙሴ...ለሮቤል...የሰጠው፤* ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ በአርኖን ወንዝና (የሞዓብ ወሰን) በሐሴቦን (የሴዎን

[21]ይህም በደጋው አገር የሚገኙትን ከተሞች
ሁሉና መቀመጫውን በሐሴቦን አድርጎ
የገዛውን የአሞራውያንን ንጉሥ የሴዎንን
ግዛት በሙሉ ያካትታል:: ሙሴ ሴዎን
ንና በዚያው ምድር ተቀማጭ የነበሩ
ትን መሳፍንት፣ አዊ፣ ሮቆም፣ ሱር፣
ሑርና ሪባ የተባሉትን የምድያም አለ
ቆች ድል አደረጋቸው:: [22]በጦር ሜዳ ከሞ
ቱት ሌላ እስራኤላውያን የቢዖርን ልጅ
ምዋርተኛውን በለዓምን በሰይፍ መትተው
ገደሉት:: [23]የሮቤል ነገድ ወሰን የዮርዳኖስ
ወንዝ ነው፤ የሮቤል ነገድ በየጐሣቸው የወ
ረሷቸው ከተሞችና መንደሮ ቻቸው እነዚህ
ነበሩ፤
[24]ሙሴ በየጐሣቸው መድቦ ለጋድ ነገድ
የሰጠው ርስት ይህ ነው፤
[25]ድንበራቸው ኢያዜር፣ የገለዓድን ከተ
ሞች በሙሉ በረባት አጠገብ እስካለው እስከ
አሮዔር የሚደርሰውን የአሞናውያን አገር
እኩሌታ፣ [26]ከሐሴቦን እስከ ራማት ምጽጴና
ከዚያም እስከ ብጦኒም፣ ከመሃናይም እስከ
ደቤር ግዛት ያለውን፣ [27]በሸለቆው ውስጥ
ደግሞ ቤትሀራምን፣ ቤትኒምራን፣ሱኮ
ትን፣ ጻፎንንና እስከ ኪኔሬት* ባሕር
ጫፍ የሚደርሰውን ከዮርዳኖስ በስተ
ምሥራቅ ያለውን ቀሪውን የሐሴቦን ንጉሥ
የሴዎንን ግዛት ያካትታል፤ [28]የጋድ ነገድ
በየጐሣቸው የወረሷቸው ከተሞችና መን
ደሮቻቸው እነዚህ ነበሩ::
[29]ሙሴ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ማለት
ለገሚሱ የምናሴ ቤተሰብ ዘሮች በየጐሣቸው
የሰጣቸው ርስት ይህ ነው፤
[30]ድንበራቸው ከመሃናይም አንሥቶ ባሳ
ንን በሙሉ ይጨምርና፣ በባሳን ያሉትን
ሥልሳ የኢያዕር ከተሞች ሁሉ ይዞ የባ
ሳን ንጉሥ የዐግን ግዛት ሁሉ የሚያካትት
ሲሆን፣ [31]የገለዓድን እኩሌታ፣ በባሳን የዐግ

13፥22 ዘኁ30፥27፤ ዘኁ22፥5፤23፥23
13፥23 1ዜና5፥7
13፥25 ዘኁ21፥32፤ ዘዳ3፥11፤ኢሱ 21፥39፤ 12፥2
13፥26 ዘፍ32፥21 ዘኁ21፥25፤ኢሱ 10፥3፤ኤር49፥3
13፥27 ዘፍ33፥17፤ ዘኁ32፥3፤34፥11፤ መሳ12፥1፤መዝ48፥2
13፥28 ዘፍ46፥16፤ ዘኁ32፥33፤ሕዝ48፥27
13፥30 ዘፍ32፥2፤ ዘኁ21፥33፤32፥41፤ ኢሱ12፥4፤
13፥31 ዘፍ50፥23፤ ዘኁ21፥33፤ኢሱ17፥5


*27 የገሊላ ባሕር ነው::

ከተማ) መካከል የሚገኝ ምድር ነው::

13፥22 *የቢዖርን ልጅ... በለዓምን፤* በለዓም በአማልክት መንፈስ የተያዘ ሰው እንደ ነበር ይገመታል (ዘኁ 22፥24፤ 2ጴጥ 2፥15-16፤ ይሁዳ 11):: ምድያማውያን የእስራኤልን ሕዝብ በጣዖት አምልኮና በዝሙት ርኵሰት ባሳቱና በዚህም በደላቸው እግዚአብሔር በቀጣቸው ጊዜ በለዓም በሰይፍ ተገድሎአል (ዘኁ 25፥31፥8)::

13፥24 *ሙሴ... ለጋድ ...የሰጠው፤* በደቡብ በኩል ከሐሴቦን ጀምሮ፣ የዮርዳኖስን ወንዝ በመከተል እስከ ገሊላ ባሕር ደቡባዊ ጫፍ ድረስ የሚዘልቀው ማእከላዊው ክፍል ነው:: ይህም በአብዛኛው የገለዓድን ምድር የሚጨምር ቢሆንም፣ ስም የተሰጣቸውን ቦታዎች ሁሉ ማመልከት ስለማይቻል፣ በጋድና በምናሴ ነገድ እኩሌታ መካከል የሚገኘውን ትክክለኛ ድንበር በውል መለየት አስቸጋሪ ነው::


13፥29 *ሙሴ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ... የሰጣቸው፤* ከገሊላ ባሕር በስተ ምሥራቅና በስተ ሰሜን በኩል የሚገኝ ምድር ነው፤ ላይኛውን የገለዓድ ምድርም ያጠቃልላል:: ይህን ምድር ለመያዝ አመራር ይሰጥ የነበረው ማኪር ነው (ዘኁ 32፥32:39-42)::




4.የሰሜኑ ዘመቻ

በነሐስ ዘመን መጨረሻ ላይ ኢያሱ አሦርን በእሳት አቃጠለ ኢሱ 11:13:: የተለያዩ ቁፈራዎች እንደሚጠቁሙት የፈረሱበት ዘመን የሚታወቅ ሦስት ግልጽ የፍርስራሽ ድርብርቦሽ አሉ፤ ከእነዚህ አንዱ ከከነዓን መያዝ ጋር ታሪካዊ ግንኙነት እንዳለው ማስረጃ ተገኝቶለታል::

ቈፋሪዎቹ ኢያሱ፣ ያቃጠላት ከተማ ከድርብርቦሹ የመጨረሻዋን እንደሆን (በ1230 ዓ.ቅ.ክ) ቢናገሩም ሌሎች ግን ከሦስቱ ድርብርቦሾች የመጀመሪያ ታች ያለችውን እንደሆን ይናገራሉ (በ1400 ዓ.ቅ.ክ)::




1.ወደ ከነዓን መግባት

የእስራኤል ነገዶች በምድረ በዳ ለአርባ ዓመታት ተጉዘው ወደ ከነዓን በደረሱ ጊዜ ሁለት የአሞራውያን ነገሥታትን በባሳን ማሸነፍ ነበረባቸው:: በሙሴ አመራር ሥር እያሉ በዮርዳኖስ ማዶ ያለውን አገር በቍጥጥር ሥር ለማዋል ምድያማውያንን አሸንፈዋል::

የከነዓን መያዝ በዚያን ዘመን ኃበዝ በሆነ ጦረኛ የታቀደ ስልት ይመስላል:: እስራኤል ኢያሪኮን መያዟ ሜዳማ ቦታዎች መሸጋገሪያዎችን መንገዶችን በቁጥጥር ሥር በማድረግ ለሌላ ጊዜ የመነሻ ጣቢያ እንዲኖራት አድርጓል:: በመቀጠልም ቤቴልን፣ ጊብዓንና ላይኛው ቤትሖሮን አካባቢ መያዟ የፍልስጥኤም መካከለኛ ክልል እንድትቈጣጠር ረድቷታል:: በደቡብና በሰሜን በተለያዩ ጦርነቶች የተባበሩ ኀይላትን ለማሸነፍ እንድትችል ይህ ቦታ አስተዋጽኦ አድርጓል::

መንግሥት ዋና ከተማ የሆኑትን አስታሮ
ትንና ኤድራይን ይጨምራል፤ እነዚህ ለም
ናሴ ልጅ ለማኪር ዘሮች የተሰጡ ሲሆን፣
ይህም ለግማሾቹ የማኪር ልጆች በየጐሣቸው
የተሰጡ ናቸው።

[32]ሙሴ ከኢያሪኮ በስተ ምሥራቅ፣ ከዮር
ዳኖስ ማዶ በሞዓብ ሜዳ ሳለ የሰጣቸው
ርስት ይህ ነበር። [33]ለሌዊ ነገድ ግን ሙሴ
ርስት አልሰጠም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚ
አብሔር እንደ ተናገራቸው እርሱ ራሱ ርስ
ታቸው ነውና።

## ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ስላለው ምድር አከፋፈል

**14** ካህኑ አልዓዛር፣ የነዌ ልጅ ኢያሱና
የእስራኤል የየነገዱ ጐሣ አባቶች
የደለደሉላቸው፣ እስራኤላውያንም በከነዓን
ምድር የወረሱት ርስት ይህ ነው። [2]ርስታ
ቸውም እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት
በሰጠው ትእዛዝ መሠረት፣ ለዘጠኙ ነገድና
ለእኩሌታው ነገድ በዕጣ ተከፋፈለ። [3]ሙሴ
ለሁለቱ ነገድና ለእኩሌታው፣ የዮርዳኖስን
ምሥራቅ ክፍል ርስት አድርጎ ሰጣቸው፤
ሌዋውያኑ ግን አብረዋቸው እንዲካፈሉ አላ
ደረገም፤ [4]የዮሴፍ ልጆች ምናሴና ኤፍሬም
ሁለት ነገዶች ሆነው ነበርና፤ ለሌዋውያኑ
ግን ከሚኖሩባቸው ከተሞች እንዲሁም ለበግ፣
ለፍየልና ለከብት መንጎቻቸው መሰማሪያ እን
ዲሆን አብሮ የተከለለላቸውን ምድር ብቻ
እንጂ ሌላ አልሰጣቸውም፤ [5]ስለዚህ እስራ
ኤላውያን እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠ
ረት፣ ምድሪቱን ተካፈሉ።

## ኬብሮን ለካሌብ ተሰጠች

[6]የይሁዳም ሰዎች በጌልገላ ወደ ኢያሱ
ቀረቡ፤ ከዚያም የቄኔዛዊው የዮፎኒ ልጅ
ካሌብ እንዲህ አለው፤ "እግዚአብሔር በቃ
ዴስ በርኔ ስለ አንተና ስለ እኔ፣ የአምላክ
ሰው ለሆነው ለሙሴ የተናገረውን ታውቃ
ለህ። [7]የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ምድሪቱን

13፥32 ዘኍ26፥3፤ 22፥1
13፥33 ቍ14፤ዘኍ 26፥62፤18፥20፤ኢሱ 18፥7፤ሕዝ44፥28
14፥1 ዘፀ6፥23፤ዘኍ 26፥53፤34፥17-18፤ ኢሱ11፥23፤19፥51፤ 21፥1፤መዝ16፥6፤136 ፥21
14፥2 ዘሌ16፥8፤ ዘኍ34፥13
14፥3 ዘኍ32፥33፤ 34፥14፤35፥2፤ኢሱ 13፥14
14፥4 ዘፍ41፥52፤ ዘኍ35፥2-3፤ኢሱ 21፥2፤መሳ1፥29
14፥5 ዘኍ34፥13
14፥6 ዘኍ13፥6፡26፤ 14፥30፡38፤ዘዳ11፥30 ፤33፥1
14፥7 ዘኍ1317፡30፤ 14፥6-9፤ኢሱ 15፥3


13፥33 *እግዚአብሔር ... ርስታቸው ነውና፤* ቍ 14 እንዲሁም ዘዳ 18፥1-8 እና የዘዳ 18፥1 ማብ ይመ።

*14፥1-15፤* ለሚቀጥለው ክፍል (ም 15-19) አጭር መግቢያ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ለካሌብ ያሳየውን ታማኝነትም በተለየ ሁኔታ ይገልጻል።

14፥1 *ካህኑ አልዓዛር፤* አልዓዛር የአሮን ልጅ ስለ ሆነና፣ ሊቀ ካህናትም ስለ ነበረ፣ ዕጣ የመጣል ከፍተኛው ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ ነው። ኡሪምና ቱሚም ሥራ ላይ ሳይውሉ አልቀሩም (የዘጸ 28፥30ን፤ የ1ሳሙ 2፥28ን ማብ ይመ)።

14፥4 *ምናሴና ኤፍሬም፤* የዮሴፍ ልጆች ናቸው። ያዕቆብ እንደ ራሱ ልጆች አድርጎ ስላሳደጋቸው (ዘፍ 48፥5)፣ በስማቸው ሁለት የተለያዩ ነገዶች ተጠርተዋል። ይህም ሌዋውያንን በክህነት ተግባር በመመደብ፣ የእስራኤል ሕዝብ በዐሥራ ሁለት ነገድ እንዲከፋፈል አድርጎአል።

14፥6 *እግዚአብሔር...የተናገረውን፤* ካሌብ ስለ ምድሪቱ በጎ ወሬ ይዞ በመጣ ጊዜ (ዘኍ 13፥30፤ 14፥6-9፤ ዘዳ 1፥34-36)፣ እግዚአብሔር ከሠላሳ ስምንት ዓመት በፊት በቃዴስ በርኔ የገባለትን የተስፋ ቃል በዚህ ጊዜ ያስታውሳል።



እንድሰልል ከቃዴስ በርኔ በላከኝ ጊዜ
የአርባ ዓመት ሰው ነበርሁ፤ እኔም ትክክለ
ኛውን ማስረጃ ይዤለት መጣሁ፤ 8አብረውኝ
ወደዚያ የወጡት ወንድሞቼ ግን፣ የሕዝቡ
ልብ በፍርሃት እንዲቀልጥ አደረጉ፤ ሆኖም
እኔ አምላኬን *እግዚአብሔርን* በፍጹም ልቤ
ተከተልሁት። 9ስለዚህም ሙሴ በዚያች ዕለት፣
'አምላክን *እግዚአብሔርን* በፍጹም ልብህ ተከት
ለኸዋልና እግርህ የረገጣት ምድር ለዘላለም የአ
ንተና የዘርህ ርስት ትሆናለች'ም ብሎ ማለልኝ።
10"አሁንም እነሆ፤ ልክ *እግዚአብሔር* እን
ዳለው ይህን ለሙሴ ከተናገረበት ጊዜ አን
ሥቶ እስራኤል በምድረ በዳ ሲንከራተት
እኔን አርባ አምስት ዓመት በሕይወት ጠብቆ
አኑሮኛል፤ ይኸው ዛሬ ሰማንያ አምስት ዓመት
ሆነኝ። 11ሙሴ በላከኝ ጊዜ የነበረኝ ብርታት
ዛሬም አብሮኝ አለ፤ ልክ እንደዚያን ጊዜ
ሁሉ አሁንም ወደ ጦርነት ለመሄድ ኀይ
ሉም ብርታቱም አለኝ። 12አሁንም እግዚአ
ብሔር በዚያች ዕለት ቃል የገባልኝን ይህ
ችን ኰረብታማ አገር ስጠኝ። ዔናቃውያን
በዚያ እንደ ነበሩና ከተሞቻቸውም ታላላ
ቅና የተመሸጉ እንደሆኑ ያን ጊዜ አንተው
ራስህ ሰምተሃል፤ ሆኖም ልክ እርሱ እንዳ
ለው *በእግዚአብሔር* ርዳታ አሳድጄ አወ
ጣቸዋለሁ።"
13ከዚያም ኢያሱ የዮፎኒን ልጅ ካሌብን
ባረከው፤ ኬብሮንንም ርስት አድርጎ ሰጠው።
14ስለዚህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኬብሮን
የቄኔዛዊው የዮፎኒ ልጅ የካሌብ ርስት
ሆነች፤ የእስራኤልን አምላክ *እግዚአብሔርን*
በፍጹም ልቡ ተከትሎአልና። 15ኬብሮን
ቀድሞ ከዔናቃውያን ሁሉ ታላቅ በሆነው
በአርባቅ ስም ቂርያትአርባቅ ተብላ ትጠራ
ነበር።
ከዚያም ምድሪቱ ከጦርነት ዐረፈች።

## ለይሁዳ ነገድ የተመደበው ድርሻ

15፥15-19ተገ ምብ-መሳ 1፥11-15

15ለይሁዳ ነገድ በየጐሣቸው በዕጣ
የተመደበው ድርሻ እስከ ኤዶም
ምድር የሚወርድ ሲሆን፣ በስተ ደቡብ
መጨረሻ እስከ ጺን ምድረ በዳ ድረስ
ይዘልቃል።
2የደቡብ ወሰናቸው፣ ከጨው ባሕርሠ
ደቡባዊ ጫፍ ካለው የባሕር ወሽመጥ
ይነሣል፤ 3ከዚያም የአቅረቢምን
መተላለፊያ በማቋረጥ በጺን በኩል
እስከ ቃዴስ በርኔ ደቡባዊ ክፍል
ይደርሳል፤ ደግሞም ሐጽሮንን አልፎ
ወደ አዳር ይወጣና ወደ ቀርቃ ይታጠ
ፋል፤ 4በአጽሞን በኩል አድርጎም ወደ
ግብፅ ደረቅ ወንዝ ይገባና መቆሚያው
ባሕሩ ይሆናል፤ እንግዲህ በደቡብ በኩል
ያለው ወሰናቸውሩ ይህ ነው።
5በምሥራቅ በኩል ያለው ወሰና
ቸው ደግሞ የጨው ባሕር ሲሆን፣
ይህም የዮርዳኖስ ወንዝ እስከሚሠርግ
በት ይደርሳል።
በሰሜን በኩል ያለው ወሰንም
የዮርዳኖስ ወንዝ ከሚሠርግበት የባሕር
ወሽመጥ ይነሣና 6ሽቅብ ወደ ቤትሖ
ግላ ይወጣል፤ ከዚያም በሰሜናዊው
ቤትዓረባ በኩል አድርጎ የሮቤል ልጅ
የቦሀን ድንጋይ እስካለበት ይደርሳል።
7ከዚያም ድንበሩ ከአኮር ሸለቆ ወደ
ዳቤር ይወጣና ከወንዙ በስተ ደቡብ
ባለው በአዱሚም መተላለፊያ ፊት
ለፊት አድርጎ በስተ ሰሜን ወደ ጌልገላ
ይታጠፋል፤ በዓይንሳሚስ ምንጭ በኩል
አልፎም ወደ ዓይንሮጌል ይወጣል።
8እንደዚሁም የሄኖምን ልጅ ሸለቆ አልፎ
ይሄድና የኢያቡሳውያን ከተማ እስከ
ሆነችው እስከ ኢየሩሳሌም ደቡባዊ
ተረተር በመዝለቅ፣ በራፋይም ሸለቆ
ሰሜን ጫፍ በኩል አድርጎ ከሄኖም
ሸለቆ በስተ ምዕራብ ካለው ኰረብታ
አናት ላይ ይደርሳል። 9ከዚያም በመ
ቀጠል ከተራራው አናት ተነሥቶ
ወደ ኔፍቶ ምንጮች በማምራት፣ በዔፍ
ሮን ተራራ ላይ ያሉትን ከተሞች አልፎ
ይወጣና ቂርያትይዓሪም ተብሎ ወደ
ሚጠራው ወደ በኣላ ቍልቍል ይወር
ዳል፤ 10ከዚያም ከበኣላ በምዕራብ በኩል
አድርጎ ወደ ሴይር ይታጠፍና ክሳሎን
ተብሎ በሚጠራው በይዓሪም ኰረብታ

ም9 ዘዳ 1፥36 ይመ። ሠ2 በዚህና በቍጥር 5 ላይ *የሙት ባሕር፤* ማለት ነው። ሩ4 ዕብራይስጡ *ወሰናችሁ፤* ይላል።

14፥8 ዘኍ13፥31፤ 14፥24፤32፥12
14፥9 ዘኍ14፥24፤ ዘዳ11፥24
14፥10 ዘኍ11፥28፤ 14፥30፤ኢሱ5፥6፤ 13፥1
14፥11 ዘፍ15፥15፤ ዘዳ34፥7
14፥12 ዘኍ13፥28፡ 33፤14፥24
14፥13 ዘፍ23፥19፤ ኢሱ10፥36፤22፥6፡7፤ መሳ1፥20፤1ሳሙ25፥ 3፤30፥14፤1ዜና6፥56
14፥14 ዘኍ14፥24
14፥15 ዘፍ23፥2፤ ኢሱ11፥23፤15፥ 13፤መሳ3፥11፤1ነገ4፥ 24፤5፥4፤1ዜና22፥9
15፥1 ዘኍ34፥3፤1 3፥21፤ኢሱ18፥5
15፥2 ዘፍ14፥3
15፥3 ዘኍ34፥4፤ ዘጸ1፥2
15፥4 ዘፍ15፥18፤ ዘኍ34፥4
15፥5 ዘፍ14፥3፤ዘኍ 34፥10፤ኢሱ18፥15-19
15፥6 ቍ61፤ኢሱ 18፥17-19፡21
15፥7 ዘጸ11፥30፤ ኢሱ7፥24፤10፥3፤ 18፥16፡17፤2ሳሙ17፥ 17፤1ነገ1፥9
15፥8 ቍ63፤ኢሱ 10፥1፤18፥16፡28፤ መሳ1፥21፤19፥10፤ 2ሳሙ5፥6፡18፡22፤ 2ነገ23፥10፤1ዜና11፥ 4፤14፥9፤2ዜና28፥3፤ ዕዝ9፥1፤ኢሳ17፥5፤ ኤር7፥31፤19፥2፡6
15፥9 ቍ10፡11፡ 29፤ኢሱ9፥17፤18፥ 15፤2ሳሙ6፥2፤ 1ዜና13፥6
15፥10 ቍ9፤ዘፍ38፥ 12፤ዘኍ24፥18፤ኢሱ 19፥22፡38፤21፥16፤ መሳ1፥33፤1ሳሙ6፥9፤ 1ነገ4፥9፤2ነገ14፥11

14፥12 *ይህችን ኰረብታማ አገር፤* ኬብሮን ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ 40 ኪ.ሜ. ያህል በመራቅ፣ በይሁዳ ተራራማ ስፍራ ከፍ ብላ የምትገኝ አገር ናት። *ዔናቃውያን፤* የ11፥21 ማብ ይመ።

14፥15 *ቂርያት አርባቅ፤* ትርጕሙ፣ "የአርባቅ ከተማ" ማለት ሲሆን፣ አርባቅ ተብሎ የተሰየመችው በዔናቃውያን አባት ስም ነው (15፥13፤21፥11)። "የአራት ከተማ" ማለትም ሊሆን ይችላል። ኬብሮን ማለት "አንድነት" ማለት ነው። *ምድሪቱ ከጦርነት ዐረፈች፤* ይሁዳውያ ንና ካሌብ ስለሚሰጣቸው ርስት ወደ ኢያሱ በመቅረብ አመልክተው የነበሩት ገና በጌልገላ የጦር ሰፈር ሳለ በመሆኑ፤ ይህን ያደረጉት ምናልባት በኢያሱ መሪነት የተካሄደው ጦርነት ከመጠናቀቁ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሊሆን ይችላል (11፥23 ይመ)።

*15፥1-63፤* ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ ከሰፈሩት ነገዶች መካከል የርስት ድርሻውን በመጀመሪያ የተቀበለው የይሁዳ ነገድ ነው። በመጀመሪያ ከሌሎች ጋር የሚያዋስናቸው ድንበር እስከ የት ድረስ እንደሆነ ተዘረዘረ፤ ከዚያም ለካሌብና ለጎቶንያል የሚሰጠው ርስት ተደለደለ፤ በመጨረሻም ለይሁዳ ነገድ የሚሰጡ የከነዓናውያን ከተሞች በየአውራጃው ስም ወጣላቸው።

15፥1 *ለይሁዳ ነገድ፤* የይሁዳ ከሌሎቹ ነገዶች ቀዳሚ መሆን በያዕቆብ ንግር ወይም ትንቢት ውስጥ ዐይነተኛ ቦታ ከመያዙም በላይ (ዘፍ 49፥8-12) በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ ተሰጥቶት ይገኛል (2ነገ 17፥18)።

15፥4 *በደቡብ በኩል ያለው ወሰናቸው፤* እዚህ ላይ የተጠቀሱት ቦታዎች ከሙት ባሕር ታችኛው ጫፍ በመነሣት ቃዴስ በርኔን አቋርጠው በዋዲ ኤል አሪሽ መግቢያ ላይ ከሚገኘው የሜዲትራኒያን ጠረፍ ጋር ሲገ ናኙ፣ አንድ ኩርባ (ደጋን) መሳይ ቅርጽ ይፈጥራሉ (የ13፥3 ማብ ይመ)።

15፥5 *በምሥራቅ በኩል ያለው ወሰናቸው፤* ከብንያም ግዛት ጋር የሚዋሰነው የይሁዳ ድንበር ከዮርዳኖስ ወንዝ መግቢያ በመነሣት፣ ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ የሄኖምን ሸለቆ በማቋረጥ ቲምና ይደርሳል፤ ከዚያም በስሜን ምዕራብ በኩል ከዮጳ በስተ ደቡብ 16 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ በባሕር ጠረፍ ላይ ወደምትገኘው ያብንኤል ድረስ (ከጊዜ በኋላ ያምኒያ/ጃምኒያ ተብላ ተሰየ ማለች) ይዘልቃል።

ሰሜናዊ ተረተር አልፎ ቀጐልቀጐል ወደ
ቤትሳሚስ በመውረድ ወደ ተምና ይሻገ
ራል:: 11ደግሞም በአቃሮን ሰሜናዊ
ተረተር አድርጎ ወደ ሽክሮን ይታጠፍና
በበኣላ ተራራ ላይ አልፎ እስከ የብኒ
ኤል ይደርሳል፤ ከዚህ በኋላ ወሰኑ ባሕሩ
ላይ ይቆማል::

12የምድሪቱ ምዕራባዊ ወሰን የታ
ላቁ ባሕር[ሀ] ጠረፍ ነው፤
እንግዲህ በየጐሣው የተደለደለውን የይሁ
ዳን ሕዝብ በዙሪያው የከበቡት ወሰኖቹ እነ
ዚሁ ናቸው::
13ኢያሱ *እግዚአብሔር* ባዘዘው መሠ
ረት፣ ከይሁዳ ድርሻ ላይ ከፍሎ ኬብሮን
የተባለችውን ቂርያትአርባቅን ለዮፎኒ ልጅ
ለካሌብ ሰጠው፤ አርባቅም የዔናቅ አባት
ነበረ:: 14ካሌብም ሦስቱን የዔናቅን ዘሮች
ሴሲንን፣ አኪመንንና ተላሚንን ከኬብሮን
አሳደዳቸው፤ 15ከዚያም በዳቤር ሕዝብ ላይ
ዘመተ፤ ዳቤር ቀድሞ ቂርያትሤፍር ትባል
ነበር:: 16ካሌብ፣ "ቂርያትሤፍርን ወግቶ
ለሚይዝ ሰው ልጄን ዓክሳን እድርለታለሁ"
አለ:: 17ስለዚህ የካሌብ ወንድም የቄኔዝ
ልጅ ጎቶንያል ከተማዪቱን ያዛት፤ ካሌብም
ልጁን ዓክሳን ዳረለት::
18ዓክሳ ወደ ጎቶንያል በመጣች ጊዜም፣
ከአባትዋ ላይ የእርሻ መሬት እንዲለምን
አጥብቃ ነገረችው::[ለ] ከአህያዋ ላይ እንደ
ወረደች ካሌብ፣ "ምን እንዳደርግልሽ ትፈ
ልጊያለሽ?" ሲል ጠየቃት::
19እርስዋም፣ "እባክህ፤ በጎ ነገር አድርግ
ልኝ፤ በኔጌብ መሬት እንደ ሰጠኸኝ ሁሉ፣
አሁንም የውሃ ምንጭ ጉድጓዶች ስጠኝ"
አለችው፤ ካሌብም የላይኛውንና የታችኛ
ውን ምንጮች ሰጣት::
20ለይሁዳ ነገድ በየጐሣቸው የተሰጣቸው
ርስት ይህ ነው፤
21በኔጌብ አካባቢ በኤዶም ድንበር ላይ
በወሰኑ ጫፍ የሚገኙት የይሁዳ ነገድ ደቡ
ባዊ ከተሞች እነዚህ ነበሩ፤
ቀብስኤል፣ ዔዴር፣ ያጉር፣ 22ቂና፣
ዲሞና፣ ዓድዓዳ፣ 23ቃዴስ፣ ሐጾር፤
ዩትናን፣ 24ዚፍ፣ ጤሌም፣ በዓሎት፣
25ሐጾርሐዳታ፣ ሐጾር የምትባለው ቂርያ
ትሐጾር 26አማም፣ ሽማዕ፣ ሞላዳ፣
27ሐጻርጋዳ፣ ሐሽሞን፣ ቤትጳሌጥ፣
28ሐጻር ሹዓል፣ ቤርሳቤህ፣ ቢዝዮትያ
29በኣላ፣ ዒዪም፣ ዓጼም፣ 30ኤልቶ

15፥11 ቀኍ9፤ኢሱ 13፥3፤19፥33
15፥12 ዘኍ34፥6
15፥13 ዘፍ23፥2፤ ዘኍ13፥22፤ኢሱ10፥ 36፤21፥12፤1ሳሙ25፥ 3፤30፥14፤1ዜና6፥56
15፥14 ዘኍ13፥ 22:33፤መሳ1+10:20
15፥16 1ዜና2፥49
15፥17 መሳ3፥9:11፤ 1ዜና4፥13፤27፥15
15፥19 ዘፍ36፥24፤ ኢሱ10፥40
15፥21 ዘፍ35፥21፤ ኢሱ10፥40፤2ሳሙ23 ፥20፤1ዜና11፥22
15፥23 ኢሱ11፥1፤ 12፥22
15፥24 ቀኍ55፤1ሳሙ 23፥14፤2ዜና11፥8
15፥25 ኢሱ11፥1
15፥26 ኢሱ19፥2፤ 1ዜና4፥28፤ነህ11፥26
15፥28 ዘፍ21፥14፤ ኢሱ19፥3፤1ዜና4፥28
15፥29 ቀኍ9፤ኢሱ 19፥3፤1ዜና4፥29
15፥30 ዘኍ14፥45፤ ኢሱ 19፥4
15፥31 ኢሱ19፥ 5፤1ሳሙ27፥6፤1ዜና 2፥49፤4፥30፤12፥1፤ ነህ11፥28
15፥32 ዘኍ34፥11፤ ኢሱ19፥7፤መሳ20፥ 45፤21፥13፤ዘካ14፥10
15፥33 ቀኍ43፤ኢሱ 19፥41፤መሳ13፥2:25፤ 16፥31፤18፥2:11፤2ዜ ና11፥10፤ነህ11፥29
15፥34 ቀኍ56፤ኢሱ 12፥17፤19፥21፤21፥ 29፤1ዜና4፥18፤ነህ3፥ 13፤11፥30
15፥35 ቀኍ48፤ዘፍ 38፥1፤ኢሱ10፥3:10፤ 1ነገ4፥10
15፥36 1ሳሙ17፥ 52፤1ዜና4፥31፤12፥4
15፥38 ኢሱ11፥3፤ 2ነገ14፥7
15፥39 ኢሱ10፥3፤ 2ነገ22፥1
15፥41 ኢሱ10፥10፤ 19፥27፤2ዜና28፥18
15፥42 ዘኍ33፥20፤ ኢሱ19፥7፤1ሳሙ30 ፥30፤1ዜና4፥32፤6፥59
15፥43 ቀኍ33
15፥44 ኢሱ19፥29፤ መሳ1፥31፤1ሳሙ23፥ 1-2፤1ዜና4፥19፤ ነህ 3፥17:18፤ሚክ1፥14:15
15፥45 ኢሱ13፥3
15፥46 ኢሱ11፥22

ላድ፣ ኪሲል፣ ሔርማ፣ 31ጺቅላግ፣
ማድማና፣ ሳንሳና 32ልባዎት፣ ሺል
ሂም፣ ዓይንና ሪሞን ናቸው፤ ባጠቃላ
ይም ከተሞቹና መንደሮቻቸው ሃያ
ዘጠኝ ናቸው::
33በምዕራቡ በኮረብታዎች ግርጌ ያሉት
ደግሞ እነዚህ ናቸው፤
ኤሽታኦል፤ ጾርዓ፣ አሽና፣
34ዛኖዋ፣ ዓይ ንጋኒም፣ ታጱዋ፣ ዓይናም፣
35የርሙት፣ ዓዶላም፣ ሰኮት፣ ዓዜቃ፣
36ሸዓራይም፣ ዓዲታይም፣ ግዴራ፣ ግዴ
ሮታይም ናቸው፤ ከተሞቹም ከነመንደ
ሮቻቸው ዐሥራ አራት ናቸው::
37ጽናን፣ ሐዳሻ፣ ሚግዳል ጋድ፣
38ዲልዓን፣ ምጽጳ፣ ዮቅትኤል፣ 39ለኪሶ፣
ቦጽቃት፣ ዔግሎን፣ 40ከቦን፣ ለሕማስ፣
ኪትሊሽ፣ 41ግዴሮት፣ ቤት ዳጎን፣ ናዕ
ማና መቄዳ ናቸው፤ ከተሞቹም ከነመን
ደሮቻቸው ዐሥራ ስድስት ናቸው::
42ልብና፣ ዔትር፣ ዓሻን 43ይፍታሕ፣
አሽና፣ ንጺብ፣ 44ቅዒላ፣ አክዚብና
መሪሳ ናቸው፤ ከተሞቹም ከነመንደ
ሮቻቸው ዘጠኝ ናቸው::
45አቃሮን በዙሪያዋ ካሉ ሰፈሮ
ችና መንደሮቿ ጋር፣ 46እንዲሁም ከአ
ቃሮን በስተ ምዕራብ በአሽዶድ አካ
ባቢ ያሉ ሰፈሮችና መንደሮቻቸው
ሁሉ፣ 47አሽዶድ በዙሪያዋ ካሉ ሰፈሮ
ችና መንደሮች ጋር፣ ጋዛ እስከ ግብፅ
ደረቅ ወንዝና እስከ ታላቁ ባሕር ጠረፍ
በመለስ ካሉት ሰፈሮቿና መንደሮቿ
ጋር::
48በኮረብታማዋም አገር የሚገኙ ከተሞች
ደግሞ እነዚህ ናቸው፤ ሳምር፣ የቲር፣
ሶኮ 49ደና፣ ዳቤር የምትባለው ቂርያ
ትስና 50ዓናብ፣ ኤሽትሞዓ፣ ዓኒም፣
51ጎሶም፣ ሖሎንና ጊሎ፤ እነዚህም ዐሥራ
አንዱ ከተሞችና መንደሮቻቸው ናቸው::
52አራብ፣ ዱማ፣ ኤሽዓን፣ 53ያኒም፣
ቤትታጱዋ፣ አፌቃ 54ሑምጣ፣ ኬብሮን

15፥47 ዘፍ15፥18፤ዘኍ34፥6፤ኢሱ11፥22 15፥48 ቀኍ35፤ኢሱ 21፥14፤መሳ10፥1፤1ሳሙ30፥27፤1ዜና6፥57 15፥49 ኢሱ10፥3
15፥50 ኢሱ11፥21፤21፥14፤1ሳሙ30፥28 15፥51 ኢሱ10፥ 41፤21፥15፤2ሳሙ15፥12፤ኤር48፥21 15፥52 ዘፍ25፥14
15፥54 ዘፍ35፥27

[ሀ]12 በዚህና በቍጥር 47 ላይ የተጠቀሰው የሜድትራንያን ባሕር ነው:: [ለ]18 ዕብራይስጥና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ በዙ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ግን (መሳ1፥14 ይመ) አጥብቆ ነገራት ያላሉ::

15፥15 *በዳቤር ሕዝብ ላይ ዘመተ፤* የ10፥38 ማብ ይመ::
15፥17 *ጎቶንያል፤* በእስራኤል ላይ መስፍን ሆኖ ስለማገልገሉ በመሳ 3፥7-11 ላይ ይመ::
15፥19 *የላይኛውንና የታችኛውን ምንጮች፤* እነዚህ ምን ጮች ዛሬም በኬብሮን ዙሪያ ለሚገኙ የእርሻ ቦታዎች አገልግሎት ይሰጣሉ::
15፥21 *ደቡባዊ ከተሞች፤* ከመጀመሪያዎቹ ሃያ ዘጠኝ መን ደሮች ውስጥ አብዛኞዎቹ የተሰጡት ለስምዖን ነገድ ነው (ከ19፥ 1-9 ጋር ያነጻጽሩ)::
15፥33 *በምዕራቡ ኮረብቶች ግርጌ፤* ይህን ቃል ለመግ ለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል "ሽጲላሕ" የሚል ሲሆን፣ ትር ጕሙም "ቈላ" ማለት ነው:: ይህ በማእከላዊ ይሁዳ ከፍተኛ ቦታዎችና በፍልስጥኤም ምድር ጠረፍ መካከል የሚገኘው ስፍራ፣ ታላቁ የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት እስከ ተነሣበት ጊዜ ድረስ በእስ ራኤል ይዞታ ሥር አልነበረም:: በዚህ ዝርዝር ውስጥ የተጠ ቀሱት ቦታዎች ለዳን ነገድ እንደገና ተሰጥተዋል (ከ19፥41-43 ጋር ያነጻጽሩ)::
15፥48 *በኮረብታማዋም አገር፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ያለው ከፍተኛ ስፍራ ነው:: ሰብዐ ሊቃናት በዚህ ዝርዝር ውስጥ ቴቆሔንና ቤተ ልሔምን ጨምሮ፣ የዐሥራ አንድ ከተሞችን ስም ጨምሮአል::

የተባለችው ቂርያትአርባቅና ጺዖር ናቸው፤
እነዚህም ዘጠኝ ከተሞችና መንደሮቻ
ቸው ናቸው።
55ማዖን፣ ቀርሜሎስ፣ ዚፍ፣ ዩጣ
56ኢይዝራኤል፣ ዮቅድዓም፣ ዛኖዋሕ፣
57ቃይን፣ ጊብዓና ተምና ናቸው፤ እነ
ዚህም ዐሥር ከተሞችና መንደሮቻቸው
ናቸው።
58ሐልሑል፣ ቤትጹር፣ ጌዶር፣ 59ማዕ
ራት፣ ቤትዓኖትና ኤልትቆን ናቸው፤ እነ
ዚህም ስድስት ከተሞችና መንደሮቻቸው
ናቸው።
60ቂርያትይዓሪም የተባለችው ቂርያ
ትበኣልና ረባት፤ እነዚህም ሁለት
ከተሞችና መንደሮቻቸው ናቸው።
61በምድረ በዳው ደግሞ እነዚህ ናቸው፤
ቤትዓረባ፣ ሚዲን፣ ስካካ፣ 62ኒብሻን፣
የጨው ከተማና ዓይንጋዲ፤ እነዚህም
ስድስት ከተሞችና መንደሮቻቸው
ናቸው።
63ነገር ግን የይሁዳ ዘሮች በኢየሩሳሌም
የሚኖሩትን ኢያቡሳውያን ከቦታቸው ሊያስ
ለቅቋቸው አልቻሉም፤ ኢያቡሳውያንም እስከ
ዛሬ ድረስ ከይሁዳ ሕዝብ ጋር በኢየሩሳሌም
አብረው ይኖራሉ።

## ለኤፍሬምና ለምናሴ ነገድ የተመደበው ድርሻ

16 ለዮሴፍ ዝርያዎች የተመደበው
ድርሻ፣ ከዮርዳኖስ ኢያሪኮ* ማለት
ከኢያሪኮ ምንጮች በስተ ምሥራቅ
ይነሣና፣ ምድረ በዳውን በማቋረጥ
በኰረብታማው አገር አድርጎ ወደ
ቤቴል ይወጣል። 2ሉዛ ከምትባለው
ከቤቴል ይነሣና በአጣሮት ወደ ሚገ
ኘው ወደ አርካውያን ግዛት ይሻገ
ራል፣ 3በዚያም በምዕራብ በኩል ቍል
ቍል ወደ የፍሌጣውያን ግዛት እስከ
ታችኛው ቤትሖሮን ምድር ይወር
ድና ወደ ጌዝር ዘልቆ ባሕሩ ላይ
ይቆማል።
4ስለዚህ የዮሴፍ ዘሮች ምናሴና ኤፍሬም
ርስታቸውን ተቀበሉ።
5ለኤፍሬም ወገን በየጐሣ በየጐሣቸው
የተሰጣቸው ድርሻ ይህ ነው፤
ድንበሩ በምሥራቅ በኩል ከአጣ
ሮት አዳር ተነሥቶ እስከ ላይኛው
ቤትሖሮን ይወጣና፣ 6እስከ ባሕሩ ይዘ
ልቃል። በስተ ሰሜን ደግሞ ከሚክም
ታት ተነሥቶ በምሥራቅ በኩል ወደ
ተአናት ሴሎ ይታጠፍና ከዚያ በማ
ለፍ እስከ ኢያኖክ ምሥራቅ ይዘል
ቃል፤ 7ከኢያኖክም በመነሣት ወደ
አጣሮትና ወደ ነዓራት ቍልቍል
ይወርድና በኢያሪኮ በኩል አድርጎ
ዮርዳኖስ ላይ ብቅ ይላል። 8ድንበሩ
አሁንም ከታጱዋ በምዕራብ በኩል
አድርጎ ወደ ቃና ወንዝ ይወርድና
ከባሕሩ ላይ ይቆማል። እንግዲህ
የኤፍሬም ነገድ በየጐሣ በየጐ
ሣቸው የተካፈሉት ርስት ይህ
ነበር። 9ይህም በምናሴ ነገድ ርስት
ውስጥ ለኤፍሬም ዘሮች የተመደቡ
ትን ከተሞች በሙሉና መንደሮቻቸ
ውን የሚያጠቃልል ነው።
10ይህ ሁሉ ሆኖ የኤፍሬም ዘሮች በጌ
ዝር የሚኖሩትን ከነዓናውያን ከዚያ
አላባረሯቸውም ነበር፤ ከነዓናውያን እስከ
ዛሬ ድረስ ከኤፍሬም ዘሮች ጋር አብ
ረው ይኖራሉ፤ ይሁን እንጂ የጕልበት
ሥራ እንዲሠሩ ይገደዳሉ።

17 ምናሴ የዮሴፍ የበኵር ልጅ እንደ
መሆኑ መጠን፣ ለነገዱ የተመደበ
ለት ድርሻ ይህ ነበር፤ የምናሴ የበኵር
ልጅ ማኪር፣ የገለዓዳውያን አባት ብርቱ
ጦረኛ ስለነበር ገለዓድና ባሳን ድርሻው
ሆኑ። 2ስለዚህ ይህ ርስት ለተቀሩት የም
ናሴ ዘሮች ማለትም ለአቢዔዝር፣ ለኬሌግ፣
ለአሥሪኤል፣ ለሴኬም፣ ለኦፌር፣ ለሸሚዳ
ጐሣዎች የተሰጠ ነው፤ እነዚህ በየጐሣ
ዎቻቸው የዮሴፍ ልጅ የምናሴ ሌሎች
ወንዶች ዝርያዎች ናቸው።
3ሰለጰዓድ የኦፌር ልጅ፣ የገለዓድ ልጅ፣
የማኪር ልጅ፣ የምናሴ ልጅ ነው። እርሱም
ሴቶች ልጆች እንጂ ወንዶች ልጆች አልነበሩ
ትም። የሴቶች ልጆቹም ስም ማህለህ፣

15፥55 ኢ-12፥22፤ 1፥16፤መሳ10፥12፤1ሳሙ-23፥24፡25፤25፥1፡2፤ 1ዜና2፥45
15፥56 ቍ34፤ኢሱ17፥16፤19፥18፤መሳ 6፥33፤1ሳሙ-25፥43፤ 1ነገ18፥45፤1ዜና3፥1፤ ሆሴ1፥5
15፥57 ዘፍ38፥12፤ ኢሱ18፥28፤24፥33፤ መሳ19፥12፡20፥4፤2ሳሙ-23፥29፤ 1ዜና11፥31
15፥58 1ዜና2፥45፤ 4፥39፤12፥7፤2ዜና11 ፥7፤ ነህ3፥16
15፥60 ቍ9፤ዘዳ 3፥11፤ኢሱ9፥17
15፥61 ቍ6፤ኢሱ 8፥15
15፥62 1ሳሙ-23፥ 29፤24፥1፤ሕዝ47፥10
15፥63 ቍ8፤ ኢሱ 10፥1፤16፥10፤17፥12፤ መሳ1፥21፤1ነገ9፥21፤ ሕዝ48፥7
16፥1 ኢሱ8፥15፤ 12፥9
16፥2 ቍ5፤ዘፍ28፥ 19፤ዘኍ32፥3፤2ሳሙ-15፥32
16፥3 ኢሱ10፥10፡33
16፥4 ኢሱ18፥5
16፥5 ቍ2፤ኢ ሱ10፥10፤18፥13
16፥6 ቍ7፤ኢሱ17፥ 7፤2ነገ15፥29
16፥7 ቍ6፤ዘኍ 32፥3
16፥8 ኢሱ12፥17፤ 17፥9፤19፥28
16፥9 ሕዝ48፥5
16፥10 ኢሱ15፥63፤ 17፥13፤መሳ1፥28-29፤1ነገ9፥16
17፥1 ዘፍ41፥51፤50 ፥23፤ዘኍ-1፥34፤ኢሱ 12፥2፡5፤1ዜና7፥14
17፥2 ዘኍ-26፥30፤ 27፥1፤ ኢሱ22፥7፤ መሳ6፥ 11፡34፤8፥2፤ 1ዜና7፥14፡18፡19
17፥3 ዘኍ-27፥1፤ 26፥33

*1 ምናልባት፣ ዮርዳኖስ ዘኢያሪኮ የዮርዳኖስ ወንዝ የጥንት መጠሪያ ሊሆን ይችላል።

15፥61 *ምድረ በዳው፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅና በስተ ደቡብ፣ ሙት ባሕርን የሚያዋስን ኖራማና ደረቅ ክልል ነው።

15፥62 *ዓይንጋዲ፤* የምትገኘው በብዙዎች ዘንድ ቀምራን እንደ ሆነች በምትታወቀው በ'የጨው ከተማ' ነው። ቀምራን የሙት ባሕር ጥቅልሉችን የጻፉ ሰዎች ይኖሩበት የነበረ ስፍራ ነው።

15፥63 *ኢያቡሳውያን፤* የይሁዳ ሰዎች በኢያቡሳውያን ከተማ ላይ የተቀዳጁት ድል በምሳ 1፥8 ላይ ተጠቅሶአል፤ ይሁን እንጂ ይህ ድል ከተማዋን እስከ ዘለቄታው እንዲይዙ አላስቻላቸውም። ብንያምም ሆነ ይሁዳ የኢያቡሳውያን ምሽግ የነበረችውን ኢየሩሳሌምን ለመያዝ አልቻሉም (መሳ 1፥21)።

*16፥1-17፥18፤* "ለዮሴፍ ቤት" (ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ የሰፈሩት ኤፍሬምና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ናቸው) በር ስትነት የተሰጠው መሬት በሁለቱ ምዕራፎች ውስጥ ተገልጾአል። ከይሁዳ ቀጥሎ ቅድሚያ የተሰጠው ለዮሴፍ ነገዶች ነው።

16፥1 *ለዮሴፍ ... የተመደበው ድርሻ፤* የያዕቆብ ዐሥራ አንደኛ ልጅ የሆነው ዮሴፍ፣ ርስቱ ለሁለቱ ልጆቹ ለኤፍሬምና ለምናሴ ስለ ተሰጠ (ዘፍ 48፥14-22)፣ በስሙ የሚጠራ ነገድ አልነበረውም። ስለዚህም፣ ኤፍሬምና ምናሴ ራሳቸውን የቻሉ ሁለት ነገዶች በመሆናቸው፣ የዮሴፍ ዘር የምድሪቱን ድርሻ የተካፈለው በእጥፍ ሊሆን ችሎአል።

16፥5 *ድንበሩ፤* የኤፍሬም ነገድ ርስት ሰሜናዊ ድንበር ኪታች ከዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ተነሥቶ በምዕራብ በኩል እስከ ሴሎ ከተማ ይደርሳል፤ ከሴኬም በስተ ደቡብ በኩል ደግሞ የዋዲ ቃናን ሸለቆ በመከተል እስከ ሜድትራኒያን ባሕር ድረስ ይዘልቃል።

16፥10 *ጌዝር፤* የ10፥33ን ማብ ይመ። ይሁን እንጂ የጕልበት ሥራም እንዲሠሩ ይገደዱ ነበር፤ ጌዝር ሰሎሞን እስከ ነገሠበት ጊዜ ድረስ በእስራኤላውያን እጅ የገባች አይመስልም (1ነገ 9፥15-16፤ እንዲሁም 2ሳሙ 5፥25 ይመ)።

17፥1 *ምናሴ የዮሴፍ የበኵር ልጅ፤* ምንም እንኳ ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች በማደጎነት ቢወስዳቸው ኤፍሬምን ቀዳሚ ቢያደርገውም (ዘፍ 48፥14፡19)፤ እዚህ ላይ የኤፍሬማውያንን ትዕቢት ለማስታወስ የምናሴ በኵርነት ተጠቅሶአል።

17፥3 *ሰለጰአድ ሴቶች ልጆች እንጂ ... አልነበሩትም፤* ሙሴ ከመሞቱ በፊት፣ እነዚህ ሴቶች ከዘመዶቻቸው ጋር ርስት

ኑዓ፣ ዔግላ፣ ሚልካ፣ ቲርጻ ይባላል::
4እነርሱም ወደ ካህኑ ወደ አልዓዛር፣ ወደ
ነዌ ልጅ ወደ ኢያሱና ወደ መሪዎቹ
ቀርበው፣ "ከወንድሞቻችን ጋር ርስት እን
ድንካፈል እግዚአብሔር ሙሴን አዞታል"
አሏቸው:: ስለዚህ ኢያሱ እግዚአብሔር ባዘ
ዘው መሠረት፣ ከአባታቸው ወንድሞች
ጋር ርስት ሰጣቸው:: 5ምናሴም ከገለዓድና
ከባሳን ምድር ሌላ፣ ዐሥር ቦታ የሚደለደል
የመሬት ክፍል በዮርዳኖስ ምሥራቅ ነበ
ረው፤ 6የምናሴ ነገድ ሴት ልጆች ከወንዶቹ
ጋር ርስት ተካፍለዋልና፤ የገለዓድ ምድር
ግን ለቀሩት የምናሴ ዘሮች ተሰጠ::
7የምናሴ ርስት ከአሴር አንሥቶ
ከሴኬም በስተ ምሥራቅ እስካለችው
እስከ ሚክምታት ይደርሳል፤ ድን
በሩም ወደ ደቡብ በመዝለቅ በዓ
ይንታጱዋ የሚኖረውን ሕዝብ ይጨ
ምራል:: 8የታጱዋ ምድር የምናሴ
ይዞታ ነበር፤ ይሁን እንጂ በድንበሩ
ላይ የምትገኘው የታጱዋ ከተማ
የኤፍሬም ዘሮች ይዞታ ነበረች፤
9ከዚያም በመቀጠል ድንበሩ በደ
ቡብ በኩል ወደ ቃና ወንዝ ይደር
ሳል:: በምናሴ ከተሞችም መካከል
የኤፍሬም ከተሞች ነበሩ፤ ያም ሆኖ
የምናሴ ድንበር የወንዙ ሰሜናዊ ክፍል
ሲሆን፣ እስከ ባሕሩ ይዘልቃል::
10በደቡብ በኩል ያለው ምድር የኤፍ
ሬም ሲሆን፣ በሰሜን በኩል ያለው
ደግሞ የምናሴ ነበር፤ የምናሴ ግዛት
እስከ ባሕሩ የሚደርስ ሲሆን፣ ሰሜ
ናዊ ድንበሩ አሴር፣ ምሥራቃዊ ድን
በሩ ደግሞ ይሳኮር ነው::
11እንዲሁም በይሳኮርና በአሴር
ውስጥ፤ ቤትሳን፣ ይብልዓም፣ የዶር
ሕዝብ፣ ዓይንዶር፣ ታዕናክና መጊዶ
በዙሪያቸው ካሉ ሰፈሮቻቸው ጋር
የምናሴ ነበሩ፤ ሦስተኛውም ናፎት
ነው[ሀ]::
12ይሁን እንጂ የምናሴ ዘሮች እነዚህን
ከተሞች መያዝ አልቻሉም፤ ከነዓናው
ያን የያዙትን ላለመልቀቅ ቍርጥ ሐሳብ
አድርገው ነበርና:: 13እስራኤላውያን በበ
ረቱ ጊዜ ግን ከነዓናውያንን የጕልበት
ሥራ እንዲሠሩ አስገደዷቸው እንጂ ከዚያ
ፈጽመው አላባረሯቸውም ነበር::
14የዮሴፍ ዘሮች ኢያሱን፣ "ቍጥራችን
ብዙ ነው፤ እግዚአብሔርም አብዝቶ ባርኮ
ናል፤ ታዲያ እንዴት ርስታችን አንድ ዕጣና
አንድ ድርሻ ብቻ ሆነ?" አሉት::
15ኢያሱም መልሶ፣ "ቍጥራችሁ ይህን
ያህል በዝቶ ኰረብታማው የኤፍሬም ምድር
እስከዚህ የሚጠባችሁ ከሆነ፣ ወደ ፌሬዛ
ውያንና ወደ ራፋይም ምድር ወጥታችሁ
ደኑን ለራሳችሁ መንጥሩ" አላቸው::
16የዮሴፍም ዘሮች፣ "ኰረብታማው አገር
አይበቃንም፤ደግሞም በሜዳው ላይ ያሉት
በቤትሳንና በሰፈሮችዋ፣ እንዲሁም በኢይዝ
ራኤል ሸለቆ የሚኖሩት ከነዓናውያን ሁሉ
የብረት ሠረገሎች አሏቸው" አሉት::
17ኢያሱ ግን ለዮሴፍ ዘሮች ለኤፍሬምና
ለምናሴ እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ ቍጥራ
ችሁ ብዙ፣ እጅግም ኀያል እንደመሆናችሁ
ድርሻችሁ አንድ ብቻ አይሆንም፤ 18ነገር
ግን ደን የለበሰው ኰረብታማው አገር የእና
ንተ ነው፤ ሂዱችሁ መንጥሩት፣ ዳር ድን
በሩ ሁሉ የእናንተ ይሆናል፤ ከነዓናውያን
የብረት ሠረገላ ቢኖራቸውና ብርቱዎች ቢሆ
ኑም እንኳ ከዚያ ታስወጧቸዋላችሁ::"

## የቀሪው ምድር መከፋፈል

18 መላው የእስራኤላውያን ማኅበር
በሴሎ ተሰበሰቡ፣ የመገናኛውንም
ድንኳን እዚያው ተከሉ፤ ምድሪቱም ጸጥ ብላ

[ሀ]11 ይኸውም ናፎት ዶር ነው::

17፥4 ዘኍ27፥5-7
17፥5 ኢሱ13፥30-31
17፥7 ቍ10፤ዘፍ12፥6፤ኢሱ16፥6፤19፥24:31፤21፥6:30፤21፥21፤24፥25፤መሳ1፥31፤5፥17፤6፥35፤7፥23፤9፥1
17፥8 ኢሱ12፥17
17፥9 ኢሱ16፥8
17፥10 ቍ7፤ዘፍ30፥18፤ሕዝ48፥5
17፥11 ቍ10:16፤ኢሱ11፥2፤12፥21፤መሳ1፥27፤1ሳሙ28፥7፤31፥10፤2ሳሙ21፥12፤1ነገ4፥12፤9፥15፤2ነገ9፥27፤1ዜና7፥29፤መዝ83፥10፤ሕዝ 48፥4
17፥12 ኢሱ15፥63
17፥13 መሳ1፥27-28
17፥14 ዘኍ26፥28-37
17፥15 ዘፍ14፥5፤ኢሱ3፥10፤15፥8፤18፥16፤2ሳሙ5፥18፤18፥6፤23፥13፤ኢሳ15፥8፤17፥5
17፥16 ቍ11:18፤ኢሱ15፥56፤መሳ1፥19፤4፥3:13፤1ሳሙ29፥1
17፥17 ሕዝ48፥5
17፥18 ቍ16፤1ሳሙ1፥1
18፥1 ቍ10:8፤9፤ዘፀ27፥21፤40፥2፤ኢሱ19፥51፤21፥2፤መሳ18፥31፤21፥12:19፤1ሳሙ1፥3፤3፥21፤4፥3፤1ነገ14፥2፤መዝ78፥60፤ኤር7፥12፤26፥6፤40፥2፤41፥5፤ሐሥ 7፥45

እንዲያገኙ ቃል ገብቶላቸው ነበር (ዘኍ26፥33፤ 27፥1-7 ይመ)::

17፥5 *ዐሥር ቦታ የሚደለደል የመሬት ክፍል፤* ከይሁዳ ቀጥሎ ሰፊ ይዞታ ያገኘው ምናሴ ነው:: ከዚያም ዐሥሩ የመሬት ክፍል ለአምስቱ ወንድማማቾችና (ከኦፌር በቀር) ለአምስቱ የኦፌር ሴቶች ልጆች ተሰጠ:: ወንድሞች የሌሏቸው ሴቶች ልጆች ርስት የመካፈል መብታቸው እንዴት እንደሚጠበቅ የሚናገረውን ሕግ በዘኍ 27፥8-11 ላይ ይመ::

17፥11 *ቤትሳን ... መጊዶ፤* እነዚህ ጠንካራና ኀይለኛ ምሽግ የነበራቸው ከተሞችና በምናሴ፣ በይሳኮርና በአሴር የጋራ ድንበር ላይ የሚገኙ ሌሎች ከተሞች ለብዙ ጊዜ በእስራኤላውያን አልተያዙም ነበር:: ንጉሥ ሳኦል በጦር ሜዳ ሲሞት፣ ድል አድራጊዎቹ ፍልስጥኤማውያን ሬሳውን በቤትሳን ከተማ ቅጥር ግንብ ላይ በምስማር ቸንከሩት (1ሳሙ 31፥10 ይመ)፤ ይህም፣ ከተማዋ ከፍልስጥኤማውያን ጋር የጋራ ስምምነት እንደ ነበራት ያሳያል::

17፥13 *እስራኤላውያን በበረቱ ጊዜ፤* ምናልባት የዳዊትንና የሰሎሞንን ዘመን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (የ16፥10 ማብ ይመ)::

17፥14 *የዮሴፍ ዘሮች ... "ቍጥራችን ብዙ ነው"፤* ኤፍሬምንና ምናሴን ማለት ነው (ቍ 17 ይመ):: ምንም እንኳ ለሁለቱ የዮሴፍ ልጆች የተከፋፈለው ርስት ለየብቻ ቢጠቀስም፣ (16፥5፤17፥11)፣ እዚህ ላይ ለዮሴፍ ነገዶች የተደለደለው ድርሻ እንደ አንድ ተወስዶአል (16፥1:4 ይመ)::

17፥15 *ኰረብታማው የኤፍሬም ምድር፤* በበኵር ልጁ ስም የሚጠራ የዮሴፍ ነገዶች ርስት ነው (የቍ 1ን ማብ ይመ):: *ደኑን ለራሳችሁ መንጥሩ፤* ይህ የከነዓን ምድር ክፍል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነበር:: እስራኤላውያን የተመደበላቸውን ርስት የሚመለከቱት ለእርሻና ለግጦሽ የሚሆን የተመነጠረ ቦታ ካላቸው የከተሞች ብዛት አኳያ እንጂ፣ ከተሞቹ ከሚገኙበት ክልል ስፋት አንጻር አይመስልም:: ለዮሴፍ ነገዶች የተመደበላቸው ርስት በዚያን ጊዜ እንደ ሌሎቹ ነገዶች ርስት ብዙ ሕዝብ አልሰፈረበትም ነበር:: *ፌርዛውያንና ... ራፋይም፤* ምንም እንኳ ፌርዛውያን በከነዓን ምድር በስተ ምዕራብ በሚገኘው የዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ (3፥10፤12፥8)፣ የራፋይም ሰዎች ደግሞ ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ባለው በባ ግዛት ይኖሩ እንደ ነበር ቢታወቅም (12፥4፤ 13፥12)፣ እዚህ ላይ የተጠቀሱት እንደ ጎረቤት ሕዝብ ነው:: የዘፍ 13፥17ን፤ የዘዳ 2፥11 ማብ ይመ::

17፥16 *በሜዳው ላይ፤* የጦር ሠረገሎች ማገልገል የሚችሉት ሜዳማ በሆነ ቦታ ላይ ብቻ ነው:: *የብረት ሠረገሎች፤* የሠረገላው አንዳንድ ክፍሎች የተሠሩት ከብረት ነው (የ2ሳሙ 8፥7 ማብ ይመ)፤ ምናልባትም የሠረገላው አግዳሚ ብረት የተሠራው ከብረት ሊሆን ይችላል:: ከብረት በተሠሩ ነገሮች መጠቀም በዚያን ጊዜ አዲስ ግኝት ነበር (የ11፥6 ማብ ይመ)::

*18፥1-19፥51፤* ርስት ሊደለደልላቸው የቀሩ ሰባት ነገዶች:- ብንያም፣ ስምዖን፣ ዛብሎን፣ ይሳኮር፣ አሴር፣ ንፍታሌምና ዳን ናቸው:: ለእነዚህ ነገዶች በሴሎ ዕጣ የተጣለው ለኢያሱ የተለየ ርስት ከተሰጠው በኋላ ነው::

18፥1 *ሴሎ፤* ከቤቴል ሰሜን ምሥራቅ 16 ኪ.ሜ. ያህል ርቀት ላይ፣ ከቤቴል ወደ ሴኬም በሚወስደው አውራ መንገድ ወደ ምሥራቅ ትንሽ ወጣ ብሎ የሚገኝ ከተማ ነው:: *የመገናኛውንም ድንኳን፤*

ተገዛችላቸው:: 2ዳሩ ግን ርስት ገና ያልተሰጣ
ቸው ሰባት የእስራኤል ነገዶች ነበሩ::
3ስለዚህ ኢያሱ እስራኤላውያንን እንዲህ
አላቸው፤ "የአባቶቻችሁ አምላክ *እግዚአብ
ሔር* የሰጣችሁን ምድር ለመውረስ ቸል
የምትሉት እስከ መቼ ነው? 4አሁንም ከእ
ያንዳንዱ ነገድ ሦስት ሦስት ሰው ምረጡ፤
እኔም ምድሪቱን ተዘዋውረው እንዲያጠኑና
እያንዳንዱም ነገድ መውረስ የሚገባውን
ድርሻ ዝርዝር መግለጫ ጽፈው እንዲ
ያመጡ እልካቸዋለሁ፤ ከዚያም ወደ እኔ
ይመለሳሉ:: 5ምድሪቱንም ሰባት ቦታ ይከፍ
ሏታል፤ ይሁዳ በደቡብ፣ የዮሴፍ ዘሮች
በሰሜን በኩል የተመደበላቸውን ርስት ይዘው
ይኖራሉ:: 6የሰባቱን የመሬት ክፍፍል ዝር
ዝር መግለጫ ጽፋችሁ ወደኔ ታመጡና በአ
ምላካችን *በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ* እጥልላ
ችኋለሁ:: 7ሌዋውያኑ ግን *ለእግዚአብሔር*
የሚሰጡት የክህነት አገልግሎት ርስታቸው
ስለ ሆነ በእናንተ መካከል ድርሻ አይኖራቸ
ውም፤ ጋድ፣ ሮቤልና የምናሴ ነገድ እኩሌ
ታም *የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴ በምሥራቅ
ዮርዳኖስ የሰጣቸውን ርስት ቀደም አድር
ገው ወስደዋል::"
8ሰዎቹ የምድሪቱን ሁኔታ ለማጥናትና
ለመመዝገብ ጉዞ ሲጀምሩ ኢያሱ፣ "ሂዱ
ችሁ የምድሪቱን ሁኔታ አጥኑና በዝርዝር
ከጻፋችሁ በኋላ ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም
እዚሁ ሴሎ *በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ* እጥልላ
ችኋለሁ" አላቸው:: 9ስለዚህም ሰዎቹ ሄደው
ምድሪቱን ተዘዋውረው አዩ፤ ከነከተሞቿም
ሰባት ቦታ ከፍለው በጥቅልል ብራና ላይ በዝ
ርዝር ጻፉ፤ ከዚያም በሴሎ ሰፈር ወዳለው
ወደ ኢያሱ ተመለሱ:: 10ኢያሱም በሴሎ *በእግ
ዚአብሔር ፊት ዕጣ* ጣለላቸው፤ ምድሪቱ
ንም እንደየነገዱ ደልድሎ ለእስራኤላው
ያን አከፋፈላቸው::

## ለብንያም ነገድ የተመደበው ድርሻ

11ለብንያም ነገድ የሆነው የመጀመሪ
ያው ዕጣ በየጐሣ በየጐሣው ወጣ፤ በዕጣ
የደረሳቸውም ምድር የሚገኘው በይሁዳና
በዮሴፍ ነገዶች ርስት መካከል ሲሆን እንደ
ሚከተለው ነው፤
12በሰሜን ያለው ድንበራቸው ከዮር
ዳኖስ ይነሣና የኢያሪኮን ሰሜናዊ ተረ
ተር አልፎ፣ በስተ ምዕራብ ወዳለው
ኰረብታማ ምድር በማምራት፣ እስከ
ቤትአዌን ምድረ በዳ ይዘልቃል::
13ከዚያ ደግሞ ወደ ደቡብ ሎዛ ማለት
ወደ ቤቴል ተረተር ይሻገርና በታች
ኛው ቤትሖሮን በስተ ደቡብ ባለው
ተራራ በኩል አድርጎ ወደ አጣሮት
አዳር ይወርዳል::
14በስተ ደቡብ ያለው ድንበር ከቤት
ሖሮን ትይዩ ካለው ኰረብታ ተነ
ሥቶ፣ በምዕራብ በኩል ወደ ደቡብ
በመታጠፍ፣ የይሁዳ ነገድ ከተማ ወደ
ሆነችው ወደ ቂርያትበኣል ማለት
ወደ ቂርያትይዓሪም ያልፋል፤ ይህ
እንግዲህ በምዕራብ በኩል ያለው ድን
በር ነው::
15በስተ ደቡብ ያለው ድንበር ደግሞ
በምዕራብ በኩል ከቂርያትይዓሪም
ጥግ ይነሣና እስከ ነፍቶ ውሃ ምንጭ
ይዘልቃል፤ 16ይኸው ድንበር ከራፋ
ይም ሸለቆ በስተ ሰሜን ባለው በሄ
ኖም ሸለቆ ትይዩ ቍልቍል ወደ
ኰረብታው ግርጌ ይወርዳል፤ ከዚ
ያም ከኢያቡሳውያን ከተማ በደ
ቡብ በኩል ባለው ተረተር አድርጎ
ወደ ሄኖም ሸለቆ በመውረድ እስከ
ዓይንሮጌል ይዘልቃል:: 17ደግሞም
ወደ ሰሜን ይታጠፍና በቤት ሳሚስ
በኩል አድርጎ እስከ ጌሊሎት ይዘ
ልቃል፤ ከዚያም በአዱ ሚም መተ
ላለፊያ ትይዩ እስካለው እስከ ሮቤል
ልጅ እስከ ቦሀን ድን ጋይ ይወር
ዳል:: 18ወደ ቤትዓረባ ሰሜናዊ ተረ
ተር በመቀጠል ቍልቍል ወደ ዐረባ
ይወርዳል:: 19ከዚያም ሰሜናዊን የቤት
ሖግላንን ተረተር አልፎ ይሄድና በስተ
ደቡብ የዮርዳኖስ ወንዝ እስከሚገባ
በት እስከ ሙት ባሕር ወሽመጥ
ይዘልቃል፤ ይህም ደቡባዊ ድንበሩ
ነው::
20በምሥራቅ በኩል ያለው ድንበር፣
ራሱ የዮርዳኖስ ወንዝ ነው::
ይህ እንግዲህ የብንያም ነገድ ጐሣዎች
በርስትነት የወረሷት ምድር ዳር ድንበሮቿ
ሁሉ እነዚህ ነበሩ::
21የብንያም ነገድ በየጐሣቸው የያዟቸው ከተ
ሞች እነዚህ ናቸው፤
ኢያሪኮ፣ ቤትሖግላ፣ ዓመቀጺጽ፣
22ቤት ዓረባ፣ ዘማራይም፣ ቤቴል፣ 23ዓዊም፣

18፥4 ቍ8፤ሚክ 2፥5
18፥5 ኢሱ15፥1፤ 16፥1-4
18፥6 ዘሌ16፥8
18፥7 ኢሱ13፥8:33
18፥8 ቍ1:4
18፥10 ቍ1፤ዘኍ 33፥54፤34፥13፤ኢሱ 19፥51፤ኤር7፥12
18፥12 ኢሱ7፥2፤ 8፥15
18፥13 ዘፍ28፥19፤ ዘኍ32፥3፤ኢሱ 12፥9፤16፥5
18፥14 ኢሱ9፥ 17፤10፥10
18፥15 ኢሱ15፥9
18፥16 ኢሱ15፥7: 8፤17፥15
18፥17 ኢሱ፤15፥6: 7፤22፥10
18፥18 ኢሱ11፥2፤ 15፥6
18፥19 ዘፍ14፥3፤ ኢሱ15፥6
18፥20 1ሳሙ9፥1
18፥21 ኢሱ15፥6
18፥22 ኢሱ15፥6፤ 16፥1፤2ዜና13፥4
18፥23 ዘዳ2፥23፤መሳ 6፥11:24፤8፥27:32፤9 ፥5፤1ሳሙ13፥17

የማደሪያውን ድንኳንና (የዘዳ 27፥21 ማብ ይመ) የኪዳኑን ታቦት ማለት ነው:: የመገናኛው ድንኳን እስከ ሳሙኤል ዘመን ድረስ በሴሎ ተቀምጦ ነበር (1ሳሙ 4፥3)::

18፥3 *ለመውረስ፤* ከድል በኋላ ሰፈራ መቀጠል ነበረበት፤ ይህም በመጀመሪያ ጥናት ማድረግን፣ ከዚያም ተገቢ የሆነ ድልድል ማካሄድን፣ ቀጥሎም ምድሪቱን ሙሉ በሙሉ መያዝን ያጠቃልላል:: ነገር ግን በብሔራዊ ጦርነትና (ኢያሱ) በነገድ ጦርነት (መሳ 1-2) መካከል ልዩነት እንዳለ መታወቅ አለበት::

18፥5 *በሰሜን፤* ከይሁዳ ምድር አንጻር ነው::

18፥6 *ዕጣ እጥልላችኋለሁ፤* የ14፥1 ማብ ይመ::

18፥7 *ለእግዚአብሔር የሚሰጡት የክህነት አገልግሎት ርስታቸው ስለ ሆነ፤* 13፥14፤ እንዲሁም ዘዳ 18፥1-8 እና የዘዳ 18፥1 ማብ ይመ::

18፥9 *ጥቅልል ብራና፤* መዛግብት የሚቀመጡት በዚህ መልክ ሳይሆን አይቀርም፤ ይሁን እንጂ ይህን ሐረግ ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም የተወሰነ ነገርን የሚያመለክት አይደለም::

18፥11 *ለብንያም ... ዕጣ፤* በሁለቱ ኀያላን ነገዶች ማለትም በይሁዳና በኤፍሬም መካከል የሚገኝ ቀጣና ነው:: ይህ ቀጣና በሰሜን በኩል ከኤፍሬም ደቡባዊ ድንበር ጋር አንድ ሲሆን (የ16፥1 ማብ ይመ)፣ በደቡብ በኩል ያለው ድንበር ደግሞ ከይሁዳ አብዛኛው ሰሜናዊ ድንበር ጋር አንድ ነው (የ15፥5 ማብ ይመ)::

18፥23 *ዓዊም፤* የጋይ ሰዎች ማለት ነው::

ፋራ፣ ኤፍራታ፣ [24]ክፊርዓሞናይ፣ ዖፍኒ
እንዲሁም ጋባ ናቸው፤ እነዚህም ከነመን
ደሮቻቸው ዐሥራ ሁለት ከተሞች ናቸው።
[25]ገባዖን፣ ራማ፣ ብኤሮት፣ [26]ምጽጳ፣
ከፊራ፣ አሞቂ፣ [27]ሬቄም፣ ይርጵኤል፣
ተርአላ፣ [28]ጼላ፣ ኤሌፍ፣ የኢያቡሳው
ያን ከተማ ኢየሩሳሌም፣ ጊብዓ እንዲ
ሁም ቂርያት ነበሩ፤ እነዚህም ከነመንደ
ሮቻቸው ዐሥራ አራት ከተሞች ናቸው።
እንግዲህ የብንያም ነገድ በየጐሣቸው የወ
ረሱት ይህ ነበር።

### ለስምዖን ነገድ የተመደበው ድርሻ

19፥2-10 ተጓ ምብ-1 ዜና 4፥28-33

**19** ሁለተኛው ዕጣ ለስምዖን ነገድ በየ
ጐሣ በየጐሣው ወጣ፤ ርስታቸውም
ዙሪያውን በይሁዳ ነገድ ርስት የተከበበ
ነበር፤ [2]ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፤
ቤርሳቤህ፣ ሼባ፣ ሞላዳ፣ [3]ሐጸር
ሹዓል፣ ባላ፣ ዔጼም፣ [4]ኤልቶላድ፣
በቱል፣ ሔርማ፣ [5]ጺቅላግ፣ ቤትማርካ
ቦት፣ ሐጸርሱሳ፣ [6]ቤተ ለባኦትና ሻሩሔን
ነበሩ፤ እነዚህ ዐሥራ ሦስት ከተሞችና
መንደሮቻቸው ናቸው።
[7]ዓይን፣ ሪሞን፣ ዔቴርና ዓሻን የተባ
ሉት አራት ከተሞቻቸውና መንደሮቻ
ቸው፣ [8]ደግሞም እስከ ባዕላትብኤር ወይም
ኔጌብ ውስጥ እስካለው እስከ ራማት
ድረስ ባሉት ከተሞች ዙሪያ የሚገኙት
መንደሮች ሁሉ ከእነዚሁ ጋር ይጠ
ቃለላሉ።
እንግዲህ በየጐሣው የተደለደለው የስም
ዖን ነገድ ርስት ይህ ነበር። [9]የይሁዳ ነገድ
የያዘው ርስት እጅግ ሰፊ ስለ ነበር፣ ከይ
ሁዳ ነገድ ድርሻ ተከፍሎ ለስምዖን ነገድ
በርስትነት ተሰጠ ፤ ከዚህ የተነሣም የስም
ዖን ነገድ በይሁዳ ነገድ ድርሻ ርስት ሊካ
ፈል ቻለ።

### ለዛብሎን ነገድ የተመደበው ድርሻ

[10]ሦስተኛው ዕጣ ለዛብሎን ነገድ በየጐሣ
በየጐሣው ወጣ፤
የርስታቸውም ድንበር እስከ ሣሪድ
ይደርሳል፤ [11]ወደ ምዕራብም በመሄድ
በመርዓላ በኩል ያልፋል፤ ደባሼትን
ተጠግቶም በዮቅንዓም አጠገብ እስካ
ለው ወንዝ ድረስ ይዘልቃል። [12]ከሣሪ
ድም ወደ ምሥራቅ በመታጠፍ፣ የፀ
ሓይ መውጫ ወደ ሆነው አገር ወደ
ኪስሎትታቦር በመዝለቅ እስከ ዳብራት
ሄዶ ወደ ያፊዓ ያቀናል፤ [13]ከዚያም
ወደ ምሥራቅ በመቀጠል፤ ወደ ጋትሔ
ፍርና ወደ ዒትቃጺን ይዘልቃል፤ ከዚያ
ደግሞ ወደ ሪሞን በመሄድ፣ ወደ ኒዓ
ይታጠፋል። [14]በስተ ሰሜንም በኩል
ወደ ሐናቶን ይዞርና በይፍታሕ
ኤል ሸለቆ ላይ ይቆማል። [15]ደግ
ሞም ቀጣትን፣ ነህላልን፣ ሺምሮ
ንን፣ ይዳላንና ቤተ ልሔምን
ይጨምራል፤ እነዚህም ከነመንደሮቻ
ቸው ዐሥራ ሁለት ከተሞች ናቸው።
[16]እነዚህ ሁሉ ለዛብሎን ነገድ ርስት ሆነው
ለየጐሣ ለየጐሣው የተደለደሉ ከተሞችና
መንደሮቻቸው ነበሩ።

### ለይሳኮር ነገድ የተመደበው ድርሻ

[17]አራተኛው ዕጣ ለይሳኮር ነገድ በየጐሣ
በየጐሣው ወጣ፤ [18]ምድራቸውም የሚከ
ተሉትን ያካትታል፤
ኢይዝራኤል፣ ከስሎት፣ ሱነም፣
[19]ሐፍራይም፣ ሺኦን፣ አናሐራት፣
[20]ረቢት፣ ቂሶን፣ አቤጽ፣ [21]ሬሜት፣
ዐይንጋኒም፣ ዐይንሐዳ እንዲሁም
ቤትጳጼጽ። [22]ድንበራቸውም ታቦ
ርና፣ ሻሕጹማን፣ ቤትሳሚስን ይነ
ካና በዮርዳኖስ ላይ ያቆማል፤ እነዚህ
ከነመንደሮቻቸው ዐሥራ ስድስት
ከተሞች ናቸው።
[23]እነዚህ ለይሳኮር ነገድ ርስት ሆነው
ለየጐሣ ለየጐሣው የተደለደሉ ከተሞችና
መንደሮቻቸው ነበሩ።

### ለአሴር ነገድ የተመደበው ድርሻ

[24]አምስተኛ ዕጣ ለአሴር ነገድ በየጐሣ
በየጐሣው ወጣ፤ [25]ምድራቸውም የሚከተ
ሉትን ያካትታል፤
ሔልቃት፣ ሐሊ፣ ቤጤን፣ አዚፍ፣
[26]አላሜሌክ፣ ዓምዓድ እንዲሁም ሚሽ
አል። ድንበሩ በስተ ምዕራብ ቀርሜ
ሉስንና ሺሖርሊብናትን ይነካል፣
[27]ከዚያም በምሥራቅ በኩል ወደ
ቤት ዳጎን ይመለስና ዛብሎንንና የይ
ፍታሕኤልን ሸለቆ ይዞ ካቡልን
በስተ ግራ በመተው በሰሜን በኩል
ወደ ቤትዔሜቅና ወደ ንዒኤል
ይቃናል። [28]በመቀጠልም ወደ ዔብ
ሮን*፣ ወደ ረአብ፣ እንዲሁም ወደ
ሐሞንና ወደ ቃና ሸቅብ ወጥቶ
እስከ ታላቁ ሲዶና ይደርሳል። [29]ድን
በሩ ወደ ራማ ከዞረ በኋላ ወደ ተመ
ሸገው ወደ ጢሮስ ከተማ ታጥፎ ወደ

*28 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጂዎች ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ ነገር ግን ጥቂት ቅጂዎች ኢሱ21:30 ይመ፣ አብዶን ይላሉ።

18፥24 ኢሱ21፥17፤ 1ሳሙ13፥3:16፤ 14፥5፤1ነገ15፥22፤ 2ነገ23፥8፤ኢሳ10፥29
18፥25 ኢሱ9፥3: 17፤10፥40፤መሳ4፥5፤ 19፥13፤1ሳሙ1፥1:19 ፤2፥11፤7፥17፤25፥1፤ 1ነገ15፥17:21፤ዕዝ 2፥25:26፤ነህ7፥29፤1 1፥33፤ኢሳ10፥29፤ ኤር31፥15፤40፥1
18፥26 ኢሱ9፥17፤ 11፥3፤ዕዝ 2፥25፤ ነህ7፥29
18፥28 ኢሱ9፥17፤ 10፥1፤15፥8:57፤2ሳሙ 21፥14፤ሕዝ 48፥23
19፥1 ዘፍ49፥7
19፥2 ዘፍ21፥14፤ ኢሱ15፥26፤1ነገ19፥3
19፥3 ኢሱ15፥28:29
19፥4 ዘኍ14፥ 45፤ኢሱ15፥30
19፥5 ኢሱ15፥31
19፥7 ኢሱ15፥32:42
19፥8 ኢሱ10፥40
19፥9 ዘፍ49፥7፤ሕዝ 48፥24
19፥10 ቍ12:16: 27:34፤ኢሱ21፥7:34፤
19፥11 ኢሱ12፥22
19፥12 ቍ10፤ኢሱ 21፥28፤1ዜና6፥72
19፥13 ኢሱ11፥22፤ 15፥32
19፥14 ቍ27
19፥15 ዘፍ35፥19፤ ኢሱ11፥1፤21፥35
19፥16 ቍ10፤ሕዝ 48፥26
19፥17 ዘፍ30፥18
19፥18 ኢሱ15፥56፤ 1ሳሙ28፥4፤1ነገ1፥3፤ 2ነገ4፥8
19፥20 ኢሱ21፥28
19፥21 ኢሱ15፥34
19፥22 ኢሱ15፥10፤ መሳ4፥6:12፤8፥18፤ መዝ89፥12፤ኤር46፥18
19፥23 ዘፍ49፥15፤ ኢሱ17፥10፤ሕዝ48፥ 25
19፥24 ኢሱ17፥7
19፥25 ኢሱ11፥1
19፥26 ኢሱ12፥22፤ 21፥30፤1ነገ18፥19፤ 2ነገ2፥25
19፥27 ቍ10:14፤ ኢሱ15፥41፤1ነገ9፥13
19፥28 ቍ30፤ዘፍ 10፥19፤ዘኍ13፥21፤ኢሱ 16፥8፤21፥30፤መሳ1፥ 31፤1ዜና6፥74:76
19፥29 ኢሱ15፥44፤ 18፥25፤መሳ5፥17፤ 2ሳሙ5፥11፤24፥7፤ ዕዝ3፥7፤መዝ45፥ 12፤ኢሳ23፥1፤ኤር

19፥1 *ሁለተኛው ዕጣ ለስምዖን ...፤* በይሁዳ ድንበር (15፥21) በኔጌብ በይሁዳ ደቡባዊ ድንበር ውስጥ የሚገኙ ከተሞች ናቸው (1ዜና 4፥24-42)።

19፥10 *ሦስተኛው ዕጣ ለዛብሎን ...፤* ለዚህ ነገድ የደረሰው ከገሊላ ባሕር በስተ ምዕራብ በኩል የሚገኘው ታችኛው የገሊላ ክፍል ወይም በአዲስ ኪዳን በናዝሬት አውራጃ ውስጥ የሚገኘው ክፍል ነው።

19፥17 *አራተኛው ዕጣ ለይሳኮር ...፤* ከገሊላ ባሕር በስተ ደቡብ ምዕራብ በኩል የሚገኝና እስከ ቤትሳንና በስተ ምዕራብ በኩል እስከ ኢይዝራኤል ሸለቆ ይደርሳል። በሰሜን በኩል ላለው ወሰን ደግሞ ምልክቱ ደብረ ታቦር ተራራ ነው።

19፥24 *አምስተኛው ዕጣ ለአሴር ...፤* ለአሴር የተሰጠው ርስት በባሕር ጠረፍ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን፣ በስተ ሰሜን በኩል በፊንቄ እስከምትገኘው እስከ ሲዶና፣ በስተ ደቡብ በኩል ደግሞ እስከ ቀርሜሎስ ተራራ ይደርሳል።

ሖሳ ይመለስና በአክዚብ በኩል
ሜድትራኒያን ባሕር ደርሶ ይቆማል፤
30ይህም የዑማን፣ የአፌቅንና የረአ
ብን ምድር ይጨምራል፡፡ በዚህም
ሃያ ሁለት ከተሞችና መንደሮቻ
ቸው ይገኛሉ፡፡
31እነዚህ ለአሴር ነገድ ሆነው በየጐ
ሣው የተደለደሉ ከተሞችና መንደሮቻ
ቸው ነበሩ፡፡

### ለንፍታሌም ነገድ የተመደበው ድርሻ

32ስድስተኛው ዕጣ ለንፍታሌም ነገድ በየ
ጐሣ በየጐሣው ወጣ፤
33ድንበራቸውም ከሔሌፍና በጻዕነ
ኒም ካለው ከትልቁ የወርካ ዛፍ ይነ
ሣና በአዳሚኔቄብና በየብኒኤል አልፎ
ወደ ለቁም በመምጣት ዮርዳኖስ ላይ
ይቆማል፤ 34ድንበሩ በአዝኖት ታቦር
ያልፍና ወደ ምዕራብ በመታጠፍ ሑቆቅ
ላይ ይቆማል፤ ይኸው ድንበር በደ
ቡብ ዛብሎንን፣ በምዕራብ አሴርን፣
በምሥራቅ ዮርዳኖስን ይነካል[ጎ]፡፡ 35የተ
መሸጉትም ከተሞች እነዚህ ናቸው፤ ጺዲ
ም፣ ጼር፣ ሐማት፣ ረቃት፣ ኬኔሬት፣
36አዳማ፣ ራማ፣ አሶር፣ 37ቃዴስ፣ ኤድራይ፣
ዐይንሐጾር፣ 38ይርኦን፣ ሚግዳልኤል፣
ሖሬም፣ ቤትዓናትና ቤትሳሚስ፡፡ እነዚህ
ከነመንደሮቻቸው ዐሥራ ዘጠኝ ከተሞች
ናቸው፡፡
39እነዚህ ለንፍታሌም ነገድ ርስት ሆነው በየጐ
ሣው የተደለደሉ ከተሞችና መንደሮች ነበሩ፡፡

### ለዳን ነገድ የተመደበው ድርሻ

40ሰባተኛው ዕጣ ለዳን ነገድ በየጐሣው
ወጣ፤ 41የወረሱትም ምድር የሚከተሉትን
ያካትታል፤
ጾርዓ፣ ኤሽታኦል፣ ዒርሼሜሽ፣
42ሸዕለቢን፣ ኤሎን፣ ይትላ፣ 43ኤሎን፣
ተምና፣ አቃሮን፣ 44ኢልተቄ፣ ገባቶን፣
ባዕላት፣ 45ይሁድ፣ ብኔብረቅ፣ ጋትሪ
ሞን፣ 46ሜያርቆንና በኢዮጴ ፊት ለፊት
ያለው ርቆን፡፡
47ነገር ግን የዳን ዘሮች ርስታቸው አልበ
ቃቸውም፣ ወደ ሌሼም ወጥተው አደጋ
በመጣል ያዟት፤ ሰዎቹንም በሰይፍ ስለት
ፈጅተው ይዞታቸው አደረጓት፤ በዚያው
ሰፈሩ፤ ስሟንም ለውጠው በአባታቸው ስም
ዳን አሏት፡፡
48እነዚህ ለዳን ነገድ ርስት ሆነው በየጐሣው
የተደለደሉ ከተሞችና መንደሮች ነበሩ፡፡

### ለኢያሱ የተመደበው ድርሻ

49እስራኤላውያን ድርሻ ድርሻቸውን ከያዙ
በኋላ፣ ለነዌ ልጅ ለኢያሱ በመካከላቸው
ርስት ሰጡት፤ 50እግዚአብሔር ባዘዘውም
መሠረት በኰረብታማው የኤፍሬም ምድር
የምትገኘውን ተምናሴራ የምትባለውን የፈ
ለጋትን ከተማ ሰጡት፤ እርሱም ከተማዪቱን
ሠራ፤ መኖሪያውም አደረጋት፡፡
51እንግዲህ ካህኑ አልዓዛር፣ የነዌ ልጅ ኢያ
ሱና የእስራኤል ነገድ የየጐሣ መሪዎች ሴሎ
ላይ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ፣ በእግዚ
አብሔር ፊት ዕጣ ያደላደሉት ርስት ይህ
ነው፤ የምድሪቱንም አከፋፈል በዚህ ሁኔታ
ፈጸሙ፡፡

### የመማጠኛ ከተሞች

20፥1-9ማመ-ዘኍ35፥9-34፤ዘዳ4፥41-43፤19፥1-14

20 ከዚያም እግዚአብሔር ኢያሱን እን
ዲህ አለው፤ 2"በሙሴ በኩል በነገር
ኋችሁ መሠረት የመማጠኛ ከተሞች እንዲ
ለዩ ለእስራኤላውያን ንገራቸው፤ 3ሳያስበው
ድንገት ሰው የገደለ ማንኛውም ሰው ወደ
ዚያ በመሸሽ ከደም ተበቃዩ እንዲያመልጥ
ከተማዪቱ መጠለያ ትሁን፡፡

25፥22፤ሕዝ26፥2
19፥30 ቍ28፤ኢሱ 12፥18
19፥31 ዘፍ30፥13፤ ኢሱ17፥7፤ሕዝ48፥2
19፥33 ኢሱ15፥11፤ መሳ4፥11
19፥34 ቍ10፤1ዜና 6፥75
19፥35 ኢሱ11፥2፤ 1ዜና2፥55
19፥36 ኢሱ11፥ 1፤18፥25
19፥37 ዘኍ21፥33፤ ኢሱ12፥22
19፥38 ኢሱ15፥10፤ መሳ1፥33
19፥39 ሕዝ48፥3
19፥41 ኢሱ15፥33
19፥42 ኢሱ10፥12
19፥43 ዘፍ38፥12፤ ኢሱ13፥3
19፥44 ኢሱ21፥23፤ 1ነገ9፥18፤15፥27፤16 ፥15፤2ዜና8፥6
19፥45 ኢሱ21፥24፤ 1ዜና6፥69
19፥46 2ዜና2፥ 16፤ዕዝ3፥7፤ዮና 1፥3፤ሐሥ9፥36
19፥47 ዘዳ3፥14፤መ ሳ 18፥1፡7፡14፡27፡29
19፥48 ዘፍ30፥6
19፥50 ኢሱ24፥30፤ መሳ2፥9
19፥51 ኢሱ14፥1፤ 18፥10፤23፥10፤ ሐሥ13፥19
20፥3 ዘሌ4፥2፤ ዘኍ35፥12
20፥4 ዘፍ23፥10፤ ኢሱ7፥6፤ኤር38፥7
20፥6 ዘኍ35፥12
20፥7 ዘፍ12፥6፤35፥ 27፤ኢሱ10፥36፤

[ጎ]34 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ነገር ግን የዕብራይስጡ ቅጅ *ምስራቅ ይሁዳንና ዮርዳኖስን፤* ይላል፡፡

19፥32 *ስድስተኛው ዕጣ ለንፍታሌም፤* በአብዛኛው ከገሊላ ባሕር በስተ ሰሜን የሚገኝ ስፍራ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ሁሌሕ ተብሎ የሚጠራውን ሸለቆና በስተ ምዕራብ በኩል ያለውን የአሴርን ምድር ያካትታል፡፡ ደቡባዊ ጫፉም ከገሊላ ባሕር ታችኛው ጫፍ ጋር ይጋጠማል፡፡

19፥40 *ሰባተኛው ዕጣ ለዳን ...፤* በኤፍሬምና በይሁዳ እንዲሁም በምዕራብ የብንያም ምድር መካከል የሚገኝና የደጋን ቅርጽ ያለው ምድር ነው፡፡ በስተ ሰሜን ምዕራብ በኩል የሚገኘው የዳን ምድር እስከ ኢዮጴ ወደብ ይደርሳል፡፡

19፥47 *የዳን ዘሮች ... ችግር ገጥሞአቸው ስለ ነበር፤* በዚህ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ አሞራውያን፣ "የዳን ነገድ በኰራብታማው ምድር ብቻ እንዲወሰን ወደ ሜዳው አገር እንዲወርድ... አልፈቀዱለትም" (መሳ 1፥34)፤ በዚህም ምክንያት ከነገዶቹ ብዙ ዎቹ ወደ ላይኛው የዮርዳኖስ ሸለቆ ፈለሱ፤ በዚያም ሌሳ የተባለ ችውን ከተማ ያዙ (መሳ 18፥2-10፡27-29)፤ ስሟንም ቀይረው ዳን አሏት፡፡

19፥49 *ለኢያሱ ... ርስት ሰጡት፤* የተስፋዋን ምድር (ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ የሚገኘውን ምድር) አከፋፈል ወይም አመዳደብ በሚያወሳው ክፍል ውስጥ ለካሌብ ስለ ተመደ በው ርስት የተነገረው በመጀመሪያ ሲሆን (14፥6-15)፣ ለኢያሱ ስለ ተመደበው ርስት የተነገረው ደግሞ በመጨረሻ ነው፡፡ እንግዲህ ከምድረ በዳው ትውልድ ለተገኙት ለእነዚህ ሁለት የእግዚአብሔር አገልጋዮች የተመደበው ርስት (ዘኍ 13፥30፤ 14፥6፡24፡30 ይመ) ለየነገዱ የተሰጠው ርስት እንዴት እንደ ተከፋፈለ የሚያወሳውን ታሪክ (14፥6-19፥49) ያካትታል፤ ሁለ ቱም የጠየቁትን ርስት አግኝተዋል፡፡ ለኢያሱ ርስት የተመደ በለት ከሁሉ መጨረሻ መሆኑ ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ኢያሱ ንጉሥ ወይም የጦር አዛዥ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ተስፋዪቱ ምድር መርቶ እንዲያገባ የተሾመ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው፡፡

19፥50 *ተምናሴራ፤* በኤፍሬም ምድር በስተ ደቡብ ምዕ ራብ በኩል በባሕሩ ትይዩ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ ኢያሱም የተቀበ ረው በዚህ ቦታ ነው (24፥30)፡፡

*20፥1-9፤* እግዚአብሔር ምድሪቱን ለየነገዶቹ ካከፋፈለ በኋላ፣ ከዚህ ቀጥሎ የሚሰጣቸው መመሪያ በተለይ የነፍስ ግድያ ወንጀል እንዳይስፋፋ የሚከላከሉ የፍትሕ አካላት በየክልሉ እንዲ መሠረቱ የሚያስችል የአስተዳደር ሥርዐት እንዲኖር (የ13፥1-32 ማብ ይመ) ነው፡፡ ይህም ፍትሕ እንዳይዛባና በምድሪቱም ደም አፍሳሽ እንዳይኖር ይከላከላል፡፡ የተመረጡት ከተሞች ለሌዋው ያን ከተመደቡት፣ የሙሴ ሕግ ከሚታወቅባቸውና ከሚከበርባ ቸው ከተሞች መካከል ነው፡፡

20፥2 *በሙሴ በኩል በነገርኋችሁ መሠረት፤* ዘኍ 35፥6-34 ይመ፡፡

20፥3 *ከደም ተበቃዩ፤* "ዋርሳ" (ሩት 3፥9) ወይም "መድኃኒት" ተብሎ (መዝ 19፥14) ሊተረጕም ይችላል፡፡ ተበቃይ ይሆን የነበረው የሚሰጠውን ኀላፊነት በሚገባ የሚወጣ የሚቅ የቅርብ ዘመድ ነው (ዘሌ 24፥17፤ ዘኍ 35፥16-28 ይመ)፡፡

[4]“ገዳዩ ከነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ
በሚሸሽበት ጊዜ፣ በከተማዪቱ መግቢያ
በር ላይ ቆሞ ጕዳዩን ለከተማዪቱ ሽማግ
ሌዎች ይንገራቸው፤ ከዚያም እነርሱ ወደ
ከተማቸው አስገብተው የሚኖሩበትን ስፍራ
ሰጥተውት አብሮአቸው ይቀመጥ:: [5]ደም
ተበቃዩ ተከታትሎት ቢመጣ፣ ሆን ብሎና
በክፋት ተነሣሥቶ ወንድሙን የገደለው ባለ
መሆኑ፣ ሰዎቹ ነፍሰ ገዳዩን አሳልፈው አይ
ስጡት:: [6]በማኅበሩ ፊት ለፍርድ እስኪ
ቀርብና በዚያ ጊዜ የሚያገለግለው ሊቀ
ካህናት እስኪሞት ድረስ በዚያች ከተማ
ይቆይ:: ከዚያም ወደ ቤቱ፣ ሸሽቶ ወደ
መጣበት ከተማ ሊመለስ ይችላል::”

[7]ስለዚህም በኰረብታማው በንፍታሌም
ምድር በገሊላ ቃዴስን፣ በኰረብታማው
በኤፍሬም ምድር ሴኬምን፣ በኰረብታማው
በይሁዳ ምድር ኬብሮን የምትባለውን
ቂርያትአርባቅን ለዩ:: [8]እንደዚሁም ከዮር
ዳኖስ ማዶ ከኢያሪኮ' በስተምስራቅ በሮቤል
ነገድ ይዞታ ውስጥ ከፍታ ባለው ምድረ
በዳ ያለችውን ቦሶርን፣ በጋድ ነገድ ይዞታ
ውስጥ ባለችው በገለዓድ የምትገኘውን ራሞ
ትንና በምናሴ ነገድ ይዞታ ውስጥ በባሳን
የምትገኘውን ጎላንን ለዩ:: [9]ሳያስበው በድ
ንገት ሰው የገደለ ማንኛውም እስራኤላዊ
ወይም በመካከላቸው የሚኖር ማንኛውም
መጻተኛ ወደ ተለዩት ከተሞች መሸሽ
ይችላል፤ በማኅበሩ ፊት ከመቆሙ አስቀድ
ሞም ደም ተበቃዩ መግደል የለበትም::

## ለሌዋውያን የተመደቡ ከተሞች

21÷4-39 ተጓ ማብ-1ዜና 6÷54-80

**21** የሌዋውያን ቤተሰብ አለቆች ወደ
ካህኑ ወደ አልዓዛር፣ ወደ ነዌ ልጅ
ወደ ኢያሱና ወደ ሌሎቹ የእስራኤል ነገድ
አባቶች ዘንድ ቀረቡ፤ [2]በከነዓን ምድር
በሴሎም፣ “*እግዚአብሔር* የምንኖርባቸውን
ከተሞች፣ ከብቶቻችን ከሚሰማሩባቸው
ቦታዎች እንድትሰጡን በሙሴ በኩል አዞ
ልን ነበር” አላቸው:: [3]ስለዚህ እስራኤላ
ውያን ከወረሱት ምድር ላይ የሚከተሉ
ትን ከተሞችና መሰማሪያዎች *እግዚአብ
ሔር* ባዘዘው መሠረት ለሌዋውያኑ ሰጡ፤

[4]የመጀመሪያው ዕጣ ለቀዓት ዘሮች በየጐ
ሣቸው ወጣ፤ የካህኑ የአሮን ዝርያዎች ለሆ
ኑት ሌዋውያን ከይሁዳ፣ ከስምዖንና ከብ
ንያም ነገዶች ዐሥራ ሦስት ከተሞች በዕጣ
ተመደቡላቸው:: [5]ለቀሩት ለቀዓት ዘሮች
ደግሞ ከኤፍሬምና ከዳን ነገድ ጐሣዎች፣
እንዲሁም ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ጐሣ
ዎች ዐሥር ከተሞች በዕጣ ተመደቡላቸው::

[6]ለጌርሶን ዝርያዎች ከይሳኮር፣ ከአ
ሴር፣ ከንፍታሌም ነገድ ጐሣዎችና ባሳን
ውስጥ ካለው ከምናሴ ነገድ እኩሌታ
ጐሣዎች ዐሥራ ሦስት ከተሞች ተመደ
ቡላቸው::

[7]ለሜራሪ ዝርያዎች በየጐሣቸው ከሮ
ቤል፣ ከጋድና ከዛብሎን ነገዶች ዐሥር
ከተሞች ተመደቡላቸው::

[8]ስለዚህ እስራኤላውያን *እግዚአብሔር*
በሙሴ በኩል ባዘዘው መሠረት፣ እነዚህን
ከተሞችና መሰማሪያቸውን ለሌዋውያኑ
በዕጣ መደቡላቸው::

[9]ከይሁዳና ከስምዖን ነገዶች ደግሞ ከዚህ
በታች በስም የተጠቀሱትን ከተሞች በዕጣ
መደቡላቸው:: [10]እነዚህም ከተሞች የሌዊ
ልጆች፣ የቀዓት ጐሣዎች ለሆኑት ለአ
ሮን ዝርያዎች ተመደቡ፤ ይህም የሆነው
የመጀመሪያው ዕጣ ለእነርሱ ስለ ወጣላ
ቸው ነበር፤

[11]እነርሱም በተራራማው የይሁዳ
ምድር ያለችውን ኬብሮን የተባለች
ውን ቂርያት አርባቅን በዙሪያዋ
ካለው መሰማሪያ ጋር ሰጧቸው፤
አርባቅ የዔናቅ አባት ነበረ:: [12]ይሁን
እንጂ በከተማዪቱ ዙሪያ ያሉትን
ዕርሻዎችና መንደሮች ለዮፎኒ ልጅ
ለካሌብ ርስት አድርገው ሰጡት::
[13]እንደዚሁም ለነፍስ ገዳይ መማጠኛ

12÷22፤ሉቃ1÷39
20÷8 ኢሱ12÷2:
5፤21÷36፤1ዜና6÷71:
78:80
20÷9 ዘፀ21÷13፤
ዘሌ4÷2
21÷1 ኢሱ14÷1
21÷2 ዘሌ25÷32፤
ዘኍ35÷2-3፤ኢሱ
14÷4፤18÷1
21÷4 ቍ19፤
ዘኍ3÷17
21÷5 ቍ26
21÷6 ዘፍ30÷18፤
ዘኍ3÷17፤ኢሱ17÷7
21÷7 ቍ40፤ዘፀ
6÷16፤ኢሱ19÷10
21÷11 ዘፍ23÷2፤
ኢሱ10÷36
21÷12 ኢሱ15÷13
21÷13 ዘኍ33÷20፤
35÷6

'8 ምናልባት፣ *ዮርዳኖስ ዘኢያሪኮ፤* የዮርዳኖስ ወንዝ የጥንት መጠሪያ ሊሆን ይችላል::

20÷4 *በከተማይቱ ... በር፤* ፍርድ የሚተላለፍበት የተለመደ ቦታ ሲሆን፣ የአገር ሽማግሌዎችም ለሕዝቡ ዳኝነት የሚሰጡት እዚሁ ነው (ሩት 4÷1 እና ማብ፤ እንዲሁም ኢዮ 29÷7 ይመ)::

20÷6 *በማኅበሩ፤* በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ ጎልማሳ ወንዶች የሚገኙበት ጉባኤ ነው:: ሽማግሌዎቹ ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ የእነርሱ ድርሻ ምን እንደ ሆነ በግልጽ አይታወቅም (ቍ4)፤ ሆኖም የተሰጠው ፍርድ ትክክለኛ መሆኑንና አለመሆኑን ይመሰክሩ ይሆናል (ዝግ ችሎት ትክክለኛ ፍርድ ሊሰጥበት አይችልም):: *ሊቀ ካህናቱ እስኪሞት፤* ዘኍ 35÷25-28 ይመ:: በሊቀ ካህናቱ ሞት ስርየት ወይም ምሕረት ይገኝ ነበር::

20÷7 *ቃዴስን ... ለዩ፤* ጸሐፊው ተመሳሳይ ድምፀት ያላቸውን ቃላት በመጠቀም በልዩ የመልእክት ማስተላለፊያ ዘዴ ተጠቅሞአል፤ ይኸውም ቃዴስ ማለት “ቅዱስ” ወይም “የተለየ” ማለት ሲሆን፣ “የተለየውን (ከተማ) ለዩ” የሚል ነው:: ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ የሚገኙት ሁለቱ ከተሞች ቀደም ሲል ተለይተዋል፤ ስለ ሴኬም 8÷30-35 እና ማብ እንዲሁም ዘፍ 12÷6-7፤ ስለ ኬብሮን ዘፍ 23÷2፤49÷29-32 ይመ:: የከተሞቹ መልከዐ ምድራዊ አቀማመጥ ጠቀሜታ ነበረው፤ አንዱ በስተ ሰሜን፣ አንዱ በመኻል አገር፣ አንዱ ደግሞ በስተ ደቡብ ይገኙ ነበር (ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኙትና የመማፀኛ ከተማ በመሆን ያገለገሉት ሦስቱ ከተሞች ቅደም ተከተላቸው መገለባበጡን በቍ 8 ላይ ይመ፤ ቦሶር በስተ ደቡብ፣ ራሞት በመኻል አገር፣ ጎላን በስተ ሰሜን)::

20÷9 *ወይም ... ማንኛውም መጻተኛ፤* በእስራኤላውያንና በመጻተኞች መካከል እኩል የሕግ ከለላ ለመኖሩ ማስረጃ ነው (ከዘሌ 19÷33-34፤ ዘዳ 10÷18-19 ጋር ያነጻጽሩ)::

*21÷1-45፤* በመጨረሻ ሌዋውያን የተመደቡላቸውን ከተሞችና የግጦሽ መሬት ተረከቡ፤ የካህናት ወገኖች ግን ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ነበር (ቍ 10 ይመ)::

21÷4 *ለቀዓት ዘሮች፤* ሦስቱ የሌዊ ወንዶች ልጆች:- ቀዓት፣ጌድሶንና ሜራሪ ናቸው (ዘፀ 6÷16፤ ዘኍ 3÷17):: *ከይሁዳ፣ ከስምዖንና ከብንያም፤* ለእነዚህ ነገዶች የተመደበው ርስት ለኢየሩሳሌም ከተማ ቅርብ ሲሆን፣ ከጊዜ በኋላ ቤተ መቅደሱ የተሠራው በዚሁ ስፍራ ነው:: የተቀሩት ቀዓታውያን የተመደበላቸውን ከተሞች የወሰዱት ከሚያጎራብቷቸው ጐሣዎች ነው::

21÷11 *ኬብሮን፤* የካሌብ ከተማ ነበረች (14÷13-15):: ካህናትና ሌዋውያን ከሌላው ነዋሪ ጋር በተመደበላቸው ከተሞች ውስጥ የሚገኝ ቦታ ይሰጣቸው ነበር::

የሆነችውን ኬብሮንንና ልብናን ከነ
ማሰማሪያቸው ለካህኑ ለአሮን ልጆች
ሰጧቸው፤ 14ደግሞም የቲርን፣ ኤሽ
ትሞዓን፣ 15ሖሎንን፣ ዳቤርን፣ 16ዐይ
ንን፣ የጣንና ቤትሳሚስን ከነማሰ
ማሪያቸው ሰጧቸው፤ እነዚህ ዘጠኙ
ከተሞች ከሁለ ነገዶች ይዞታ ላይ
ተከፍለው የተሰጡ ናቸው::
17ከብንያም ነገድ ገባዖን፣ ጌባዕ፣
18ዓናቶትና አልሞን የተባሉትን አራት
ከተሞች ከነመሰማሪያዎቻቸው ሰጧቸው::
19ለካህናቱ ለአሮን ዝርያዎች ከነመሰማሪያ
ቸው የተሰጧቸው ከተሞች ዐሥራ ሦስት
ነበሩ::
20የሌዊ ልጅ የቀዓት ጐሣዎች ለሆኑት ለሌ
ሎቹ ደግሞ ከኤፍሬም ነገድ ላይ ተከፍ
ለው የሚከተሉት ከተሞች በዕጣ ተመደቡ
ላቸው::
21በተራራማው በኤፍሬም ምድ
ርም ለነፍስ ገዳይ መማጠኛ የሆነ
ችው ሴኬምና ጌዝር፣ 22ቂብጻይ
ምና ቤትሖሮን ከነማሠማሪያዎቻ
ቸው አራት ከተሞች ተሰጡአቸው::
23እንዲሁም ከዳን ነገድ ኤልተ
ቄን፣ ገባቶን፤ 24ኤሎንና ጋትሪ
ሞን ከነመሰማሪያዎቻቸው አራት
ከተሞች ተሰጧቸው::
25ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ደግሞ
ታዕናክና ጋትሪሞን ከነመሰማሪያዎ
ቻቸው ሁለት ከተሞች ተሰጧቸው::
26እነዚህ ዐሥር ከተሞች ሁሉ ከነመሰ
ማሪያዎቻቸው ለተቀሩት የቀዓት ጐሣ
ዎች ተሰጧቸው::
27የጌርሶን ወገኖች ለሆኑት ለሌሎቹ
የሌዊ ጐሳዎች የተሰጧቸው የሚከተ
ሉት ናቸው፤
ከምናሴ ነገድ እኩሌታ በባሳን
ውስጥ ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ የሆ
ነችው ከተማ ጎላንና በኤሽትራ እነ
ዚህ ሁለት ከተሞች ከነመሰማሪያ
ዎቻቸው፤
28ከይሳኮር ነገድ፣
ቂሶን፣ ዳብራት፣ 29የርሙትና ዓይ
ንጋ ኒም፣ እነዚህ አራት ከተሞች
ከነመሰማሪያዎቻቸው፤
30ከአሴር ነገድ፣
ሚሽአል፣ ዓብዶን፣ 31ሔልቃትና
ረአብ እነዚህ አራት ከተሞች
ከነመሰማሪያዎቻቸው፤
32ከንፍታሌም ነገድ፣

21፥14 ኢሱ15፥48:50
21፥16 ዘኍ34፥11፤ኢሱ15፥10:55
21፥17 ኢሱ9፥3፤18፥24፤ነህ11፥31
21፥18 2ሳሙ23፥27፤1ነገ2፥26፤ዕዝ2፥23፤ነህ7፥27፤11፥32፤ኢሳ10፥30፤ኤር1፥1፤11፥21፤32፥7
21፥19 ቍ4፤2ዜና31፥15
21፥21 ኢሱ10፥33፤17፥7
21፥22 ኢሱ10፥10፤1ሳሙ1፥1
21፥23 ኢሱ19፥44
21፥24 ኢሱ10፥12፤19፥45
21፥25 ኢሱ12፥21
21፥26 ቍ5
21፥27 ዘኍ35፥6፤ኢሱ12፥5
21፥28 ዘፍ30፥18፤ኢሱ19፥12:20
21፥29 ኢሱ10፥3፤15፥34
21፥30 ኢሱ17፥7፤19፥26:28
21፥31 ኢሱ19፥28
21፥32 ዘኍ35፥6፤ኢሱ 12፥22
21፥33 ቍ6
21፥34 ኢሱ12፥22፤19፥10
21፥35 ኢሱ19፥15
21፥36 ዘኍ21፥23፤ዘዳ2፥32፤ኢሱ20፥8፤መሳ11፥20
21፥37 ኢሱ13፥18
21፥38 ዘፍ32፥2፤ዘዳ4፥43፤ኢሱ12፥2
21፥39 ኢሱ13፥25
21፥40 ቍ7
21፥41 ዘኍ35፥7
21፥43 ዘዳ11፥31፤17፥14፤34፥4
21፥44 ዘፀ23፥31፤33፥14፤ዘዳ6፥19፤21፥10
21፥45 ኢሱ23፥14፤ነህ9፥8

በገሊላ ውስጥ ለነፍሰ ገዳይ መማ
ጠኛ የሆነችው ከተማ ቃዴስ፣ ሐሞ
ትዶርና ቀርታን እነዚህ ሦስት ከተ
ሞች ከነመሰማሪያዎቻቸው፤
33ለጌድሶናውያን ጐሣዎች የተመደ
ቡት ከተሞች ሁሉ ከነመሰማሪያዎቻ
ቸው ዐሥራ ሦስት ነበሩ::
34የሜራሪ ጐሣዎች ለሆኑት ለተቀሩት
ሌዋውያን የተሰጧቸው የሚከተሉት
ናቸው፤
ከዛብሎን ነገድ ዮቅንዓም፣ ቀርታ፣
35ዲሞናና ነህላል፣ እነዚህ አራት
ከተሞች ከነመሰማሪያዎቻቸው::
36ከሮቤል ነገድ፣
ቦሶር፣ ያህጽ፣ 37ቅዴሞትና ሜፍዓት፣
እነዚህ አራት ከተሞች ከነመሰማሪያዎ
ቻቸው፤
38ከጋድ ነገድ፣
በገለዓድ ውስጥ ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ
የሆነችው ከተማ ራሞት መሃና
ይም፣ 39ሐሴቦንና ኢያዜር፣ እነዚህ
አራት ከተሞች ከነመሰማሪያዎቻ
ቸው::
40የሜራሪ ጐሣዎች ለሆኑት ለተቀሩት ሌዋ
ውያን የተመደቡት ከተሞች ሁሉ ዐሥራ
ሁለት ነበሩ::
41እንግዲህ እስራኤላውያን ርስት አድር
ገው ከያዙት ምድር ለሌዋውያኑ የተሰጧ
ቸው ከተሞች ከነመሰማሪያዎቻቸው ባጠቃ
ላይ አርባ ስምንት ነበሩ:: 42እነዚህም ከተ
ሞች እያንዳንዳቸው በዙሪያቸው መሰማሪያ
ዎች ነበሯቸው፤ መሰማሪያ የሌለው ከተማ
አልነበረም::
43ስለዚህ እግዚአብሔር ለቀድሞ አባቶ
ቻቸው ይሰጣቸው ዘንድ የማለላቸውን
ምድር ሁሉ ለእስራኤል ሰጠ፤ እነርሱም
ምድሪቱን ወረሱ፣ መኖሪያቸውም አደረ
ጓት:: 44እግዚአብሔር ለቀድሞ አባቶቻቸው
እንደ ማለላቸው በዙሪያቸው ካሉት አሳረፋ
ቸው፤ አንድም ጠላት ሊቋቋማቸው አልቻ
ለም፤ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ሁሉ
አሳልፎ በእጃቸው ሰጥቶአቸዋልና:: 45እግዚ
አብሔር ለእስራኤል ቤት ከሰጠው መልካም
የተስፋ ቃል አንዳችም አልቀረም፤ ሁሉም
ተፈጽሞአል::

## ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ርስት ያገኙ ነገዶች ወደ ቤታቸው ተመለሱ

22 በዚህ ጊዜ ኢያሱ የሮቤልንና የጋ
ድን ነገዶች፣ እንዲሁም የምናሴን

21፥27 *የጌርሶን ወገኖች፤* ለአሴር፣ ለንፍታሌምና ለይሳኮር ነገዶች ከተሰጠው ርስት በስተ ሰሜን በኩል የሚገኙትን ከተሞች ተቀበሉ::

21፥34 *የሜራሪ ጐሣዎች፤* ዐሥራ ሁለቱ ከተሞቻቸው በሮቤል፣ በጋድና በዛብሎን ምድር ተበታትነው ይገኙ ነበር::

*21፥43-45፤* ይህ ክፍል፣ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ሊሰጣቸው በመሐላ ቃል የገባላቸውን ምድር እንዴት እንደ ሰጣቸው በጭሩ የሚገልጽ መደምደሚያ ነው (ዘፍ 15፥18-21 *ይመ*):: ምድሪቱን ሙሉ በሙሉ የመያዙ ተግባር ገና ተግባራዊ አልሆነም (23፥4-5፤ መሳ 1፥2 *ይመ*)፤ ይሁን እንጂ ሕዝባዊ ዘመቻው ተጠናቅቆአል፤ እስራኤልም በመጨረሻ የተስፋዪቱን ምድር ወርሳለች:: የወረሰችውንም ከእጇ የሚያስጥል አንዳችም ኀይል በከነዓን አልቀረም::

21፥44 *በዙሪያቸው ... አሳረፋቸው፤* የ1፥13 ማብ ይመ::

*22፥1-34፤* ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ የመጡት የሁለቱ ነገድ እኩሌታ በጦርነቱ ጊዜ ታማኞች ስለ ነበሩ፣ በኢያሱ ተመስግነው ወደ ወረሱት ምድር እንዲሄዱ ተደረገ:: ነገር ግን "የምስክር መሠዊያ" ብለው የሠሩት መሠዊያ (ቍ 26-27:34 *ይመ*) በሌሎች እስራኤላውያን ዘንድ መደናገርን በማስከተሉ ሕዝቡ ሊቀጣቸው ፈልጎ ነበር፤ ሆኖም

ነገድ እኩሌታ ጠርቶ፣ 2እንዲህ አላቸው፤
“የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ያዘዘውን
ሁሉ ጠብቃችኋል፤ እኔም ያዘዝኋችሁን
በሙሉ ፈጽማችኋል፤ 3ከረጅም ጊዜ ጀምሮ
እስከ ዛሬ ድረስ ወንድሞቻችሁን አልተዋች
ሁም፤ አምላካችሁ *እግዚአብሔር* የሰጣችሁን
ተልእኮ በሚገባ ተወጥታችኋል:: 4አሁንም
አምላካችሁ *እግዚአብሔር* በሰጣችሁ ተስፋ
*መሠረት* ወንድሞቻችሁን አሳርፎአቸዋል፤
ስለዚህ *የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴ ከዮርዳ
ኖስ ማዶ ርስት አድርጎ በሰጣችሁ ምድር
ወዳለው ቤታችሁ ተመለሱ:: 5*የእግዚአብሔር*
ባሪያ ሙሴ፣ አምላካችሁን *እግዚአብሔርን*
እንድትወዱ፣ በመንገዱ ሁሉ እንድትሄዱ፣
ትእዛዙን እንድትፈጽሙ፣ እርሱም አጥብ
ቃችሁ እንድትይዙት እንዲሁም በፍጹም
ልባችሁ፣ በፍጹም ነፍሳችሁ እንድታገለግ
ሉት የሰጣችሁን ትእዛዙንና ሕጉን ነቅታ
ችሁ ጠብቁ::”

6ከዚያም ኢያሱ መርቆ አሰናበታቸው፤
እነርሱም ወደ ቤታቸው ተመለሱ:: 7ሙሴ
ለምናሴ ነገድ እኩሌታ በባሳን ምድር
ርስት ሰጥቶአቸው ነበር፤ ለቀረው እኩሌታ
ደግሞ ኢያሱ ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ
ከወንድሞቻቸው ጋር ርስት ሰጣቸው::
ኢያሱ ወደ ቤታቸው እንዲገቡ ባሰናበ
ታቸው ጊዜ መረቃቸው፤ 8እንዲህም
አላቸው፤ “ብዙ ሀብት ይዛችሁ ማለትም
አያሌ የከብት መንጋ፣ ብርና ወርቅ፣
ናስና ብረት እንዲሁም ቊጥሩ እጅግ
የበዛ ልብስ ይዛችሁ ወደ ቤታችሁ
ተመለሱ፤ ከጠላት የተገኘውንም ይህን
ምርኮ ከወንድሞቻችሁ ጋር ተካፈሉት”
አላቸው::

9ስለዚህ የሮቤልና የጋድ ነገዶች እንዲ
ሁም የምናሴ ነገድ እኩሌታ እስራኤላው
ያንን ከነዓን ውስጥ ባለችው በሴሎ
ትተው፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሙሴ አማ
ካይነት ወደ ተቀበሏት ርስታቸው፣ ወደ
ገለዓድ ምድር ተመለሱ::

10የሮቤልና የጋድ እንዲሁም የምናሴ
ነገድ እኩሌታ በከነዓን ምድር ወዳለችው፣
የዮርዳኖስ አጠገብ ወደምትገኘው ገሊሎት
ወደ ተባለች ስፍራ ሲደርሱ በወንዙ አጠ
ገብ ግዙፍ መሠዊያ ሠሩ:: 11የእስራኤላው
ያን ይዞታ በሆነችው በከነዓናውያን ምድር
ወሰን በገሊሎት ላይ መሠዊያ መሥራታቸ
ውን፣ ሌሎቹ እስራኤላውያን በሰሙ ጊዜ፣
12በእነርሱ ላይ ለመዝመት፣ የእስራኤል
ማኅበር ሁሉ በሴሎ ተሰበሰቡ::

13ስለዚህም እስራኤላውያን የካህኑ የአልዓ
ዛርን ልጅ ፊንሐስን በገለዓድ ምድር ወደ
ሚኖሩት ወደ ሮቤልና ወደ ጋድ እንዲሁም
ወደ ምናሴ ነገድ እኩሌታ ላኩ፤ 14ከእር
ሱም ጋር እያንዳንዱን የእስራኤልን ነገድ
የሚወክሉ ዐሥር አለቆች አብረው ላኩ፤ እነ
ዚህም እያንዳንዳቸው ከእስራኤላውያን ጐሣ
ዎች የተውጣጡ የየቤተ ሰቡ አለቆች ነበሩ::

15እነርሱም በገለዓድ ምድር ወዳሉት ወደ
ሮቤላውያን፣ ወደ ጋዳውያንና ወደ ምናሴ
ነገድ እኩሌታ ሄደው እንዲህ አሏቸው፤
16“*መላው የእግዚአብሔር* ጉባኤ እንዲህ
ይላል፤ ‘በእስራኤል አምላክ ላይ እንዲህ
ያለ ክህደት የፈጸማችሁት ለምንድን ነው?
*እግዚአብሔርን* ከመከተልስ እንዴት ወደ
ኋላ ትላላችሁ? እንዴትስ ዛሬ *በእግዚ
አብሔር* ላይ ዐምፃችሁ ለራሳችሁ *መሠዊያ*
ትሠራላችሁ? 17በፌጎር የተሠራው ኀጢአት
አይበቃንምን? ምንም እንኳ *በእግዚአብሔር*
ጉባኤ ላይ መቅሠፍት ቢወርድም፣ እስከ
ዛሬዪቱ ዕለት ድረስ ራሳችንን ከዚያች
ኀጢአት አላነጻንም:: 18እናንተ፣ አሁንም
*እግዚአብሔርን* ከመከተል ወደ ኋላ ትላላ
ችሁን?

“‘ዛሬ እናንተ *በእግዚአብሔር* ላይ
ብታምፁ፣ እርሱ ደግሞ ነገ በመላው እስራ
ኤል ጉባኤ ላይ ይቈጣል:: 19የወረሳችኋት
ምድር ረክሳ እንደ ሆነ፣ *የእግዚአብሔር*
*ማደሪያ* ወደ ተተከለበት ወደ *እግዚአብሔር*
ምድር መጥታችሁ ከእኛ ጋር ርስት ተካ
ፈሉ፤ ነገር ግን ከአምላካችን *ከእግዚአብሔር*
*መሠዊያ* በስተቀር ሌላ *መሠዊያ* ሠርታ
ችሁ *በእግዚአብሔርም* ሆነ በእኛ ላይ አታ
ምፁ:: 20የዛራ ልጅ አካን፣ እርም የሆነውን
ነገር በመውሰድ ኀጢአት ስለ ሠራ፣ በመ
ላው የእስራኤል ጉባኤ ላይ ቍጣ አልመጣምን?

22፥2 ዘኍ32፥25
22፥4 ዘፀ33፥14፤ ዘኍ32፥18:22፤ዘዳ3፥20፤ኢሱ1፥13-15
22፥5 ዘዳ5፥29፤6፥5፤ኢሱ23፥11፤ኢሳ43፥22፤ ሚል3፥14
22፥6 ዘፍ24፥60፤ ዘፀ39፥43
22፥7 ዘኍ32፥19፤ኢሱ12፥5፤14፥13፤17፥2፤ሉቃ24፥50
22፥8 ዘፍ49፥27፤ ዘኍ31፥22:27፤ዘዳ20፥14፤1ሳሙ30፥16፤ 2ሳሙ1፥1፤ኢሳ9፥3
22፥9 ዘኍ32፥26፤ ኢሱ18፥1
22፥10 ቊ19:26-27፤ኢሱ18፥17፤ ኢሳ19፥19፤56፥7
22፥12 ኢሱ18፥1
22፥13 ዘኍ3፥32፤ 25፥7፤ኢሱ24፥33
22፥14 ቊ32፤ ዘኍ1፥4
22፥16 ዘዳ7፥3፤ 12፥13-14፤1ሳሙ13፥13፤15፥11
22፥17 ዘኍ23፥28፤ 25፥1-9
22፥18 ዘሌ10፥6
22፥19 ቊ10፤ዘፀ 26፥1
22፥20 ዘሌ10፥6፤ኢ ሱ7፥1:5፤መዝ7፥11

ከቅጣቱ ለጥቂት አመለጡ::

22፥2 *ሙሴ ያዘዘውን ሁሉ፤* ከነዓንን ለመያዝ በሚዋጉበት ጊዜ ከተቀሩት ሌሎች ነገዶች ጋር እንዲተባበሩ ሙሴ አዞአቸው ነበር (ዘኍ 32፥16-27፤ ዘዳ 3፥18)::

22፥5 *እግዚአብሔርን ... እንድትወዱ ... በፍጹም ልባችሁ ... እንድታገለግሉት፤* ሙሴም ሆነ ኢያሱ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ ፍቅርና ከልብ የሆነ አገልግሎት እንደሚያስፈልግ ተረድተዋል:: በጥንት መካከለኛው ምሥራቅ “ፍቅር” የሚለው ቃል የፖለቲካ ቃል በመ ሆኑ፣ ለአንድ ንጉሥ ከልብ መታዘዝ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል::

22፥8 *ከወንድሞቻችሁ ጋር ተካፈሉት፤* በምርኮ የተገኙ ንብረቶችን እኩል መካፈል አስፈላጊ መሆኑን ሙሴም ተረድቶ ነበር (ዘኍ 31፥25-27)::

22፥10 *ገሊሎት፤* በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም መሠረት ከኢያሪኮ ቀጥላ የምትገኘዋ ጌልገላ ናት፤ ሆኖም ከሴሎ በስተ ምሥራቅ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ (18፥17) የምትገኘዋ ሳትሆን እንደማት ቀር በበለጠ ይታሰባል::

22፥11 *እስራኤላውያን በሰሙ ጊዜ፤* ከሣዱ እሆናለሁ ብሎ ከልክ በላይ መጨነቅ ትክክለኛ ወዳልሆነ ድምዳሜ ያደርሳል:: እነርሱ ያቆሙት መሠዊያ በሴሎ ያለውን እውነተኛውን መ ሠዊያ የሚቀናቀን መሰላቸው::

22፥12 *በእነርሱ ላይ ለመዝመት፤* ሊቀጧቸው ነው (ከዘዳ 13፥12-18፤ ከመሳ 20 ጋር ያነጻጽሩ):: *በሴሎ ተሰበሰቡ፤* በእግዚ አብሔር ፊት በመገናኛው ድንኳን አጠገብ ማለት ነው::

*22፥13-14፤* ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኙትን ነገዶች በእግዚ አብሔር ላይ ከተነሣሡበት ዐመፅ ለመመለስ ተሰሚነት ያላቸው መልእክተኞች ተላኩ::

22፥16 *እንዴት...?* የቀረበባቸው ክስ፤ ክህደትንና ዐመፅን ፈጽማችኋል የሚል ከባድ ክስ ነበር::

22፥17 *ፌጎር፤* አንዳንድ እስራኤላውያን ብዔልፌጎር የተባለውን የከነዓናውያንን አምላክ ሲያመልኩበት የነበረ ቦታ ነው (ዘኍ 25፥1-5)::

22፥19 *ረክሳ እንደ ሆነ፤* ነዋሪዎቿን በሚበክል የአረ ማውያን አምልኮ ማለት ነው:: *እግዚአብሔር ምድር፤* የተስፋ ዪቱ ምድር ስፋት ከዮርዳኖስ ማዶ ያለውን አገር ጨምሮ አያው ቅም:: ከነዓን እግዚአብሔር የእኔ ናት ያላትና ለአብርሃም፣ ለይ ስሐቅና ለያዕቆብ ዘሮች ሊሰጣቸው ቃል የገባላቸው ምድር ናት::

22፥20 *አካን ... በመላው የእስራኤል ጉባኤ፤* የ7፥1-26

በሠራው ኀጢአት የሞተውም[†] እርሱ ብቻ
አልነበረም።”
[21]ከዚያም የሮቤልና የጋድ ነገዶች እንዲ
ሁም የምናሴ ነገድ እኩሌታ ለእስራኤል
ጐሣ መሪዎች እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው፤
[22]“ኀያሉ አምላክ፣ እግዚአብሔር! ኀያሉ
አምላክ፤ እግዚአብሔር! እርሱ ያውቃል! እስ
ራኤልም ይህን ይወቅ! ይህ የተደረገው በማ
መፅ ወይም ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ
ከሆነ፣ ዛሬ አትማሩን! [23]መሠዊያውን የሠ
ራነው እግዚአብሔርን ከመከተል ወደ ኋላ
ለማለት፣ የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል
ቍርባን ልናሳርግበት ወይም የኅብረት
መሥዋዕት[^] ልናቀርብበት አስበን ከሆነ፣
ራሱ እግዚአብሔር ይበቀለን።
[24]“እኛማ ይህን ያደረግነው፣ ወደፊት
ዘሮቻችሁ ለዘሮቻችን እንዲህ እንዳይሏቸው
ፈርተን ነው፤ ‘ከእስራኤል አምላክ ከእግዚ
አብሔር ጋር ምን ግንኙነት አላችሁ?
[25]እናንት የሮቤልና የጋድ ልጆች፤ እግዚ
አብሔር ዮርዳኖስን በመካከላችን መለያ
ድንበር ስላደረገው፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ
ድርሻ የላችሁም።’ ስለዚህ ዘሮቻችሁ፣ የእኛ
ዘር እግዚአብሔርን እንዳይፈራ ሊያደርጉ
ይችላሉ።
[26]“እኛም ‘እንነሣና መሠዊያ እንሥራ፤
የምንሠራው መሠዊያ ግን ለሚቃጠል
መሥዋዕት ወይም ለሌላ መሥዋዕት ማቅረ
ቢያ አይውልም’ ያልነው ለዚህ ነው።
[27]በሌላም በኩል የሚቃጠል መሥዋዕ
ታችንን፣ ሌላውን ቍርባናችንንና የኅብረት
መሥዋዕታችንን ይዘን በተቀደሰው ስፍራ
እግዚአብሔርን እንደምናመልክ መሠዊያው
በእኛና በእናንተ እንዲሁም በሚቀጥሉት
ትውልዶች መካከል ምስክር ይሆናል። ስለ
ዚህ ወደፊት ዘሮቻችሁ ዘሮቻችንን፣ ‘ከእግ
ዚአብሔር ዘንድ ድርሻ የላችሁም’ ሊሏ
ቸው አይችሉም።
[28]“እኛም፣ ‘ወደ ፊት እኛንም ሆነ ዘሮቻ
ችንን እንዲህ የሚሉ ከሆነ፣ “እነሆ፤ አባቶቻ
ችን የሠሩትን የእግዚአብሔርን መሠዊያ
ምሳሌ ተመልከቱ፤ ይህ በእኛና በእናንተ
መካከል ምስክር እንዲሆን እንጂ፣ ለሚቃጠል
መሥዋዕትና ለሌላ መሥዋዕት ማቅረቢያ
አይደለም ብለን እንመልሳለን’ አልን።
[29]“በማደሪያው ድንኳን ፊት ካለው ከእግዚ
አብሔር መሠዊያ ሌላ፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት
ወይም ለእህል ቍርባን እንዲሁም ለሌላ መሥ
ዋዕት ማቅረቢያ የሚሆን መሠዊያ በመሥራት
ዛሬ በእግዚአብሔር ላይ እናምፅን? እርሱን
ማምለካችንንም እንተውን? ይህ ከእኛ ይራቅ!”
[30]ካህኑ ፊንሐስና የእስራኤላውያን የጐሣ
መሪዎች የነበሩት የማኅበረ ሰቡ አለቆች
የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ወገኖች ያሉትን
በሰሙ ጊዜ ተደሰቱ። [31]የካህኑ የአልዓዛር
ልጅ ፊንሐስም፣ የሮቤልን የጋድንና የምና
ሴን ወገኖች “በዚህ ነገር እግዚአብሔርን
አልበደላችሁምና፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር
መሆኑን ዛሬ ዐውቀናል፤ እነሆ እስራኤላው
ያንን ከእግዚአብሔር እጅ አድናችኋል”
አላቸው።
[32]ከዚያም የካህኑ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐ
ስና መሪዎቹ፣ ከሮቤልና ከጋድ ወገኖች
ጋር በገለዓድ ምድር ከተነጋገሩ በኋላ፣ ወደ
ከነዓን ተመልሰው፣ ሁኔታውን ለእስራ
ኤላውያን ነገሩ። [33]እስራኤላውያንም ይህን
ሲሰሙ ደስ ብሎአቸው እግዚአብሔርን
አመሰገኑ፤ ከዚያም የሮቤልና የጋድ ወገኖች
የሚኖሩበትን አገር በጦርነት ለማጥፋት
የመሄድን ነገር አላነሡም።
[34]የሮቤልና የጋድ ወገኖችም፣ እግዚ
አብሔር አምላክ ለመሆኑ፣ ይህ በመካከላ
ችን ምስክር ነው፤ በማለት መሠዊያውን
“ምስክር” ብለው ጠሩት።

## ኢያሱ ለመሪዎች የተናገረው የመሰናበቻ ቃል

23 እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በዙ
ሪያቸው ካሉት ጠላቶቻቸው ሁሉ
ካሳረፋቸው እነሆ፣ ብዙ ዘመን አለፈ፤ በዚህ
ጊዜ ኢያሱ በጣም አርጅቶ፣ ዕድሜውም
ገፍቶ ነበር፤ [2]ኢያሱ እስራኤልን ሁሉ አለ
ቆቻቸውን፣ መሪዎቻቸውን፣ ፈራጆቻቸው
ንና ሹማምንታቸውን በሙሉ ጠርቶ እንዲህ
አላቸው፤ “እኔ አርጅቻለሁ፤ ዕድሜዬም
ገፍቶአል። [3]አምላካችሁ እግዚአብሔር ስለ
እናንተ ሲል በእነዚህ ሕዝቦች ሁሉ ላይ
ያደረገውን ማናቸውንም ነገር እናንተው ራሳ
ችሁ አይታችኋል፤ ስለ እናንተ የተዋጋ
ላችሁ ራሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነው።
[4]ከዮርዳኖስ እንሥቶ በስተ ምዕራብ እስካለው

[†]20 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው። [^]23 በዚህና በቍጥር 27 ላይ በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* በመባል ይታወቃል።

22፥22 ዘዳ10፥17፤ 1ሳሙ2፥3፤16፥7፤1ነገ 8፥39፤1ዜና28፥9፤መዝ 11፥4፤40፥9፤44፥21፤50፥1፤139፥4፤ኤር17፥10
22፥23 ዘዳ12፥11፤ 18፥19፤1ሳሙ20፥16፤ኤር41፥5
22፥27 ዘፍ21፥30፤ ዘዳ12፥6፤ኢሱ24፥27፤ ኢሳ19፥20
22፥28 ዘፍ21፥30
22፥29 ዘፀ26፥1፤ ኢሱ24፥16
22፥31 2ዜና15፥2
22፥32 ቍ14
22፥33 1ዜና29፥20፤ ዳን2፥19፤ሉቃ2፥28
22፥34 ዘፍ21፥30
23፥1 ዘዳ12፥9፤ኢሱ 13፥1፤21፥44
23፥2 ኢሱ7፥6፤13፥1፤24፥1
23፥3 ዘፀ14፥14፤ ዘዳ20፥4
23፥4 ዘኍ34፥2፡

ማብ ይመ።

22፥22 *ኀያሉ አምላክ፣ እግዚአብሔር!* የመዝ 50፥1 ማብ ይመ። ይህን የተቀደሰ ስም ደጋግመው የጠሩት የገቡበት ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑንና በደለኞች ሆነው ቢገኙ፤ የሚመጣባቸውን ቅጣት አሜን ብለው የሚቀበሉ መሆኑን ለመግለጽ ነው፥

22፥27 *ምስክር፤* መሠዊያው ካልተጠረበ ድንጋይ የተሠራ ሳይሆን አይቀርም (8፥31፤ ዘፀ 20፥25 ይመ)፤ ይህም ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ነገዶች ምንም እንኳ ከተስፋዪቱ ምድር ውጭ ቢኖሩም፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው እንዲገኙና እርሱንም በመገናኛው ድንኳን ለማምለክ መብት ያላቸው መሆኑን ለመመስከር ነው። የመጽሐፈ ኢያሱ ጸሓፊ ከጠቀሳቸው የመታሰቢያ ሐውልቶች ውስጥ ይህ ስድስተኛው ነው (የ10-27 ማብ ይመ)።

22፥31 *እስራኤላውያንን ... አድናችኋል፤* የተናገሩት ቃል ከእግዚአብሔር ፍርድ የተነሣ በሌሎቹ ነገዶች ላይ ሊመጣ ያለውን ቅጣት ተከላክሎአል (የቍ 20 ማብ ይመ)።

*23፥1-16፤* የእግዚአብሔር አገልጋይ ኢያሱ፣ ጌታ የሰጠውን ድል ሁሉ እያስታወሰ፣ የመሰናበቻ ንግግር ያደርጋል፤ ከዚህም በተጨማሪ ሕዝቡ ገና መውረስ ያለበት ቦታ እንዳለና ለእግዚአብሔርም የኪዳን ሕግ ታማኝ ሆኖ እንዲኖር ያሳስባል። የሕዝቡ ተልእኮ በዚህ ዓለም የእግዚአብሔር መንግሥት ካህናት ሆኖ መኖር ነው።

23፥1 *ካሳረፋቸው፤* የ1፥13 ማብ ይመ። *ዕድሜውም ገፍቶ፤* ኢያሱ በዚህ ጊዜ ዕድሜው 110 ደርሶ ነበር (24፥29)።

እስከ ታላቁ ባሕር[ሀ] ድረስ በሙሉ ካሸነፍኋ
ቸው ሕዝቦች ያልወረሳችሁትን ቀሪ ምድር
ርስት እንዲሆን ለየነገዶቻችሁ እንዴት
አድርጌ በዕጣ እንዳከፋፈልኋችሁ አስታ
ውሱ:: 5ራሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከፊ
ታችሁ ያስወግዳቸዋል፤ ከፊታችሁም ያሉብ
ትን ስፍራ ያስለቅቃቸዋል፤ አምላካችሁ እግ
ዚአብሔር በሰጣችሁም ተስፋ መሠረት
ምድራቸውን ትወርሳላችሁ::

6"በርቱ፤ ወደ ግራም ወደ ቀኝም ሳትሉ
በሙሴ የሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ
ለመጠበቅና ለማድረግ እጅግ በርቱ:: 7በመ
ካከላችሁ ከቀሩት ከእነዚህ ሕዝቦች ጋር
አትተባበሩ፤ የአማልክቶቻቸውን ስም አት
ጥሩ፤ አትማሉባቸው፤ አታገልግሏቸው፤ አት
ስገዱላቸውም፤ 8ነገር ግን እስካሁን እንዳደ
ረጋችሁት ሁሉ አምላካችሁን እግዚአብሔርን
አጥብቃችሁ ያዙ::

9"እግዚአብሔር ታላላቅና ኀያላን ሕዝቦ
ችን ከፊታችሁ አሳድዶ አስወጥቶአቸዋል፤
እስከ ዛሬም ድረስ ማንም ሊቋቋማችሁ
አልቻለም:: 10አምላካችሁ እግዚአብሔር በሰ
ጣችሁ ተስፋ መሠረት የሚዋጋላችሁ ስለ
ሆነ፣ ከእናንተ አንዱ ሰው ሺውን ያሳድ
ዳል:: 11ስለዚህ አምላካችሁን እግዚአብሔርን
ለመውደድ ተጠንቀቁ::

12ነገር ግን ከእርሱ ተመልሳችሁ ተርፈው
በመካከላችሁ ከሚገኙት ከእነዚህ ሕዝቦች
ጋር ብትተባበሩ፣ በጋብቻም ብትተሳሰሩና
ብትቀላቀሉ፣ 13አምላካችሁ እግዚአብሔር
ከእንግዲህ ከፊታችሁ እንደማያወጣቸው ይህን
ልታውቁ ይገባል፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር
ከሰጣችሁ ከዚህች መልካም ምድር እስክት
ጠፉ ድረስም ወጥመድና አሽክላ፣ ለጀርባችሁ
ጅራፍ፣ ለዐይኖቻችሁም እሾኽ ይሆኑባች
ኋል::

14"እነሆ፤ አሁን የምድርን ሁሉ መንገድ
ልሄድ ነው፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰ
ጣችሁ መልካም ተስፋ ሁሉ አንዲቱን
እንኳ እንዳላስቀረባችሁ፣ በፍጹም ልባችሁ
በፍጹም ነፍሳችሁ ታውቃላችሁ፤ አንዱም

6፥ኢሱ19፥51፤መዝ 78፥55
23፥5 ቍ-13፤ዘፀ 23፥30፤መሳ2፥21፤መዝ 44፥5፤ኢር46፥15
23፥6 ዘዳ17፥20፤ 28፥61፤ኢሱ1፥7
23፥7 ዘፀ20፥5፤23፥ 13፤ኤር5፥7፤12፥16
23፥8 ዘዳ10፥20
23፥9 ዘዳ7፥24፤ 11፥23
23፥10 ዘፀ14፥14፤ ዘሌ26፥8፤መሳ3፥31
23፥11 ዘዳ4፥15፤ ኢሱ22፥5
23፥12 ዘፍ34፥9፣ ዘፀ34፥16፤መዝ 106፥34-35
23፥13 ቍ-5፤ዘፀ10፥ 7፤ዘኍ33፥55፤ዘዳ1፥8፤ 1ነገ9፥7፤2ነገ25፥21
23፥14 ኢሱ21፥45፤ 1ነገ2፥2፤መዝ119፥ 140፤145፥13
23፥15 ዘሌ26፥17፤ ዘዳ28፥15፤ኢሱ24፥20፤ 1ነገ8፥56፤14፥10፤2ነገ 22፥16፤ኢሳ24፥6፤34፥ 5፤43፥28፤ኤር6፥19፤ 11፥8፤33፥14፤35፥17፤ 39፥16፤40፥2፤ሚል4፥6
24፥1 ዘፍ12፥6፤ 49፥2፤ኢሱ7፥6፤23፥2፤ 1ሳሙ12፥7፤1ነገ8፥14
24፥2 ዘፍ11፥26:32
24፥3 ዘፍ1፥28፤12፥ 1:2፤21፥3
24፥4 ዘፍ14፥6፤25፥26፤ 46፥5-6፤ዘኍ24፥18
24፥5 ዘፀ3፥10፤ 12፥51
24፥6 ዘፀ14፥9: 22:23
24፥7 ዘፀ14፥10:20:

ሳይቀር ሁሉም ተፈጽሞአል:: 15ነገር ግን
አምላካችሁ እግዚአብሔር የሰጣችሁ መል
ካሙ ተስፋ በሙሉ እንደ ተፈጸመ ሁሉ፣
እንደዚሁም አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣ
ችሁ ከመልካሚቱ ምድር እስኪያጠፋችሁ
ድረስ ክፉውን ነገር ያመጣባችኋል:: 16አምላ
ካችሁ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ኪዳን ብታፈ
ርሱ፣ ሄዳችሁም ሌሎችን አማልክት ብታገለግ
ሉና ብትሰግዱላቸው የእግዚአብሔር ቍጣ በላ
ያችሁ ይነዳል፤ ከሰጣችሁም ከመልካሚቱ
ምድር በፍጥነት ትጠፋላችሁ::"

## ቃል ኪዳኑ በሴኬም ታደሰ

24 ከዚያም ኢያሱ የእስራኤልን ነገዶች
ሁሉ በሴኬም ሰበሰበ፤ የእስራኤል
ንም ሽማግሌዎች፣ መሪዎች፣ ፈራጆችና ሹማ
ምንት ጠራ፤ እነርሱም በእግዚአብሔር ፊት
ቆሙ::

2ኢያሱም ሕዝቡን ሁሉ እንዲህ አላቸው፤
"የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ 'የቀድሞ አባቶቻችሁ፣ የአብርሃም
ንና የናኮርን አባት ታራን ጨምሮ ከብዙ
ዘመን በፊት ከወንዙ ማዶ ኖሩ[ለ]፤ ሌሎች
ንም አማልክት አመለኩ:: 3እኔ ግን አባታ
ችሁን አብርሃምን ከወንዙ ማዶ ካለው ምድር
አምጥቼ፣ በከነዓን ምድር ሁሉ መራሁት፤
ዘሮቹን አበዛሁለት፤ ይስሐቅንም ሰጠሁት::
4ለይስሐቅ ያዕቆብንና ዔሳውን ሰጠሁት፤
ለዔሳውም ኰረብታማውን የሴይርን ምድር
ርስት አድርጌ ሰጠሁት፤ ያዕቆብና ልጆቹ
ግን ወደ ግብፅ ወረዱ::

5"'ከዚያም ሙሴንና አሮንን ላክሁ፤ ባመ
ጣሁት መቅሰፍት ግብፃውያንን አስጨ
ንቄ፣ እናንተን ከዚያ አወጣኋችሁ:: 6አባቶ
ቻችሁን ከግብፅ ባወጣኋቸው ጊዜ፣ ወደ
ባሕሩ መጣችሁ፤ ግብፃውያንም በሠረገሎ
ችና[ሐ] በፈረሰኞች እስከ ቀይ ባሕር[መ] ድረስ
ተከታተሏቸው:: 7እነርሱ ግን ወደ እግዚ

[ሀ]4 የሜድትራንያን ባሕር ነው:: [ለ]2 በዚህ እንዲሁም ቍጥር 3:14 እና 15 ላይ የተጠቀሰው የኤፍራጥስ ወንዝ ነው:: [ሐ]6 ወይም ሠረገለኞች ተብሎ መተርጐም ይቻላል:: [መ]6 ዕብራይስጡ ያም ሳሙፍ ይላል፤ ይኸ ውም የደንገል ባሕር ማለት ነው::

23፥6 *ለመጠበቅና ለማድረግ … በርቱ፤* እግዚአብሔር በመጽሐፉ መግቢያ ላይ የሰጠውን መመሪያ የሚያስተጋባ ነው (1፥7-8፤ 22፥5 ይመ):: *የሕግ መጽሐፍ፤* ከሙሴ ዘመን ጀምሮ የተጻፉትን ቀኖናውያን መጻሕፍት የሚያመለክት ነው (ከዘዳ 30፥10:19፤ 31፥9:24:26 ጋር ያነጻጽሩ)::

23፥11 *አምላካችሁን እግዚአብሔርን ለመውደድ፤* የንግግሩ ሁሉ ማጠቃለያ ነው (የ22፥5 ማብ ይመ)::

23፥12 *ነገር ግን ከእርሱ ተመልሳችሁ፤* ሕዝቡ በተስፋዪቱ ምድር መኖር የሚችለው ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ እስከ ተገኘና በዙሪያውም ከሚገኘው የጣዖት አምልኮ እስከ ተለየ ድረስ ብቻ ነው:: ሕዝቡ ይህን መመሪያ ሙሉ በሙሉ መፈጸም ካልቻለ፣ ከተስፋዪቱ ምድር ተጠራርጎ ይወገዳል (ከቍ 13:15-16፤ ከ2ነገ 17፥7-8፤ ከ2ዜና 7፥14-20 ጋር ያነጻጽሩ):: *ብትተባበሩ በጋብቻም ብትተሳሰሩ፤* እስራኤላውያን በብሔራዊም ሆነ በቤተሰብ ደረጃ ከከነዓናውያን ጋር ጨርሶ እንዳይተባበሩ እግዚአብሔር ከልክሎአቸዋል፤ ምክንያቱም እንደዚህ ዐይነቱ ኅብረት ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት ያመቻምቻል (ዘፀ 34፥15-16፤ ዘፀ 7፥2-4 ይመ)::

23፥13 *ወጥመድና አሽክላ፤* ኢያሱ እዚህ ላይ የሰጠው ማስጠንቀቂያ በዘፀ23፥33፤34፥12፤ ዘዳ 7፥16 ላይ የተነገረውን ያስተጋባል::

*24፥1-33፤* ኢያሱ የእስራኤልን ነገዶች በሙሉ በሴኬም እንደ ገና ሰብስቦ፣ የገቡትን ቃል ኪዳን እንዲያድሱ ጥሪ ያደርግላቸዋል (8፥30-35 ይመ)፡ ኢያሱ የእግዚአብሔር አገልጋይና በሕዝቡ ላይ ባለው የእግዚአብሔር አገዛዝ መካከለኛ እንደ መሆኑ ይህን ጥሪ የማቅረብ ሥልጣን አለው፡ በዚህ ረገድ የሙሴን አርኣያነት ተከትሎአል፤ ሙሴ አገልግሎቱን በጨረሰ ጊዜ ሕዝቡ የገባውን ቃል ኪዳን እንዲያድስ ጥሪ አድርጎ ነበር፤ ይህ በኦሪት ዘዳግም ተጽፎ ይገኛል።

24፥2 *እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤* በቍ 2-13 ላይ እንደ ተጠቀሰው በእግዚአብሔር ስም እንዲህ ባለ ሥልጣን መናገር የሚችለው፣ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል መካከለኛ እንዲሆን የተሾመ ብቻ ነው:: *ከብዙ ዘመን በፊት፤* በጥንት የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝቦች ልማድ መሠረት በሁለት ወገኖች መካከል ውል (ቃል ኪዳን) ሲደረግ፣ ሁለቱ ወገኖች ቃል ኪዳን ከመጋባታቸው በፊት ከዚህ ቀደም የነበራቸው ግንኙነትና ታሪክ እንደ ገና ይወሳል፤ እዚህም ላይ የተደረገው ይኸው ነው:: ኢያሱ እዚህ ላይ የሚያተኵረው፣ አብርሃም ብዙ አማልክትን ከሚያመልክ ቤተሰቡ እንዴት ተለይቶ እንደ ሄደ፣ እስራኤላውያን ከግብፅ እንዴት እንደ ወጡና እግዚአብሔር ሕዝቡን በከነዓን ምድር እንዴት እንዳሰፈረ በሚያወሳው ታሪክ ላይ ነው:: *ከወንዙ፤* የኤፍራጥስ ወንዝ ነው፤ ቍ 3:14:15 ይመ::

24፥6 *ቀይ ባሕር፤* አማራጭ ትርጒሙን ይመ::

አብሔር ጮኹ፤ እርሱም በእናንተና በግብ
ፃውያን መካከል ጨለማ እንዲሆን አደረገ።
ባሕሩን በላያቸው አመጣ፤ አሰጠማቸውም።
በግብፃውያን ላይ ያደረግሁትንም ራሳችሁ
በዐይናችሁ አያችሁ፤ በምድረ በዳም ብዙ
ጊዜ ኖራችሁ።
8" 'በምሥራቅ ዮርዳኖስ ወደሚኖሩት
ወደ አሞራውያን ምድር አመጣኋችሁ፤
እነርሱ ወጓችሁ፤ እኔ ግን አሳልፌ በእ
ጃችሁ ሰጠኋቸው፤ ከፊታችሁ አጠፋኋ
ቸው፤ እናንተም ምድራቸውን ወረሳ
ችሁ። 9የሞዓብ ንጉሥ የሴፎር ልጅ
ባላቅ፣ እስራኤልን ለመውጋት ተነሣ፣
እናንተንም መጥቶ ይረግማችሁ ዘንድ
ወደ ቢዖር ልጅ ወደ በለዓም መልእክ
ተኛ ላከ፤ 10እኔ ግን በለዓምን ልሰማው
አልፈለግሁም፤ ስለዚህ ደግሞ ደጋግሞ
መረቃችሁ፤ እኔም፤ ከባላቅ እጅ ታደግ
ኋችሁ።
11" 'ከዚያም ዮርዳኖስን ተሻገራችሁ ወደ
ኢያሪኮ መጣችሁ፤ አሞራውያን፣ ፌርዛ
ውያን፣ ከነዓናውያን፣ ኬጢያውያን፣ ጌርጌ
ሳውያን፣ ኤዊያውያንና ኢያቡሳውያን እንደ
ወጓችሁ ሁሉ፤ የኢያሪኮም ነዋሪዎች ወጓ
ችሁ። 12በፊታችሁ ተርብ ላክሁ፤ ይህም
እነርሱንና ሁለቱን የአሞራውያን ነገሥታት
ጭምር ከፊታችሁ አሳደደ፤ ይህ ደግሞ በራ
ሳችሁ ሰይፍና ቀስት ያደረጋችሁት አይደ
ለም። 13ስለዚህ ያልደከማችሁበትን ምድ
ርና ያልሠራችኋቸውን ከተሞች ሰጠኋችሁ፤
እነሆ፤ በከተሞቹ ትኖራላችሁ፤ ካልተከላች
ሁት የወይን ተክልና የወይራ ዛፍ ትበላላ
ችሁ።'
14"አሁንም እግዚአብሔርን ፍሩ፤ በፍጹም
ታማኝነትም ተገዙለት። የቀድሞ አባቶ
ቻችሁ ከወንዙ ማዶና በግብፅ ያመለኳቸ
ውን አማልክት ከእናንተ አርቁ፤ እግዚአ
ብሔርን ብቻ አምልኩ። 15እግዚአብሔርን
ማምለክ የማያስፈልግ መስሎ ከታያችሁ
ግን፣ የቀድሞ አባቶቻችሁ ከወንዙ ማዶ
ካመለኳቸው አማልክት ወይም በምድራ
ቸው የምትኖሩባቸው አሞራውያን ከሚያ
መልኳቸው አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ
የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ፤ እኔና
ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።"
16ከዚያም ሕዝቡ እንዲህ ሲል መለሰ፤
"ሌሎችን አማልእክት ለማምለክ ብለን እግ
ዚአብሔርን መተው ከእኛ ይራቅ። 17እኛ
ንና የቀደሙ አባቶቻችንን ከዚያ ከጦር
ነት ምድር ከግብፅ ያወጣን፣ በፊታችንም
እነዚያን ታላላቅ ምልክቶች ያደረገ ማነው?
ራሱ አምላካችን እግዚአብሔር አይደለምን?
በጕዞአችን ላይና ባለፍንባቸውም ሕዝቦች
ሁሉ ዘንድ የጠበቀን እርሱ ነው። 18እንዲ
ሁም እግዚአብሔር በምድሪቱ የሚኖሩትን
አሞራውያንን ጨምሮ ሕዝቦችን ሁሉ ከፊ
ታችን አሳደደ፤ ስለዚህ እኛም እግዚአብሔ
ርን እናመልካለን፤ አምላካችን ነውና።"
19ኢያሱም ሕዝቡን እንዲህ አለ፤ "እግዚ
አብሔርን ማምለክ አትችሉም፤ እርሱ
ቅዱስ አምላክና፤ ቀናተኛ አምላክ ነው፤ ዐመ
ፃችሁን ወይም ኀጢአታችሁን ይቅር አይ
ልም። 20እግዚአብሔርን ትታችሁ ባዕዳን አማ
ልክትን የምታመልኩ ከሆነ፣ መልካም ነገር
ካደረገላችሁ በኋላ ተመልሶ ክፉ ነገር ያደ
ርግባችኋል፤ ያጠፋችኋልም።"
21ሕዝቡ ግን ኢያሱን፣ "የለም! እኛ እግ
ዚአብሔርን እናመልካለን" አሉት።
22ከዚያም ኢያሱ፣ "እንግዲህ እግዚአብሔርን
ለማምለክ መርጣችኋልና በራሳችሁ ላይ ምስክ
ሮች ናችሁ" አላቸው። እነርሱም፣ "አዎን ምስ
ክሮች ነን" ሲሉ መለሱ።
23ኢያሱም፣ "እንግዲህ በመካከላችሁ ያሉ
ትን ባዕዳን አማልክት አስወግዱ፤ ልባችሁ
ንም ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአ
ብሔር መልሱ" አላቸው።
24ሕዝቡም ኢያሱን፣ "እኛ አምላካችንን
እግዚአብሔርን እናመልካለን፤ እንታዘዝለ
ታለንም" አሉት።
25በዚያን ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል
ኪዳን አደረገ፤ የሚመሩበትንም ደንብና
ሥርዐት እዚያው ሴኬም ሰጣቸው። 26ኢያሱም

28፥19፥4፥ዘዳ1፥46
24፥8 ዘፀ23፥23፤ ዘኍ21፥31
24፥9 ዘኍ22፥2፡6፤23፥7
24፥10 ዘኍ23፥11፤ ዘዳ23፥5
24፥11 ዘፍ15፥18-21፤ዘፀ14፥29፤23፥23፤ዘዳ7፥1፤ኢሱ3፥10፤6፥1
24፥12 ዘፀ23፥28፡31፤መዝ44፥3፡6-7፤135፥11
24፥13 ዘዐ6፥8፤ ዘዳ6፥10-11
24፥14 ቍ23፤ዘፍ31፥19፤ዘፀ12፥12፤18፥11፤20፥3፤ዘኍ25፥2፤ዘዳ10፥12፤11፥28፤18፥13፤መሳ10፥16፤ሩት1፥15፤1ሳሙ12፥14፡24፤ኢዮ23፥15፤መዝ19፥9፤119፥120፤ኢሳ55፥7፤ሕዝ23፥3፤ 2ቆሮ1፥12
24፥15 ዘፍ35፥2፤ መሳ6፥10፤ሩት1፥15፡16፤2፥12፤1ነገ18፥21፤ዳን3፥18
24፥16 ኢሱ22፥29
24፥17 ዘፀ10፥1፤ መሳ6፥8
24፥18 ዘፍ28፥21፤ ዘፀ23፥31፤ዘዳ33፥27፤ሐሥ7፥45
24፥19 ዘፀ20፥5፤23፥21፤34፥7፤ዘሌ11፥44፤20፥26
24፥20 ኢሱ23፥15፤ 1ሳሙ12፥25፤1ዜና28፥9፡20፤2ዜና24፥18፤ ሆሴ13፥1፤ሐሥ7፥42
24፥22 ቍ27፤ዘዳ25፥9፤ሩት4፥10፤መዝ119፥30፡173፤ኢሳ8፥2፤43፥10፤44፥8፤ኤር42፥5፤ሚል2፥14
24፥23 ቍ14፤1ነገ8፥58፤መዝ119፥36፤141፥4፤ኤር31፥33
24፥24 ዘፀ19፥8፤ ኤር42፥6
24፥25 ዘፀ15፥25፤ 24፥8፤ኢሱ17፥7

24፥10 *በለዓምን ልሰማው አልፈለግሁም፤* እግዚአብሔር የበለዓምን ጸሎት አለመስማቱ ብቻ ሳይሆን፣ ርግማኑንም ወደ በረከት ለውጦታል (ዘኍ 23፥24 ይመ)።

24፥12 *ተርብ፤* ታችኛው (ሰሜናዊው) ግብፅ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ተርብን ብሔራዊ አርማ አድርጎ ይጠቀምበት ነበር፤ ስለዚህ እዚህ ላይ ግብፃውያን በከነዓን ላይ ለመዝመት ያዘጋጁትን ወታደራዊ ኀይል ሊያመለክት ይችላል። ሆኖም "ተርብ" የሚለው ቃል ስለ እስራኤላውያን የተነገረውንና በከነዓናውያን ላይ ፍርሃት ያስከተለውን ዜና ያመለክታል (2፥11፤ 5፥1፤ 9፥24)። የዘፀ 23፥38 ማብ ይመ።

24፥14 *እግዚአብሔርን ፍሩ፤* እግዚአብሔርን ታመኑ፣ አገልግሉ፤ አምልኩ ማለት ነው። *የቀድሞ አባቶቻችሁ ከወንዙ ማዶና በግብፅ ያመለኳቸውን አማልክት፤* ቍ2 ይመ። ኢያሱ፣ እስራኤላውያን የቀድሞ አባቶቻቸው በመስጴጦምያና በግብፅ ያመልኳቸው ከነበሩት ባዕዳን አማልክት ፈጽሞ እንዲርቁ አሳሰባቸው። የታራ ቤተሰቦች በዑርና በካራን በነበሩት ወቅት "ናና" ወይም "ሲን" የተባለ የጨረቃ አምላክን ያመልኩ ነበር። በዘፀ 32፥4 ላይ የምናገኘው የወርቅ ጥጃ ምስል የግብፃውያንን አማልክት ስለ ማምለካቸው አንዱ ምሳሌ ነው። ይህ የወርቅ ጥጃ የተቀረጸው ምናልባት በግብፃውያን ዘንድ ቅዱስ ተደርጎ በሚታየው "በአጲስ" ቅርጽ ነው፤ የዘፀ 32፥4 ማብ ይመ (በሌላ በኩል ደግሞ ኢዮርብዓም በቤቴልና በዳን ያሠራቸው የወርቅ ጥጃዎች ምናልባት አማልክትን ለማስጋለብ የሚያመች ቅርጽ ያላቸው ሳይሆኑ አይቀርም፤ 1ነገ 12፥28-29 ይመ)።

24፥15 *እኔ ... ግን፤* ኢያሱ ለእግዚአብሔር ያለውን ታማኝነት በሕዝቡ ሁሉ ፊት አስታወቀ፤ ኢያሱ እንዲህ ያደረገው ሕዝቡ የእርሱን አርአያነት ይከተላል በሚል እምነት ነው።

*24፥17-18፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ባወጣበት ታምራዊ ሁኔት ላይ የተመሠረተ የእምነት መግለጫ ሲሆን፣ የተደመደመውም "እርሱ ... አምላካችን ነው" በሚለው ሐረግ ነው።

24፥19 *አትችሉም፤* ከመጠን በላይ በራስ መተማመን የሚያመጣውን አደጋ በአጽንዖት የሚገልጽ ነው።

24፥22 *ምስክሮች፤* ቍ 27 ይመ፤ አንዱ የውል አካል ነው (ዘዳ 30፥19 ይመ)።

24፥23 *ባዕዳን አማልክት፤* አማልክቱ ከእንጨት ወይም ከብረት በተሠሩ ጣዖታት የሚወከሉ፣ ሊሰበሩና ሊደቁ የትም ሊወረወሩ የሚችሉ ናቸው።

24፥25 *ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን፤* ይህ ኪዳን ሕዝቡ የገባውን ቃል ኪዳንና እግዚአብሔርም ለሕዝቡ የሰጠውን ሥርዐትና ሕግ ያካትታል።

እነዚህን ቃሎች በእግዚአብሔር የሕግ መጽ
ሐፍ ጻፋቸው፤ ትልቅ ድንጋይም ወስዶ በባ
ሉጥ ዛፍ ሥር፣ በተቀደሰው በእግዚአብሔር
ስፍራ አጠገብ አቆመው::
[27]ኢያሱም ሕዝቡን ሁሉ፣ "እነሆ፤ ይህ
ድንጋይ፣ እግዚአብሔር የተናገረንን ሁሉ
ሰምቶአል፣ በእኛም ይመሰክርብናል፤ እናን
ተም በአምላካችሁ ዘንድ እውነተኞች ሆና
ችሁ ባትገኙ ምስክር ይሆንባችኋል" አላቸው።

## ኢያሱ በተሰፋዪቱ ምድር ተቀበረ

24፥29-31ተጓ ምብ-መሳ 2፥6-9

[28]ከዚያም ኢያሱ ሕዝቡን ሁሉ ወደየ
ርስቱ እንዲሄድ አሰናበተ::
[29]ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ባሪያ የነዌ ልጅ
ኢያሱ በመቶ ዐሥር ዓመቱ ሞተ:: [30]በኩረብታ
ማው በኤፍሬም አገር በምትገኘው፣ ከገዓስ
ተራራ በስተ ሰሜን ባለችው በራሱ ርስት
በተምናሴራ ቀበሩት::
[31]ኢያሱ በሕይወት ⁄ በነበረበት ዘመን
ሁሉ፣ ከኢያሱም በኋላ በሕይወት በኖሩትና
እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ሁሉ
በሚያውቁት ሽማግሌዎች ዘመን ሁሉ
እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አመለኩ::
[32]እስራኤላውያን ከግብፅ ያወጡት የዮ
ሴፍ ዐፅም፣ ያዕቆብ ከሰኬም አባት ከኤ
ሞር በመቶ ሰቅል" ብር በገዛው በሴኬም
ምድር ተቀበረ፤ ይህችም የዮሴፍ ዘሮች
ርስት ሆነች::
[33]እንዲሁም የአሮን ልጅ አልዓዛር ሞተ፤
እርሱም በኩረብታማው በኤፍሬም አገር
በሚገኘው ለልጁ ለፊንሐስ በዕጣ በደረሰው
በጊብዓ ምድር ተቀበረ::

"32 ዕብራይስጡ አንድ መቶ ከሲታሃስ ይላል፤ ክብደቱና ዋጋው በትክክል የማይታወቅ የገንዘብ ዐይነት ነው::

24፥26 ዘፍ12፥6፤ 28፥18፤ዘጸ17፥18፤ 27፥2፤28፥61፤31፥24፤መሳ4፥11
24፥27 ቊ22፤ዘፍ 21፥30፤28፥18፤ዘኍ 11፥20፤ኢሱ7፥11፤ 22፥27፤ምሳ30፥9፤ ዕንገ2፥11
24፥28 መሳ21፥23:24
24፥29 ዘፍ50፥22፤ መሳ1፥1
24፥30 ኢሱ19፥50፤ 2ሳሙ23፥30
24፥31 ኢሱ7፥6
24፥32 ዘፍ33፥19፤ 47፥29-30፤ዮሐ4፥5፤ ሐሥ7፥16፤ዕብ11፥22
24፥33 ዘፀ6፥25፤ ኢሱ15፥57፤22፥13፤ 1ሳሙ9፥4፤1ነገ4፥8

24፥26 *ትልቅ ድንጋይ፤* በኢያሱ አገልግሎት ማክተሚያ ላይ ሕዝቡ የገባውን ቃል ኪዳን ለማስታወስ የቆመ ድንጋይ ነው፤ እግዚአብሔር በአገልጋዩ አማካይነት ለሕዝቡ ያደረገውን ለማስታወስ በምድሪቱ ከቆሙት የመታሰቢያ ሐውልቶች መካከል ይህ ሰባተኛው ነው (የ22፥27 ማብ ይመ):: ከእነዚህ የመታሰቢያ ሐውልቶች መካከል አንዱ የኢያሪኮ ፍርስራሽ ነው (6፥26 ይመ)፡ እስራኤላውያን የተስፋዪቱን ምድር መውረሳቸው ራሱ አንዱ ምስክር ነው (ሰባት ቍጥር ሙሉ ቍጥር ነው)፤ ይህም እስራኤላውያን ምድሪቱን እንዴት ሲወርሱ እንደቻሉና በምድሪቱም መኖር የሚችሉት የገቡትን ኪዳን መጠበቅ ሲችሉ ብቻ እንደሆን ሲመሰክር ይኖራል:: ምድሪቱ የራሷን ታሪክ ራሷ ትናገራለች:: *የባሉጥ ዛፍ፤* የዘፍ 12፥6 ማብ ይመ:: *በተቀደሰው በእግዚአብሔር ስፍራ አጠገብ፤* ምናልባት በዚያው ቆሞ የነበረን መሠዊያ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፤ ኢያሱ በጌባል ተራራ አጠገብ የሠራውን መሠዊያ የሚያመለክትም ሊሆን ይችላል (8፥30)፤ ወይም ደግሞ "ለእግዚአብሔር በተቀደሰው የወርካ ዛፍ ሥር" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል (ከዘፍ 12፥6 ጋር ያነጻጽሩ):: ቁም ነገሩ፣ በድንጋዩ ላይ የተጻፈው ኪዳን በሕዝቡ ሁሉ መነበቡ ነው (24፥27)::

*24፥29-33፤* በዚህ ክፍል ውስጥ ሦስት ቀብሮች ተፈጽመዋል:: የጥንት ሰዎች በገዛ አገራቸው የመቀበር ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው በመሆኑ፣ የእነዚህ ቀብሮች ማስታወሻዎች የታሪኩን መደምደምና የዘመኑን ማብቃት ብቻ ሳይሆን፣ እስራኤል በእርግጥ የተስፋዋን ምድር እንደ ወረሰች ያስገነዝባሉ፤ እግዚአብሔርም የገባውን ቃል ኪዳን ጠብቆአል::

24፥29 *መቶ ዐሥር፤* የዚህን ቁጥር ልዩ ትርጉም ለመገንዘብ የዘፍ 50፥26 ማብ ይመ::

24፥30 *በተምናሴራ ቀበሩት፤* 19፥50 እና ማብ ይመ::

*24፥31፤* በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ የተነገረው ታሪክ የእስራኤል ሕዝብ በወቅቱ ምን ያህል ታማኝ እንደ ነበር የሚገልጽ ነው:: ጸሓፊው ከዚህ በኋላ የሚመጣው ትውልድ ከቀድሞው ምን ያህል እንደሚለይ ከወዲሁ አስተውሎአል::

24፥32 *የዮሴፍ ዐፅም፤* የዮሴፍን ዐፅም ወደ ሴኬም መመለስ አስፈላጊ የሆነው፣ ያዕቆብ ከኤሞር የገዛት ምድር በመሆኗ ብቻ ሳይሆን (ዘፍ 33፥19)፣ ሴኬም የዮሴፍ ልጆች የኤፍሬምና የምናሴ ማእከል መሆን ስለሚገባትም ጭምር ነው:: በተጨማሪም ዮሴፍ ሊሞት በተቃረበበት ሰዓት የተገባለት መሐላ በተገባለት መሠረት መፈጸሙን ያመለክታል (ዘፍ 50፥25፤ ዘፀ 13፥19)::

24፥33 *አልዓዛር፤* አሮን ሙሴን እንዳገለገለ ሁሉ አልዓዛርም ኢያሱን ያገለገለ ሊቀ ካህናት ነበር:: *ጊብዓ፤* በብንያም ምድር የምትገኘዋ ከተማ ሳትሆን፣ በኤፍሬም ምድር ሴሉ አጠገብ ያለችዋ ናት::